የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የግብርና ግብይት ሥርዓት መጠናከሪያ ጥናት

# የመጨረሻ ሪፖርት

ህዳር 2012 (እ.ኤ.አ)

**JAPAN INTERNATIONAL COOPERATION AGENCY (JICA)**

**OVERSEAS MERCHANDISE INSPECTION CO., LTD.**
**NIPPON KOEI CO., LTD.**

| |
|---|
| ET |
| JR |
| 12-006 |

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳያዊ ሪፐብሊክ
የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Southern Nations Nationalities and Peoples Regional Government

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳያዊ ሪፐብሊክ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የግብርና ግብይት ሥርዓት መጠናከሪያ ጥናት

The Development Study on the Strengthening Agricultural Marketing System
in Southern Nations Nationalities and Peoples Region
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

## የመጨረሻ ሪፖርት

FINAL REPORT

ህዳር 2012 (እ.ኤ.አ)


November 2012


**JAPAN INTERNATIONAL COOPERATION AGENCY (JICA)**

**OVERSEAS MERCHANDISE INSPECTION CO., LTD.**

**NIPPON KOEI CO., LTD.**

# የጥናቱ አካባቢ



ADMINISTRATIVE MAP OF SOUTHERN NATIONS NATIONALITIES AND PEOPLE`S REGIONAL STATE
N
OROMIA
OROMIA
OROMIA
OROMIA
OROMIA
Gambella
Gambella
SUDAN
KENYA
SHEKA
Keffa
Konta
Dawuro
Gamo Gofa
Bench Maji
South Omo
Basketo
YEM
Hadiya
Gurage
Silti
Alaba
Kembata Tembaro
Wolayita
Sidama
Gedeo
Amaro
Burji
Derashe
Konso
LEGEND
International boundary
Region boundary
Wereda boundary
Town
Lakes
Caution :
All boundaries on this map are not considered authoritative
Source : SNNPRS - BoFED, Feb. 2010

## ፎቶ-1 ፡ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እና አቅም ግንባታ


ወረዳዎች ኮምፑተር ከነፕሪንቱ ሲረከቡ


የወረዳ ሠራተኞች የኮምፑተር ስልጠና ሲወስዱ


የገበያ ዋጋ የማስታወቂያ ቦርድ ለወረዳዎች ተሰጥቷል


በገበያ ቦታ አርሶአደሩ የገበያ ዋጋ ሲመለከቱ


በትግበራ ፕሮጀክት 02 አማካኝነት ለወረዳ እና ሕ/ሥራ ማህበራት የተሰጠ ስልጠና ፕሮግራም


የጥናት ቡድኑ ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02 ያዘጋጀው የእህል ናሙና መያዥያ ሣጥን


የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ሠራተኞች የመስክ ጉንኝት


የም/ፕሬዝዳንትና የግብርና ቢሮ ኃላፊ ግቡኝት

## ፎቶ-2 : እሴት የመጨመር ተግባር



በጥናት ቡድኑ የተሠራ ማንጎ ማውረጃ



ፍራፍሬ ማጓጓዣ ጋሪ ስተዋወቅ



በጥናት ቡድኑ የተሠራ አቮካዶ መሰብሰቢያ ማዕከል



በጋራ አቮካዶ ሽያጭ ሲፈጸም



እርጥብ ካሳቫ መቁረጫ ማሳሪያ ማሳ ውስጥ በሥራ ላይ



ንፁህ፣ ትንንሽ የካሳቫ ቁርጥራጫ በፀሐይ ሲደርቅ



ዝንጅብል ማጠቢያ ቁሳቁስ። በግፊት በሚሠራ መሣሪያ ዝንጀብል ሲታጠብ



የታጠበ ዝንጅብል ማድረቂያ ቦታ

## ፎቶ-3 ፡ የገበያ መሠረተልማት



የተለመደ የአካባቢ ገበያ በደረቅ ወቅት



በዝናብ ወቅት የአካባቢ ገበያ በውሃ ሲጥለቀለቅ



በጥናት ቡድኑ የተገነባ የቦሎቄ የገበያ ማዕከል



አርሶአደሮችና ነጋዴዎች ቦሎቄ ሲገበያዩ



የሕ/ሥራ ማህበር 100 ቶን የሚይዝ መጋዘን.



ለቢሮ የተሠሩ ቤቶች በመጋዘንነት ሲያገለግሉ



በጥናት ቡድኑ የተገነባ ባለ500 ቶን ዘመናዊ መጋዘን



መተላለፍያ መስመርና ኩንታል መደርደሪያ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳያዊ ሪፐብሊክ
# በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል
# የግብርና ግብይት ሥርዓት መጠናከሪያ ጥናት

## የመጨረሻ ሪፖርት

### የገጽ ማውጫ


የጥናቱ አካባቢ ከርታ
ፎቶ

**ምዕራፍ 1 መግቢያ**
1.1 የጥናቱ ዳራ ....................................................1-1
1.2 የጥናቱ ዓላማ ....................................................1-2
1.2.1 የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ ....................................................1-2
1.2.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ....................................................1-2
1.3 የጥናቱ አካባቢና የታለሙ ሰብሎች ....................................................1-2
1.3.1 የጥናቱ አካባቢ ....................................................1-2
1.3.2 የታለሙ ሰብሎች ....................................................1-2
1.4 አቻ ድርጅቶችና እስትሪንግ ኮሚቴ ....................................................1-2
1.4.1 አቻ ድርጅቶች ....................................................1-2
1.4.2 እስትሪንግ ኮሚቴ ....................................................1-2
1.5 የጥናቱ አድማስ ....................................................1-3
1.5.1 የጥናቱ የጊዜ ሠሌዳ ....................................................1-3
1.5.2 የመሪ ዕቅድ ዝግጅት ....................................................1-3
1.6 የጥናቱ አፈጻጸም ....................................................1-4
1.6.1 ምዕራፍ 1 ....................................................1-4
1.6.2 ምዕራፍ 2 ....................................................1-4
1.6.3 በጃፓን ያቻ ባለሙያዎች ስልጠና ....................................................1-5
1.7 የሪፖርቱ ጥንቅር ....................................................1-5

**ምዕራፍ 2 የሀገሪቱና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ገጽታ**
2.1 የግብርና ሥነምህዳርና የሲሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ....................................................2-1
2.1.1 የግብርና ሥነምህዳር ሁኔታ ....................................................2-1
2.1.2 ሶሽዩ-ኢኮኖሚ ሁኔታ ....................................................2-4
2.2 የሰብል ልማት ገጽታ ....................................................2-7
2.2.1 የሀገሪቱ የሰብል ልማት ....................................................2-7
2.2.2 በደ/ብ/ብሕ/ክ/ የሰብል ልማት ....................................................2-8
2.3 የግብርና ትምህርትና ኤክስቴንሽን ....................................................2-10
2.3.1 የግብርና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ....................................................2-10
2.3.2 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ....................................................2-11
2.3.3 የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከል ....................................................2-11
2.4 የግብርና አስተዳደር አደረጃጀት ....................................................2-13
2.4.1 የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ....................................................2-13
2.4.2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ቢሮ ....................................................2-13
2.4.3 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብይተና ሕ/ሥራ ቢሮ ....................................................2-14
2.5 የግብርና ግብይት ፖሊሲ ....................................................2-17
2.5.1 የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የግብርና ግብይት እስትራቴጂ ....................................................2-17
2.5.2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የክልላዊ ግብርና ግብይት እስትራቴጂ ....................................................2-18
2.5.3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የልማት ኮሪደር እቅድ ....................................................2-19

2.6 በጥናቱ የሌሎች ለጋሾች ድርጅቶች እንቅስቃሴና ህብረት ....2-21
2.6.1 ዓለም አቀፍ ገንዘብ ለግብርና ልማት (ኢፋድ) ....2-21
2.6.2 የዓለም የምግብ ፕሮግራም ....2-22
2.6.3 የግብርና እደገት ፕሮግራም- የዓለም ባንክ ....2-24
2.6.4 የጃይጃ አንድ መንደር አንድ ምርት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ኦቮፕ) ....2-27

ምዕራፍ 3 የጥናት አካባቢ አሁን ያለው ሁኔታ
3.1 የተመረጡ እህሎች የምርት የግብይትና የድህረምርት አያያዝ ....3-1
3.1.1 የብርዕ ሰብል ....3-1
3.1.2 ጥራጥሬ ....3-11
3.1.3 አትክልት ....3-16
3.1.4 ፍራፍሬ ....3-27
3.1.5 ሥራሥር እህሎች ....3-37
3.1.6 ሌሎች ሰብሎች ....3-43
3.2 ድህረምርት ማቀነባበርና እሴት መጨመር ....3-50
3.2.1 ብርዕና ጥራጥሬ ....3-50
3.2.2 የፍራፍሬና አትክልት ዘርፍ ....3-54
3.2.3 የአካባቢ የአግሮ ኘሮሰስንግ ማሽን የሚፈርኩ ተቋማት ....3-58
3.3 የግብርና የገበያ መረጃ አገልግሎት ....3-62
3.3.1 የሀገሪቱ የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ....3-62
3.3.2 ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት ....3-69
3.3.3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግስት የግብርና የገበያ መረጃ ሥርዓት አሠራር ....3-70
3.3.4 ለግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎትና የመረጃ ልማት ያሉ ሀብቶች ....3-75
3.4 በአሁኑ ወቅት ያለው የግብርና ግብይት መሠረተልማት ....3-79
3.4.1 የመንገድ ሁኔታ ....3-79
3.4.2 የግብርና መጋዘን ....3-83
3.4.3 የገበያ ቦታ ....3-86
3.4.4 ቴሌኮሚኒኬሽን ....3-90
3.4.5 በመንገድ ዳር የሚደረግ ግብይት ....3-91
3.5 የሕ/ሥራ ማህበራት ወቅታዊ እንቅስቃሴ ....3-92
3.5.1 በኢትዮጵያ የሕ/ሥራ ማህበራት ወቅታዊ ሁኔታ ....3-92
3.5.2 ወቅታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት ሁኔታ በደቡብ ክልል ....3-94
3.5.3 የሕ/ሥራ ማህበራት ዋና ዋና ስራዎች ....3-101
3.5.4 የሕ/ሥራ ዩኒያኖችና ሕ/ሥራ ማህበራት አስተዳደርና ፋይናንስ ....3-105
3.5.5 ለሕብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ ....3-115
3.6 የአሁኑ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅታዊ አሠራር ....3-120
3.6.1 የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት ....3-120
3.6.2 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት እንቅስቃሴ ....3-124
3.7 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የምግብ ዋስትና እንቅስቃሴ ....3-126
3.7.1 በግብርና ቢሮ ቅድመ ማስጠንቀቅያና ምግብ ዋስት የሥራ ሂደት ....3-126

ምዕራፍ 4 ሊተኮሩ የሚገቡ ጉዳዮችና ችግሮች ማጠቃለያ
4.1 በተመረጡ ሰብሎች ሊተኮሩ የሚገባ ጉዳዮች ....4-1
4.1.1 የብርዕና አገዳ ሰብሎች ....4-1
4.1.2 ጥራጥሬ ....4-2
4.1.3 አትክልት ....4-2
4.1.4 ፍራፍሬ ....4-4
4.1.5 ሥራሥር ሰብሎች ....4-6
4.1.6 ሌሎች ሰብሎች ....4-7
4.2 የሁሉንም የሚነካኩ ጉዳዮች ....4-8
4.2.1 የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ....4-8

4.2.2 የግብይት መሠረተልማት ....4-10
4.2.3 የአርሶአደሮች ድርጅቶች/ የሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች ....4-10
4.2.4 የምግብ ማቀነባበር (አግሮ ፕሮሰሲንግ)....4-13
4.3 ሰብሎችን በሥርጭት ሁኔታ መደልደል....4-13
4.4 ዞናዊ ባህሪይ....4-15
4.4.1 ዞናዊ ባህሪይ በሰብል ልማት ....4-15
4.4.2 ዞናዊ ባህርይ በስብል ግብይት....4-20
4.5 የተጠቃሚዎች ድልድል ....4-23
4.6 ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችና ፍላጐቶች በሰብል ዓይነትና አካባቢ....4-25

**ምዕራፍ 5 መሪ ዕቅድ**
5.1 የመሪ ዕቅድ ዝግጅት መርህና ዘዴ ....5-1
5.1.1 የመሪ ዕቅዱ አድማስ....5-1
5.1.2 የዕቅድ ዝግጅት መሠረታዊ መርህ....5-1
5.1.3 የዕቅድ ዝግጅት ሂደት ....5-1
5.1.4 የሙከራ ፕሮጀክቶች (የማረጋገጫ ጥናት) ....5-2
5.2 መሪ ዕቅድ ....5-5
5.2.1 የልማት ግብ....5-5
5.2.2 የወቅታዊ ሁኔታ እይታ....5-5
5.2.3 የልማት እስትራቴጂ ማዘጋጃ መሪ ሀሣብ....5-6
5.2.4 የልማት አስትራቴጂ....5-7
5.2.5 መሠረታዊ እስትራቴጂ 1: የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማጠናከር ....5-7
5.2.6 መሠረታዊ እስትራቴጂ 2: ከፍተኛ እሴት ጭማሪ ግብይት በማስተዋወቅ ትርፍ ማሳደግ ....5-12
5.2.7 መሠረታዊ እስትራቴጂ 3: የገበያ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ብቃት ያለው የገበያ መሠረተልማት ማሻሻል....5-23
5.2.8 መሠረታዊ እስትራቴጂ 4: የግብርና ግብይት ተቋማዊ ስርዓት መጀመርና ማስተካከል ....5-29
5.3 የመሪ ዕቅድ ፕሮግራም ....5-33
5.3.1 የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ማልማት ....5-33
5.3.2 የከፍተኛ እሴት ጭማሪ የግብይት የማስፋፋት እቅድ....5-35
5.3.3 ለግብርና ምርቶች የገበያ መሠረተልማት ማቀድ ....5-38
5.3.4 ለሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች የአቅም ግንባታ ማጠናከሪያ ዕቅድ ....5-40

**ምዕራፍ 6 የፕሮጀክት ዕቅድ**
6.1 ፕሮጀክት እቅድ ማዘጋጃ ፖሊሲ....6-1
6.2 የፕሮጀክት ዕቅድ ባህሪይ መለኪያዎች ....6-1
6.3 የፕሮጀክት ዕቅዶች ዝርዝር....6-2
6.4 የፕሮጀክት ዕቅድ ....6-6
6.4.1 የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ልማት ....6-6
6.4.2 ለከፍተኛ እሴት ጭማሪ ማስፋፋያ ዕቅድ....6-14
6.4.3 ለግብርና ምርቶች ገበያ መሰረተ ልማት ዕቅድ ....6-53
6.4.4 የሕብረት ሥራ ማህበራት/ ዩኒየኖች አቅም ማጠናከሪያ ዕቅድ ....6-80

**ምዕራፍ 7 ማሳሰቢያ**....7-1

**ዕዝል**
**ዕዝል** 1 Minutes of Meetings on S/W for the Study
**ዕዝል** 2 Scope of Work for the Study
**ዕዝል** 3 Minutes of Meetings on the Study

## ም ስ ል

ምስል 1-1 አጠቃላይ የጥናቱ የጊዜ ሠሌዳ ....................1-3
ምስል 2.1-1 በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሁኔታ ....................2-2
ምስል 2.1-2 ብሔራዊ የህዝብ ብዘት ሁኔታ ....................2-4
ምስል 2.1-3 የደ/ብ/ብ/ህ/የህዝብ ብዛት ፒራሚድ ....................2-5
ምስል 2.1-4 የክልሎች የእርሻ መሬት ይዞታ ....................2-5
ምስል 2.1-5 የዋጋ ንረቱ አኳኋን (2003-08 እ.ኤ.አ) ....................2-6
ምስል 2.1-6 የውጪና የገቢ ዕቃዎችና አገልግሎቶች አኳኋን (2000-08 እ.ኤ.አ) ....................2-6
ምስል 2.3-1 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የገበሬ ማስልጠኛ ማዕከላት ሽፋን ....................2-12
ምስል 2.4-1 የግብርና ቢሮ ድርጅታዊ መዋቅር ....................2-15
ምስል 2.4-2 የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮድርጅታው መዋቅር ....................2-16
ምስል 3.1-1 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የብርዕ ሰብልና ጥራጥሬ የገበያ ፍሰት ....................3-3
ምስል 3.1-2 የበቆሎ ችርቻሮ ዋጋ ....................3-6
ምስል 3.1-3 የጤፍ ችርቻሮ ዋጋ ....................3-8
ምስል 3.1-4 የስንዴ ችርቻሮ ዋጋ አኳኋን ....................3-11
ምስል 3.1-5 የባቄላና አተር አማካይ የችርቻሮ ዋጋ ....................3-14
ምስል 3.1-6 በደቡብ ክልል የአትክልት የገበያ ስንሰለት ....................3-18
ምስል 3.1-7 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ወርሃዊ የአበሻ ጎመን ዋጋ /ጥር-ታህ 2009 (እ.ኤ.አ) ....................3-19
ምስል 3.1-8 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የበርበሬ ምርት የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ....................3-22
ምስል 3.1-9 በአላባ ገበያ የበርበሬ ገበያ ሰንሰለት ....................3-23
ምስል 3.1-10 ወርሃዊ የበርበሬ ዋጋና የምርት ወቅት ....................3-25
ምስል 3.1-11 የፍራፍሬ የግብይት ሰንሰለት ....................3-28
ምስል 3.1-12 የአቮካዶ የአምራች ዋጋ (2009 እ.ኤ.አ) እና ምርት መሰብሰቢያ ወቅት ....................3-30
ምስል 3.1-13 የማንጐ የምርት ወቅት ....................3-31
ምስል 3.1-14 የአምራቾች የሙዝ ዋጋ (2009 እ.ኤ.አ) እና ምርትመሰብሰቢያ ወቅት ....................3-35
ምስል 3.1-15 በከምባታ ጠምባሮ ዞን የዝንጅብል (እርጥብ/ደረቅ ምርት) የግብይት ሰንሰለት ....................3-46
ምስል 3.1-16 የአምራቾች የእርጥብ ዝንጅብል ዋጋና የተከላ ወቅት (2009 እ.ኤ.አ) ....................3-47
ምስል 3.3-1 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የችርቻሮ ዋጋ መሰብሰቢያ የገበያ ቦታዎች አቀማመጥ ....................3-64
ምስል 3.4-1 ዞናዊ የመንገድ ጥግገት በእስኩዌር ኪ.ሜትር ....................3-81
ምስል 3.4-2 የየዞኑ የመንገድ ጥግጊት በ1000 ሰው ....................3-81
ምስል 3.4-3 ከወረዳና ዞን ዋና ከተማ መካካል ያለው እርቀት ....................3-82
ምስል 3.4-4 የገበያ ቦታ ብዛት፣ በገበያ መጠንና በዞን ....................3-87
ምስል 3.5-1 በደቡብ ክልል ዩኒየኖችና ፌደሬሽን ያሉበት ሥፍራ ....................3-96
ምስል 3.5-2 በአዋጅ የተገለፀው ድርጅታዊ ቻርት ....................3-98
ምስል 3.5-3 በግብርና ህ/ሥራ ማህበራት ጥቅሞች እይታ ....................3-100
ምስል 3.5-4 በሕ/ሥራ ማህበራት አማካይነት የሚካሄደው የእህል ግብይት ....................3-101
ምስል 3.5-5 የሙዝ ግብይት በሕ/ሥራ ማህበራት አማካይነት ....................3-103
ምስል 3.5-6 የማዳበሪያ ግብይት ፍሰት ቻርት በ2009 ዓ/ም ....................3-105
ምስል 3.5-7 የገጠር ፋይናስ ፈንድ የሥራ አፈፃፀም ዘዴ ....................3-118
ምስል 3.6-1 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅታዊ መዋቅር ....................3-121
ምስል 3.7-1 ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስትና የሥራ ሂደት ድርጅታዊ መዋቅርና ተግባር ....................3-126
ምስል 4-1 በማምረትና በሥርጭት መካከል ያለው የብስለት መጠን ሃሣቦዊ ምሥል ....................4-14
ምስል 4-2 የዋና ዋና ብርዕና አገዳ ሰብል የምርት መጠን በዞን ....................4-15
ምስል 4-3 የብርዕና አገዳ ሰብል የሥርጭት መጠን በዞን ....................4-16
ምስል 4-4 የጥራጥሬ ምርት መጠን በዞኖች ....................4-16
ምስል 4-5 የጥራጥሬ ሥርጭት መጠን በዞን ....................4-17
ምስል 4-6 የአትክልት ምርት መጠን በዞን ....................4-18
ምስል 4-7 የአትክልት ሥርጭት መጠን በዞን ....................4-18

ምስል 4-8 ፍራፍሬ ምርት መጠን በዞን ....................................................................4-19
ምስል 4-9 የፍራፍሬ የሥርጭት መጠን በዞን.............................................................4-19
ምስል 4-10 የሥራሥር ምርት መጠን በዞን ...........................................................4-20
ምስል 4-11 የሥራሥር ሥርጭት መጠን በዞን .........................................................4-20
ምስል 4-12 በእያንዳዱ ዞን ለሽያጭ የሚመረት ሰብል እምቅ አቅም ..............................4-21
ምስል 4-13 ሀሳባዊ ከርታ፡ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ እስትራቴጅካዊ የገቢ ማስገኛ ሰብሎች ...............4-23
ምስል 4-14 የገበያ ሥፍራ ብዛትና የሕዝብ ብዛት በዞን ..............................................4-25
ምስል 5-1 የመሪ ዕቅዱ ዝግጅት ሂደት .......................................................................5-2
ምስል 5-2 የመሪ ዕቅዱ ፅንሰ ሀሳባዊ ሥዕላዊ መግለጫ ...................................................5-7
ምስል 5-3 የመንገድ ዳር የገጠር ማስፋፊያ ማዕከል ሥዕላዊ ገጽታ ..................................5-28
ምስል 5-4 የመንገድ ዳር የገጠር ማስፋፊያ ማዕከል የግንባታ ቦታ መምረጫ የሥራ ፍሰት .5-29
ምስል 5-5 የፍራፍሬ ምርት ብክነት መቋቋሚያ ፕሮግራም የአፈፃፀም ጊዜ ሠሌዳ...............5-36
ምስል 5-6 የአትክልት ማጓጓዣ ዘመናዊ ማድረግያ ፕሮግራም የአፈፃፀም ጊዜ ሠሌዳ.........5-37
ምስል 6-1 የእያንዳንዱ ፕሮጀክት እስትራቴጂዎች፣ የተመረጠ አካባቢ እና የተመረጠ ሰብል ..6-5

## ሠንጠረዥ

ሠንጠረዥ 2.1-1 የኢትዮጵያ የግብርና ሥነምህዳር ቀጠና ክፍፍል .......................................2-2
ሠንጠረዥ 2.1-2 መሠረታዊ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የተፈጥሮ ሁኔታ መረጃ ..................................2-3
ሠንጠረዥ 2.1-3 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ሥምህዳር ቀጠናዎች ........................................2-3
ሠንጠረዥ 2.1-4 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የእርሻ መሬት ይዞታ ......................................................2-6
ሠንጠረዥ 2.2-1 የሰብል ምርት በክልል .........................................................................2-7
ሠንጠረዥ 2.2-2 የስብል አጠቃቀም ..............................................................................2-8
ሠንጠረዥ 2.2-3 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ሰብል ልማት በዞን.........................................................2-9
ሠንጠረዥ 2.3-1 በኢትዮጵያ የግብርና ትምህርት የሚሰጥባቸው ተቋማት ........................2-10
ሠንጠረዥ 2.3-2 በደ/ብ/ብ/ክ/ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ የነበሩ ተማሪዎች ብዛት.......................................................................2-11
ሠንጠረዥ 2.3-3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የልማት ሠራተኛ ብዛትና አርሶአደር ጥመርታ .................2-12
ሠንጠረዥ 2.5-1 ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርናና ገጠር ልማት እስትራቴጂ እቅድ የተመረጡ ምርቶች፣ ስልታዊ ግብና የዝርዝር ስራ እቅድ ......................................2-18
ሠንጠረዥ 2.5-2 የልማት ኮሪዶር እቅድ.........................................................................2-20
ሠንጠረዥ 2.6-1 የኢፋድ/አሚፓ የተመረጡ ወረዳዎችና ምርቶች .......................................2-21
ሠንጠረዥ 2.6-2 በዓለም የምግብ ፕሮግራም ተሳታ ዩኒያኖች የተሰራጨ መገልገያዎች .......2-23
ሠንጠረዥ 2.6-3 የፕሮጀክት ወጪ ዝርዝር የበጀት ምንጭ ማጠቃለያ...............................2-24
ሠንጠረዥ 2.6-4 የግብርና እድገት ፕሮግራም ወረዳዎችና የተመረጡ ምርቶች ..................2-25
ሠንጠረዥ 2.6-5 የአርሶ አደር ቡድኖች የስራ አይነት እና የፕሮጀክቱ ተባባሪዎች ..............2-27
ሠንጠረዥ 3.1-1 የኢትዮጵያ የብርዕ ሰብል ምርትና የገበያ ሽያጭ መጠን...........................3-1
ሠንጠረዥ 3.1-2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የብርዕ ሰብል ምርትና የሽያጭ መጠን............................3-2
ሠንጠረዥ 3.1-3 የበቆሎ ምርትና የገበያ ሽያጭ መጠን በክልልና ዞን/ልዩ ወረዳ..................3-4
ሠንጠረዥ 3.1-4 የጤፍ ምርትና የገበያ ሽያጭ መጠን በክልልና ዞን/ልዩ ወረዳ....................3-6
ሠንጠረዥ 3.1-5 የኢትዮጵያ የጤፍና በቆሎ ምርት ደረጃ ..................................................3-9
ሠንጠረዥ 3.1-6 የስንዴ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ.............................3-9
ሠንጠረዥ 3.1-7 በኢትዮጵያ የጥራጥሬ ምርትና የገበያ ድርሻ ..........................................3-11
ሠንጠረዥ 3.1-8 በደ/ብብ/ሕ/ክ/ የጥራጥሬ ምርትና የገበያ ድርሻ.........................................3-12
ሠንጠረዥ 3.1-9 የባቄላ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ.............................3-13
ሠንጠረዥ 3.1-10 የቦሎቄ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ .......................3-15
ሠንጠረዥ 3.1-11 የአተር ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ.........................3-16
ሠንጠረዥ 3.1-12 በኢትዮጵያ የአትክልት* ምርትና የገበያ ድርሻ መጠን..........................3-17
ሠንጠረዥ 3.1-13 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የአትክልት ምርትና የገበያ ድርሻ መጠን .......................3-17
ሠንጠረዥ 3.1-14 የጎመን ምርትና የገበያ መጠን በዞን.....................................................3-18
ሠንጠረዥ 3.1-15 በኢትዮጵያ የቃሪያ ምርት የገበያ ድርሻ.................................................3-20
ሠንጠረዥ 3.1-16 የቃሪያ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና ልዩ ወረዳ...................................3-21

ሠንጠረዥ 3.1-17 በኢትዮጵያ የበርበሬ ምርትና የገበያ ድርሻ....3-21
ሠንጠረዥ 3.1-18 የበርበሬ ምርትና ገበያ ድርሻ በዞንና በልዩ ወረዳ....3-22
ሠንጠረዥ 3.1-19 በድህረምርትና በሽያጭ እንቅስቃሴ የአርሶአደሮች መረጃ ማጠቃለያ....3-23
ሠንጠረዥ 3.1-20 የቲማቲም ምርትና ገበያ ድርሻ በዞን....3-26
ሠንጠረዥ 3.1-21 በኢትዮጵያና ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ፍራፍሬ ምርት የገበያ ድርሻ....3-27
ሠንጠረዥ 3.1-22 በችርቻሮ ሱቅቆች ያለው ብልሽት....3-29
ሠንጠረዥ 3.1-23 የአቮካዶ ምርትና የገበያ መጠን በዞን....3-29
ሠንጠረዥ 3.1-24 የማንጎ ምርትና የሽያጭ መጠን በዞን....3-31
ሠንጠረዥ 3.1-25 የማንጎን ምርት አርሶአደሩ የሚሰበስብበት ዘዴ....3-32
ሠንጠረዥ 3.1-26 የሙዝ ምርትና የሽያጭ መጠን በዞን....3-33
ሠንጠረዥ 3.1-27 በምርትና ግብይት መካከል ያለ ልዩነት....3-34
ሠንጠረዥ 3.1-28 የሙዝ የዋጋ ሁኔታ (ከአርባምንጭ ወደ አ/አበባ)....3-35
ሠንጠረዥ 3.1-29 የጋሞ ጎፋ የሙዝ ኤክስፖርት ውጤት....3-36
ሠንጠረዥ 3.1-30 የፓፓያ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞን....3-37
ሠንጠረዥ 3.1-31 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የእንሰት ክልላዊና የዞን ምርት....3-37
ሠንጠረዥ 3.1-32 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የስኳር ድንች ክልላዊና ዞናዊ ምርት....3-39
ሠንጠረዥ 3.1-33 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የጎዳሬ ክልላዊና የዞን ምርት....3-40
ሠንጠረዥ 3.1-34 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የካሳቫ ምርት....3-43
ሠንጠረዥ 3.1-35 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የሸንኮራ አገዳ ክልላዊ ምርት....3-43
ሠንጠረዥ 3.1-36 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የዝንጅብል ምርት (2008/2009 እ.ኤ.አ)....3-45
ሠንጠረዥ 3.1-37 በከምባታ ጠምባሮ ዞን የዝንጅብል ምርት (2006/07-2008/09 እ.ኤ.አ)..3-45
ሠንጠረዥ 3.1-38 የሃዶሮ ገበያ የዝንጅብል ዋጋ ከ2003/04-2007/08 (እ.ኤ.አ)....3-48
ሠንጠረዥ 3.2-1 የታወቁ የፍራፍሬና አትክልት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች/ቢዝነስ....3-54
ሠንጠረዥ 3.2-2 ዓመታዊ የምርምር ልማት ዕቅድና አፈጻጸም....3-58
ሠንጠረዥ 3.2-3 ብረታ ብርት ድርጅት (ሶዶ)....3-59
ሠንጠረዥ 3.2-4 የእንጨት ሥራ ድርጅት (ሶዶ)....3-59
ሠንጠረዥ 3.2-5 የሠላም ሀዋሣ የሽያጭ ምዝገባ....3-60
ሠንጠረዥ 3.3-1 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የአምራች ዋጋ መሰብሰቢያ ቦታ ብዛት....3-64
ሠንጠረዥ 3.3-2 የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ መደበኛ የዋጋ መረጃ መሰብሰቢያ የገበያ ማዕከላት....3-65
ሠንጠረዥ 3.3-3 በኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ ድህረገጽ ዋጋ መረጃ የሚሰጥባቸው ሰብሎች....3-65
ሠንጠረዥ 3.3-4 በዓለም የምግብ ፕሮግራም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የዋጋ መረጃ የሚሰበሰብባቸው ወረዳዎች....3-67
ሠንጠረዥ 3.3-5 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የእንስሳት መረጃ አውታርና የእውቀት ስርዓት የተሸፈኑ የገበያ ማዕከላት....3-68
ሠንጠረዥ 3.3-6 በ2008 የተመረጡ 15 የገበያ ሥፍራዎች....3-71
ሠንጠረዥ 3.3-7 መረጃ የሚሰበስቡ ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች....3-72
ሠንጠረዥ 3.3-8 የመረጃ ማሰባሰቢያ ምርቶችሰብልና ሌሎች....3-72
ሠንጠረዥ 3.3-9 የባለሙያዎች ቁጥር በዞን/ልዩ ወረዳ የግብይት ሥራ ሂደት (ሰኔ 2010 እ.ኤአ)....3-74
ሠንጠረዥ 3.3-10 ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 የዝንጅብል ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በጥቅም ላይ የሚውሉ የግንኙነት ዕቃዎች (መጋቢት 2011 እ.ኤ.አ)....3-75
ሠንጠረዥ 3.3-11 ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ቦሎቂ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በጥቅም ላይ የሚውሉ የግንኙነት ዕቃዎች (ሰኔ 2011 እ.ኤ.አ)....3-76
ሠንጠረዥ 3.4-1 የመንገድ አውታር ደረጃና ኃላፊነት....3-79
ሠኝጠረዥ 3.4-2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የመንገድ ሁኔታ....3-81
ሠንጠረዥ 3.4-3 የደ/ብ/ሕ/ክ/ የመንገድ ዕቅድ 2010/11-2014/15 (እ.ኤ.አ)....3-83
ሠንጠረዥ 3.4-4 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የመጋዘን ሁኔታ....3-84

ሠንጠረዥ 3.4-5 በሲዳማ ኤልቶ ዩኒያን ሥር ያሉ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘን ....................3-85
ሠንጠረዥ 3.4-6 የገበያ ቦታ ቆጠራ ደሰሳ ውጤት....................3-87
ሠንጠረዥ 3.4-7 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የህዝብ ብዛት በገበያ ቦታ (2000 ዓ/ም 2007-08 እ.ኤ.አ) ....................3-89
ሠንጠረዥ 3.4-8 የቴሌኮሚኒኬሽን ግብ....................3-90
ሠንጠረዥ 3.4-9 የደ/ብ/ብሕ/ክ/ የቴሌኮሚኒኬሽን ሁኔታ (ታህሣስ 2009 እ፣ኤ.አ) ....................3-91
ሠንጠረዥ 3.5-1 ሀገር አቀፍ የሕ/ሥራ ማህበራት እውነታ....................3-92
ሠንጠረዥ 3.5-2 የሕ/ሥራ ማህበራትና የአባላት ብዛት....................3-93
ሠንጠረዥ 3.5-3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ሁኔታ (2007 እ/ኤ/አ).....3-95
ሠንጠረዥ 3.5-4 የሕ/ሥራ ዩኒያን ቆጠራ ውጤት ....................3-97
ሠንጠረዥ 3.5-5 በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ የተሸጠ እህል መጠን....................3-102
ሠንጠረዥ 3.5-6 የሲዳማ ኤልቶ ዩኑያን ትርፍና ኪሳራ....................3-110
ሠንጠረዥ 3.5-7 የሲዳማ ኤልቶ የሂሣብ ባላንስ ሽት ....................3-111
ሠንጠረዥ 3.5-8 የሂሳብ ዘመን (አንጋጫ የሕ/ሥራ ማህበር ዩኒያን) ....................3-112
ሠንጠረዥ 3.5-9 የሂሳብ መግለጫ (ቦሎሶ ቦምቤ ሕ/ሥራ ማህበር)....................3-113
ሠንጠረዥ 3.5-10 የእህል ሰብል ንግድ ሁኔታ (ቦና ሕ/ሥራ ማህበር) ....................3-114
ሠንጠረዥ 3.6-1 በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል የተደረገ የእህል ግብይት ሚያዝያ 2008-2012....................3-122
ሠንጠረዥ 3.6-2 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘን አድራሻና የመያዝ አቅም ....................3-123
ሠንጠረዥ 4-1 ሰብሎችን በሥርጭት ሁኔታ መደልደል....................4-14
ሠንጠረዥ 4-2 የብርና አገዳ ሰብል አንፃራዊ ሽያጭ በአምራችና ዞን (%)....................4-15
ሠንጠረዥ 4-3 የጥራጥሬ ሰብል አንፃራዊ ሽያጭ በአምራችና ዞን (%) ....................4-17
ሠንጠረዥ 4-4 የአርሶአደሮች ድልድል በገበያ እንቅስቃሴ....................4-24
ሠንጠረዥ 4-5 የትኩረት ጉዳዮችና ፍላጎት በሰብል ዓይነት ባ አካባቢ ....................4-26
ሠንጠረዥ 5-1 የጊዜያዊ መሪ ዕቅዱን ለማረጋገጥ ተግባራዊ የሆኑ 10 የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ....................5-4
ሠንጠረዥ 5-2 ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ማስፋፊያ የተመረጡ ሰብሎችና ዞኖች/ወረዳዎች ....................5-9
ሠንጠረዥ 5-3 በ6 ሰብሎች ደረጃ በደረጃ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የሚስፋፋት አካሄድ ....................5-10
ሠንጠረዥ 5-4 የፍራፍሬ ማውረጃ ቁሳቁስ ለማስተዋወቅ የተመረጡ ወረዳዎች ....................5-15
ሠንጠረዥ 5-5 የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሥርዓት የመዘርጋት ሂደት....................5-34
ሠንጠረዥ 6-1 የፕረጀክት ዕቅድ ዝርዝር ....................6-3

**** ****

# ምዕራፍ 1 መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በሚሊዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብ በየዓመቱ ሥር በሰደደ የምግብ ዕጥረት ሲጠቃ ስለነበረ የምግብ ዋስትናን ማሻሻል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፓብልክ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የቆየ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በነደፈችው የተፋጠነና ዘላቂ ልማት ለደህነት ቅነሳ ዕቅድ የተቀላጠፈ የግብርና ገበያ ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችል እስትራቴጂ ተነድፏል፡፡ ይህም የምግብ ዋስትናን የሚያሻሽል ከመሆኑም ባሻገር ገበያ መር ግብርናን ያስፋፋል፡፡ ስለሆነም የግብይት ሥርዓትን በማሻሻል የግብርና ምርት የጥራት ቁጥጥርን ማስፋፋት፣ የገበያ መረጃ ሥርዓትን መዘርጋት፣ ጉዳዩ የሚያገባቸውን አካላት (ነጋዴዎች፣ ሕ/ሥራ ማህበራት/ ዩኒያኖች) አቅም ማጎልበትና የግብርና የሕ/ሥራ ማህበራትን ማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

በሚያዝያ 2008 (እ.ኤ.አ) የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት ዘመናዊ በሆነ መንገድ የአምስት የግብርና ምርት ውጤቶችን በማጫረት መገበያየት ጀምሯል፡፡ እነዚህም የግብርና ምርት ውጤቶች በቆሎ፣ ቦሎቄ፣ ስንዴ፣ አተርና ቡና ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት ዓላማ፡ 1) ሚዛናዊና ግልጽ ግብይት ሥርዓትን ማስፋፋት፣ 2) የምርት ሥርጭትና ክፍፍልን ማሻሻል (መገዘን፣ ማጓጓዝ፣ ወ.ዘ.ተ.)፣ 3) የጥራት ደረጃና ማረጋገጫ ሴርቲፍኬት አሰጣጥ ሥርዓትን በማስተዋወቅ በግብይት ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን ሥጋት መቋቋም፣ እና 4) ጠቃሚ የገበያ መረጃ ማሰራጨት ናቸው፡፡ የገበያ ማዕከላትን እንዲሁም ለገበያ የሚቀርቡ ምርት ውጤቶች ቁጥር የመጨመር ዕቅድም ተጥሏል፡፡

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግሥት የእህል ሰንሎች በማምረት በሀገሪቱ በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በክፍተኛ ፍራፍሬ፣ አትክልትና ሥራሥር ተክሎችን በማምረትና ለገበያ በማቅረብ የታወቀ ነው፡፡በሀገሪቱ በአለፉት አሥር ዓመታት የነፍስ ወከፍ የብርዕ ሰብል ፍጆታ በ40% ጨምሯል፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ፍላጎትና ፍጆታም እንዲሁ አድጓል፡፡ በመሆኑም የተፋጠነ ዘላቂ ልማት ለድህነት ቅነሳ ዕቅድ እስትራቴጂ እንደተመለከተው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ግብይት ሥርዓት ማሻሻል የተቀላጠፈ የግብርና ግብይት እንዲሁም የአመጋጋብ ሥርዓትን የማበልጸግ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በ2006 (እ.ኤ.አ) የግብርን ግብየት ኤጀንሲን የክልሉን የግብርና ግብይት ሥርዓት ማሳደግ በሚያስችል መልኩ ተቋቁሟል፡፡ ኤጀንሲውም ክልላዊ የገበያ መረጃ ሥርዓትን በመዘርጋት የሚመለከታቸው አካላትንና የሥራ ኃላፊዎችን አቅም በማጎልበት እገዛ መስጠት ጀምሯል፡፡ ይሁንና እልባት ሊሰጣቸው የሚገቡ ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከእነዚህም የገበያ መሠረተ ልማትና ተቋማትን ማሻሻል፤ ለአርሶአደሩ ተገቢ የድጋፍ አገልግሎት ማስፋፋትና የሚመለከታቸው አካላት አቅም ማጎልበት ወ.ዘ.ተ. ይገኙበታል፡፡

በዚህ ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግሥት የጃፓን መንግሥት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ግብይት ሥርዓት ማሻሻያ ጥናት እንዲደግፍ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት የጃፓን ዓለም አቀፍ ተርአዶ ድርጅት (ጃይካ) በመጋቢት ውር 2009 (እ.ኤ.አ) ለዝግጅት የሚረዳ ቅኝትና ጥናት አካሂዷል፡፡ በጥናቱም መነሻ የጃፓን መንግሥት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የግብርና ግብይት ሥርዓት ማሻሻያ የጥናት ፕሮጀክት ለማካሄድ ወስኗል፡፡ የጥናቱም የሥራ አድማስ በመስከረም ወር 2009 (እ.ኤ.አ) ተላይቷል፡፡ (በዕዝል 1 እና 2 ተመልክቷል)፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

### 1.2.1 የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ

(1) የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ምርቶችን እሴት ማሻሻል፣ እና
(2) የክልሉን የግብርና ግብይትን ሥርዓት በማጠናከር የምግብ ዋስትናን ማሻሻል ናቸው፡፡

### 1.2.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

(1) የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የተቀላጠፈ የግብርና ግብይት ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል መሪ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ እና
(2) በጥናቱ ሥራ ሂደት ውስጥ ለኢትዮጵያዊያን አቻ ባለሙያዎች፣ አርሶአደሮች፣ የሕ/ሥራ ማህበራት፣ የግብርና ሕ/ሥራ ዩኒያችና ነጋዴዎች አቅም ማጎልነት ናቸው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አካባቢና የታለሙ ሰብሎች

### 1.3.1 የጥናቱ አካባቢ

(1) ጥናቱ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ሙሉ በሙሉ ይሸፍናል፡፡
(2) የጥናቱን ውጤት ለመፈተሽ የሚረዱ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን በጥናቱ ሂደት ውስጥ በሚከተሉት 8 ዞኖችና 3 ልዩ ወረዳዎች ተመርጧል፡፡
ጉራጌ፣ ሃያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ጋሞጎፋ እና ሲልጤ ዞኖች አላባ፣ አማሮ እና ቡርጂ ልዩ ወረዳዎች

### 1.3.2 የታለሙ ሰብሎች

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ብርዕ ሰብል | : በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ |
| 2. | ጥራጥሬ | : አተር፣ ቦሎቄ፣ ባቄላ |
| 3. | አትክልት | : ጎመን፣ አርንጓዴ እና ቀይ በርበሬ |
| 4. | ፍራፍሬ | : አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ |
| 5. | ሥራሥር ተክሎች | : ካሳቫ፣ እንሰት፣ ስኳር ድንች፣ ጎዳሬ |
| 6. | ሌሎች ሰብሎች | : ሽንኩራ አገዳ፣ ቅመማ ቅመም እንደ ዝንጅብል፣ እርድና ሌሎች |

## 1.4 አቻ ድርጅቶችና እስትሪንግ ኮሚቴ

### 1.4.1 አቻ ድርጅቶች

በግብርና ገጠር ልማት ቢሮ ሥር የተዋቀሩት የግብርና ግብይት የሥራ ሂደት፣ የሕ/ሥራ ልማት የሥራ ሂደት እና የግብርና ኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት አቻ ድርጅቶች ነበሩ፡፡

የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ከጥቅምት 2010 (እ.ኤ.አ) በኂላ በሁለት ተክፍሎ የግብርና ቢሮ እና የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በመሆን እንደገና ተዋቀረ፡፡ በዚሁ መነሻ ታህሣሥ 2101 (እ.ኤ.አ) በተካሄደ ስብሰባ በቃለ ጉባኤ እንደተመከተው በግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ (የግብይት የሥራ ሂደት እና የሕ/ሥራ ልመት የሥራ ሂደት) በግብርና ቢሮ (የኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት) የጥናቱ አቻ ድርጅቶች እንዲሆኑ መረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡ (በዕዝል 3 ይመልከቱ)፡፡

### 1.4.2 እስትሪንግ ኮሚቴ

በኢትዮጵያ በኩል የእስትሪንግ ኮሚቴ አባልነት የግብርና ቢሮ እና የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ እንደገና መዋቀርን ተከትሎ ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን ዝርዘሩም አንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

<u>በኢትዮጵያ በኩል</u>

1. የግብርና ቢሮ ኃላፊ (ሰብሳቢ)
2. የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ
3. የግብይት የሥራ ሂደት፣ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ
4. ሕ/ሥራ ልማት የሥራ ሂደት፣ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ
5. ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሥራ ሂደት፣ የግብርና ቢሮ
6. ቅድመ ማስጠንቀቂያና የምግብ ዋስትና የሥራ ሂደት፣ የግብርና ቢሮ
7. ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
8. የክልሉ መንገዶች ባለሥልጣን
9. ሌሎች በሊቀመንበሩ በኩል የሚወከሉ የሚመለከታቸው ድርጅቶች


<u>በጃፓን በኩል</u>

1. የጃፓን የጥናት ቡድን
2. ጃይካ የኢትዮጵያ ጽ/ቤት

## 1.5 የጥናቱ አድማስ

### 1.5.1 የጥናቱ የጊዜ ሠሌዳ

የጥናቱ አጠቃላይ የሥራ ጊዜ ሠሌዳ በሚከተለው ቻርት ተመልክቷል፡፡ ጥናቱ ጥር 2010 እስከ ህዳር 2012 (እ.ኤ.አ) በአሉ 35 ወራት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል፡፡




**ምስል 1-1 አጠቃላይ የጥናቱ የጊዜ ሠሌዳ**

### 1.5.2 የመሪ ዕቅድ ዝግጅት

ጥናቱ በአራት ዘርፍ የተዋቀረ ለግብርና ግብይት ልማት የሚያገለግሉ እስትራቴጅዎችና ፕሮጀክቶችን ለማዘጋጀት ዓላማ አርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አራቱ የግብርና ግብይት ዘርፎች (1) የግብርና ግብይት ተቋም፣ (2) የገበያ መሠረተ ልማት፣ (3) የገበያ መረጃ፣ እና (4) እሴት መጨመር (የጥራት ማሻሻል) ናቸው፡፡

ተግባራዊ ሊሆን የሚችል እስትራቴጅዎችን/ዕቅዶችን ለመንደፈ ዘርዘር ያለ ነባራዊ ሁኔታዎችን የሚቃኝ ጥናት በማካሄድ ችግሮች/የተለያዩ ጉዳዮች የተለዩ ሲሆን የልማት እስትራቴጅዎች/ ዕቅዶች በምዕራፍ 1 ወቅት ተረቀዋል፡፡ የጥናቱ የልማት ንድፈ-ሀሳብ የሙከራ ፕሮጅክቶች በተካሄዱበት ምዕራፍ 2 ወቅት ተፈትሸዋል፡፡ ከሙከራ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተገኘ ውጤትና ተሞክሮ ተመሥርቶ የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2017 እ.ኤ.አ) የተቀረጸ ሲሆን ከላይ በተመለከቱ አራት ዘርፎች አኳያ አፈጻጸም ዕቅድና መርሐግብር ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.6 የጥናቱ አፈጻጸም

### 1.6.1 ምዕራፍ 1

(1) በአንደኛ ዓመት የመጀመሪያ መስክ ሥራ (ጥር -- ሚያዝያ 2010 እ.ኤ.አ)

ሀ) ለእስትሪንግ ኮሚቴ የቅኝት ጥናት ሪፖርት ገለጻና ውይይት
ለ) የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርና ልማት መረጃና የተለያዩ ጽሑፎች በማሰባሰብ መመርመር
ሐ) የመስክ ቅኝት በማድረግ የግብርና ምርት ልማትና ግብይት ተጨናጥ ሁኔታ መረዳት
መ) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት (1) ማዘጋጀትና ለግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ማቅረብ

(2) በአንደኛ ዓመት ሁለተኛ መስክ ሥራ (ሐምሌ -- መስከረም 2010 እ.ኤ.አ)

ሀ) ለእስትሪንግ ኮሚቴ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት (1) ማቅረብና መወያየት
ለ) የግብርና ግብይት ሥርዓት የሚሻሻልበትንና ተገቢ ምላሽ የሚሰጥበትን ሁኔታ ችግሮችንና የተለያዩ ጉዳዩችን በመለየት መመርመር
ሐ) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ዕቅድ የአቅም ግንባታ መርሐግብር ማዘጋጀት፡፡ ከቀረቡ 20 የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች 10 ፕሮጀክቶችን ከግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ እንዲሁም ጃይካ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር ተመርጠዋል፡፡
መ) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅትና ከድርጅቱ ውጪ ያለውን የስንዴ ጥራት ማወዳደሪያ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክትን ተመለከተ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ጋር መወያየት፡፡
ሠ) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን ያካተተ መሸጋገሪያ ሪፖርት (1) ማዘጋጀትና በመስከረም ወር 2011 (እ.ኤ.አ) ለእስትሪንግ ኮሚቴ ማቅረብና መወያየት

### 1.6.2 ምዕራፍ 2

(1) በሁለተኛ ዓመት የተካሄደ መስክ ሥራ (ጥር --ነሐሴ 2011 እ.ኤ.አ)

ሀ) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ሰነድና ጊዜያዊ የመሪ ዕቅድ እስትራቴጅዎች ያካተተ መሸጋገሪያ ሪፖርት (1) ለእስትሪንግ ኮሚቴ መግለጽና መወያየት
ለ) ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶቹ አቻ ባለሙያዎች ምደባ ማካሄድ
ሐ) አሥሩን የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ማድረግ መጀመር
መ) የመነሻ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ
ሠ) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት (2) የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በማካተት ማዘጋጀት እንዲሁም ለእስትሪንግ ኮሚቴ ማቅረብና መወያየት፡፡ ይህም በሚያዝያ 2011 (እ.ኤ.አ) ተካሂዷል፡፡
ረ) በሌሎች ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ድጋፍ ከሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ጋር የሚኖረውን የሥራ ትብብር ማመቻቸት (ዓለም የምግብ ፕሮግራም/ግዢ ለልማት፣ ዓለም ባንክ/ የግብርና ዕድገት ፕሮግራም፣ ዓለም አቀፍ ገንዘብ ለግብርና ልማት/ የግብርና ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት)
ሰ) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጀትና ከድርጅቱ ውጪ ያለውን የስንዴ ጥራት ማወዳደሪያ ሙከራ ተግባራዊ ማድረግ
ሸ) የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት መርሀ ማዘጋጀት
ቀ) በሁለተኛ ዓመት የተካሄደ የመስክ ሥራ ውጤቶችን በማጠናቀር መሸጋገሪያ ሪፖርት (2) ማዘጋጀት፤ ለእስትሪንግ ኮሚቴ ነሐሴ 2011 (እ.ኤ.አ) በማቅረብ መግለጫ በመስጠት ውይይት ተካሂዷል፡፡

(2) በሦስተኛ ዓመት የመጀመሪያ መስክ ሥራ (ጥቅምት 2011--መጋቢት 2012 እ.ኤ.አ)

ሀ) የአስሩን የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን የአቅም ግንባታ መርሐግብርን ጨምሮ

ተግባራዊነቱን መከታተል

ለ) ከሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች የተገኘውን ውጤትና ተሞክሮ ግልጽ ለማድረግ የውስጥ ግምገማዎችን ማካሄድ

ሐ) ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት የቀረበ ቴክኒካዊ ሀሳብ፤ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጀትና ከገበያ ድርጅቱ ውጪ ያለውን የስንዴ ጥራት ማወዳደሪያ ጥናት ሪፖርት ለድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ቀርቧል፡፡ የጥናቱን ውጤት በመጠቀም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጀት ስንዴ አጫርቶ የማገበያት ሥራውን እንዲያስቀጥል ከጥናት ቡድኑ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

መ) የመሪ ዕቅዱን መሠረታዊ መርሆችን አጠናቆ የመለየት እንዲሁም ከሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች በተገኘው ውጤትና ተሞክሮ ተመስርቶ ጊዜያዊ የፕሮጀክት ዕቅዶችን ማዘጀት፡፡

ሠ) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት (3) ማዘጋጀትና በመጋቢት ወር 2012 (እ.ኤ.አ) ለአስትሪንግ ኮሚቴ ማቅረብ፣ ገለፃና ውይይት ማድረግ

ረ) የስልጠና እና የኤክስቴንሽን አጋዥ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን (መስል፣ ፖስተር፣ ወ.ዘ.ተ) የማዘጋጀት ሥራ ማጠቃለል፡፡

### (3) በሦስተኛ ዓመት ሁለተኛ መስክ ሥራ (ነሐሴ 2011--ጥቅምት 2012 እ.ኤ.አ)

ሀ) ከግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ጋር በረቂቅ ዕቅድ ላይ ገለፃ በመድግ መወያየት

ለ) በአምስት ዓመቱ መሪ ዕቅድ ላይ ለተለያዩ ዕርዳታ ሰጪ/ መንግሥታዊ ያለሆነ ድርጅቶች[1] ሴሚናር መስጠት

ሐ) የጥናቱንና የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ቁሳቁስ/ መገልገያ ማሣሪያዎች ለግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ማስረከብ

### 1.6.3 በጃፓን ያቻ ባለሙያዎች ስልጠና

ቴክኒካዊ ሙያን ከማስተላለፊ አኳያ 2 የአቻ ባለሙያዎች ስልጠና ጃፓን ተካሂዷል፡፡ መጀመሪያ ስልጠና በጥቅምት ወር 2010 (እ.ኤ.አ) ሁለተኛው ድግሞ ግንቦት 2012 (እ.ኤ.አ) ተካሂዷል፡፡

## 1.7 የሪፖርቱ ጥንቅር

ዋና ሪፖርት ከ1-7 ያሉትን ምዕራፎች አካቷል፡፡
ምዕራፍ 1 የጥናቱን መግቢያ፣ ዳራ፣ ዓላማ እና አጠቃላይ አወቃቀሩን ይገልፃል፡፡ በምዕራፍ 2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ አጠቃላይ ሁኔታ በአጭሩ ተብራርቷል፡፡ በምዕራፍ 3 ውስጥ በአሁኑ ወቅት ያለው አመራረት፣ በጥናቱ የታለሙ ሰብሎች ድኅረምርት አያያዝ፣ ግብይትና ተያያዥነት ያለው የሥራ ዘርፎችን ይገልፃል፡፡ በጥናቱ ወቅት የተለዩ ችግሮችና የልማት ጉዳዮች/ አርስቶች በምዕራፍ 4 ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

በምዕራፍ 5 በመጀመሪያው ክፍል የመሪ ዕቅዱ የተዘጋጀበት ሂደት ተብራርቷል፡፡ የልማት ዓላማና የአፈጻጸም ዘዴ (ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ እሴት መጨመር፣ የገበያ መሠረተ ልማት፣ የገበያ መረጃ አገልግሎት እና የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች አቅም ማሻሻያ ጥረት ተደጋጋፊነት በአለው መንገድ ማስኬድ) በቀጣይነት ቀርቧል፡፡ ከዚያም በኋላ የአራቱ ሥራ ዘርፎች የልማት እስትራቴጂ፤ (1) የገበያ መረጃ አገልግሎት ሥርዓት ማጠናከር፣ (2) ተጨማሪ እሴት ያለው ገበያን ማስተዋወቅ ትረፋማነትን ማሳደግ፣ የግብይት ተግባራትን ለማቀላጠፍ የሚረዳ የገበያ መሠረተ ልማትን ማሻሻል፣ እና የግብርና ግብይት ተቋማዊ ሥርዓት ማስተካከያና አቅም ግንባታ

[1] ሴሚናሩ በመጀመሪያ ነሐሴ 2012 (እ.ኤ.አ) ለማካሄድ ታስቦ ነበር፡፡ ይሁንና በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ወደ ጥቅምት ወር 2012 (እ.ኤ.አ) ተሸጋግሯል፡፡

ተጠቃልዋል፡፡ በምዕራፍ 5 የተመለከተው የልማት እስትራቴጂን መሠረት በማድረግ የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን በሌሎች አካባቢዎች ወይንም ሌሎች የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው ስብሎችን ለማስፋፊት ተግባራዊ የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ዕቅድ በምዕራፍ 6 ተመልክቷል፡፡ ምዕራፍ 7 የተነደፉ ፕሮጀክት ዕቅዶች ተፈጻሚ እንዲሆኒ የሚያነሳሳና የሚቀሰቅስ ማጠቃለያ ተካቷል፡፡

# ምዕራፍ 2 የሀገሪቱና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ገጽታ


## 2.1 የግብርና ሥነምህዳርና የሲሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ

### 2.1.1 የግብርና ሥነምህዳር ሁኔታ


ኢትዮጵያ 3.28-11.48 ድግሪ ሰሜናዊ ላቲቲዩድ እና 33.00-47.52 ድግሪ ምሥራቃዊ ሎንግቲዩድ መካከል ትገኛለች፡፡ ሀገሪቱ የባህር በር የሌላት ሲሆን በስተሰሜን ኤርትሪያ፣ በሰተሰሜናዊ ምሥራቅ ጂቡቲ፣ በስተምሥራቅ ሶማሌ፣ በሰተደቡብ ኬንያ እና በሰተምዕራብ ሱዳን ያዋሱኗታል፡፡ የሀገሪቱ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 1,104,300 እስኩዌር ኪ.ሜትር ነው፡፡ በምስል 1 ላይ እንደተመለከተው ሀገሪቱ ትልቅ የመሬት ከፍታ ቦታዎች ልዩነት (ልዩነቱም ከ110 ሜትር ከባህር ወለል በታች ከሚገኘው ደናክል ዝቅተኛ ሥፍራ እስከ 4620 ሜትር ከባህር ወለል በላይ የሚገኘው በኢትዮጵያ ክፍተኛውን ራስ ዳሽን ተራራ ይደርሳል) ያላት ሲሆን በሀገሪቱ ከፍተኛ የአየር ንብረት ልዩነቶችንም ያመጣል፡፡ እንደ ኮኤፐያን የአየር ንብረት ክፍፍል ሰሜናዊ ተራራማ ቦታዎች ቴምፐሬት ክረምት አነስተኛ ዝናብ የአየር ንብረት፣ ደቡባዊ አካባቢዎች ቴምፐሬት እርጥበታማ የአየር ንብረት፣ በደቡብና ምዕራብ የሚገኙ ዝቅተኛ ቦታዎች ትሮፒካል ሳቫና የአየር ንብረት፣ አፋር እና ሶማሌ ክፊል በርሃ እስከ በርሃ አየር ንብረት ውስጥ ይካተታሉ፡፡

ዝናብን በተመለከተ በምስል 2 እንደሚታየው በአጠቃላይ ምዕራባዊ ከፍተኛ ቦታዎች ከፍተኛ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠንም ከ1200 ሚ.ሜትር በላይ ነው፡፡ በተቃራኒው አብዛኛው አፋርና ሶማሌ አካባባ የሚገኘው ዝቅተኛ ቦታ አነስተኛ ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከ400 ሚ.ሜትር በታች ነው፡፡


በኢትዮጵያ የሰብል ልማት በዓመታዊ የዝንብ ስርጭት ላይ በአብዛኛው የተመሠረተ ነው፡፡ በምስል 3 ላይ እንደተመለከተው መኸር እና በልግ የሚባሉ ሁለት ዋኝኛ የዝናብ ወቅቶች አሉ፡፡ መኸር ረዥሙ የዝናብ ወቅት ሲሆን ከሰኔ እስከ መስከረም ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡፡ በልግ አጭሩ የዝናብ ወቅት ሲሆን ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለውን ጊዜ ያሸፍናል፡፡ አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል የመኸር እና በልግ የዝናብ ወቅቶች ያሉት ሲሆን የሚጀምሩበትም ጊዜ ይለያያል፡፡ በሰሜን የመኸር ወቅት ቀደም ብሎ በሰኔ ወር አጋማሽ አካባቢ የሚጀምር ሲሆን በደቡብ እስከ ጥቅምት ወር ዘግይቶ ይጀምራል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ አካባቢዎች ያለው የሰብል ልማት በአብዛኛው ከመኸር ዝናብ ጋር ተያያዥነት አለው፡፡




1. ከመሬት ከፍታ




2. ዓመታዊ ዝናብ




3. የዝንብ ሥርጭት




4. የግብርና ሥነመህዳር ቀጠና

ምንጭ: CSA, EDRI, IFPRI; Atlas of the Ethiopian Rural Economy

**ምስል 2.1-1 በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሁኔታ**

በኢትዮጵያ የግብርና ሥነምህዳር የሚወሰነው በመሬት ከፍታ ላይ ተመሥቶ ነው፡፡ ከዚህ በታች እንተጠቀሰው 6 ዋና ዋና የሥነምህዳር ቀጠናዎች አሉ፡፡ ከስድሰቱ ቀጠናዎች ሦስቱ ዋንኛ የእህል ሰብል አብቃይ ናቸው፡፡ እነርሱም ቆላ፣ ወይናደጋ እና ደጋ ይባላሉ፡፡ በተለይም ወይናደጋ እና ደጋ ለእህል ምርት ምቹ ሲሆኑ ስንዴ፣ ጤፍና በቆሎ የሚመረትባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ 2.1-1 የኢትዮጵያ የግብርና ሥነምህዳር ቀጠና ክፍፍል**

| | ቀጠና | የመሬት ከፍታ | | የሰብል ምርት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በርሃ | ዝቅተኛ መሬት | < 500 ሜትር ከባህር ወለል በላይ | በጣም ውስን (በምስራቅ በርሃማ አካባቢ) ሥራሥርና በቆሎ (ምዕራብ ርጥበታማ አካባቢ) |
| 2 | ቆላ | | 500 < 1500 ሜትር ከባህር ወለል በላይ | ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ሰሊጥ፣ አኩሪ አተር፣ ኦቾሎኒ |
| 3 | ወይናደጋ | ከፍተኛ መሬት | 1500 < 2300 ሜትር ከባህር ወለል በላይ | ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሽምብራ |
| 4 | ደጋ | | 2300 < 3200 ሜትር ከባህር ወለል በላይ | ገብስ፣ ስንዴ፣ የቅባት እህሎች፣ ጥራጥሬ |
| 5 | ውርጭ | | 3200 < 3700 ሜትር ከባህር ወለል በላይ | ገብስ |
| 6 | ቁር | | >3700 ሜትር ከባህር ወለል በላይ | የግጦሽ ቦታ |

ምንጭ: Data from CSA, EDRI, IFPRI; Atlas of the Ethiopian Rural Economy

**<u>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል</u>**

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የሚገኘው በሀገሪቱ ደቡባዊና ደቡብ-ምዕራብ አካባቢ ነው፡፡ ክልሉም 4.43-8.53 ድግሪ ሰሜናዊ ላቲቱዩድና 34.88-39.14 ደግሪ ምሥራቃዊ ሎንግቱዩድ ማካካል ይገኛል፡፡ ክልሉን ኬንያ በስተደቡብ፣ ሱዳን በደቡባዊ ምዕራብ፣ ጋምቤላ ክልል በስተሰሜናዊ ምዕራብ እና ኦሮሚያ በስተሰሜናዊ ምዕራብ፣ በሰተሰሜን እና ምሥራቅ ያዋሱኑታል፡፡ አጠቃላይ የክልሉ ቆዳ ስፋት 110,932 እስኩዌር ኪ.ሜትር የሚገመት ሲሆን የሀገሪቱን 10% ያህል ይሆናል፡፡ የክልሉ መሠረታዊ የተፈጥሮ ሁኔታ መረጃ እንሚከተው ተመልከቷል፡፡

### ሠንጠረዥ 2.1-2 መሠረታዊ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የተፈጥሮ ሁኔታ መረጃ

| ተ.ቁ. | ዞን/ ልዩ ወረዳ | ጠቅላላ መሬት (እስኩዌር ሜትር) | ዓመታዊ አማካይ የአየር ሙቀት (ድግሪ ሴትግሬድ) | ዓመታዊ አማካይ የዝናብ መጠን (ሚ.ሜትር) | ከመሬት ከፍታ (ሜትር) |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክልል | 110,931.90 | 7.5 - >27.5 | 400 - 2200 | 376 - 3500 |
| 1 | ጉራጌ | 5,932.00 | 7.5 - 25.0 | 801 - 1400 | 1001 - 3500 |
| 2 | ስልጤ | 2,537.50 | 10.1 - 22.5 | 801 - 1200 | 1501 - 3500 |
| 3 | ሃዲያ | 3,850.20 | 12.6 - 27.5 | 801 - 1400 | 501 - 3000 |
| 4 | ከምባታ ጠምባሮ | 1,523.60 | 12.6 - 27.5 | 1001 - 1400 | 501 - 3000 |
| 5 | ወላይታ | 4,471.30 | 15.1 - 27.5 | 801 - 1600 | 501 - 3000 |
| 6 | ሲዳማ | 6,972.10 | 10.1 - 25.0 | 801 - 1600 | 1001 - 3500 |
| 7 | ጌድኦ | 1,347.00 | 12.6 - 22.5 | 1001 - 1800 | 1501 - 3000 |
| 8 | ጋሞ ጎፋ | 12,581.40 | 10.1 - 27.5 | 801 - 1800 | 501 - 3500 |
| 9 | ዳውሮ | 4,436.70 | 15.1 - 27.5 | 1201 - 1800 | 501 - 3000 |
| 10 | ከፋ | 10,602.70 | 10.1 - >27.5 | 1001 - 2200 | 501 - 3500 |
| 11 | ሸካ | 2,134.30 | 15.1 - 25.0 | 1800 - 2200 | 1001 - 3000 |
| 12 | ቤንች ማጂ | 19,965.80 | 15.1 - >27.5 | 400 - 2000 | < 500 - 2500 |
| 13 | ደቡብ ኦሞ | 23,535.00 | 10.1 - >27.5 | 400 - 1600 | 376 - 3500 |
| 14 | አላባ ልዩ ወረዳ | 855.00 | 17.6 - 22.5 | 601 - 1200 | 1501 - 2500 |
| 15 | የም ልዩ ወረዳ | 724.50 | 15.1 - 22.5 | 801 - 1400 | 501 - 3000 |
| 16 | ኮንታ ልዩ ወረዳ | 2,196.80 | 15.1 - 27.5 | 1401 - 1800 | 501 - 3000 |
| 17 | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | 407.50 | 17.6 - 27.5 | 1401 - 1600 | 501 - 2000 |
| 18 | አማሮ ል ወረዳ* | 1,597.20 | 12.6 - 25.0 | 801 - 1000 | 501 - 3000 |
| 19 | ቡርጂ ልዩ ወረዳ* | 1,374.60 | 15.1 - 27.5 | 801 - 1000 | 501 - 2500 |
| 20 | ደራሼ ልዩ ወረዳ* | 1,532.40 | 15.1 - 27.5 | 601 - 1600 | 501 - 2500 |
| 21 | ኮንሶ ልዩ ወረዳ* | 2,354.30 | 17.6 - 27.5 | 601 - 1200 | 501 - 2000 |

ማስታወሻ፡ 4 ልዩ ወረዳዎች (አማሮ፣ ቡድረጂ፣ ድራሼ፣ ኮንሶ) በመዋሃድ ሰገን አካባቢ የሚባል አዲስ ዞን ታህሣሥ 2011 (እ.ኤ.አ) መስርተዋል፡፡ ከነሐሴ ወር 2011 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ክልሉ 14 ዞኖችና 4 ልዩ ወረዳዎች አሉት፡፡
ምንጭ: የክልሉ አስታስቲክስ አብስትራክት (2006-07 እ.ኤ.አ)

ክልሉ ከዚህ በታች እንተገለጸው 5 የግብርና ሥነምህዳር ቀጠናዎች አሉት፡፡ እነርሱም ከፊል በረሃ፣ ቆላ፣ ወይናደጋ፣ ደጋና ውርጭ የሚባሉ ሲሆን 350 እስከ 4200 ሜትር ከባህር ወለል መካከል ይገኛሉ፡፡ አብዛኛው የክልሉ አካባቢ 80% የሚሆነው ቆላ እና ወይና ደጋ አካባቢ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች እንተመለከተው በክልሉ ብዙ አይነት ስብሎች ይለማሉ፡

### ሠንጠረዥ 2.1-3 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ሥምህዳር ቀጠናዎች

| ተ.ቆ. | ቀጠና | አካባቢ | | አማካይ የአየር ሙቀት | የመሬት ከፍታ | ተስማሚ ሰብሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፊል በርሃ | 9,540 እስኩዌር ሜትር | 8.6 % | >27.5 ድግሪ ሴ.ግሬድ | 376 - 500 ሜ | - ዘንዳጋ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሩዝ<br>- አኩሪ አተር፣ ሱፍ፣ ሰሊጥ<br>- ጥጥ፣ ስኳር ድንች፣ ካሳቫ፣ ሸንኮራ አገዳ |
| 2 | ቆላ | 54,246 እስኩዌር ሜትር | 48.9 % | 22.5-27.5 ድግሪ ሴ.ግሬድ | 500 - 1300 ሜ | - ዘንዳጋ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሩዝ<br>- በሎቄ፣ አኩሪ አተር፣ ሲፍ፣ ሰሊጥ<br>- ጥጥ፣ ስኳር ድንች፣ ካሳቫ፣ ሸንኮራ አገደ፣ በርበሬ፣ ብርቱካን፣ ቡና |
| 3 | ወይና ደጋ | 37,606 እስ.ኩዌር ሜትር | 33.9 % | 17.5-22.5 ድግሪ ሴ.ግሬድ | 1300 - 2200 ሜ | - ዘንዳጋ, በቆሎ፣ ማሽላ፣ ሩዝ ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ ዳጉሳ<br>- አኩሪ አተር፣ ሲፍ፣ በሎቄ፣ ሄምቡራ፣ ምስር፣ ኑግ፣ ባቄላ፣ አተር<br>- ስኳር ድንች፣ በርበሬ፣ ቡርቱካን፣ ቡና፣ ሻይ ቅጠል፣ ድንች፣ እንሰት |
| 4 | ደጋ | 9,318 እስኩዌር ሜትር | 8.4 % | 12.5-17.5 ድግሪ ሴ.ግሬድ | 2200 - 3000 ሜ | - ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ ዳጉሳ<br>- ሱፍ፣ ሹምቡራ፣ ምስር፣ ኑግ፣ አተር፣ ተልባ፣ ድንች፣ እንሰት |

| ተ.ቁ. | ቀጠና | አካባቢ | | አማካይ የአየር ሙቀት | የመሬት ከፍታ | ተስማሚ ሰብሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ውርጭ | 222 እስኩዌር ሜትር | 0.2 % | 7.5-12.5 ድግሪ ሴ.ግሬድ | 3000 - 3500 ሜ | - በንስ፣ ዳጉሳ<br>- አተር፣ ባቄላ፣ ተልባ፣ ድንች፣ እንሰት |

ምንጭ: የኢትዮጵያ የአየር ንብረትና የግብርና ሥነምህዳር ሀብት (NMSA 1996 እ.ኤ.አ)


## 2.1.2 ሶሽዩ-ኢኮኖሚ ሁኔታ

### (1) የህዝብ ጉኔታ[1]

ሀገሪቱ ዘጠኝ ክልላዊ ምንግሥታትና ሁለት ልዩ አስተዳደር አካባቢዎች አሉዋት፡፡ እንደዓለም ጠቋሚ መረጃ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት በ2008 (እ.ዘ.አ) 80,713,434 እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን ዓመታዊ የህዝብ ዕድገትም ለአለፉት 2 አሥር ዓመታት 3 % ነበር፡፡

| Geographic Area | መልክአምድራዊ አካባቢ | 1995-2000 Rural ገጠር | 1995-2000 Urban ከተማ | 1995-2000 Total ጠቅላላ | 2001-2005 Rural ገጠር | 2001-2005 Urban ከተማ | 2001-2005 Total ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| National | ብሔራዊ | 2.74 | 4.38 | 2.92 | 2.57 | 4.10 | 2.73 |
| Tigray | ትግራይ | 2.5 | 4.9 | 2.85 | 2.3 | 4.5 | 2.67 |
| Afar | አፋር | 2.2 | 3.8 | 2.39 | 2.0 | 4.1 | 2.20 |
| Amhara | አማራ | 2.6 | 4.9 | 2.86 | 2.5 | 4.4 | 2.67 |
| Oromia | ኦሮሚያ | 2.8 | 5.1 | 3.09 | 2.6 | 4.7 | 2.87 |
| Somali | ሶማሌ | 2.3 | 4.5 | 2.58 | 2.3 | 4.5 | 2.63 |
| Benishangul Gumuz | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 2.5 | 4.7 | 2.57 | 2.4 | 4.4 | 2.54 |
| SNNP | ደብብህ | 3.1 | 5.3 | 3.26 | 2.8 | 4.8 | 2.92 |
| Gambela | ጋምቤላ | 2.2 | 4.7 | 2.62 | 2.2 | 4.4 | 2.57 |
| Harari | ሐረሪ | 2.5 | 4.2 | 3.50 | 2.6 | 3.8 | 3.49 |
| Addis Ababa | አዲስ አበባ | -- | 2.9 | 2.90 | -- | 2.8 | 2.80 |
| Dire Dawa | ድሬዳዋ | 2.2 | 4.8 | 4.00 | 2.3 | 4.3 | 3.80 |

Data source: 2004 projections based on 1994 Ethiopian Population and Housing Census, Central Statistical Agency.




የየክልሉ የህዝብ ዕድገት ደረጃ (%) የህዝብ ብዛት ነጥብ ካርታ (1 dot=500 people)

ምንጭ: CSA, EDRI, IFPRI; Atlas of the Ethiopian Rural Economy


**ምስል 2.1-2 ብሔራዊ የህዝብ ብዘት ሁኔታ**

**<u>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል</u>**

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ 13 ዞኖችና 8 ልዩ ወረዳዎች፣ 126 ወረዳዎች እና 3678 የገጠር ቀበሌዎች ነበሩት፡፡ ከተማ በተመለከተ 22 የከተማ አስተዳደሮች እና 114 ምስክርነት ያገኙ በማዘጋጃ ቤት የሚተዳደሩ ከተሞች ያሉ ሲሆን በሥራቸው 238 የከተማ ቀበሌዎች[2] ይዘዋል፡፡ አጠቃላይ የህዝብ 15,760,743 ሲሆን ወደ 50.2% ሴቶች ሲሆኑ 91% የሚሆነው በገጠር ነዋሪ ነው፡፡ ክልሉ ከሀገሪቱ ህዝብ ወደ 20% የያዘ ሲሆን በህዝብ ብዛትም ከኦሮሚያና አማራ ክልሎች በመቀጠል በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የክልሉ ህዝብ በአብዛኛው በወጣት የተዋቀረ ነው፡፡ ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት 45% የሚሆነው የክልሉን ህዝብ ይሸፍናሉ፡፡ ከ65 ዓመት በላይ በሆነ የዕድሜ ክልል ያሉ 2.2% ብቻ ይሆናሉ፡፡ ከ15-64 ዓመት የዕድሜ ክል ያሉ 52.8% ናቸው፡፡ አማካይ የቤተሰብ ብዛት 4.6 ሰው ሲሆን አማካይ የህዝብ ጥግግት 142 ሰው በአንድ እስኩዌር ኪ.ሜትር ነው፡፡

[1] በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ቁጥሮች በሙሉ የተገኙት ከዓለም የልማት ጠቋሚ መረጃ፣ መስከረም 2009 (እ.ኤ.አ)

[2] ምንጫ፡ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ክልላዊ እስታስቲክስ አብስትራክት (2006-07 እ.ኤ.አ), ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ ሰኔ 2007 (እ.ኤ.አ). 4 ለልዩ ወረዳዎች አማሮ፣ ቡርጂ፣ ደራሼና ኮንሶ) ተዋህደው የሰገን አካባቢ ዞን ከታህግሥ 2011 (እ.ዘ.አ) መስርተዋል፡፡ ከነንሴ 2011 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ 14 ዞኖችና 4 ልዩ ወረዳዎች አሉት





ምስል 2.1-3 የደ/ብ/ብ/ህ/የህዝብ ብዛት ፒራሚድ

(2) የእርሻ መሬት ይዞታ

በኢትዮጵያ መሬት በጋራ ባለቤትነት ሥር የሚገኝ ሲሆን እያንዳንዱ አርሶአደር በባሌቤትነት ሊይዝ አይችልም፡፡ ይሁንና መሬት ላልተወሰነ ጊዜ ለእየአንዳንዱ ቤተሰብ የተሰጠ ሲሆን ማከራየትና ለወራሾቻቸው ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች በአማካይ 1.03 ሄ/ር መሬት በቤተሰብ ደረጃ ያላቸው ሲሆን 95% የሚሆነው የሀገሪቱ የሰብል ምርት ያመርታሉ፡፡ በምስል 2.2-3 እንደተመለከተው 82% የሚሆነው አርሶአደር ቤተሰቦች ከ2 ሄ/ር በታች መሬት ያላቸው ሲሆን ወደ 17% የሚሆኑት ከ2-5 ሄ/ር መሬት አላቸው (2005/06 (እ.ዘ.አ)፡፡ በአሁኑ ወቅት የአነስተኛ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬት ከህዝብ ብዛት የተነሳ በብዛት የተከፋፈለና የተቆራረጠ ነው፡፡ (በ1975 እ.ኤ.አ አማካይ የአንድ አርሶአደር ቤተሰብ ይዞታ 1.91 ሄ/ር ነበር)፡፡




ምንጭ: ማዕከላዊ እስታስቲክስ ባለሥልጣን "የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2005/06 (እ.ኤ.አ)"

ምስል 2.1-4 የክልሎች የእርሻ መሬት ይዞታ

<u>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል</u>

የክልሉ የእርሻ መሬት ይዞታ እጅግ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ የተቆራረጠ ነው፡፡ እንደ ማዕከላዊ እስታስቲክስ ባለሥልጣን መረጃ መሠረት 50% የሚሆነው የክልሉ አርሶአደር ቤተሰብ ከ0.5 ሄ/ር በታች የመሬት ይዞታ አለው፡፡ ለአነስተኛ የተቆራረጠ የእርሻ መሬት ይዞታ መኖር ከፍተኛ የህዝብ ብዛት መጨመር በምክንያትነት የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 2.1-4 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የእርሻ መሬት ይዞታ**


| ድልድል | % አርሶ አደር ቤተሰብ |
|---|---|
| ከ 0.1 ሄ/ር በታች | 9.2% |
| 0.1-0.5 ሄ/ር | 46.0% |
| 0.51-1.0 ሄ/ር | 26.6% |
| 1.1 -2.0 ሄ/ር | 14.7% |
| ከ 2.0 /ር በላይ | 4.7% |

ምንጭ: 2001 (እ.ኤ.አ) ማእከላዊ እስታስቲክስ ባለሥልጣን የግብርና ቤተሰብ ዳሰሳ ጥናት


### (3) የኢኮኖሚ ሁኔታ

የሀገሪቱ አጠቃላይ ብሔራዊ ምርት በ2008 (እ.፣ኤ.አ) 26.49 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገመተ ሲሆን በአለፉት 3 ተከታታይ ዓመታት የ11% ዕድገት እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ የነፍስ ወከፍ አጠቃላይ ብሔራዊ ገቢ 280 የአሜሪካን ዶላር በ2008 (እ.ኤ.አ) ሲገመት የነፍስ ወከፍ የመግዛት አቅምን መሠረት በማድረግ 870 የአሜሪካን ዶላር ይሆናል፡፡ ከሀገሪቱ አጠቃላይ ምርት የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ 43% የሚሸፍን ሲሆን ወደ 85% የሚሆነውም ህዝብ በዚሁ ክፍለ ኢኮኖሚ ሥር ይገኛል፡፡

በአለፉት 6 ዓመት የታየው የዋጋ ንረት ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ በ2003 (እ.ኤ.አ) የተከሰተው ድርቅ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አስከትሏል፡፡ በመሆኑም የዋጋ ንረቱ በ2004 (እ.ኤ.አ) ቀንሷል፡፡ ይሁንና የዋጋ ንረቱ ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ ይገኛል፡፡ በ2008 (እ.ኤ.አ) የዋጋ ንረቱ ከፍተኛ በመሆኑ 29% የደረሰ ሲሆን ከአለፈው ዓመት በ1.7 እጅ በልጧል፡፡




**ምስል 2.1-5 የዋጋ ንረቱ አኳኋን (2003-08 እ.ኤ.አ)**




**ምስል 2.1-6 የውጪና የገቢ ዕቃዎችና አገልግሎቶች አኳኋን (2000-08 እ.ኤ.አ)**

ከዚህ በላይ የየዓመቱ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የውጪና ገቢ ዕቃዎችን አገልግሎቶች ጥመርታ ቀርቧል፡፡ የውጪ ንግድ ጥመርታ ከገቢ ንግድ ጥመርታ አንፃር ዝቅተኛ ሲሆን ለአለፉት 10 ዓመታት ከ13%-15% ልዩነት አሳይቷል፡፡ ዋንኛ የወጪ ንግድ ምርቶች ቡናና የቅባት እህሎች ናቸው፡፡ ነገር ግን የእነዚህ ምርቶች በቀላሉ የዓለም ገበያ ሁኔታና የአየር ፀባይ ተጽዕኖ ይደርስባቸዋል፡፡

## 2.2 የሰብል ልማት ገጽታ

### 2.2.1 የሀገሪቱ የሰብል ልማት

ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሠረት ነው፡፡ ከአጠቃላይ ህዝቡ ወደ 85% የሚሆነው ኑሮው በግብርና ላይ የተመሥረተ ነው፡፡ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትም በከፍተኛ ደረጃ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የተመረኮዘ ሲሆን ግብርና 43% አጠቃላይ የሀገሪቱን ብሔራዊ ምርትና 60% የወጪ ምንዛሪ ግኝትን ይይዛል፡፡ ይሁንና ባህላዊ የሆነ የአነስተኛ አርሶአደሮች እርሻ አሁንም ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ አብዛኛው አርሶአደሮች ቅይት እርሻን የሚያዘወትሩ ሲሆን የሰብል ልማትና የከብት እርባታን ያካሂዳሉ፡፡ ለሰብል ልማትም ከፍተኛው ትኩረት ይሰጣሉ፡፡

ሰብል ልማት የአትዮጵያ ግብርና ልማት ዋንኛ አካል ሲሆን አብዛኛው ህዝብ መተደዳሪያ ነው፡፡ የሰብል ልማት በሀገሪቱ ሶሽዮ ኢኮኖሚ ያለው ሚና የጎላ ሲሆን ዋንኛ የምግብ ምንጭ በመሆን ለኢንዱስትሪ በጥሬ ዕቃነት እንዲሁም ለውጪ ምንዛሪ ግኝት አስተዋጽኦ አለው፡፡ የሰብል ልማት በአብዛኛው በአነስተኛ ባለይዞታ አርሶአደሮች (አነስተኛ ባለይዞታ አርሶአደሮች 95% የሀገሪቱን የሰብል ምርት ያመርታሉ) በዝናብ ላይ በመመርኮዝ ባህላዊ በሆነ መንገድ ነው የሚያመርቱት፡፡ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችና ግብአት አጠቃቀም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ምርታማነትም አነስተኛ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የአርሶአደር ቤተሰብ ገቢ ዝቅተኛ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የብርዕ ሰብሎች (በቆሎ፣ ማሽላ፣ ስንዴ፣ ገብስና ጤፍ) ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ጥራጥሬ፣ ቅባት እህል፣ ሥራሥር፣ አትክልትና ቋሚ ሰብሎች (ቡና፣ ፍራፍሬ፣ ወ.ዘ.ተ.) በተለያየ ደረጃ የሚመረቱ ሲሆን በህብረተሰቡ መተዳደሪያነት ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ጉልህ ሚና አላቸው፡፡

በሀገሪቱ ምዕራባዊ በኩል ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ የኦሮሚያ ምዕራብ ክፍል፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና ትግራይን የያዘ ክፍል ዋንኛ የሰብል ልማት የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ የሚከተለው ሠንጠረዥ የክልሎችን የሰብል ልማት ሁኔታን ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.2-1 የሰብል ምርት በክልል**

| ክልል | ጠቅላላ ምርት (ቶን) | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብርዕ ሰብል | ጥራጥሬ | የቅባት እህል | አትክልት | ሥራሥር | ቋሚ ተክል |
| ኦሮሚያ | 7,178,940 | 774,526 | 284,998 | 224,901 | 517,958 | 782,290 |
| አማራ | 4,545,031 | 913,909 | 213,250 | 79,354 | 309,865 | 134,269 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል | 1,246,267 | 182,173 | 5,181 | 274,158 | 350,964 | 934,029 |
| ትግራይ | 1,041,527 | 83,622 | 109,823 | 16,186 | 18,874 | 4,890 |
| ቤንሻንጉል | 232,013 | 8,951 | 35,474 | 2,897 | 7,720 | 8,789 |
| ሶማሌ | 163,550 | 860 | 3,248 | 34 | 4,910 | 7,112 |
| አፋር | 41,827 | 28 | 695 | 486 | 1,196 | 686 |
| ጋምቤላ | 24,078 | 222 | 140 | 841 | 2,118 | 631 |
| ሐረር | 13,099 | 21 | 2,783 | 0 | 0 | 0 |
| ድሬዳዋ | 10,073 | 318 | 114 | 0 | 0 | 0 |
| ኢትዮጵያ | 14,496,406 | 1,964,630 | 655,705 | 598,857 | 1,213,605 | 1,872,695 |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ባለሥልጣን "የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ) ጥራዝ. VII (ቡልቲን 446)"

ኦሮሚያ፣ አማራና ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ አብዛኛው የሰብል ልማት የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ክልሎች የሀገሪቱን 91.2% ሰብል ምርት ያመርታሉ፡፡ ለብርዕ ሰብል፣ ጥራጥሬ፣ አትክልትና ቋሚ ሰብሎች ልማት ያላቸው አስተዋጽኦ 89.5%፣ 95.2%፣ 96.6% እና 98.8%

እንደቅድተከተሉ ነው፡፡ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአትክልትና ቋሚ ሰብሎች ልማት ጉልህ ቦታ አለው፡፡

በአነስተኛ አርሶአደሮች የሚካሄደው የሰብል ልማት በአብዛኛው ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚመረት ሲሆን ለሽያጭ የሚቀርበው የተወሰነ ነው፡፡ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ እንደተመለከተው የሰብል ምርት አጠቃላይ መረጃ መሠረት ዋንኛ የምግብ ሰብል (ብርዕ ሰብልና ጥራጥሬ) ወደ 60-65% የሚሆነው ምርት ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚውል ሲሆን 15-20% የሚሆነው ብቻ ለገበያ ይቀርባል፡፡ አትክልትና ሥራሥር ተክሎችን በተመለከተ 16-19% የሚሆነው ለሽያጭ ይቀርባል፡፡ የቅባት እህልና ቋሚ ሰብሎች በአብዛኘው ለሽያጭ የሚመረቱ ሰሆን 37-52% የሚሆነው ለገበያ ይቀርባል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.2-2 የሰብል አጠቃቀም**

| የሰብል ዓይነት | አጠቃላይ ምርት (ቶን) | አጠቃቀም በመቶኛ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የቤት ውስጥ ፍጆታ | ሽያጭ | ዘር | የጉልበት ዋጋ በዓይነት | የእንስሳት መኖ | ሌሎች |
| በርዕ ሰብል | 14,496,406 | 65.59 | 15.75 | 13.84 | 1.25 | 0.57 | 3.00 |
| ጥራጥሬ | 1,964,630 | 60.90 | 21.03 | 15.11 | 0.75 | 0.33 | 1.88 |
| የቅባት እህል | 655,704 | 32.89 | 51.84 | 12.40 | 1.42 | 0.10 | 1.35 |
| አትክልት | 598,857 | 77.67 | 18.93 | 1.15 | 0.36 | 0.11 | 1.78 |
| ሥራሥር ተክል | 1,213,604 | 71.88 | 16.33 | 9.76 | 0.30 | 0.53 | 1.19 |
| ቋሚ ሰብል | 1,872,695 | 57.60 | 37.42 | 0.92 | 0.60 | 0.77 | 2.69 |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ባለሥልጣን "የግብርና ናሙና ቅኝት 2008/09 (እ.ኤ.አ) ጥራዝ. VII (ቡልቲን 446)"

## 2.2.2 በደ/ብ/ብሕ/ክ/ የሰብል ልማት

ክልሉ በተለያየ የአየር ንብረት የበለጸገ በመሆኑ የተለያዩ ሰብሎችን እንቡናᎍ በቆሎᎍ ስንዴᎍ ጤፍᎍጥራጥሬᎍ የቅባት እህሎችᎍ እንሰትᎍ ሥራሥርᎍ ፍራፍሬᎍ አትክልትና ቅመማ ቅመም ያመርታል፡፡ የሀገቱ 40% የሚሆነው የቡና ምርት የሚመረተው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ሲሆን በቅመማ ቅመም ምርትም ጉልህ ቦታ አለው፡፡

በሠንጠረዥ 2.2-1 እንደተመለከተው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በሰብል ምርት የጎላ ድርሻ አለው፡፡ የብርዕ ሰብልና ጥራጥሬ በተመለከተ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ 8.6% እና 9.3% ድርሻ እንደቅድመ ተከተል አለው፡፡ አትክልትᎍ እንደቡናᎍ ፍራፍሬና እንሰት የመሳሰሉ ቋሚ ሰብሎች ልማት አስመልክቶ ክልሉ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሲሆን ከሀገሪቱ ምርት 45.6% እና 49.9% ድርሻ እንደቅድመ ተከተሉ አለው፡፡

በክልሉ ውስጥ በተፈጥሯዊ ሁኔታን መሠረት በማድረግ የተለያየ አስተራረስ ዘዴን በመጠቀም የሰብል ልማት ይካሄዳል፡፡ ከተወሰነ የእርሻ መሬት የሚገኘውን ምርት ለማሳደግ ሲባል የብዙ ሰብሎችን ልማት በአንድ ወቅት ማካሄድ የተለመደ ነው፡፡ በአብዛኛው የተለመደው መንቲያ ሰብል ልማትᎍ በቅይጥ ሰብል ልማትᎍ አንዱ ሰብል ከአሸተ በኂላ ሰይሰበሰብ በሥሩ ሌላ ሰብል መዝራት እና ሰብል አቀያይሮ/አዘዋውሮ መዝራት በስፋት የተለመዱ ናቸው፡፡

ከብርዕ ሰብል በቆሎᎍ ጤፍᎍ ስንዴᎍ ገብስና ማሽላ በክልሉ የሚመረቱ ዋንኛ ሰብሎች ናቸው፡፡ ጥራጥሬᎍ የቅባት እህልᎍ ፍራፍሬᎍ አትክልትᎍ ቅመመቅመም በክልሉ የተለያየ አካባቢዎች ይመረታሉ፡፡ ቡና ለሀገሪቱ ሆነ ለክልሉ እጅግ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያለው ሰብል ነው፡፡ የክልሉ የሰብል ልማት በዞን የሚገልጽ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

### ሠንጠረዥ 2.2-3 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ሰብል ልማት በዞን

| ዞን/ ልዩ ወረዳ | ጠቅላላ ምርት (ቶን) | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብርዕ ሰብል | ጥራጥሬ | የቅባት እህል | አትክልት | ሥራሥር ተክል | ቋሚ ተክል |
| ጉራጌ | 146,928 | 13,440 | 1,279 | 39,746 | 15,637 | 26,689 |
| ስልጤ | 131,310 | 10,277 | 108 | 51,030 | 771 | 8,174 |
| ሃዲያ | 174,440 | 13,170 | 985 | 31,751 | 8,885 | 64,280 |
| ከምባታ ጠምባሮ | 44,776 | 6,051 | 128 | 10,071 | 25,884 | 32,618 |
| ወላይታ | 59,745 | 18,094 | 31 | 9,579 | 60,380 | 51,016 |
| ሲዳማ | 123,033 | 15,555 | 38 | 53,944 | 14,984 | 388,869 |
| ጌድኦ | 11,376 | 4,405 | 31 | 12,030 | 4,339 | 56,228 |
| ጋሞ ጎፋ | 133,150 | 16,049 | 435 | 9,304 | 93,712 | 92,302 |
| ዳውሮ | 23,249 | 9,594 | 240 | 4,043 | 25,479 | 21,352 |
| ካፋ | 114,060 | 38,372 | 256 | 12,867 | 25,414 | 81,972 |
| ሸካ | 18,883 | 2,913 | 3 | 2,119 | 7,726 | 28,837 |
| ብንች ማጂ | 54,914 | 7,989 | 69 | 7,517 | 31,774 | 36,826 |
| ደቡብ ኦሞ | 50,619 | 8,687 | 728 | 1,688 | 10,270 | 9,916 |
| አላባ | 57,609 | 1,173 | 59 | 23,258 | 1,509 | 1,316 |
| የም | 18,889 | 2,874 | 172 | 1,297 | 2,311 | 4,046 |
| ኮንታ | 11,795 | 3,372 | 20 | 584 | 15,820 | 5,134 |
| ባስኬቶ | 3,173 | 532 | 577 | 130 | 3,923 | 2,344 |
| አማሮ | 7,713 | 1,688 | 0 | 1,840 | 284 | 15,306 |
| ቡርጂ | 4,517 | 1,610 | 4 | 456 | 156 | 653 |
| ደራሼ | 24,396 | 3,044 | 0 | 782 | 1,386 | 1,758 |
| ኮንሶ | 31,694 | 3,286 | 21 | 124 | 321 | 4,393 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 1,246,269 | 182,175 | 5,184 | 274,160 | 350,965 | 934,029 |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ባለሥልጣን "የግብርና ናሙና ቅኝት 2008/09 (እ.ኤ.አ) ጥራዝ. VII (ቡልቲን 446)"

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ሃዲያ ዞን በእህል ሰብል ልማት የሚታወቅ ሲሆን የስንዴ፣ በቆሎ፣ ጤፍና ጥራጥሬ ምርት ከአካባበው ፍጆታ በላይ የሚመረት በመሆኑ በብዛት በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ወጪ ለገበያ ይውላሉ፡፡

በስተምሥራቅ የሚገኘው የክልሉ አካባቢ፤ ሲዳማና ጌድኦ ዞኖች በቅይጥ እርሻ ቡና፣ እንሰት፣ ሥራሥር፣ ፍራፍሬና አትክልት በማምረት ይታወቃሉ፡፡ ሲዳማና ጌድኦ ስፔሻሊቲ የሲዳማ ቡና እና የይጋጨፌ ቡና በማምረት ዝነኛ ናቸው፡፡

በክልሉ ሰሜናዊ አካባቢ በቆሎ፣ ስንዴና ጤፍ በትርፍነት ይመረታል፡፡ ይህም አካባቢ ከፍተኛ የአትክለልት ልማት የሚካሄድበት ሲሆን የጉራጌ ጎመንና በርበሬ በማመረት ጉልህ ሥፍራ አለው፡፡ ለአዲስ አበባ እና ሻሸመኔ ገበያዎች ለሽያጭ ይቀርባሉ፡፡

ማዕከላዊ የክልሉ አካባቢ እንደጎዳሬ እና ስኳር ድንች የመሳሰሉ የሥራሥር ተክሎች በትርፍነት ያመርታል፡፡ የተወሰነ የምርት ውጤቶችንም ለአዲስ አበባ ገበያ ይቀርባል፡፡ ድቡልቡል ድንችም በክልሉ በስፋት የሚመረት ሲሆን ከምባታ ጠምባሮ፣ ሃዲያ፣ ጉራጌ፣ ሲልጤ እና ወላይታ ዞኖች የገላ ድርሻ አላቸው፡፡

ምዕራባዊ የክልሉ አካባቢዎች በጫካ ቡና እና የጫካ ማር በማመረት ዝናን ያተረፉ ናቸው፡፡ የዚህ አካባቢ ቡና የከፋ እና የጅማ ቡና በመባል ለሽያጭ ይቀርባል፡፡

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በፍራፍሬ ምርት ታዋቂ ነው፡፡ ሙዝ፣ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ አናናስ፣ ፓፓያ በማምረት ከፍተኛ የሀገሪቱን ገበያ ድርሻ ይይዛል፡፡ በተለይም የአርባምንጭ የሙዝ ምርት በሀገሪቱ በከተሞች (አዲስ አበባ፣ ናዝሬት፣ ሻሸመኔ፣ ሃዋሳ፣ ወ.ዘ.ተ) የሚገኘውን ገበያ በበላይነት ተቆጣጥሯል፡፡

እንሰት ዋንኛ የምግብ ሰብል ሲሆን የክልሉ መካከለኛና ከፍተኛ ቦታዎች የዕለት ተለት አመጋገብ አካል ነው፡፡ ሲዳማ፣ ጌድኦ፣ ሸከና ደውሮ ዞኖች እንዲሁም አማሮ እና ኮንታ ልዩ ወረዳዎች በብዛት እንሰት ያመርታሉ፡፡ ቆጮ እና ቡላ በመባል የሚታወቁ የእንሰት ምርት ውጤቶች በክልል ውስጥና ከክልል ውጪ ለገበያ ይቀርባሉ፡፡

## 2.3 የግብርና ትምህርትና ኤክስቴንሽን

### 2.3.1 የግብርና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት

በሀገር ውስጥ ቢያንስ 19 ዩኒቨርስቲዎች/ ኮሌጆች በመጀመሪያ ድግሪ ደረጃ የግብርና ትምህርት ፕሮግራሞች ያላቸው ሲሆን 7 ዩኒቨርስቲዎች የግብርና የድኅረ-ምረቃ ፕሮግራሞች ያካሄዳሉ፡፡ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው በ2007/08 (እ.ኤ.አ) በመጀመሪያ ድግሪ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉ 14535 ተማሪዎች የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ ውስትም 2865 ሴቶች ነበሩ፡፡ በዚህ ወቅት የድኅረ-ምረቃ ፕሮግራም ይከታተሉ የነበሩ ተማሪዎች ብዛት 686 ሲሆን 72 ሴቶች ነበሩ፡፡

**ሠንጠረዥ 2.3-1 በኢትዮጵያ የግብርና ትምህርት የሚሰጥባቸው ተቋማት**

| | የዩኒቨርስቲ/ ኮሌጅ ስም | ፋካልቲ/ ዲፓርትመንት | አጠቃላይ የተማሪ ብዛት | ሴቶች ተማሪዎች |
|---|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ድግሪ ፕሮግራም** | | | | |
| 1 | አዲስ አበባ | የእንስሳት ሕክምና | 383 | 21% |
| 2 | አርባ ምንጥ | ግብርና | 208 | 22% |
| 3 | ባህር ዳር | ግብርናና የሥነምህዳር ሳይንስ | 978 | 17% |
| 4 | ዲላ | ግብርና | 237 | 20% |
| 5 | ጎንደር | የእንስሳት ሕክምና | 264 | 19% |
| 6 | ሐረማያ | የእንስሳት ሕክምና<br>ቢዝነስ ኢኮኖሚክስ (ሕ/ሥራ)<br>የግብርና ኮሌጅ | 3,460 | 17% |
| 7 | ሃዋሣ | ቢዝነስ ኢኮኖሚክስ (ሕ/ሥራ)<br>የግብርና ኮሌጅ<br>ቴክኖሎጂ (አግሮ ኢነጂነሪንግ.<br>የእስሳት ህክምና.<br>ወንዶ ገነት ደን ኮሌጅ | 3,180 | 22% |
| 8 | ጂማ | ግብርናና የእንስሳት ሕክምና | 1,439 | 21% |
| 9 | አምቦ | ሕ/ሥራ፣ የእጽዋት ሳይንስ፣ የእንስሳት ሳይንስ፣ የገጠር ልማት፣ ግብይት | 1,092 | 21% |
| 10 | መቀሌ | የተፈጥሮ ሀብት ምጣኔና አስተዳደር<br>የእንስሳት ሕክምና | 1,774 | 18% |
| 11 | ወለጋ | የግብርና ኮሌጅና የገጠር ልማት | 193 | 18% |
| 12 | መዳ ወላቦ | የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት | 248 | 21% |
| 13 | ደብረማርቆስ | የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት | 189 | 17% |
| 14 | ወላይታ ሶዶ | የግብርና | 187 | 21% |
| 15 | አክሱም | የግብርናና የገጠር ልማት | 217 | 26% |
| 16 | ደብረብርሃን | የግብርናና የገጠር ልማት | 92 | 25% |
| 17 | ጂጂጋ | ግብርና | 155 | 18% |
| 18 | ሚዛን/ቴፒ | ግብርና | 102 | 24% |
| 19 | ሰመራ | ግብርና | 137 | 31% |
| | ድምር | | 14,535 | 20% |
| **ድኅረ- ምረቃ ፕሮግራም** | | | | |
| 1 | አዲስ አባበ | የእንስሳት ሕክምና | 98 | 9% |
| 2 | ባህርዳር | ግብርናና የሥነምህዳር ሳይንስ | 43 | 2% |
| 3 | ሀረማያ | የግብርና ኮሌጅና | 195 | 5% |
| 4 | ሃዋሣ | የግብርና ኮሌጅና | 195 | 23% |
| | | ወንዶ ገነት ደን ኮሌጅ | 31 | 0% |
| 5 | ጂማ | ግብርናና የእንስሳት ሕክምና | 18 | 11% |
| 6 | አምቦ | ሕ/ሥራ አስተዳደር | 34 | 6% |
| | | -ተባይ መከላከል | 10 | 20% |
| 7 | መቀሌ | የተፈጥሮ ሀብት ምጣኔና አስተዳደር | 62 | 2% |
| | ድምር | | 686 | 10% |

ማስታወሻ: በቀለም ምልክት የተደረገበት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የሚገኙ ናቸው

ምንጭ: ዓመታዊ የትምህርት አብስትረክት 2000 ዓ/ም (2007/08 እ.ኤ.አ) ትምህርት ሚኒስቴር

### 2.3.2 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የመንግሥት ፕሮግራም ሲሆን ግብርናን ጨምሮ በተለያዩ መስኮች 10ኛ ክፍልና ከዚያ በላይ የጠናቀቁ ወጣቶችን በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ይሰጣል፡፡ በሀገሪቱ በአጠቃላይ በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና በእያንዳዱ ክልል የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሥር የሚተዳደር 25 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛዎች አሉ፡፡ እንደትምህርት ሚኒስቴር መረጃ መሠረት ወደ 10% የሚሆኑ የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞች በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ትምህታቸውን ይከታተላሉ፡፡ በ2007/08 (እ.ኤ.አ) 25033 ተማሪዎች በግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠና ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን 16.4% የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡

የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ፕሮግራም የሚካሄደው (1) እንስሳት እርባታ፣ (2) ሰብል ልማት፣ (3) የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ (4) የእንስሳት ጤና፣ እና (5) ሕ/ሥራ ሲሆኑ የ2 ዓመት የክፍል ውስጥ ስልጠናና የ8 ወር የመስክ ስልጠና ከተሰጠ በኂላ በዲፕሎማ ደረጃ ይመረቃሉ፡፡ ከምረቃ በኂላ እነዚህ ሰልጣኞች በክልል ግብርና ቢሮ በኩል ተቀጥረው በልማት ሠራተኛነት ወደ ቀበሌዎች እና/ ወይንም ገበሬ ማስልጠኛ ማዕከላት ተመድበው ለአርሶአደሩ የቴክኒክ ስልጠና መስጠትና የሙያ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ 3 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ የሚገኙ ሲሆን ወደ 4500 የሚሆኑ ተማሪዎች እንደሚከተለው የተለያየ ከርሶች ሲወስዱ ነበር፡፡

**ሠንጠረዥ 2.3-2 በደ/ብ/ብ/ክ/ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ የነበሩ ተማሪዎች ብዛት**


| የማሰልጠኛ ስም | ዲፓርትመንት | | | | | | | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እንስሳት ሳይንስ | | | እጽዋት ሳይንስ | | | የተፈጥሮ ሀብት | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ዲላ | 381 | 106 | 487 | 463 | 94 | 557 | 454 | 42 | 496 | 1,298 | 242 | 1,540 |
| ሚዛን | 485 | 119 | 604 | 531 | 61 | 592 | 601 | 45 | 646 | 1,617 | 225 | 1,842 |
| ወላይታ | 336 | 73 | 409 | 370 | 55 | 425 | 289 | 35 | 324 | 995 | 163 | 1,158 |
| ድምር | 1,202 | 298 | 1,500 | 1,364 | 210 | 1,574 | 1,344 | 122 | 1,466 | 3,910 | 630 | 4,540 |

ምንጭ: ዓመታዊ የትምህርት አብስትረክት 2000 ዓ/ም (2007/08 እ.አረ.አ) ትምህርት ሚኒስቴር

### 2.3.3 የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕክል

የገበሬ ማስልጠኛ ማዕከል በእያንዳንዱ የክልል ግብርና ቢሮ አማካኝነት ተቋቁሞ በሥራቸው በሚገኙ የኤስቴንሽን አገልግሎት የሥራ ሂደት ተገቢው ክትትል ይደረግላቸዋል፡፡ የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከል ሚና 1) ለአካባቢ አርሶአደሮች ተከታታይ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣ 2) በተሸሻሉ የግብርና ተግራት ላይ ስልጠና እና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ እና 3) አስፈለጊ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የገበሬ ማስልጠኛ ሦስት የልማት ሠራተኞች ያሉት ሲሆን የሙያ መስመራቸውም 1) እንስሳት ዕርባታ፣ 2) የተፈፍሮ ሀብት፣ እና 3) ሰብል ልማት ናቸው፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ አማካይ የገበሬ ማስልጠኛ ሽፋን በ2010 (እ.ኤ.አ) 52% ነበረ፡፡ ሽፋንን በተመለከተ በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ልዩነቶች ታይተዋል፡፡ በደቡብ ኦሞ ዞን 20% የነበረ ሲሆን ከምባታ ጠምባሮ ዞን 90% ደርሷል፡፡ በ2006/07 (እ.ኤ.አ) በአጠቃላይ 12800 የልማት ሠራተኞች የነበሩ ሲሆን የልማት ሠራተኛና የአርሶአደር ጥመርታ 1፡199 ነበር፡፡ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የልማት ሠራተኛና የአርሶአደር ጥመርታ በ 1/3 ቀንሷል፡፡




ምንጭ: የጃይካ ጥናት ቡድን፤ ከግብርና ኤክስቴንሽን አገልጎሎት የሥራ ሂደት የተገኘ መረጃ፤ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ 2010 (እ.ኤ.አ)

## ምስል 2.3-1 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የገበሬ ማስልጠኛ ማዕከላት ሽፋን

## ሠንጠረዥ 2.3-3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የልማት ሠራተኛ ብዛትና አርሶአደር ጥመርታ

| መት | 2001/02 | 2002/03 | 2003/04 | 2004/05 | 2005/06 | 2006/07 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የልማት ሠራተኛ ብዛት | 3,583 | 3,559 | 8,286 | 10,370 | 10,664 | 12,801 |
| የልማት ሠራተኛ አርሶአደር ጥመርታ | 1:600 | 1:682 | 1:302 | 1:233 | 1:233 | 1:199 |

ምንጭ: መሠረታዊ መረጃና አፈጻጸም ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፤ ሚያዝያ 2010 (እ.ኤ.አ)

## 2.4 የግብርና አስተዳደር አደረጃጀት

### 2.4.1 የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር

የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብልክ መንግሥት ከአሉት 17 ሚኒሰረቴር መሥራያ ቤቶች[3] አንዱ ነው። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ገበያ ተኮር የሆነ ዘመናዊ ግብርና ሥርዓት የማስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠባባቅ ማልማትና በዘላቂነት መጠቀም፣ ዘመናዊ የግብርና ግብይት ሥርዓትን ተግባራዊ የማድረግ፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አቅም የማጎልበት፣ እና በልማት ሥራ ሴቶችና ወጣቶችን አቅም በመጠናከር ተጠቃሚ የማድረግ ዓላማ አለው። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ዕራይና ተልዕኮ የሚከተለው ነው።

**ራዕይ :** ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚጠቀም የዳበረ ግብርናና ከድህነት የተላቀቀ ህብረተሰብ መፍጠር

**ተልዕኮ:** ሕብረተሰቡን ከድህነት የሚያላቅቅ የላቀ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዘርፉን እምቅ ሀብትና አቅም የሚጠቀም ከፍተኛ ምርታመነት ደረጃ ላይ የደረሰ ለኢኮኖሚያዊ መዋራዊ ለውጥ መሠረት መጣል የሚያስችል ዘመናዊ የግብርነ ሥርዓት መዘርጋት

የግንቦት 2010 (እ/ኤ/አ) ሀገር አቀፍ ምርጫ ተከትሎ ጥቅምት 2010 (እ.ኤ.አ) የአቶ መለስ መንግሥት ለ3ኛ ጊዜ ሥልዓን ይዞል። የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒሰቴር እንደገና ተዋቅሮ የግብርና ሚኒስቴር የተባለ ሲሆን ቀደም ሲል በግብናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር የነበረው የገጠር ልማት ዘርፍ ወደ ሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ተዘዋውሯል። በቀድሞ ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር የነበረው የግብይት የሥራ ክፍል ወደ ንግድ ሚኒስቴር ተዛውሯል።

### 2.4.2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ቢሮ

በ3ተኛ የአቶ መለስ የሥልጣን ዘመን እንደገና በተዋቀረው የፌዴራል ምንግሥት ተከትሎ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግሥት የግብርነና ገጠር ልማት በሮን እንደገና አዋቅሯል። በዚሁ መሠረት የጃይካ የጥናት ቡድን አቻ ድርጅቶች የሆኑ ሀለት ቢሮዎች ማለትም የግብርና ቢሮ እና ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ተዋቅረዋል።

ቀድሞ በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሥር የነበሩት የግብርና ግብይት ዋና የሥራ ሂደትና የሕ/ሥራ ልማት ዋና የሥራ ሂደት ተዋህደው አዲሱን የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ መስርተዋል። ቢሮውም ገበያ ተኮር የሆነ ግብርና ልማትን የሕ/ሥራ ማህበራትንና አርሶአደር ቡድኖች በመጠናከር እና የተለያየ አቅም ግንባታ በማካሄድ ቀልጣፋ እንደሚያደርግ ይጠበቃል። የግብርና ቢሮ ዋንኛ ተግባርና ትኩረትም የግብርና ምርት ማስፋፋት እና ተስማሚ ቴክኒዎሎጆችን ማፍጠር ነው።

የመዋቅር ለውጡ የፌዴራል መንግሥት ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ተንተርሶ ነው የተካሄደው። የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ አደረጃጀት ዓይነት በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢ የሌለ ሲሆን ለወደፊት በዚህ ሁኔታ ለማደራጀት የክልሉተሞክሮ ትኩረት ስቧል። በድርጅታዊ አወቃቅር ላይ የታዩ ዋና ለውጦች እንደሚከተለው የቀረበ ሲሆን የግብርና ቢሮ ድርጅታዊ መዋቅር በምስል 2.4-1 ተመልክቷል።

1) አዲስ የተመሠረተ ክፍል :የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ
2) የተወገደ ክፍል :የገጠር ፋይናነስ አስተዳደር
3) ተለወጠ ክፍል :
   3.1 የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት ትኩረት የተሰጣቸውን ምርቶች መሠረት በማድረግ በሦስት እንደሚከተለው ተከፍሏል።
      ሀ. የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት
      ለ. የእንስሳት ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን ዋና የሥራ ሂደት

---
[3] እስከ መስከረም 2010 (እ.ኤአ)

ሐ. የሰብል ልማት ኤክስቴንሽን ዋና የሥራ ሂደት

3.2 የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደርና ጥበቃ ዋና የሥራ ሂደት ወደ ባለሥልጣን ደረጃ አድርጓል፡፡

3.3 የህዝብ ግንኙነት አገልግሎት ቀልጣፋ በሆነ ምንገድ ዝርዝር መረጃ መስጠት እንዲችል በሁለት ክፍሎች እንደሚከተለው ተከፍሏል፡፡

ሀ. የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ደጋፊ የሥራ ሂደት

ለ. የሰው ሀብት መረጃና እስታስቲክስ ደጋፊ የሥራ ሂደት

3.4 የኦዲት አገልግሎት ስሙን በመቀየር የውስጥ ኦዲት ደጋፊ የሥራ ሂደት የተባለ ሲሆን ዝርዝር ተግባሩም ተመሳሳይ ነው፡፡

3.5 የሕ/ሥራ ልማት ኤጀንሲ እና የግብርና ግብይት ዋና የሥራ ሂደት ተዋህደው አዲሱን የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮን ቀደም ሲል እንተገለጸው ተዋህደው መስረቷል፡፡

4) የሠራተኛ ብዛት፡ በክልል ቢሮ ደረጃ ጥር 2011 (እ.ኤ.አ) 173 ሠራተኞች ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ቢሮ፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ የቀበሌ ልማት ሠራተኞችን ጨምሮ 19500 እንደሆን ይገመታል፡፡


5) በጀት፡ ብር 97,716,229.00 (ሐምሌ 2010-ሰኔ 2011 እ.ኤ.አ)

### 2.4.3 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብይተና ሕ/ሥራ ቢሮ


የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በቀድሞ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሥር የነበሩትን የግብርና ግብይት ዋና የሥራ ሂደትና የሕ/ሥራ ልማት ኤጄንሲን በመካታት በአዲስ መልክ ተዋቅሯል፡፡ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ይዘት እንደሚከተለው ሲሆን ድርጅታዊ መዋቅሩም በምስል 2.4-2 ተመልክል፡፡

1) በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሥር በነበረበት ወቅት የግብርና ግብይት ዋና የሥራ ሂደት ይባል የነበረው በተመሳሳይ መልኩ የግብርና ግብይት ዋና የሥራ ሂደት ተብሏል፡፡ የባለሙያዎች ብዛት (የሥራ ሂደት ባለቤትና ኤክስፐርቶችን ጨምሮ) 8 ከነበረው እስከ ነሐሴ 2012 (እ.ኤ.አ) በአለው ጊዜ ወደ 17 አድርሷል፡፡ የባለሙያ የሥራ ስምሪትን በተመለከተ በ3 ዘርፍ ተመድበዋል፡፡ እነርሱም የምርት ጥራት ቁጥጥር፣ የገበያ ማስፋፋትና ትስስር፣ እና መረጃና የዳታ ክምችት ይባላሉ፡፡
2) ቀደም ሲል በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የሕ/ሥራ ልማት ኤጀንሲ ይባል የነበረው በአሁኑ ወቅት የሕ/ሥራ ዋና የሥራ ሂደት ተብሏል፡፡ በሥሩ የሚገኘው የሰው ኃይል 20 ሲሆን በ3 የሥራ መስክ ተደራጅቷል፡፡ የሥራ መስኮችም የሕ/ሥራ ማደረጃ፣ የሕ/ሥራ ማስፋፊያ እና የሕ/ሥራ ኦዲት በመባል ይታወቃሉ፡፡
3) የሰው ኃይል ብዛት፡ 86 (ነሐሴ 2012 እ.ኤ.አ በቢሮ ያለ)
4) በጀት፡ አጠቃላይ ብር 6,651,492.94.00 (ህዳር 2010- ሰኔ 2011 (እ.ኤ.አ), ጥር 2011 (እ.ኤ.አ እንደ ተገኘ መረጃ)

የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በአዲስ መልክ መደረጃትን ተከትሎ በዞንና በወረዳ ደረጃ የግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ተዋቅረው በአብዛኛው አዲስ ጽ/ቤት ከፍተዋል፡፡ ነገር ግን በበጀት እጥረት የተነሳ ለአብዛኛው የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶእና መገልገያዎች አልተሟሉም፡፡




ምስል 2.4-1 የግብርና ቢሮ ድርጅታዊ መዋቅር




** የሠራተኛ ብዛት (በጥር 2011 እ.ኤ.አ) ያለው በቅንፍ ውስጥ ( )*

**ምስል 2.4-2 የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮድርጅታው መዋቅር**

## 2.5 የግብርና ግብይት ፖሊሲ

### 2.5.1 የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የግብርና ግብይት እስትራቴጂ

የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ፈጣንና ዘላቂ የግብርና ልማት ለማምጣት የሚያስችል የግብርና ግብይት እስትራቴጂ በ2005 (እ.ኤ.አ) አዘጋጅቷል፡፡ የፖሊሲ ሰነዱ የሚያተኩረዉ የግብርና ምርት ለዉጪና ለሀገር ዉስጥ ገበያ በመጠንና በጥራት የማቅረብ ሂደትን ለማሳደግና በገበያ ፍላጎት የተመሰረተ የግብርና ግብይት ቴክኖሎጂ ለማቅረብ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የፖሊሲ ሰነዱ ብቃት ያለዉ ሁሉም ባለጉዳዩች (አምራቾች፤ ነጋዴዎች እና ሸማቾች) ተጠቃሚ የሚሆኑበት የገበያ ስርአት ለማቋቋም ትኩረት ይሰጣል፡፡ ፖሊሲዉ የሚከተሉት አላማዎችና እስትራቴጂዎች አሉት፡፡

(1) የግብአት ፍላጎት ትንበያ ስርአት ማጠናከር
- የፍላጎት ትንበያ አቅም ማጠናከር
- የአሠራር መመሪያ ማውጣት ስልጠና በመስጠት የትንበያ አቅም ማሳደግ
- ስለግብአት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለአምራቾችና አቅራቢዎች መስጠት
- የትንበያ ስርአት ማጠናከር

(2) ብቁ የሆነ የግብርና ምርትና የግብአት ልዉዉጥ ስርአት መዘርጋት
- በፌዴራል ደረጃ የአቅርቦት ሂደትን በማጠናከር ለክልሎችና ለሌሎችም ተጠቃሚዎች በፍላጎት ላይ ተመስርቶ ማቅረብ
- ወደ ሀገር ውስጥ ተፈላጊ የግብርና ግብአት የመስገባት አቅምን ማጠናከር፡፡ ይህም ለአስመጪዎች የሚደረገውን የውጪ ምንዛሪ መመደብና ተፈላጊ ግብአት አይነትና ብዛት መረጃ መስጠትን ያካትታል
- የግብርና ግብአት የዉጭ ምንዛሬ ምደባንና የተፈላጊ ግብአት አይነትና መጠንን ጨምሮ ለአስመጪዎች የአቅርቦት አቅም ማጠናከር
- ምርትን ለገበያ አሰባበስቦ የማቅረብን አሠራር በማሻሻል የገበያ ሰንሰለትን በጋራ በመገበያየት ማሳጠርና የግብርና ምርት አቅርቦት መጨመር
- በገበያ ተዋንያን መካከል ግንኙነት መፍጠር
- በአምራቾችና በገዢዎች መካከል በኮንትራት የማምረትና ሽያጭ አሰራርን ማጠናከር
- የጨረታ ግብይት ስርአት ማስፋፋትና ማጠናከር
- በመጋዘን የመቀበልን፣ የቆጠራና የዱቤ ግብይት አሰራርን ማስፋፋትና ማጠናከር

(3) የገበያ ስርአትን በጥራት ደረጃ ደረጃ ላይ ተመስርቶ ማደራጀት
- የጥራት ደረጃ ማዉጣት
- የግብአት የጥራት ደረጃና የቁጥጥር ስርአት ማቋቋም
- የምርት የጥራት ደረጃና የቁጥጥር ስርአት ማቋቋም
- ለግብርና ግብአት የማረጋገጫ ስርአት ማቋቋም
- ለኤክስፖረት የግብርና ምርት የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ስርአት መዘርጋት
- የግብርና ምርት ወደ ዉጪ ለመላክ የማሳወቅና የማስፋፋት ስራ መስራት (የድምጽና የምስል እንዲሁም የህትመት ስራ በማዘጋጀት፤ በናሙና፤ በኤግዚቢሽን በመሳተፍ)

(4) የግብይት መሠረተ ልማት ማስፋፋትና ማጠናከር
- መንገድ ማስፋፋት
- መጋዘኖችን ማጠናከርና ማስፋፋት
- የትራንስፖርት አገልግሎት ማጠናከርና ማስፋፋት

(5) የፋይናንስ አቅምና የዋስትና ሽፋን ማጠናከር
- የብድር አገልግሎት ለአርሶአደሮችና ለነጋዴዎች ማጠናከር
- ለገጠር ባንኮች የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት
- በገጠር ባንኮችና በሕ/ሥራ ማህበራት መካከል ግንኙነት ማጠናከር

(6) የግብይት ሕግና ደንቦች መኖራቸዉን ማረጋገጥ
- ነባር ደንቦችና መመሪያዎችን መገምገምና አስፈላጊ ማሻሻያዎችን ማድረግ
- የቆዳና ሌጦ ግብይት አዋጅ ማዘጋጀት
- በግብርና ምርቶች ላይ የዋጋና የጥራት ደረጃ መመሪያ ማዘጋጀት

- በኮንትራት ማምረትና ግብይት የስምምት ደንቦች ማዘጋጀት
- በመጋዘን የመቀበልና የንብረት ቆጠራ የብድር ስርአት አተገባበር ደንብያ ማዘጋጀት
- የገበያ ማእከላት ማቋቋምና የአስተዳደር ስርአት መመሪያ ማዘጋጀት
- ለአምራቾች ለነጋዴዎች ለሸማቾችና ለመንግስት አስፈጻሚ አካላት በአዳዲስና በተሻሻሉ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማገጋጀት

(7) የግብይት መረጃ ስርአት ማቋቋምመዘርጋት
- የግብርና ምርትና ግብአት ቀበሌን፤ ከዞን፤ ከክልል፤ ከፌዴራልና ዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያስተሳስር የግብርና የመረጃ ስርአት መዘርጋት
- ስለሚገኘዉ ጥቅምና አጠቃቀምን ጭምሮ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ማዘጋጀት
- የአቅርቦት፣ የፍላጎት፤ የዋጋ፤ የቦታ፣ ምርት የሚገዙ ሀገሮች የንግድ ህግና ደንብ፤ የጥራት ደረጃ መመዘኛ፣ የገዥዎች ፀባይ፤ የዓለም አቀፍና የሀገሮች ሁለትዮሽ ስምምነት ወዘተ መረጃ ማሰባሰብ።

ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች አንፃር በአሁኑ ወቅት ያለውን ደካማ ጎን እግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የፌዴደራል ፖሊሲ ሰነድ የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት የኃላፊነት በግልፅ ያስቀምጧል። ይህ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁሉም ደረጃ ፖሊሲና እስትራቴጅዎችን በብቃትና ቅልጥፍና ከማስፈጸም አኳያ የለውን ተግባርና የኃፊነት ወሰን የመሳሰሉት ነው። ይሁንና የፖሊሲ ሰነዱ የድርጊት መርሐግብርና የጊዜ ሰሌዳ አላስቀመጠም።

### 2.5.2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የክልላዊ ግብርና ግብይት እስትራቴጂ

መስከረም 2009 (እ.ኤ.አ) የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የ5 አመት ክልላዊ የግብርናና ገጠር ልማት እስትራቴጂ እቅድ ከ2010 እስከ 2015 (እ.ኤ.አ) ያለውን ጊዜ የሚሸፍን አዘጋጅቷል። የእቅድ ሰነዱ 6 የግብርና ምርቶች ማለትም ቡና፤ ጥራጥሬ፤ የቅባት እህሎች፤ የብርዕ ሰብል፤ ቅመማቅመም እና አትክልትና ፍራፍሬ እስትራቴጂክ ግብ ያላቸዉ በማለት ይመድባቸዋል።

የእስትራቴጂክ እቅዱ በግልፅ እንደሚያሳየዉ እነዚህ የእስትራቴጂክ ግብ ያላቸዉ ምርቶች በ2015 (እ.ኤ.አ) የሚደርሱበትን ግብ ተጥሏል። (ሠንጠረዡን ከታች ይመልከቱ) ይሁን እንጂ እንደ ብሔራዊ የእስትራቴጂክ እቅድ የእስትራቴጂክ ግቡን ለመድረስ በተጨባጭ ተግባራዊ ሊሆን የሚያስችል መርሐግብርም ሆነ የአፈፃፀም ስልት አልተዘጋጀም።

**ሠንጠረዥ 2.5-1 ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርናና ገጠር ልማት እስትራቴጂ እቅድ የተመረጡ ምርቶች፣ ስልታዊ ግብና የዝርዝር ስራ እቅድ**

| የተመረጡ ሰብሎችና እስትራቴጂክ ግብ | ዝርዝር ሥራ እቅድ |
|---|---|
| [ቡና]<br>በ2009 (እ/ኤ/አ) የምርት ግምት 113010 ቶን የእስትራቴጂክ የምርት ግብ በ2015 (እ.ኤ.አ) 471269 ቶን<br>(282761 ቶን የታጠበ 188508 ቶን በደረቅ) | • አምራቾችን፣ የሕ/ሥራ ማህበራትንና ነጋዴዎችን በጥራትና በመጠን እንዲያሻሽሉ መደገፍ<br>• ለቡና ነጋዴዎችና ለሕ/ሥራ ማህበራት መደገፍ የሚያስችል የመጋዘንና የብድር ድጋፍ መመሪያ ማዘጋጀት<br>• ወቅታዊ የገበያ መረጃ ማቅረብ<br>• የቡና ጥራት ሳይበላሽ ለረዥም ጊዜ ማቆየት የሚያስችል ምቹ መጋዘን ለሚሠራበትን ሁኔታ ማመቻቸት<br>• ለምርት ማሰባሰብ፤ማጓጓዝና በመጋዘን መቆየት የሚያስችል የተሻሻለ አያያዝ መረጃ ማቅረብ<br>• ለተሻለ ዋጋ የሚያበቃ የጥራትና ሀቀኛ የግብይት ስርአት መፍጠር<br>• የቡና ጥራት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን ማቋቋም<br>• የአዳዲስ የቡና መፈልፈያ እንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ ማበረታታት<br>• የሕጋዊ አሰራር ማእቀፍ ማዘጋጀት ማሳወቅና ተግባራዊ ማድረግ<br>• የእሸት ቡና መፈልፈያ/ማድረቂያ ኢንዲስትሪዎች |

| የተመረጡ ሰብሎችና እስትራቴጂክ ግብ | ዝርዝር ሥራ እቅድ |
|---|---|
| | ሥራቸዉን በሙሉ ኃይላቸዉ እንዲሠሩ መከታተልና ድጋፍ መስጠት<br>• ለሕ/ሥራ ማህበራት የብደር አገልግሎት ማመቻቸት<br>• ችግሮችን በጥናት ላይ ተመስርቶ መለየትና ማሻሻያ ሀሳቦችን ማመንጨት<br>• የብዙሀኑን መገናኛና ዌብ ሳይቶችን በመጠቀም ምርቱን ማስተዋወቅና ማስፋፋት<br>• የጥራት እዉቅና ማረጋጋጫ ማዉጣት |
| [ጥራጥሬ]<br>በ2009 (እ.ኤ.አ) የምርት ግምት 120498 ቶን እስትራቴጂክ የምርት ግብ በ2015 (እ.ኤ.አ) 201548 ቶን<br>የገበያ አቅርቦትን በ 55% ከፍ ለማድረግ | • አምራቾችን፤ የሕ/ሥራ ማህበራትንና ነጋዴዎችን በጥራትና በመጠን እንዲያሻሽሉ መደገፍ<br>• ወቅታዊ የገበያ መረጃ ማቅረብ<br>• የምርት ጥራት ለረዥም ጊዜ ማቆየት የሚያስችል ምቹ መጋዘን እንዲቋቋም ማመቻቸት<br>• ምርት በሚሰበሰብበት፣ በሚጓጓዝበትና በመጋዘን በሚቆየት ወቅት በጥንቃቄ መየዝ የሚያስችል የተሻሻለ አያያዝ መረጃ መስጠት<br>• ፍታዊና የተረጋጋ የግብይት ሥርዓት እንዲኖርና በጥራት ላይ ተመስርቶ የተሻለ ዋጋ መክፈል እንዲለመድ መሥራት<br>• የሕጋዊ አሰራር ማእቀፍ ማዘጋጀት፤ ማስተዋወቅና ተግባራዊ ማድረግ<br>• ለሕ/ሥራ ማህበራት የብድር አገልግሎት ማመቻቸት<br>• ችግሮችን በጥናት መለየትና የተሻሉ ሀሳቦችን ማመንጨት<br>• የብዙሃን መገናኛና ዌብ ሳይቶችን በመጠቀም ምርቱን ማስተዋወቅና ማስፋፋት<br>• የግብይትን ማእከላትን ማቋቋም<br>• የጥራት እዉቅና ማረጋገጫ ማዉጣት |
| [የቅባት እህል]<br>በ2009 የምርት ግምት 18277 ቶን<br>በ2015 እስትራቴጂክ ግብ 22775 ቶን | ከላይ ለጥራጥሬ ከተቀመጠዉ የሥራ እቅድ ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ |
| [የብርዕ ሰብል]<br>በ2009 የምርት ግምት 1257123 ቶን<br>በ2015 (ኢ.ኤ.አ) እስትራቴጂክ የምርት ግብ 2141596 ቶን | ለጥራጥሬ ከተቀመጠዉ የሥራ አቅድ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በተጨማሪ<br>• የእህል ማበጠሪያ መሳሪያ የማስታዋወቅ ሥራ ማመቻቸት<br>• በጥራትና በገበያ ፍላጎት የተመሰረተ የምርት ደረጃ ማዉጣት |
| [ቅመማቅመም]<br>በ2009 የምርት ግምት 425873 ቶን<br>በ2015 (ኢ.ኤ.አ) እስትራቴጂክ የምርት ግብ 533167 ቶን | ለጥራጥሬ ከተቀመጠዉ የሥራ እቅድ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በተጨማሪ<br>• የማበጠሪያ መሳሪያ የማስታዋወቅ ሥራ ማመቻቸት<br>• በጥራትና በገበያ ፍላጎት የተመሰረተ የምርት ደረጃ ማዉጣት |
| [አትክልትና ፍራፍሬ]<br>በ2009 የምርት ግምት 1161014 ቶን<br>በ2015 (ኢ.ኤ.አ) እስትራቴጂክ የምርት ግብ 382.043 ቶን | ለጥራጥሬ ከተቀመጠዉ የሥራ እቅድ ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ |

ምንጭ፡ ከግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የ 5 አመት የልማት እቅድ በጥናት ቡድን ተጠቃሉ የተወሰደ፡፡

### 2.5.3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የልማት ኮሪደር እቅድ

የክልሉ መንግስት የልማት ኮሪዶር እቅድ ዝግጅት እንዲያጠናቅቅ በ2008 (እ/ኤ.አ) አንድ ግብር ኃይል አቋቁሟል፡፡ ግብረ ኃይሉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ማለትም ከግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፤ ከንግድና ኢንዱስተሪ ቢሮ፤ ከዉሃ ሀብት ልማት ቢሮ፣ ከማእድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ፣ ከሥራና ከተማ ልማት ቢሮና ከኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተወጣጣ ነበር፡፡

የልማት ኮሪደር እቅድ አላማዉ ለእስትራቴጂክ ምርቶች የሚሆን የአግሮ ኢንዲስትሪ ስብስብ የልማት ኮሪደር መቋቋም ነው፡፡ በአፈፃፀም እስትራቴጂዉ መሰረት እነዚህ የልማት ማእከላት የልማት ጥረቶችን ጉዳዩ በሚመለከታቸዉ የተለያዩ አካላት ማለትም ከግል ድርጅቶች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መንግስታዊ ድርጅቶች መካከል የእርስ በእርስ ግንኙነት እና ትብብር የማመቻቸትና የማስፋፋት ሀላፊነት አለባቸዉ፡፡ ይህ እቅድ ጉጉትና እቅዱን ተግባራዊ ሊሆን የሚችልና አድስ አይነት አቀራረብ ያለዉ ይመስላል፡፡

በሚቀጥለዉ ሠንጠረዥ እንደተመለከተዉ እቅዱ የእስትራቴጂክ ምርቶችና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች በእያንዳንዱ የልማት ኮሪዶር እንዲስፋፉ ነዉ፡፡ ሆኖም አሁንም በሀሳብ ደረጃ እንጂ በተጨባጭ ግልጽ ድርጊት መርሐግብር አልተቀመጠም፡፡

## ሠንጠረዥ 2.5-2 የልማት ኮሪዶር እቅድ

| | ኮሪዶርና ዞን | የሚቋቋም የልማት ማዕከል (ከተማ/ከተማ-ዞን) | ዋና የእስትራቴጂ ግብ ምርት | ንኡስ ግብ ያላቸዉ ምርቶች | የሚቋቋሙ/የሚጋበዙ ኢንዱስትሪዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሲዳማ፣ጌዲኦ፣አማሮ<br>• ምስራቃዊ የቡና ቀጠና<br>• ምስራቃዊ ደጋ ቀጠና | ወናጎ-ጌዲኦ<br>ሀዋሳ-ሲዳማ<br>በንሳ-ሲዳማ | ቡና | ፍራፍሬ<br>ጥራጥሬ<br>አትክልት<br>ሸንኮራ<br>አገዳ | የምግብ ዘይት አምራች<br>አነስተኛ ደረጃ የስኳር ማቀነባበሪያ |
| 2 | አ/ምንጭ፣ኮንሶ፣ኦሞራቴ<br>ሀባያና ጫሞ ሀይቆችና ደጋ አካባቢዎች | ገረሴ ጋሞ ጎፋ | ፍራፍሬ<br>አሳ | የደጋ<br>ፍራፍሬ | ደረቅ ፍራፍሬ |
| 3 | አባያ ጫሞ፣ ሶዶ፣ሀላባ፣ ሻሸመኔ፣ናዝሬት፣ አ.አ<br>• ማዕከላዊ የብርዕ ሰብል ዞን | አርባምንጭ-ጋሞ ጎፋ | ---- | የብርዕ<br>ሰብሎች | የምግብ ዘይት<br>የአትክልት ማቀነባበሪያ<br>(የቲማቲም ድልህ) |
| 4 | ቴፒ፣ማሻ፣ጋምቤላ<br>• ምዕራባዊ ቀጠና 1<br>• ምዕራባዊ ቀጠና 2<br>• ምዕራባዊ ቀጠና 3 | ቤንች-ቤንች<br>ማጂ<br>ማሻ-ሸካ<br>ጊምቦ-ከፋ | ደን ነክ<br>ያልሆኒ<br>የጫካ<br>ምርቶች | ቅመማቅ<br>መም እና<br>ማር ሰም | የቲማቲም ድልህ<br>የእርድ ቀለም ፋብሪካ |
| 5 | ቦንጋ፣ሚዛን፣ደቡብ ሱዳን<br>• ማዕከላዊ ኦሞ ጊቤ ቀጠና | ተርጫ-ዳዉሮ | ቅመማቅ<br>መም | ፍራፍሬ<br>የቅባት<br>እህል | አቮካዶ ቅባት<br>የዝንጅብል ቅባት<br>የባህር ዛፍ ቅባት<br>ፋብሪካ |
| 6 | ማእላዊ ጋሞ ጎፋ፣ ወላይታ፣ አ.አ<br>• የላይኛዉ ስምጥ ሸለቆ | ክበት-ሰሊጥ | በርበሬ<br>ጥራጥሬ | ፍራፍሬ | - |
| 7 | ሃዲያ፣ስልጤ፣ጉራጌ<br>• ሰሜናዊ ደጋ 1<br>• ሰሜናዊ ደጋ 2 | አገና- ጊራጌ<br>ሆሳእና- ሃድያ | ስንዴ | ፍራፍሬ<br>እንሰት<br>ሥራሥር | የምግብ ማቀነባበሬያ<br>ፋብሪካ<br>የእህል ወፍጮ<br>የብስኩት ፋብሪካ |
| 8 | ከፋ፣ኮንታ፣ዳዉሮ፣ወላይታ፣ ሀላባ፣አ.አ<br>• ማዕከላዊ ቀጠና 1<br>• ምዕራባዊ ቀጠና 2<br>• ምዕራባዊ ቀጠና 3 | ሶዶ- ወላይታ<br>ሸንሸቾ-ከማባታ<br>ጠምባሮ<br>ሳዉላ- ጋሞጎፋ | ጥራጥሬ | ቀይስር<br>ፍራፍሬ<br>ጥጥ<br>ቅባት<br>እህል<br>ቅመም<br>ኦቾሎኒ | የብርዕ ሰብል<br>ማቀነባበሪያ<br>የምግብ ዘይት<br>የእርድ ማቀነባበሪያ |
| 9 | የአርብቶ አደር<br>ኮሪደር | ጅንካ-ደቡብ ኦሞ | የእንስሳት<br>እርባታ<br>ጥጥ | ፍራፍሬ | የኦሞ ግድብ ግንባታ |

ምንጭ፡ የጥናት ቡድን ከግብርናና ልማት ኮሪዶር እቅድ በማጠቃለያ የተወሰደ፡፡

## 2.6 በጥናቱ የሌሎች ለጋሾች ድርጅቶች እንቅስቃሴና ህብረት

### 2.6.1 ዓለም አቀፍ ገንዘብ ለግብርና ልማት (ኢፋድ)

ኢፋድ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚሆን ከ1980 (እ/ኤ.አ) ጀምሮ በድምሩ 190 ሚሊዮን ዶላር ወጪ አድርጓል፡፡ የኢፋድ እስትራቴጂ በኢትዮጵያ ላይ የሚያተኩረዉ ዘላቂ የቢተሰብ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና በድህነት ያሉ የገጠር ህብረተሰብ በተለይም አነስተኛ አርሶአደሮች እና አርብቶ አደሮች እንዲሁም በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ ሴቶች ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶችን መደገፍ ላይ ነዉ፡፡ ዓለማዎቹ እንደሚከተለዉ ሊዘረዘሩ ይችላሉ፡-

1) የተሻሻሉ የግብርናና የእንስሳት እርባታ ምርት ቴክኖሎጂ ማስፋፋት
2) ለገጠር ህብረተሰብ አስተማማኝ የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት ማጠናከር
3) በግብርናና በከብት እርባታ በሚተዳደሩ ህብረተሰብ ባለቤትነትና አስተዳደር የሚሠራ ግድብ መስኖ ተቋማት መገንባት
4) ብቁ የሆነ የማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነት ማጠናከር

በኢፋድ ድጋፍ በኢትየጵያ በመካሄድ ላይ ካሉት ፕሮግራሞች የግብርና ግብይት ማሻሻያ ፕሮግራም (አሚፕ) አንዱ ነዉ፡፡ የአሚፕ የሥራ እንቅስቃሴዎች የድህረ ምርት አያያዝ ስልጠና፤ የገበያ መረጃ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት፣ የደረጃ ምዘና፣ አደረጃጀት፣ የንግድ አመራር እና የኤች.አይ.ቪ. በግብርና ግብይት ላይ ያለዉን ተፅእኖ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ አሚፕ የ7 ዓመት ፕሮግራም ሲሆን ተግባራዊ የሚሆነዉ ከ2006 እስከ 2013 (እ.ኤ.አ) ነዉ፡፡

አሚፕ በደቡብ ክልል ካሉት 134 ወረዳዎች ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም 40 ወረዳዎችን (8 ልዩ ወረዳዎችን ጨምሮ) መርጧል፡፡ ኢፋድ የወረዳ ምርጫ መመዘኛ እንደሚከተለዉ አስቀምጧል፡፡

1) የግብርና ምርቶችን ለማምረትና ለአቅራቢ ያለው እምቅ ሀብት
2) የመሠረተ ልማት በተለይም የመንገድ መኖር
3) በቂ የልማት ጣቢያ ሠራተኛና የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከል
4) በቂና የተደራጀ የወረዳ ግብይት ኤጀንሲ ጽ/ ቤት እና ሠራተኛ መኖር
5) የመስኖ መሬት መኖር
6) ጠንካራ የሕ/ሥራ ማህበራት መኖር የሚሉት ናቸዉ፡፡

**ሠንጠረዥ 2.6-1 የኢፋድ/አሚፕ የተመረጡ ወረዳዎችና ምርቶች**

| | ዞን/ ልዩ ወረዳ | የተረጠ ወረዳ | በአሚፕ ወረዳዋች የተመረጡ ምርቶች | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቡና | ቅመማ ቅመም | ብርዕ ሰብል | ጥራጥሬ | አትክልታና ፍራፍሬ | ማር | ቅቤ | ቆጮ | ቆዳና ሌጦ | በግ ደለበ | ዱባ ፍሬ | ኩሸ | ቅባት እህል |
| 1 | ከምባታ | ዶዮገና | | | X | X | | | | | | | | | |
| 2 | ጠምባሮ | ሃዳሮ ጡንጦ | X | X | | | | | | | | | | | |
| 3 | ሃዲያ | ጊቤ | X | | | | | X | | | | | | | |
| 4 | | ሌሞ | | | X | X | | | | | | | | | |
| 5 | | ሚሻ | | | X | X | | | | | | | | | |
| 6 | | ሶሮ | | | X | | | | | | | | | | |
| 7 | ወላይታ | ቦሎሶ ቦምቤ | X | X | | | | | | | | | | | |
| 8 | | ቦሎሶ ሶሬ | X | X | | | | | | | | | | | |
| 9 | | ዳሞት ጋሌ | X | | | X | | | | | | | | | |
| 10 | | ሶዶ ዙሪያ | X | | | X | | | | | | | | | |
| 11 | ሲዳማ | አለታ ወንዶ | X | | | | X | | | | | | | | |
| 12 | | ቤንሳ | X | | | | | | X | | | | | | |
| 13 | | ዳሌ | X | | | | X | | | | | | | | |
| 14 | | ደራ | X | | | | X | | | | | | | | |
| 15 | | ሸበዲኖ | X | | | | | X | | | | | | | |

| | ዞን/ ልዩ ወረዳ | የተረጠ ወረዳ | በአሚፕ ወረዳዋች የተመረጡ ምርቶች | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቡና | ቅመማ ቅመም | ብርዕ ሰብል | ጥራጥሬ | አትክልትና ፍራፍሬ | ማር | ቀቤ | ቆጮ | ቆዳና ሌጦ | በግ ድለባ | ዱባ ፍሬ | ካሳቫ | ቅባት እህል |
| 16 | ጋሞ ጎፋ | አርባምንጭ | | | | | X | | | | X | | | | |
| 17 | | ቦረዳ | | | X | | X | | | | | | | | |
| 18 | | ደንባ ጎፋ | | | | X | | | X | | | | | | |
| 19 | | መሎ | X | | | | | | X | | | | | | X |
| 20 | ዳውሮ | ማረቃ | | | X | | | | | | | | | | |
| 21 | ጉራጌ | አብሽጌ | | X | X | | | | | | | | | | |
| 22 | | ጉመር | | | X | | X | | | | | | | | |
| 23 | | መስቃን | | X | X | | | | | | | | | | |
| 24 | | ሶዶ | | | X | | | | | | X | | | | |
| 25 | ስሊጤ | ላንፍሮ | | X | X | | | | | | | | | | |
| 26 | | ስልጢ | | X | X | | | | | | | | | | |
| 27 | ቤንች ማጂ | ደቡብ ቤንች | X | X | | | | | | | | | | | |
| 28 | | ሸኮ | X | | | | | X | | | | | | | |
| 29 | ጌዲኦ | ወናጎ | X | | | | | | | X | | | | | |
| 30 | | ይርጋጨፌ | X | | | | | | | X | | | | | |
| 31 | ደቡብ ኦሞ | ደቡብ አሪ | X | X | | | | | | | | | | | |
| 32 | | ማሌ | X | | | | | | | | | | X | | |
| 33 | ሸካ | የኪ | X | X | | | | | | | | | | | |
| 34 | ከፋ | ጨና | X | | | X | | | | | | | | | |
| 35 | | ጊንቦ | X | | | | | X | | | | | | | |
| 36 | | ጠሎ | | | | X | | | | | | X | | | |
| 37 | ደራሼ ልዩ ወረዳ | | X | | X | | | | | | | | | | |
| 38 | አማሮ ልዩ ወረዳ | | X | | X | | | | | | | | | | |
| 39 | ቡርጂ ልዩ ወራዳ | | | | X | X | | | | | | | | | |
| 40 | ኮንሶ ልዩ ወረዳ | | | | | X | | | | | | | | X | |
| | | አጠቃላይ ድምር | 23 | 10 | 15 | 10 | 6 | 4 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |

የብርዕ ሰብል፡ በቆሎ፣ገብስ፣ ስንዴ፣ ጤፍ　　ቅመማ ቅመም፡ እርድ፣ ዝንጅብል፣ ኮሮሪማ፣ በርበሬ
ጥራጥሬ፡ ቦሎቄ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ኦቾሎኒ　　የቅባት እህል፡ ሰሊጥ
አትክልት እና ፍራፍሬ፡ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ አናናስ፣ ቲማቲም የተለያዩ አትክልቶች
ምንጭ፡- የኢፋድ/ግግማና የጥናት ቡድን

<u>ኢፋድ/አሚፕ በከጥናት ቡድኑ ጋር ያልዉ ህብረት</u>

የጃይካ ጥናት ቡድን ከኢፋድ/አሚፕ ጋር በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት አፈፃፀም (የታጠበና የደረቀ ዝንጅብል ማምረትና ከገዢ ጋር የማገናኘት) ተባብሯል፡፡ በተለይ በሃድሮ ጡንጦና በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳዎች በኢፋድ/አሚፕ ለታቀፉ የአርሶአደር ቡድኖች የዝንጅብል ማጠቢያ ዘዴ በሠርቶ ማሳያ ተግባራዊ አሠራሩን እንዲያዩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ ለጥራት ማሻሻያና ለእሴት ጭማሪ የሚሆን አግብብነት ያለዉ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም መረጃና የፍራፍሬ መሰብሰቢያና የካሳቫ መቁርጫ መሳሪያ ለኢፋድ/አሚፕ አርሶአደር ቡድኖች ተሰጥቷዋል፡፡

### 2.6.2 የዓለም የምግብ ፕሮግራም

የዓለም የምግብ ፕሮግራም ላለፉት በርካታ አስርት ዓመታት በኢትዮጵያ የምግብ እርዳታ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል ሁለቱ ከጃይካ የጥናት ቡድን አላማ ጋር የሚመሳሰሉ ናቸዉ፡፡ አንደኛው ግዢ ለእድገት የሚባል ሲሆን ሌላኛዉ የአከባቢ ሀብትን በማስተዳደር ለዘላቂ ኑሮ ማብቃት የሚል ነው፡፡

#### (1) ግዢ ለእድገት

የዓለም የምግብ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ለምግብ እርዳታ ከአገር ዉስጥ ገበያ የሚገዛቸዉ የምግብ አይነቶች አሉ፡፡ ከ2003 እስከ 2008 (እ.ኤ.አ) ባሉት ዓመታት የዓአለም የምግብ ፕሮግራም 146.5

ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዋጋ የሚያወጡ 573593 ቶን የብርዕ ሰብል፣ ጥራጥሬ፣ የተቀመመ ምግብ[4] እና ጨዉ ከአገር ዉስጥ ገበያ ገዝቷል፡፡ የጨረታ አዘገጃጀቱና ሂደቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመሆኑ ለአነስተኛ ነጋዴዎች ለሕ/ሥራ ማህበራት ለዩኒየኖች ለመሳተፍ እንቅፋት ሆኗል፡፡

ከዚህ አንፃር ከመስከረም 2008 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ የዓለም የምግብ ፕሮግራም አዲስ ከአካባቢ ግዥ መፈጸም የሚያስችል ግዥ ለዕድገት ፕሮግራም ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ይህም ብርዕና ጥራጥሬ ሰብሎች ከአርሶአደሩ መግዛት ያስችላል፡፡ ግዝ ለዕድገት በ5 ዓመት (2008-2013 እ.ኤ.አ) ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ከ5 ዓመት በኋላ የፕሮግራሙ አፈጻጸም ተገምግሞ እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡ የዚህ ፕሮግራም አላማ የአነስተኛ አርሶአደሮችን ገቢ ለማሳደግና ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶች የጥራት ተፈላጊነት ግንዛቤ ለማሳደግ ነዉ፡፡ በዚህ ፕሮግራም የሚሳተፉ ከ2 ሄ/ር በታች የመሬት ይዞታ ያላቸዉ አርሶአደሮች ናቸዉ፡፡ በእርግጥ ከበርካታ አርሶአደሮች የቀጥታ የእህል ግዢ ለመፈጸም ለዓለም የምግብ ፕሮግራም አመቺ አይደለም፡፡ ስለዚህ ከአምራቾች ዩኒየኖችና አነስተኛ ነጋዴዎች ለመግዛት ወሰኗል፡፡ በዚህ መሠረት የዓለም የምግብ ፕሮግራም የገንዘብና የሥራ አመራር ብቃታቸዉን እንዲሁም ቀደም ሲል ያለቸውን ውጤት መሠረት በማድረግ የአምራቾች ዩኒየኖችን መርጧል፡፡

በ2008 (እ.ኤ.አ) 15 ዩኒያኖችን እህል ሰብል እንዲያቀርቡ ተመርጠዋል፡፡ በ2010 (እ.ኤ.አ) አንድ ዩኒያን ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በተጨማሪነት ተመርጧል፡፡ እስከ 2012 (እ.ኤ.አ) ባለው ጊዜ 16 ዩኒያኖች (9 ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ 4 ከኦሮሚያ፣ 2 ከአማራ እና 1 ከአዲስ አበባ) በግዥ ለዕድገት ፕሮግራም እየተሳተፉ ነው፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ከ8 ዩኒያኖች በ2010 (እ.ኤ.አ) የዓለም የምግብ ፕሮግራም 2200 ቶን ቦሎቄና 3900ቶን በቆሎ ለመግዛት እቅድ ነበረው፡፡ ሆኖም ከግዢ ሂደት መዝግየትና ከአምራቾች ዩኒያኖች የአቅም ማነስ የተነሳ ሊገዛ የቻለዉ 1789 ቶን ቦሎቄና 2650 ቶን በቆሎ ብቻ ነዉ፡፡

የዓለም የምግብ ፕሮግራም የብርዕ ሰብልና ጥራጥሬ ግዢ የሚፈፅመዉ በራሱ የጥራት ደረጃ መመዘኛ መሠረት ነዉ፡፡ በዚህ መሠረት በ4 ክልሎች ለ15 የተመረጡ ዩኒያኖች (በሚቀጥለዉ ሠንጠረዥ የተዘረዘሩ እቃዎችንና መሣሪያዎችን) የጥራት ደረጃቸዉን አቅም እንዲያሳድጉ አሰራጭቷል፡፡ ሳሳካዋ አፍሪካ አሶሴሽን ከተባለ ድርጅት ጋር በገባዉ የኮንትራት ዉል መሠረት ከእነዚህ አምራቾች ዩኒያኖች ለተመረጡ የንብረት ክፍል ኃላፊዎችና ሠራተኞች ነሐሴ 2010 (እ.ኤ.አ) ስልጠና እንዲያገኙ አድርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.6-2 በዓለም የምግብ ፕሮግራም ተሳታ ዩኒያኖች የተሰራጨ መገልገያዎች**

| | ዝርዝር | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | መመርመሪያ | 15 |
| 2 | ጠንቀሳቃሽ ናሙና መካፋፈያ | 15 |
| 3 | ጉጠት | 15 |
| 4 | የእርጥበት መለኪያ | 75 |
| 5 | ሚዛን (ዲጂታል ሚዛን 2000 ግራም x 0.1 ግራም) | 75 |
| 6 | ማጠኛ ሸራ (18 ሜተር x 12 ሜትር) | 12 |
| 7 | ፀረ-ተባይ መርጫ (12 -15 ሊትር) | 15 |
| 8 | ተንቀሳቃሽ ጎኒያ መስፍያ ማሽን | 15 |
| 9 | ወንፊት የበቆሎ፣ ስንዴ፣ ማሽላ፣ ቦሎቄ እና ባቄላ | 15 |
| 10 | የተለያዩ እህል ማበጠሪያ (1 ቶን በሰዓት፣ ሠላም ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኝ የተሠራ) | 20 |
| 11 | በሰው ኃይል የሚሠራ በቆሎ መፈልፈያ (አነስተኛ መጠን ያለው 1.5 ቶን በሰዓት፣ ሠላም ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኝ የተሠራ) | 550 |
| 12 | በቆሎ መፈልፈያ (1.5 ቶን በሰዓት፣ ሠላም ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኝ የተሠራ) | 28 |

ምንጫ፡ ዓለም የምግብ ፕሮግራም ኢትዮጵያ ጽ/ቤት

[4] የተቀመመ ምግብ መካከል አንዱ ፋሚክስ ¥¥¥¥¥ ሚባለው ከተቆላ በቆሎ ድብልቅ ነው፡፡ ፋሚክስ ኢትዮጵያ ውስጥ 7-8 የሚሆኑ የግል የምግብ ማቀነባበሪያ ፋቢርካዎች በብቸኝነት ያመርታሉ፡፡ እያንዳዱ ፋብሪካ 5000 ቶን የብርዕ ሰብል ፋሚክስ ማምረት በየአመቱ ይገዛሉ፡፡

**ከጥናት ቡድኑና ከአለም የምግብ ፕሮግራም/ግዢ ለልማት መካከል ያለዉ ህብረት**

የዓለም የምግብ ፕሮግራም የእቃዎችና የመሳሪያዎች አጠቃቀም ጎን ለጎን በድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂ አስመልክቶ ግዢ ለእድገት ተሳታፊ ዩኒያኖች ስልጠና ይሰጣል ነገር ግን ስልጠናዉ በንድፈሀሳብ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የክህሎት እጥረት በመፍጠሩ ሰልጣኞች በቀጥታ ተግባራዊ ለማድረግ ተቸግረው ነበር፡፡ ስለሆነም ስልጠናዉን ዉጤታማ ለማድረግ የስልጠነዉን ይዘትና የስልጠና ማቴሪያሎች መመርመር አስፈላጊ ነበር፡፡ የጥናት ቡድኑ በአደረገው ጥናት መሠረት ሕ/ሥራ ማህበራት የንብረት ክፍል ሰራተኞች ስራቸዉን በብቃት ለመወጣት የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂ እወቀትና ክህሎት እንደሚጎላቸው ሊያረጋግጥ ችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የጥናት ቡድኑና የዓለም የምግብ ፕሮግራም በጋራ ዉይይት በግዢ ለእድገት ማዕቀፍ ዉስጥ የጥናት ቡድኑ የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂ በተመለከተ ለተሳታፊዎች ቀላልና ተግባራዊ ክህሎት የሚጣስጨብጥ ስልጠና በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች 02 እና 08 አዘጋጅቷል፡፡ በዚህ መሠረት የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቱ የስልጠና ቁሳቁሶችን እንደ ምስል ካርድና ፖስተሮችን አዘጋጅቶ ለግዢ ለእድገት ተሳታፊ ዩኒየኖችና በሥራቸው ለሚገኙ 19 መሠረታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት ስልጠና ሰጥቷል፡፡

**(2) የአከባቢ ሀብትን በመቆጣጠር በማስተዳደር ለዘላቂ ኑሮ እደገት ማብቃት**

የዓለም የምግብ ፕሮግራም ከአስቸካይ የምግብ እርዳታ በተጨማሪ የምግብ ለሥራ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ምግብ ለሥራ ፕሮግራም ከምግብ እርዳታ ፕሮግራሞች አንዱ ሲሆን ተጠቃሚዎች የምግብ እርዳታ የሚያገኙት በጉልበት ሥራ በሚያበረክቱት መጠን ነዉ፡፡ የምግብ ለሥራ ፕሮግራም ብዙ ጊዜ የሚነሳዉ ብዙ አይነት ህዝባዊ ሥራዎች ጋር የሚያያዝ እንደመሆኑ ብዙም ውጤታማ አለመሆኑ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የአከባቢ ሀብት በመቆጣጠርና በማስተዳደር ለዘላቂ ኑሮ እድገት ማብቃት ፕሮግራም በደን መልሶ ማልማትንና የተፋሰስ ዉሃ አስተዳደር ላይ ያተኩራል፡፡ የተፋሰስ ዉሃ አስተዳደር የዉሃ ማጠራቀም፤ የገጠር መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና እና ገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞችን ያካትታል፡፡ የጥናት ቡድኑ በመጀመሪያ ደረጃ ከአከባቢ ሀብት ቁጥጥርና አስተዳደር ለዘላቂ ኑሮ እድገት ጽ/ቤት ጋር ህብረት ለመፍጠር አስቦ ነበር ሆኖም ተጨባጭ የሆነ ህብረት መመስረት አልተቻለም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የተመረጡ ወረዳዎች ዋና ጥያቄያቸዉ የእቃዎችና በተለይም የጭነት መኪናዎች ስለነበረ ነዉ፡፡

### 2.6.3 የግብርና እደገት ፕሮግራም- የዓለም ባንክ

የግብርና እድገት ፕሮግራም ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ የተገመተዉ በሰኔ 2010 (እ/ኤ/አ) ነበር፡፡ ሆኖም ለተወሰነ ጊዜ ዘግይቶ ተጀምሯል፡፡ በደቡብ ክልል ለፕሮግራሙ 19 ወረዳዎች ተመርጠዋል፡፡ የፕሮግራሙ ቅድመ ግምገማ ሚሽን በየካቲት 2010 (እ/ኤ.አ) እንዳቀረበው ሪፖርት የግብርና እድገት ፕሮግራም ጠቅላላ በጀት 250 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ ሲሆን 87.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል የሚመደብ ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.6-3 የፕሮጀክት ወጪ ዝርዝር የበጀት ምንጭ ማጠቃለያ**

| ዘርፍ | የበጀት ምንጭ (ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) | | | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| | በጋራ የተዋጣ | ጎን ለጎን | ድምር | |
| **1. የግብርና ምርትን ማሳደግና ገበያ ተኮር ማድረግ** | 67 | 45 | 112 | 45 |
| 1.1 ተቋትን ማጠናከርና ማስፋፋት | 34 | 0 | 34 | 14 |
| 1.2 ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋፋት | 27 | 0 | 27 | 11 |
| 1.3 የግብይትና አግሪ-ቢዝነስ ልማት | 6 | 45 | 41 | 20 |
| **2. የገጠር መሠረተልማት ልማትና አስተዳደር** | 117 | 0 | 117 | 47 |
| 2.1 የአነስተኛ የገጠር መሠረተልማት ልማትና አስተዳደር | 70 | 0 | 70 | 28 |
| 2.2 የአነስተኛ የገበያ መሠረተልማት ልማትና አስተዳደር | 41 | 0 | 41 | 16 |

| ዘርፍ | የበጀት ምንጭ (ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) | | | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| | በጋራ የተቀዋጣ | ጎን ለጎን | ድምር | |
| **3. የፕሮጀክት አስተዳደር፣ ክትትልና ግምገማ** | 16 | 5 | 21 | 8 |
| 3.1 የፕሮጀክት አስተዳደር | 14 | 0 | 14 | 6 |
| 3.2 ክትትልና ግምገማ | 2 | 5 | 7 | 3 |
| **ድምር** | 200 | 50 | 250 | 100 |

ማስታወሻ፡ የበጀት ምንጭ በጋራ የተዋጣ የተባለው ከአለም ባንክ ሲሆን ጎን ለጎን የተባለዉ ከአሜሪካ የእርዳታ ድርጅት ነዉ።
ምንጭ የአለም ባንክ የኢትዮጵያ ጽ/ቤት፡

በደቡብ ክልል የ19 ወረዳዎች የምርጫ መመዘኛ

- የሶፍት ኔት ፕሮግራም ያልታቀፈ ወረዳ
- በቂ የገበያ ተደራሽነት በተለይ (በመንገድና በቴሌኮሚኒኬሽን)
- የአከባቢ የተፈጥሮ ሀብት (የዝናብ ስርጭት፤የአፈር ለምነት፤የአከባቢዉ የሀብት አለኝታነት እና የሚበቅሉ የእህል አይነቶች
- ተቋማዊ አቋም (የሲቪል ባለሙያዎች ብዛትና የክህሎት ደረጃ፣ ተቋማት አገልግሎት የመስጠት ጥንካሬ፣ የፋይናንስ አገልግሎት፣ የሕ/ሥራ ማህበራትና የአርሶአደር ቡድን መኖር)
- የዞኖች በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ያላቸዉ ፍቃደኝነትና ቁርጠኝነት የሚሉ ናቸዉ።

የተመረጡ ወረዳዎችና የተመረጡ የግብርና ምርት ዝርዝር በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 2.6-4 የግብርና እድገት ፕሮግራም ወረዳዎችና የተመረጡ ምርቶች

| | ዞን | ወረዳ | ህዝብ | ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ምርቶች |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሲዳማ | ወንዶ ገነት | 153,283 | በቆሎ፣ ቦሎቄ፣ ድንች፣ ገብስ፣ እንስሳት |
| 2 | | መልጋ | 114,030 | |
| 3 | | ገርቼ | 139,780 | |
| 4 | ሲሊጤ | ምዕራብ አዝርነት | 59,844 | ገብስ፣ ስንዴ፣ በርበሬ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ አፕል |
| 5 | | ምስራቅ አዝርነት | 50,722 | |
| 6 | ጉራጌ | እነሞር ኢኒር | 167,745 | ስንዴ፣ ጤፍ፣ ቡና፣ በቆሎ |
| 7 | | እንደገኛ | 53,103 | |
| 8 | ደቡብ ኦሞ | ሰሜን አሪ | 212,389 | ቡና፣ በሎቄ፣ በቆሎ፣ ኮሮሪማ፣ ኦቾሎኒ፣ ማናጎ፣ ማድለቢያ |
| 9 | | ደቡብ አሪ | 67,798 | |
| 10 | ዳውሮ | እሰራ | 53,075 | አተር፣ ቡና፣ ኮሮሪማ፣ በርበሬ፣ ማድለቢያ |
| 11 | ከፋ | ጨና | 157,085 | ቦሎቄ፣ ኮሮሪማ፣ ቡና፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ አፕል፣ ማድለቢያ |
| 12 | | ደቻ | 128,853 | |
| 13 | ቤንች ማጂ | ሰሜን ቤንች | 109,287 | አተር፣ ኮሮሪማ፣ መቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ዝንጅብል |
| 14 | | ደቡብ ቤንች | 87,182 | ቡና፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ኮሮሪማ፣ ማናጎ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ሃር |
| 15 | ጌዲኦ | ቡሌ | 108,519 | ገብስ፣ እንሰት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ በቆሎ፣ አተር፣ አፕል፣ ማድለቢያ |
| 16 | | ገደብ | 146,732 | |
| 17 | ልዩ ወረዳ | ኮንታ | 92,703 | ቡና፣ በቆሎ፣ አተር፣ ጤፍ፣ በሎቄ፣ ገብስ |
| 18 | | የም | 80,647 | ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ አተር፣ ኦቾሎኒ |
| 19 | | ባስኬቶ | 56,678 | ጤፍ፣ በቆሎ፣ ኮሮሪማ፣ ቡና |

ምንጭ፡-የግብርና እድገት ፕሮግራም

የፕሮጀክቱ እቅድ ወይም ምርጫ በፍላጎት የተመሠረተና ከታች ወደላይ አቀራረብ ከንኡስ ቀበሌና ከቀበሌ ጀምሮ የአከባቢዉ ህብረተሰብና አርሶአደር ቡድኖች የተሳተፉበት ነዉ። የመንግስት ሠራተኞች በክልል፣ በዞንና በወረዳ ያሉት የቴክኒክ ድጋፍ እና ወይም ክትትል ከጎን ለጎን የበጀት

ምንጭ ከሚንቀሳቀሱ ፕሮጀክቶች[5] በስተቀር ያደርጋሉ፡፡ የግብርና እደገት ፕሮግራም በተመረጡ ወረዳዎች በንኡስ ቀበሌ ወይም በቀበሌ ደረጃ ቀስ በቀስ እና በሁሉም ቀበሌዎች ብዙ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን በመጨረሻም በተመረጡ ወረዳዎች በሙሉ ይሸፍናል፡፡

የግብርና እድገት ፕሮግራም አካል የሆነው በአሜሪካ ተራደኦ ድርጅት የሚደገፍ የግብይትና አግሪ-ቢዝነስ ልማት ኤስ.ዲ.አይ/ቮካ የሚባል ድርጅት ተቀጥሮ በ19 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ወረዳዎች የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እያደረገ ነው፡፡ ይህ የ5 ዓመት ፕሮጀክት ሲሆን በታህሣሥ 2011 (እ.ኤ.አ) ሥራውን ጀምሯል፡፡ ሐምሌ 2012 (እ.ኤ.አ) ኤስ.ዲ.አይ/ቮካ ቢሮውን በሀዋሣ በመክፈት ፕሮጀክቶችን በማስፈጸም ላይ ይገኛል፡፡ ትኩረትም የተሰጣቸው ሰብሎች 4 ሲሆኑ እነርሱም ቡና፣ በቆሎ፣ ጤፍ እና ስንዴ ናቸው፡፡

<u>የግብርና እደገት ፕሮግራም ከጥናቱ ያለዉ ህብረት</u>

የጥናት ቡድኑ በ2011 (እ.ኤ.አ) በከምባታ ጠምባሮ ዞን ዘመናዊ መጋዘን ግንባታ፣ በሲዳማ ዞን የበሎቄ ገበያ ማዕከል ግንባታ፣ እና በከምባታ ጠምባሮ ዞን የዝንጅብል ገበያ ግንባታ የሙከራ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ እነዚህም የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክቶች የተቋም አስተዳደር ስልጠናም ያካተተ ሲሆን የመጋዘን አስተዳደር ስልጠና ለግብርና ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች እንዲሁም የገበያ አስተዳደር ስልጠና ለማዘጋጃ ቤቶች ተሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ግብርና እድገት ፕሮግራም በ2012 (እ.ኤ.አ) ለተለያዩ የግብርና ምርቶች 7 የገበያ ማዕከላትን በ6 የተመረጡ ወረዳዎች ለመገንባት ተመሳሳይ ዕቅድ ይዟል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የመንግሥት ሠራተኞች (በክልል፣ ዞን እና ወረዳ) የቴክኒክ እገዛና ክትትል በግብርና እድገት ፕሮግራም ለተያዙ ፕሮጀክቶች እንደሚሰጡ ይጠበቃል፡፡ ይሁንና እነዚህ ሠራተኞች የገበያ ማዕከልና መጋዘን የግንባታ አስመልክቶ ምንም ሥራ ልምድ የላቸውም፡፡

የጃይካ ጥናት ቡድን  የገበያ ቦታና መጋዘን የግንባታ መረጃ እንደ ዲዛይን፣ የዋጋ ዝርዝር (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ)፣ የሥራ ዝርዝር መግለጫ ወዘተ...በመስጠት ትብብር አድርጓል፡፡ የጥናት በድኑ ከዚህ ሌላ ከላይ የተገለጹት ግንባታ ከሚካሄድባቸው ዞኖችና ወረዳዎች ለተወጣጡ ባለሙያዎች የገበያ ማዕከል ግንባታ በሚመለከት አውደጥናት በማዘጋጀትና እንዲሳተፉ በማድረግ ልምዱን አካፍሏል፡፡ አውደጥናቱ  ያካተተዉ

1) አመራርን በተመለከተ፤
2) ቴክኒክን በተመለከተ፣
3) የበሊሳ ገበያ ማዕከል አመራር ኮሚቴ የልምድ ልዉዉጥ፣ እና
4) በገበያ ቀን የበሊሳ የገበያ ማዕከል ጉብኝት ማድረግ፡፡

ሁሉም የዚህ አውደጥናት ተሳታፊዎች የስልጠናዉን አግባብነትና ተጨባጭነት ስልጠናዉን ለሰጠው የጥናት ቡድን ገልፀዋል፡፡

የጥናት ቡድኑ ነሐሴ 2012 (እ.ኤ.አ) የግብርና እድገት ፕሮግራም የግንባታ ቦታዎችን ጎብኝት በማድረግ ገደብ ወረዳ ውስጥ ጮርሶ ከተማ እየተሠራ ያለውን የገበያ ማዕከል ተመልክቷል፡፡ በግቡኝት ወቅት የታዩ ጉዳዮች፡

1) ግንባታው ቁልቁለታማ ቦታ ላይ ነው እየተካሄደ ያለው፡፡ ይሁንና ከመሬቱ አቀማመጥ ጋር በሚሄድ ዓይነት መልኩ የገበያ ማዕከሉ አቀማመጥ ዲዛይን አልተደረገም፡፡
2) ወደ ገበያ ቦታ መግቢያና በውጫ ጠባብ ነው፡፡
3) በሁለት ግንባታዎች መካካል ያለው ክፍተት አነስተኛ ነው፡፡

[5] ለምሳሌየክልል ገገጠር መንገድ ባለሥልጣንና የአካባቢ አስተዳደር (ወረዳ/ቀበሌ) የመጋቢ መንገድ ግንባታን በጋራ ይከታተላሉ፡፡ የተቀናጀ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በተመለከተ የተፈጥሮ ሀብት የሥራ ሂደት፣ የክልል ግብርና ቢሮ፣ የዞን ግብርና መመሪያ እና የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ሀላፊነት ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተው በሙሉ በስልጠና ወቅት በስፋት የተገለጸና በሊላ የገበያ ማዕከል ጉብኛት ወቅት የተብራራ ቢሆንም በአግባቡ ተረድቶ ለመሥራት ረዘም ያለ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል፡፡ የግብርና እድገት ፕሮፌ,ግራም ወደ 13 የገበያ ማዕከላትን በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ እንደሚገነባ ይጠበቃል፡፡ የጥናት ቡድኑ ምህድስና ክህሎት በቀጣይ ባለው የግብባታ ወቅት እንደሚሻሻል ይጠብቃል፡፡

### 2.6.4 የጃይጃ አንድ መንደር አንድ ምርት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ኦቮፕ)

የጃይካ የአንድ መንደር አንድ ምርት ማስፋፊያ ፕሮጀክት የተጀመረዉ በመጋቢት 2010 (እ.ኤ.አ) ሲሆን የቆይታ ጊዜዉም እስከ ግንቦት 2014 (እ.ኤ.አ) ለ4 ዓመታት ነዉ፡፡ የፕሮጀክቱ አላማ የግብርና ምርት ተጨማሪ እሴት ለማስገኘት የቴክኖሎጂ/ፋይናንስ/የመረጃ ተደራሽነት እጥረት ያለባቸዉን አርሶአደሮች ለማገዝ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ ፕጀክቱ የነበረው ፈታኝ ሁኔታዎች፡- ሀ) በክልል እና በፌደራል ደረጃ ተግባራዊ ሊሂን የሚችል የአንድ መንደር አንድ ምርት ማስፋፊያ ሥርዓት መፍጠር፣ ለ) ለገጠር ልማት የሚሆን ሞዴል የመንደር ምርት በሚስፋፋት ሂደት መፍጠር ናቸዉ፡፡ የደ/ብ/ብ/ህ/ክልል የዚህ ሞዴል የሚመሰረትበት ክልል ነዉ፡

የመንደር ምርት በመፍጠርና ለገበያ አውታር ከመዘርጋት አኳያ ኦቮፕ የአርሶአደር ቡድኖችን (ከሌላ ወይንም ኩባንያ የኦቮፕ አጋር ከሚባሉት) የሙያና የግብይት እገዛ ለመስጠት አቅም ያላቸው ጋር መገናኘት እንደአቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

በነሐሴ 2012 (እ.ኤ.አ) ኦቮፕ በደቡብ ክልል ለ14 አርሶአደር ቡደኖች ድጋፍ ይሰጥ ነበር፡፡ የእነዚህ አርሶአደር ቡድኖች ያሉበት ስፍራ፣ የቡድን ስም፣ የታለመ የንግድ ሥራ አይነት (የተመረጡ ምርቶች) እና ኦቮፕ ተባባሪ አካላት እንሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.6-5 የአርሶ አደር ቡድኖች የስራ አይነት እና የፕሮጀክቱ ተባባሪዎች**

| ያለበት ቦታ(ወረዳ) | የቡድን ስም | የተመረጠ የስራ አይነት (ምርት) | የቴክኒክ ድጋፍ | የገበያ ድጋፍ |
|---|---|---|---|---|
| አንደራቻ | እድገት በአንድነት | እንሰት ማቀነባበሪ (ቆጮ፣ቡልአ) | የግብርና ሚኒስቴር፣ ሰዶ ገ/ቴክኖሎጂ ማዕከል ክልል/ዞን ግብር ቢሮ | |
| | ቡሎ ቤነናይ | | | |
| | ኩምበክቻ ቡድን | ማር | ቤዛ ማር | ቤዛ ማር |
| አርባምን ጭ ዙሪያ | ሃሬ | ሙዝ ወረቀት | ተስፋዬ | ተስፋዬ |
| | ፍቅር ማህበር | በርበሬ ድልህ (ዳታ) ማቀነባበር | ኢኮፒያ | ኢኮፒያ |
| | ኩርሼቴ | ማንጎ (ጃም) ማቀነባበር | ኢኮፒያ | ኢኮፒያ |
| ቦሎሶ ቦምቤ | ማገራ | ዝንጅብል ማጠብና ማድረቅ | ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ | ቦሜስ |
| | የእድገት ቡድን | | | |
| | ፍራፍሬ ልማት | ማነጎ(ጃም ማቀነባበሪያ) | ኢኮፒያ | ኢኮፒያ |
| ጌታ | እድገት ማህበር | ቀርከሀ ስራ | የቴክኖሎጂ ሽግግር እና መርምር ማእከል የኢት/ቱሪስት ንግድ ድርጅት | ወረዳ ኦቮፕ ኮሚቴ |
| | የ.ወ.ኤል ማህበር | ገብስ ማቀነባበር | የግብርና ሚ/ር የግብርና ቢሮ | ወረዳ ኦቮፕ ኮሚቴ |
| | የስረሼ ኢካሳይ | ኮሰረት (ቅመም) ማድረቅ | የግብርና ሚ/ር የግብርና ቢሮ | |
| ላንፋሮ | ልማት በእድገት | ቀይ በርበሬ ማቀነባበር | መልካሳ ግብርና ምርምር ማህበር | |
| | ለምለም | ማር | የግብርና ሚ/ር የግብርና ቢሮ | |

ምንጭ፡- የአንድ መንደር አንድ ምርት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ነሀሴ 2012 (እ.ኤ.አ)

**ከጥናት ቡድኑና አንድ መንደር አንድ ምርት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ያለዉ ህብረት**

ከሁለቱ የጃፓን ዓለም አቀፍ ተራደኦ ድርጅት ፕሮጀክቶች መካከል በየጊዜዉ የመረጃ ልዉዉጥ ሲካሄድ ቆይቷል። የቴክኒክ ድጋፍ በሚመለከት የጥናት ቡድኑ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 አማካኝነት በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ለሚገኙ የኦቮፐ አርሶአደር ቡድኖች ስለዝንጅብል ማጠብና ማድረቂያ መሠረተልማቶች አቋቋምና ስለዝንጅብል ማጠቢያ ዘዴ ከሙከራ ትግበራው ፕሮጀክት የተገኘውን ተሞክሮ ገለፃ ሰጥቷል።

በተጨማሪም የጥናት ቡድኑ ስለማጠቢያ መሠረተልማት ዲዛይን፣ የቦታ አቀማመጥ እና ዕቅድ ዝግጅት አስመልክቶ ለእነዚሁ የኦቮፐ ቡድኖች ምክር ሰጥቷል።

# ምዕራፍ 3 የጥናት አካባቢ አሁን ያለው ሁኔታ

## 3.1 የተመረጡ እህሎች የምርት የግብይትና የድህረምርት አያያዝ

### 3.1.1 የብርዕ ሰብል

#### (1) የብርዕ ሰብል ምርት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ዋነኛው የምግብ ፍጆታ እህል የብርዕ ሰብል ቢሆንም የሚመረተው ምርት የሀገሪቱን ፍላጐት የማያሟላ በመሆኑ ከውጭ ማስገባት የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ እና ማሽላ ዋና ዋና እህሎች ሲሆኑ ዘንጋዳ ፣አጃና ሩዝም ይበቅላሉ፡፡

በቆሎ በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን ሰፋ ባለ የአየር ፀባይ ባለበት አካባቢ በዋነኝነት በወይናደጋ አካባቢ ይመረታል፡፡ ጤፍ ፣ ስንዴ ማሽላ እና ገብስም በተመሳሳይ አየር ፀባይ ባለበት ይበቅላሉ፡፡ በአብዛኛው ስንዴ፣ ገብስ የቅባት እህልና ጥራጥሬ የአየር ፀባዩ /ከ2300-3200 ሜትር ከባህር ወለል በላይ በሆኑ ደጋ አካባቢዎች ይበቅላሉ፡፡ ማሽላና ዘንጋዳ ድርቅ የመቋቋም ችሎታ ያላቸው በመሆኑ በከፊል ደረቅና ዝቅተኛ አካባቢዎች ዋና እህሎች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ዋነኛ የእህል ምርቶች የሚበቅሉት በዋነኛ የዝናብ ወቅት (መኸር) ነው፡፡ በበልግ ዝናብ ወቅት የሚመረተው የእህል መጠን ከዓመታዊ የምርት መጠን ከ5-10% አይበልጥም፡፡ ሆኖም በደቡብ ክልል እስከ 75% የበቆሎ ምርት የሚገኘው በበልግ ዝናብ ነው፡፡

በሀገሪቱ አብዛኛው የብርዕ ሰብል የሚመረተው ኦሮሚያና አማራ ክልል ሲሆን 82% የሚሆነው የብርዕ ምርት እና 79% የገበያ ሽያጭ መጠን ያለው በነዚሁ ክልሎች ነው፡፡ በተለይ ኦሮሚያ ብቻውን ያለው ድርሻ የሀገሪቱ 50% ምርትና 49% የገበያ ሽያጭመጠን ይሆናል፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-1 የኢትዮጵያ የብርዕ ሰብል ምርትና የገበያ ሽያጭ መጠን

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | ለገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. ኦሮሚያ | 8,797,243 | 49.5% | 14.74% | 1,296,714 | 48.5% |
| 2. አማራ | 5,702,436 | 32.1% | 14.48% | 825,713 | 30.9% |
| 3. ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | 1,480,151 | 8.3% | 21.96% | 325,041 | 12.2% |
| 4. ትግራይ | 1,309,359 | 7.4% | 12.50% | 163,670 | 6.1% |
| 5. ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 306,431 | 1.7% | 13.92% | 42,655 | 1.6% |
| 6. ሶማሌ | 105,970 | 0.6% | 12.16% | 12,886 | 0.5% |
| 7. ሌሎች | 59,771 | 0.3% | 12.13% | 7,250 | 0.3% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 17,761,361 | 100.0% | 15.06% | 2,673,929 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

#### (2) የብርዕ ሰብል ምርት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል

የደቡብ ክልል በሀገሪቱ 3ኛ ትልቁ የብርዕ ሰብል አምራች አካባቢ ነው፡፡ ድርሻውን ስንመለከት 8% ምርትና 12% የገበያ ሽያጭ መጠን አለው፡፡ የብርዕ ሰብል ምርትና የገበያ ሽያጭ መጠን በደቡብ ክልል ያለው በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የብርዕ ሰብል ምርትና የሽያጭ መጠን

| ዓይነት | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. በቆሎ | 556,547 | 37.7% | 12.83% | 71,405 | 21.8% |
| 2. ጤፍ | 296,760 | 20.1% | 42.03% | 124,728 | 38.1% |
| 3. ስንዴ | 244,603 | 16.6% | 28.33% | 69,296 | 21.2% |
| 4. ገብስ | 198,213 | 13.4% | 19.42% | 38,493 | 11.8% |
| 5. ማሽላ | 175,126 | 11.9% | 13.09% | 22,924 | 7.0% |
| 6. ዳጉሳ | 4,267 | 0.3% | 6.73% | 287 | 0.1% |
| 7. አጃ | 289 | 0.0% | 7.95% | 23 | 0.0% |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ድምር | 1,475,805 | 100.0% | 21.96% | 327,156 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

ጤፍ ከፍተኛ የሽያጭ መጠን (38.1%) ያለው ሲሆን ቀጣዮቹ በቆሎ 21.8% እና ስንዴ 21.2% ድርሻ አላቸው፡፡ ሌሎች የብርዕ ሰብሎች የሚመረቱት ለቤት ፍጆታ ሲሆን የዘንጋዳና አጃ የሽያጭ ደረጃ ዜሮ ለማለት ይቻላል፡፡

(3) የገበያ ዘዴ/ሁኔታ


በአብዛኛው አነስተኛ አርሶ አደሮች ትርፍ እህል (በቆሎና ስንዴ) ለነጋዴዎች በሳምንታዊ ገበያ ቦታዎች ወይንም ለመንደር ነጋዴዎች ይሸጣሉ፡፡ እነዚህ ነጋዴዎች ጥራቱ ዝቅተኛ ለሆነው ምርት ዝቅ ያለ ዋጋ ይከፍላሉ፡፡ ጥራቱ የተሻለ ቢሆን እንኳን ዋጋ አይጨምሩም፡፡ ስለዚህ አርሶአደሮች የጥራት ደረጃውን ለማሻሻል እንደ በንፋስ ማበጠር የመሳሰለውን ሥራ ለመሥራት አይበረታቱም፡፡

በመሠረቱ የብርዕ ሰብሎች የገበያ ትስስር ብዙ የገበያ ተዋናዮችን ያካትታል፡፡ እነርሱም አምራች (አርሶአደሮች፣ ሕ/ሥራ ማህበራት፣ የሕ/ሥራ ዩኒየኖች፣ የግል እርሻና የመንግሥት እርሻ) ተቀባዮች፣ ሰብሳቢዎች፣ የግብርና/ግብይት ወኪሎች፣ደላላዎች፣ ጅምላ ነጋዴዎች፣ ቸርቻሪዎች፣ ላኪዎች/አስመጪዎች፣ የኢትዮጵያ እህል ገበያ እንተርፕራዝ፣ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ሸማቾች ወዘተ…ናቸው፡፡ እነዚህ የገበያ ተዋናዮች ብዙና የተለያየ ደረጃዎች አላቸው፡፡ የሀገር ውስጥ ጅምላ ነጋዴዎች በገበያ ትስስሩ ብዙ ጠቃሚ ሚና ይጫወትሉ፡፡ ትርፍ እህል ከአርሶአደሮች፣ ከሕ/ሥራ ማህበራት፣ ከሕ/ሥራ ዩኒየኖችና ከነጋዴዎች ከአምራቾች አካባቢ ገዝተው ወደ አ/አበባ ማዕከላዊ ገበያና አንዳንድ ጊዜ የእህል እጥረት ወደ ሚታይባቸው አካባቢዎች ያቀርባሉ፡፡ በትርፍ አምራች አካባቢ ያሉ ጅምላ ነገዴዎች እህሉን ከአርሶአደሮች፣ ሕ/ሥራ ማህበራትና ከሕ/ሥራ ዩኒየኖች ገዝተው ወደ ገጠር አካባቢ ገበያ ማዕከል ያቀርባሉ፡፡ እህል እጥረት ያለበት አካባቢ ያሉ ጅምላ ነጋዴዎች እህል ከአ/አበባ ማዕከላዊ ገበያና ከሌሎችም ዋና ዋና ገበያ ማዕከላት ገዝተው የእህል እጥረት ባሉባቸው አካባቢ ቸርቻሪዎችና ሸማቾች ይሸጣሉ፡፡

በክልሉ ሰሜናዊ አካባቢ የእህል ማጓጓዣ ዋጋ በተነፃፃሪ የተሻለ የመንገድ መሠረተልማት በመኖሩ ዝቅ ያለ ነው፡፡ ከዚህ ሰሜናዊ የእህል ምርት ዞን የሚሰበሰበው እህል ወደ አ/አበባ ማዕከላዊ ገበያና ወደ ሻሸመኔ፣ ሶዶ፣ ሆሳዕናና ወደ ሌሎችም ገበያዎች ይቀርባል፡፡

የገበያ ሰንሰለቱ ሰፊና የተወሳሰበ ነው፡፡ ብዙ የሥርጭት መስመር ያላቸው ተዋናያን አሉ፡፡ ዋናው የሥርጭት መስመር: ምርት → ነጋዴ(ሰብሳቢ)→ ጅምላ ነጋዴ→ ቸርቻሪ → ሸማች ነው፡፡ በሀገር ውስጥ በክልሎች መካካል በአለው የእህል ንግድ ደላላዎች ገበያ ትስስር

በመፍጠር ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በሚቀጥለው ምስል የበርዕና ጥራጥሬ ሰብሎች የገበያ ሰንሰለት ተከልክቷል፡፡




**ምስል 3.1-1 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የብርዕ ሰብልና ጥራጥሬ የገበያ ፍሰት**

የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን፣ የዓለም የምግብ ኘሮግራምና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የየራሳቸው የእህል የጥራት ደረጀዎች አላቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ የጥራት ደረጃዎች በሀገር ውስጥ የእህል ገበያ ላይ ተግባራዊ እየሆኑ አይደለም፡፡ የዓለም የምግብ ኘሮግራሞና ወይም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በሚሳተፉባቸው የእህል ገበያ ላይ የጥራት ደረጃ የሚወሰነው በዓይን እይታና በመነካካት ነው፡፡

ሊቻ ሃዲያ የሕ/ሥራ ዩኒየም በሃዲያ ዞን ትልቅ የስንዴ ዱቄት ፋብሪካ ያለው ሲሆን ስንዴ የሚገዛውም ከዩኒየኑ አባላት ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ከአባል አርሶአደሮች የተሰበሰበውን ስንዴ በማጣሪያ ማሽን አበጥረው ለአካባቢው ነጋዴዎች ይሸጣሉ፡፡ የዚህ ዓይነት ሥራ ለመሥራት ብቃት ያላቸው የሕ/ሥራ ዩኒየኖች በቁጥር በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ በመሠረቱ አነስተኛ አርሶአደሮች ትርፍ ምርታቸውን ለነጋዴዎች ወይንም ለሕ/ሥራ ማህበራት የሚሸጡት በግል ነው፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራትን በሚመለከት ሁለት ዓይነት አካሄዶች አሉ፡፡ አንዱ በግኘ ለዕድገት የሚሣተፉ ሕ/ሥራ ማህበራት እህሉን በዓለም የምግብ ኘሮግራም ምዘና ደረጃ መሠረት እህሉን አበጥረው በጆኒያ ይሞላሉ፡፡ ሁለተኛው አካሄድ የሕ/ሥራ ማህበሩ እህሉን አያበጥሩም ነገር ግን የምርት መጠኑን ከፍ ለማድረግ ይሰበስባሉ፡፡ በሌላ በኩል ነጋዴዎችን በሚመለከት ማበጠሪያ ማሽን ያሏቸው ሲሆን አነስተኛ የእህል ወፍጮ ያላቸው አነስተኛ ማሽን ወይንም በእጅ በማበጠር ለሸማቾች ይሸጣሉ፡፡

ምርት ከተሰበሰበ በኂላ እህሉ በጆንያ ተደርጐ በአርሶአደሩ ቤት ይቀመጣል፡፡ ምንም ዓይነት የእርጥበት ወይንም የተባይ ቁጥጥር አይደረግም፡፡ አንዳንድ አርሶአደሮች የበቆሎ ጐተራ ያሏቸው ሲሆን ጥቂት ጐተራዎች ብቻ የአይጥ መከላከያ አሏቸው፡፡ በአጠቃላይ አርሶአደሮች ስለድህረምርት አያያዝ ቴክኖሎጂ ያሏቸው ዕውቀት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ዕውቀታቸውንና ከህሎታቸውን ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

አብዛኛዎቹ የሕ/ሥራ ማህበራት ስለ መጋዘን አስተዳደር ዝቅተኛ ዕውቀት ነው ያላቸው፡፡ መጀመሪያ የገባ መጀመሪያ ይወጣል የሚባለውን የመጋዘን አሠራር ተግባራዊ የሚያደርጉ ጥቂት የሕ/ሥራ ማህበራት ናቸው፡፡ መጋዘን አየር እንዲያገኝ ማድረግ፣ ተባይ ማጥፊያ እና የማጠን ሥራዎች በጣም የተወሰኑ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሕ/ሥራ ማህበራትን የድህረምርት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የመጋዘን አስተዳደርን ጨምሮ ዕውቀትና ክህሎታቸውን ማሻሻል እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## (4) የብርዕ ሰብሎች የምርት ገበያ ሁኔታና ድህረምርት አያያዝ

### 1) በቆሎ

በኢትዮጵያ የበቆሎ ምርት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በቀጣዩ ሠንጠረዥ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ ጠቅላላ የበቆሎ ምርት መጠን 4,986,132 ቶን ይሆናል፡፡ ዋንኛው የበቆሎ አምራች አካባቢዎች ከ1500-2200 ሜትር ከባህር ወለል በላይ የሆኑ አካባቢዎች ናቸው፡፡ የኦሮሚያ ክልል ዋንኛው የበቆሎ አምራች አካባቢ ሲሆን የምርት መጠኑ 2,880,600 ቶን ሲሆን በሀገሪቱ 57.8% ይሸፍናል፡፡ የደቡብ ክልል በሀገር ደረጃ 3ኛ የበቆሎ አምራች ሲሆን የምርት መጠኑም 556,547 ቶን እና 11.2% በሀገር አቀፍ ደረጃ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የምርት መጠንና የገበያ ድርሻ በክልል፣ በዞንና በልዩ ወረዳ እንደሚከተለ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-3 የበቆሎ ምርትና የገበያ ሽያጭ መጠን በክልልና ዞን/ልዩ ወረዳ**

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | ለገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. ኦሮሚያ | 2,880,600 | 57.8% | 10.4% | 299,582 | 56.9% |
| 2. አማራ | 1,214,807 | 24.4% | 10.5% | 127,555 | 24.2% |
| 3. ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ | 556,547 | 11.2% | 12.8% | 71,238 | 13.5% |
| 4. ትግራይ | 149,853 | 3.0% | 6.5% | 9,740 | 1.9% |
| 5. ሌሎች | 184,325 | 3.7% | 9.9% | 18,248 | 3.5% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 4,986,132 | 100.0% | 10.6% | 526,364 | 100.0% |
| 10 ዋና የምርት ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች | | | | | |
| 1. ስልጤ | 96,980 | 17.4% | 5.5% | 5,334 | 7.8% |
| 2. ጋሞ ጎፋ | 77,182 | 13.9% | 13.9% | 10,728 | 15.8% |
| 3. ከፋ | 60,648 | 10.9% | 26.0% | 15,768 | 23.2% |
| 4. ጉራጌ | 56,095 | 10.1% | 7.1% | 3,983 | 5.8% |
| 5. ሲዳማ | 53,723 | 9.7% | 11.9% | 6,393 | 9.4% |
| 6.አላባ | 46,975 | 8.4% | 5.9% | 2,772 | 4.1% |
| 7. ደቡብ ኦሞ | 42,009 | 7.5% | 25.4% | 10,670 | 15.7% |
| 8. ሃዲያ | 26,801 | 4.8% | 5.9% | 1,581 | 2.3% |
| 9. ኮንሶ | 19,113 | 3.4% | 8.5% | 1,625 | 2.4% |
| 10. ቤንች ማጂ | 17,292 | 3.1% | 18.5% | 3,199 | 4.7% |
| 11. ሌሎች | 59,729 | 10.7% | 10.1% | 6,033 | 8.9% |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 556,547 | 100.0% | 12.8% | 68,086 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

ግብርና የዝናብ ውሃ ጥገኛ በመሆኑ አብዛኛው የእህል ዓይነቶች በክረምት ወቅት ይመረታሉ፡፡ የበልግ ዝናብ ባለበት አካባቢ በቆሎ በየካቲትና በመጋቢት ወራት ይዘራል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች በቆሎና ማሽላ በሚያዝያና ግንቦት ወራት ይዘራሉ፡፡ ሁለት የዝናብ ወቅት ባሉባቸው አካባቢዎች በዓመት ሁለት ጊዜ የሚዘራበት ሁኔታ አለ፡፡ ምንም እንኳን ዓመታዊ ልዩነቶች ብኖሩም ከ90-95% የእህል ምርት በመኸርና ከ5-10% በበልግ ዝናብ ወቅት ይመረታል፡፡

በደቡብ ክልል የእህል ምርት ዞን የሚባለው ማዕከላዊ እና ሰሜናዊ አካባቢ ነው፡፡ ሲዳማ፣ ጉራጌ፣ ጋሞ ጐፋ፣ ሥልጤ እና ሃዲያ ዋና ዋና የምርት አካባቢዎች ናቸው፡፡ በዋናነት በቆሎ በእነዚህ ዞኖች እስከ 75% በበልግ ወቅት ይመረታል፡፡


የበቆሎ የሽያጭ መጠኑ ዝቅ ያለ ነው፡፡ አብዛኛው ምርት እስከ 90% የሚደርሰው ለቤት ውስጥ ፍጆታ ይውላል፡፡ ገበያን በሚመለከት አርሶአደሮች ምርታቸውን በአቅራቢያ ወደ አለው ገበያና የመሰብሰቢያ ጣቢያ በአህያ፣ በፈረስ ወይም በጋሪ ያመጣሉ፡፡ አርሶአደሮች ማጠራቀሚያ ጐተራ የሌላቸው በመሆኑ ምርት ከሰበሰቡ በኂላ ብዙም ሳያቆዩ በትርፍነት ያለውን እህል ገበያ አውጥተው ይሸጣሉ፡፡ ዋነኛው የሽያጭ ማዕከል በአካባቢው ያለው ገበያ ነው፡፡ ጥሩ የመንገድ መሠረተልማት አባባቢ ያለ ከሆነ ነጋዴዎች እህሉን ከአካባቢ ገበያዎችና መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ከሰበሰቡ በኂላ ወደ አ/አበባ ማዕከላዊ ገበያና ወደ ሌሎችም የገበያ ሥፍራዎች በጭነት መኪናዎች ያጓጉዛሉ፡፡

የሽያጭ ዋጋ በተመለከተ ለ100 ኪ.ግራም በቆሎ በአርሶአደሩ ቀዬ/ማሣ ላይ ከ150-220 ብር፣ ጅምላ ዋጋ በአ/አበባ 260 ብር፣ እና የችርቻሮ ዋጋ 280 ብር ይደርሳል፡፡ ዋና ዋና የገበያ ማዕከላት ሩቅ ከሆነ በማሣ ላይ ዋጋው ይቀንሳል፡፡ ለምሳሌ በከፋ ዞን በማሣ ላይ ዋጋ 175ብር በ100 ኪ.ግራም ይሆናል፡፡ ምርት ማጓጓዝ ዋጋ በአይሱዙ የጭነት መኪና 80 ብር በ100 ኪ.ግራም ነው፡፡ የደላላ ኮሚሽን 5 ብር በ100 ኪ.ግራም ነው፡፡ ስለዚህ የጅምላ ሽያጭ ዋጋ በአ/አበባ ማዕከላዊ ገበያ 260 ብር በ100 ኪ.ግራም ይሆናል ማለት ነው፡፡


የአካባቢ የበቆሎ መሰብሰቢያ ጣቢያ


በቆሎ በገበያ ሲታይ

የበቆሎ ችርቻሮ ዋጋ ከታች ተመልክቷል፡፡ ይህ አሀዝ የሚያመለክተው የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ችርቻሮ ዋጋ መረጃ ከህዳር 2009 እስከ መስከረም 2010 (እ.ኤ.አ) በ6 ዋና ዋና (የምዕራብ አካባቢዎችን ሳያጠቃልል) ገበያዎች ያለውን ነው፡፡ ከፍተኛ ዋጋ ከህዳር እስከ የካቲት ያለው ሲሆን ከሰኔ እስከ መስከረም ያለው ዝቅተኛ ዋጋ ያሳያል፡፡ ከተማዎችን በሚመለከት ዓመታዊ አማካይ ዋጋ በአርባ ምንጭና በሀዋሣ 325 ብርና 324 ብር በ100 ኪ.ግራም እንደ ቅደም ተከተላቸው ነው፡፡ ዝቅተኛው ዓመታዊ አማካይ ዋጋ 264 ብር በ100 ኪ.ግራም የተመዘገበው በአላባ ከተማ ነው፡፡




**ምስል 3.1-2 የበቆሎ ችርቻሮ ዋጋ**

የድህረምርት በቆሎ አያያዝ በማሽን ማበጠር በተመለከተ አርሶአደሮች ጥራትን ለማሻሻል የሚያድርጉት ሥራ አነስተኛ ነው፡፡ በቆሎን በንፋስ ለማበጠር አየር ላይ መበተን በኢትዮጵያ የተለመደ አሠራር ነው፡፡ ሆኖም የእህል ጥራት ለፍሬው ደረጃ መስጠትና በማሽን ቆሻሻ መለየት ጥራትን ለማሻሻል የሚደረጉ ሥራዎች አልፎ አልፎ የሚታይ ነው፡፡ አንድአንድ ላኪዎች፣ ትላልቅ ነጋዴዎች፣ ምግብ አቀነባባሪዎችና ሕ/ሥራ ዩኒያኖች ከፍተኛ አቅም ያላቸውን ማበጠሪያዎች፣ በግራቪቲ የሚለዩ ማሽኖችን፣ የመጠን ደረጃ የሚሰጡና የሚለዩ ማሽኖችን ወዘተ.. ይጠቀማሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ሜካንካል ማሽኖችን መጠቀም በአርሶአደሮች፣ በሕ/ሥራ ማህበራት፣ በአነስተኛ ነጋዴዎችና በጅምላ ነጋዴዎች ላይ የሚያስከትሏቸው ችግሮች አሉ፡፡

2) ጤፍ

የጤፍ ምርት በገበያ መጠንና በዞን /ልዩ ወረዳ ከዚህ ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-4 የጤፍ ምርትና የገበያ ሽያጭ መጠን በክልልና ዞን/ልዩ ወረዳ**

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. ኦሮሚያ | 1,671,805 | 48.0% | 23.1% | 386,187 | 44.5% |
| 2. አማራ | 1,279,110 | 36.7% | 24.1% | 308,266 | 35.5% |
| 3. ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ | 296,760 | 8.5% | 42.0% | 124,639 | 14.4% |
| 4. ትግራይ | 209,507 | 6.0% | 19.3% | 40,435 | 4.7% |
| 5. ሌሎች | 26,306 | 0.8% | 30.4% | 7,997 | 0.9% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 3,483,488 | 100.0% | 27.7% | 867,524 | 100.0% |
| 10 ዋና የምርት ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች | | | | | |
| 1. ስልጤ | 50,642 | 17.1% | 51.2% | 25,929 | 20.8% |
| 2. ጋሞ ጎፋ | 46,475 | 15.7% | 44.7% | 20,774 | 16.7% |
| 3. ከፋ | 42,297 | 14.3% | 47.8% | 20,218 | 16.2% |
| 4. ጉራጌ | 32,706 | 11.0% | 26.8% | 8,765 | 7.0% |
| 5. ሲዳማ | 24,790 | 8.4% | 56.6% | 14,031 | 11.3% |
| 6.አላባ | 15,868 | 5.3% | 19.5% | 3,094 | 2.5% |
| 7. ደቡብ ኦሞ | 12,538 | 4.2% | 77.5% | 9,717 | 7.8% |
| 8. ሃዲያ | 12,402 | 4.2% | 53.3% | 6,610 | 5.3% |

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 9. ኮንሶ | 9,971 | 3.4% | 46.1% | 4,597 | 3.7% |
| 10. ቤንች ማጂ | 8,873 | 3.0% | 44.9% | 3,984 | 3.2% |
| 11. ሌሎች | 40,198 | 13.5% | 27.2% | 6,920 | 5.6% |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 296,760 | 100.0% | 42.0% | 124,639 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

ጤፍ በኢትዮጵያ የእህል ምርት 2ኛ ደረጃ ይይዛል። ጤፍ በኢትዮጵያ ዋንኛው የባህል ምግብ የሆነው እንጀራ የሚሠራበት እንደመሆኑ እጅግ በጣም ተፈላጊ እህል ነው። ጤፍ አብዛኛውን የሚመረተው በደጋና ቀዝቃዛ ከፍተኛ አካባቢዎች ሲሆን በዝናብ አጠር ቆላማ አካባቢዎች ተስማሚ አይደለም። ከላይኛው ሠንጠረዥ እንደተመለከተው ዓመታዊ ጠቅላላ ምርት 3,483,488 ቶን ይሆናል። ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ኦሮሚያና አማራ ክልሎች ሲሆኑ የሁለቱ ክልሎች ምርት ከሌሎች ጥቅል ምርት ይበልጣል። እስከ 85% የሀገሪቱ ምርት ይኸውም 2,950,915 ቶን የሚሆነው በእነዚህ ሁለት ክልሎች ይመረታል። 23% የሚሆኑ ምርት ይኸውም 694,453 ቶን በሀገር ውስጥ ገበያ ይሸጣል፤ በገበያ ድርሻውም 80% ይሆናል።

በደቡብ ክልል የጤፍ ምርት 4ኛ ደረጃን ይይዛል። ሃዲያ፣ ጋሞ ጐፋ፣ ጉራጌ፣ ከፋና ወላይታ ዞኖች በክልሉ ዋና ዋና የጤፍ አምራች አካባቢዎች ናቸው። ከከፋና ከዳውሮ በስተቀር በሌሎቹ በግምት እስከ 50% የሚሆነው ምርት ለገበያ ይቀርባል።


ጤፍ እንደ ሌሎቹ ሰብሎች ሁሉ የዝናብ ጥገኛ ነው። አንዳንድ አነስተኛ ልዩነቶች በክልል ደረጃ ቢኖርም ጤፍ የሚዘራው በዝናብ ወቅት አፈሩ በቂ እርጥበት ባለበት ጊዜ ነው። አብዛኛውን ጤፍ የሚዘራው በነሐሴ አጋማሽ ነው። የምርት መሰብሰቢያ ጊዜም ከህዳር እስከ ጥር ወር ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች ጥቁር ጤፍ ወይም ቡንይ በበልግ ወቅት ይዘራል።

ዋንኛ የገበያ አካባቢዎች አ/አበባ፣ ሻሸመኔ እና ሌሎች ትላልቅ ገበያዎች ናቸው። የቀዬ/ማሣ ላይ የጤፍ ዋጋ ነጭ ጤፍ ከ550-600ብር በ100 ኪ.ግራም ነው። የጅምላ ችርቻሮ ዋጋ በአ/ አበባ ገበያ በሠንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው ነው። የነጭና ጥራት ያለው ጤፍ ዋጋ ከፍ ሊል ይችላል። በደቡብ ክልል በሀዋሳ ከተማ ያለው የጤፍ ዋጋ 10 ብር በኪ.ግራም ለነጭ ጤፍ ሲሆን ለሰርገኛ ጤፍ 8 ብር በኪ.ግራም ነው።

በደቡብ ክልል የጤፍ ችርቻሮ ዋጋ ከታች ተመልክቷል። ይህ ቁጥር የሚያመለክተው የግንድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የችርቻሮ ዋጋ መረጃ ከህዳር 2009 እስከ መስከረም 2010 (እ.ኤ.አ) በ6 ዋና ዋና ገበያዎች (የምዕራብ አካባቢን ሳያጨምር) ያለውን ነው።

የነጭ ጤፍ ዋጋ ከወቅቱ ጋር መጠነኛ ልዩነት ያሣያል። ከህዳር እስከ ጥር ባሉት ወራት በሀዋሣ ከተማ ገበያ ላይ ከፍተኛ ዋጋ የሚያሣይ ሲሆን ከ1000 ብር በ100 ኪ.ግራም በላይ ይሆናል። በመሠረቱ የጤፍ ዋጋ በዚህ ወቅት ዝቅተኛ ዋጋ የሚታይበት መሆን ነበረበት። ምክንያቱም ወቅቱ እህሉ የሚመረትበትና በመጋዘን የሚከማችበት ስለሆነ ነው። ይሁን እንጂ አርሶአደሮች ምርቱን በመጋዘን ለረዥም ጊዜ የሚያስቀምጡና በተባይ ወይንም በሌሎች በሽታዎች የሚበላሽ ባለመሆኑና በእጅ እንዳለ ጥሬ ገንዘብ ስለሚቆጥሩት ነው። በሀዋሣ ከተማ ዋጋው ከየካቲት እስከ መስከረም ባለው ጊዜ ከ900 ብር እስከ 996 ብር በ100 ኪ.ግራም በመሆን ይዋዥቃል። ዓመታዊ ዋጋ 984 ብር በ100 ኪ.ግራም ሆኖ ቀጥሎ በአ/ምንጭና በወላይታ ሶዶ ከተማዎች በአማካይ 894 እና 867 ብር በ100 ኪ.ግራም እንደ ቅደም ተከተላቸው ይሆናል። የጤፍ ዋጋ በአላባና በቡታጅራ ከተማዎች ዝቅ ይላሉ።

ይህም የሚሆንበት አላባ ዝቅተኛ የሕዝብ ብዛት ያለው ሲሆን ቡታጅራ የጤፍ አምራች አካባቢ በመሆኑ ነው፡፡




**ምስል 3.1-3 የጤፍ ችርቻሮ ዋጋ**

የድህረምርት የጤፍ አያያዝ በተመለከተ ጥቂት አርሶአደሮች በአካባቢ የሚመረተውን የጤፍ መወቂያ መጠቀም በመጀመር ላይ ናቸው፡፡ ነገር ግን አብዛኛው የጤፍ ውቂያ በሰው ጉልበት የሚከናወን ነው፡፡ ከታጨደ በኋላ በፀሐይ እንዲደርቅ ተደርጐ በእርሻ ቦታ ተቆልሎ ይቆያል፡፡ ከዚያ በኋላ ከ6 እስከ 10 በሬ በመጠቀም በማሣ ላይ አውድማ ተዘጋጅቶ ይወቃል፡፡


በበሬ የሚከሄድ ውቂያ


ከውቂያ በፊት በፀሐይ ማድረቅ

የጤፍ የጥራት ደረጃ በሚመለከት የኢትዮጵያ ደረጃ (በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት) ነው ያለው፡፡ የገበያ ልውውጥ በሚመለከት በአሁኑ ጊዜ ደረጃ ተግባራዊ አልሆነም፡፡ ነጋዴዎች ጤፉ ጥራት ያለውና ንፁህ መሆን አለመሆን በዓይን እይታ ነው የሚወሰነው፡፡

### ሠንጠረዥ 3.1-5 የኢትዮጵያ የጤፍና በቆሎ ምርት ደረጃ

| ብርዕ ሰብል ዓይነት | የሚፈተሽ ነገር | ያልተጣራ ድብልቅ/በተባይ የተወጋ (%) | | | | መፈተሽ ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | |
| | ባዕድ ነገር | 1.5 | 2.5 | 3.5 | 5.0 | ES ISO 5223 |
| | ድንጋይ | 0.6 | 0.6 | 0.6 | 0.6 | ES ISO 5223 |
| ጤፍ (ነጭ) | ባዕድ ነገር | 1.5 | 2.5 | 3.5 | 5.0 | ES ISO 5223 |
| | ድንጋይ | 0.6 | 0.6 | 0.6 | 0.6 | ES ISO 5223 |
| ጤፍ (ሠርገኛ) | ባዕድ ነገር | 1.5 | 2.5 | 3.5 | 5.0 | ES ISO 5223 |
| | ድንጋይ | 0.6 | 0.6 | 0.6 | 0.6 | ES ISO 5223 |
| ጤፍ (ድብልቅ) | ባዕድ ነገር | 1.5 | 2.5 | 3.5 | 5.0 | ES ISO 5223 |
| | ድንጋይ | 0.6 | 0.6 | 0.6 | 0.6 | ES ISO 5223 |
| በቆሎ | የተሰባባረ ፍሬ | 2.0 | 3.0 | 4.0 | 5.0 | ES ISO 5223 |
| | ባዕድ ነገር | 0.5 | 1.0 | 1.5 | 2.0 | ES ISO 5223 |
| | በተባይ የተጠቃ | 3.0 | 5.0 | 7.0 | 10.0 | |
| | በሽታ | 0.5 | 1.5 | 2.0 | 3.0 | |
| | ያልበሰለ | 1.0 | 2.0 | 4.0 | 6.0 | |

ምንጭ: (1) የኢትዩጵያ ደረጃ (ጤፍ)፣ ES671:2001 (እ.ኤ.አ). (2) የኢትዩጵያ ደረጃ (በቆሎ)፣ ES671:2001 (እ.ኤ.አ).

አነስተኛ አርሶአደሮች የእህል መጋዘን ስለማይኖራቸው ትርፍ የጤፍ ምርታቸውን ከውቂያ በኂላ ወዲያውኑ ይሸጡታል፡፡ ሽያጩ የሚከናወነው በአቅራቢያው ባለው ገበያ ወይም ለአነስተኛ ነጋዴዎች ነው፡፡ በከረጢት የሞሉትን ብዙ ጊዜ 100 ኪ.ግራም የሚሆነው ወደ ገበያ ወይም በአካባቢው ወዳለው ዋና መንገድ በአህያ ጀርባ፣ በፈረስ ወይንም በአህያ ጋሪ ያጓጉዙታል፡፡

በደቡብ ክልል ነጋዴዎች ጤፍ ከማሣ ላይ እንዲሁም ከገበያ ሥፍራዎች ሰብስበው ወደ አ/አበባ፣ ሻሸመኔና ሌሎች ትላልቅ ገበያዎችና በአካባቢው ወዳሉ ገበያ ሥፍራዎች ያጓጉዛሉ፡፡

### 3) ስንዴ

ስንዴ በኢትዮጵያ የእህል ምርት 4ኛ ደረጃን ይይዛል፡፡ ስንዴ በጣም ተፈላጊ ከሆኑ ምርቶች አንዱ ቢሆንም የሚመረተው ምርት በቂ ካለመሆኑ የተነሣ የሀገሪቱን ፍላጐት አያሟላም፡፡ የምርት ጉድለቱ ከውጭ ይገባል፡፡ ስንዴ በደጋማ አካባቢዎች ይመረታል፡፡ ስንዴ ብዙ ዓይነት ዝርያዎች (ለሰላሣ፣ ጠንካራና ዱረም) የሚባሉ አሉ፡፡ ዱረም ስንዴ ማካሮኒና ፓስታ ለማምረት ያገለግላል፡፡ የዱረም ስንዴ ምርት የሽያጭ ዋጋ ከማምረቻ ጋር ሲወዳደር ዝቅ ያለ ስለሆነ የምርት መጠኑም ዝቅተኛ ነው፡፡

### ሠንጠረዥ 3.1-6 የስንዴ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. ኦሮሚያ | 1,583,213 | 55.4% | 19.6% | 310,310 | 58.4% |
| 2. አማራ | 824,862 | 28.9% | 10.4% | 85,786 | 16.2% |
| 3. ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | 244,603 | 8.6% | 33.9% | 82,920 | 15.6% |
| 4. ትግራይ | 192,508 | 6.7% | 21.5% | 41,389 | 7.8% |
| 5. ሌሎች | 10,500 | 0.4% | 25.7% | 10,753 | 2.0% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 2,855,686 | 100.0% | 18.6% | 531,158 | 100.0% |
| 10 ዋና የምርት ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች | | | | | |
| 1. ሃዲያ | 66,212 | 27.1% | 42.9% | 28,405 | 37.9% |
| 2. ስልጤ | 44,140 | 18.0% | 42.4% | 18,715 | 24.9% |
| 3. ጉራጌ | 28,249 | 11.5% | 27.3% | 7,712 | 10.3% |

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 4. ከምባታ ጠምባሮ | 22,157 | 9.1% | 23.8% | 5,273 | 7.0% |
| 5. አላባ | 8,131 | 3.3% | 51.2% | 4,163 | 5.5% |
| 6. ደቡብ ኦሞ | 7,944 | 3.2% | 21.9% | 1,740 | 2.3% |
| 7. የም | 6,488 | 2.7% | 16.0% | 1,038 | 1.4% |
| 8. ሲዳማ | 4,343 | 1.8% | 29.2% | 1,268 | 1.7% |
| 9. ዳውሮ | 3,682 | 1.5% | 17.2% | 633 | 0.8% |
| 10. ቤንች ማጂ | 1,941 | 0.8% | 14.9% | 289 | 0.4% |
| 11. ሌሎች | 51,316 | 21.0% | 11.3% | 5,799 | 7.7% |
| የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 244,603 | 100.0% | 30.7% | 75,036 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጄንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)


ምርትና የገበያ ድርሻ በክልል እንዲሁም በዞንና ልዩ ወረዳ ከላይ በሠንጠረዥ ተገልጿል። ጠቅላላ በሀገሪቱ ዓመታዊ ምርት 2,855,686 ቶን የሚደርስ ሲሆን ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ኦሮሚያና አማራ ክልሎች ናቸው። በእነዚህ ሁለት ክልሎች የሚመረተው ምርት ድርሻ 84.3% ሲሆን የገበያ ድርሻውም 74.6% ይደርሳል። የኦሮሚያ ክልል የምርትና ገበያ ድርሻ 55.4% እና 58.4% እንደቅደም ተከተላቸው ይሆናል።

ደቡብ ክልል በስንዴ ምርት 3ኛ ትልቁ አምራች አካባቢ ነው። ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ሃዲያ፣ ስልጤ፣ ጉራጌ እና ካምባታ ጣምባሮ ዞኖች ናቸው። በሽያጭ ደረጃ ሃዲያና ስልጤ ዞኖችና አላባ ልዩ ወረዳ 40% ድርሻ አላቸው። የሌሎች ዞኖች ከ30% በታች ነው። ይህ ማለት ምርቱ በአብዛኛው ለቤት ፍጆታ ይውላል ማለት ነው። ገበያን በተመለከተ አርሶአደሮች ምርታቸውን በአህያ ጀርባ፣ በፈረስ ጀርባና በአህያ ጋሪ ወደ አቅራቢያ ገበያ ወይም መሰብሰቢያ ማዕከል ያመጣሉ። ዋንኛው የሽያጭ ሥፍራዎች የአካባቢ ገበያዎች ናቸው።

የስንዴ ሽያጭ ዋጋ በ100 ኪ.ግራም በቀዬ/ማሣ ላይ 250 ብር፣ ጅምላ ሽያጭ በአ/አበባ 420 ብር፣ ችርቻሮ ዋጋ 440 ብር ነው። በደቡብ ክልል ለስላሳ ስንዴ በአሁኑ ሰዓት ችርቻሮ ዋጋ በሀዋሣ ገበያ 6 ብር በ1ኪ.ግራም ይሆናል።

የስንዴ ችርቻሮ ዋጋ ከታች ተመልክቷል። ይህ አሀዝ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የችርቻሮ ዋጋ መረጃ በህዳር 2009 እስከ መስከረም 2010 (እ.ኤ.አ) ያለው የ6 ዋና ዋና ገበያ ማዕከላት (ከምዕራብ አካባቢዎች በስተቀር) ዋጋ ያሣያል።

ይህ አሃዝ የሚያሣየው የ1ኛ ደረጃ ነጭ ስንዴ በኢትዮጵያ ደረጃ ምደባ ማለት ነው። በአሀዙ እንደተመለከተው የችርቻሮ ዋጋ በአ/ምንጭ እና በሀዋሣ ያለው ከሌሎች ከተሞች ከፍ ያለ ነው። ይኸውም ከ600 ብር ከ100 ኪ.ግራም በላይ ነው። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት እነዚህ አካባቢዎች ከዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ርቀው የሚገኙ በመሆኑ ነው። በሌላ በኩል ሌሎች አካባቢዎች አማካይ ዋጋ ዝቅ ያለ ነው። ይኸውም ከ500 ብር ከ100 ኪ.ግራም በታች ነው። አነስተኛው በቡታጅራ ከተማ ሲሆን ዋጋውም 378 ብር በ100 ኪ.ግራም ነው። እነዚህ የገበያ ማዕከላት በአብዛኛው በስንዴ አምራች አካባቢ ያሉ ናቸው። ወቅታዊ አማካይ የሽያጭ ዋጋ ከፍተኛ የሚሆነው በህዳር ወር ይኸውም ከቀጣይ ምርት ከመሰብሰቡ በፊት ነው።




ምስል 3.1-4   የስንዴ ችርቻሮ ዋጋ አኳኋን

ስንዴ ከተዘራ በኋላ ያለው ሂደት ከጤፍ ጋር ተመሣሣይነት አለው። ገበሬዎች ግን ልክ እንደ ስንዴ መውቂያ፣ መሰብሰቢያ፣ ማድረቂያና በደረጃ መለያ ያሉ ማሽኖች የሏቸውም። ስለዚህ ሁሉም ሥራ የሚሠራው በእጅ ወይም በጉልበት ነው።

በደቡብ ክልል ነጋዴዎች የስንዴን ምርት ከገበያና ከአመምራቹ ይሰበስቡና ወደ አ/አበባ፣ ሻሸመኔ፣ አርባምንጭ እና ወደ ሌሎች ትላልቅ የገበያ ስፍራዎች ያስተላልፋሉ።

### 3.1.2 ጥራጥሬ

#### (1) በኢትዮጵያ የጥራጥሬ ምርት

በኢትዮጵያ ለቤት ውስጥ ምግብነት ከሚጠቀሙት የምግብ ሰብሎች መካከል ሁለተኛ ቅልቁ ቢሆንም የዚህ የሰብል ምርት በኢትዮጵያ ውስጥ ይኼ ነው የሚባል አይደለም፤ በዓመት 1,953,200 ቶን ያህል ይመረታል። ብዙ አይነት የጥራጥሬ ምርት በሀገር ውስጥ ይመረታል። ከሚመረቱትም ዋነኛ የሚባሉት ጥራጥሬ ዝሪያዎች በሎቄ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ሽምብራ፣ እና ምስር የመሣሠሉት ናቸው። ሌሎች በሀገር ውስጥ የሚገኙ የሰብል አይነቶች እንደ ጓያና ጊብጦ የመሣሠሉት አንደ ባህላዊ የምግብ አይነት ይመረታሉ። እነዚህ ምርቶች ግን በትንሽ ዋጋ ስለሚሸጡ በተወሰኑ ወይም ጥቂት ቦታዎች ተመርተው ለሀገር ውስጥ ገበያ ይሸጣሉ።

ሠንጠረዥ 3.1-7   በኢትዮጵያ የጥራራጥሬ ምርትና የገበያ ድርሻ

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ ዋጋ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. ኦሮሚያ | 847,725 | 43.4 | 24.96 | 211,592 | 48.4 |
| 2. አማራ | 763,322 | 39.1 | 21.50 | 164,114 | 37.5 |
| 3. ደቡብ ሕዝ | 272,418 | 13.9 | 17.56 | 47,837 | 10.9 |
| 4. ትግራይ | 51,532 | 2.6 | 19.79 | 10,198 | 2.3 |
| 5. ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 16,200 | 0.8 | 20.31 | 3,290 | 0.8 |
| 6. ሶማሌ | 859 | 0.0 | 40.29 | 346 | 0.1 |
| 7. ሌሎች | 1,144 | 0.1 | 6.83 | 78 | 0.0 |
| የኢትዮጵያ ድምር | 1,953,200 | 100.0 | 21.03 | 437,456 | 100.0 |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

በኢትዮጵያ ውስጥ ጥራጥሬ ምርቶች የሚበቅሉት በብዙ ቦታዎች ሲሆን ለሀገሪቱ እንደዋነኛ የሰብል ምርት የሚያበረክቱ ክፍሎች እንደ መሀከለኛውና ምስራቅ ኦሮሚያ እና የአማራ

ክልሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ቦታዎች በአጠቃላይ የሀገሪቱን 84% የጥራጥሬ ምርትንና 86% የገበያውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡ የደቡብ ክልል በአንፃሩ በዚህ የሰብል ምርት 3ኛውን ደረጃ የያዘ ሲሆን የሚያመርተውም 272,418 ቶን ሲሆን የገበያ ድርሻ 47,837 ቶን ይሸፍናል፡፡

### (2) በደቡብ ክልል የጥራጥሬ ምርት

በዚህ ክልል ይህን ሰብል በማምረት በዋንኛነት የሚጠቀሱት ዞኖች የምዕራብና የሰሜኑ ክፍሎች ሲሆኑ ከእነዚህም እንደ ከፋ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ጉራጌ እና ሃዲያ ዞኖች ነቸው፡፡ በደቡብ ክልል ውስጥ የጥራጥሬ ምርት የሚሸፍነው የገበያ ድርሻ ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡ በሠንጠረዡ እንደምናየው በክልሉ ውስጥ 3 የተለያዩ የቦሎቄ ዓይነቶች፣ ባቄላ፣ አተር፣ ሽምብራ፣ ምስርና አኩሪ አተር ይበቅላሉ፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-8 በደ/ብብ/ሕ/ክ/ የጥራጥሬ ምርትና የገበያ ድርሻ**

| ተ.ቁ | አይነቶች | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ ዋጋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1 | ቦሎቄ | 106,279 | 39.0 | 13.88 | 14.782 | 30.9 |
| 2 | ባቄላ | 104,256 | 38.3 | 18.22 | 18.995 | 39.8 |
| 3 | አተር | 54,134 | 19.9 | 22.59 | 12.229 | 25.6 |
| 4 | ሽምብራ | 7,081 | 2.6 | 22.94 | 1,624 | 3.4 |
| 5 | ምስር | 364 | 0.1 | 22.64 | 82 | 0.2 |
| 6 | አኩሪ አተር | 304 | 0.1 | 6.33 | 19 | 0.0 |
| በደቡብ ክልል ጠቅላላ | | 272,418 | 100.0 | 17.56 | 47,702 | 100.0 |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

### (3) የግብይት ዘዴ

የጥራጥሬ ግብይት ዘዴ በዱቄት መልክ ከሚሸጠው በስተቀር ከሌሎች እህል ሰብሎች ጋር ተመሣሣይ ነው፡፡ ጥራጥሬ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የገበያ መስመሮች አሉት፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ነጩ ቦሎቄ ልክ እንደ ቡና ከ2010 (እ.ኤአ.) ጀምሮ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ አማካይነት በጨረታ እንዲሸጥ ተደርጓል፡፡ ነጋዴዎች የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደረጃን ለመጠበቅ ሲሉ የነጭ ቦሎቄን በራሳቸው ትልቅ ማበጠሪያ ካልሆነም ብዙ ሠራተኞችን በመቅጠር በጉልበት በማበጠር በገበያ ማእከሉ ለጨረታ ያቀርባሉ፡፡ የደቡብ ክልል የነጩ ቦሎቄ ምርት አነስተኛ ቢሆንም በክልሉ በብዛት የሚመረተው የቀይ ቦሎቄ ግን በአብዛኛው ወደ ጎረቤት ሀገሮች እንደ ኬኒያ ላሉ ኤክስፖርት ይደረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ቢዝነሱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በጨረታ የሚካሄድ አይደለም፡፡ በስምምነት ውስጥ የተጠቀሰውን ጥራት ለማሟላት ሲሉ ኤክስፖርት የሚያደርጉ ድርጅቶች ትልቅ ማበጠሪያ መሣሪያ መጠቀም አለባቸው፡፡ የዓለም የምግብ ኘሮግራም እነዚህን ጥራጥሬዎች በቀጥታ የሚያገኘው ግዥ የዕድገት በኩል ከሕ/ሥራ ዩኒየኖች ነው፡፡

በጥራጥሬ ግብይት ውስጥ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ሀሳቦች ሁሉ ልክ እንደ ሌሎች እህሎች አንድ አይነት ነው፡፡ የጥራት ደረጃውም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ከዓለም ምግብ ኘሮግራም በስተቀር ለሀገር ውስጥ ግብይት አልተለመደም፡፡ የጥራት ደረጃው የሚረጋገጠው በማየት እና በዳበሣ ነው፡፡ ለሸማቾች ሆነ ለባህር ማዶ ገበያ ከመሸጡ በፊት ነጋዴዎች በጥራጥሬ ውስጥ ያለውን ያልተጣሩ ነገሮችን ትልቅ የማበጠሪያ መሣሪያ በመጠቀም ወይም ብዙ ሠራተኞችን በመቅጠር ያስወግዳሉ፡፡

አርሶአደሮች ትርፍ የጥራጥሬ ምርት ለመንደር ሰብሳቢዎች ወይም ነጋዴዎች የሚሸጡበት የገበያ ሥፍራ ከዝናብና ከፀሐይ ሐሩር የሚከላከል ግንባታ የላቸውም፡፡ ነጋዴዎች የሚጠቀሙባቸው የእህል ሚዛኖች በአብዛኛው ትክክለኛ አይደሉም፡፡ ከዚህ ሌላ ነጋዴዎች

ከአርሶአደሮች የሚገዙበት ዋጋ ዝቅተኛ ነው። አምራች አካባቢ ገበያ ማሻሻያ ኘሮጀክት በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት በአርሶአደሮች፣ ነጋዴዎትና በመንግሥት አካላት በጣም የተደገፈ ኘሮጀክት ነው። ስለዚህ በተወሰኑ የገበያ ምርቶች ላይ የተሻሻለ ገበያ አሠራር በገበያ ብቃትና ፍትሃዊ በመሆን ለገበያ ልውውጥ ሥርዓት በጐ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የዋጋ ማስታወቂያ በቦርድ በመለጠፍ በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት የተደረገው የገበያ ማሻሻል ኘሮግራም በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 ተደግፎ ሲቀርብ ከአካባቢው የአስተዳደር ባለሥልጣናትና ከአርሶአደሮች ከፍተኛ ተቀባይነትን አስገኝቷል።

የቦሎቄ ዱቄት መፍጫ በምዕራፍ 3.2 የብርዕ ሰብልና የጥራጥሬ ንዑስ ክፍል የተገለጸ ቢሆንም መሠረታዊው ነገር የቦሎቄ ዱቄት የሚፈጨው በእያንዳንዱ ቀበሌ በአነስተኛ ወፍጮ ቤቶች እንጂ ለንግድ ዓላማ በከፍተኛ ደረጃ በትላልቅ የእህል ወፍጮች አይፈጭም። የቤት እመቤቶች አነስተኛ መጠን ያለውን የቦሎቄ ዱቄት በእህል ወፍጮዎች ያስፈጫሉ፤ ይህም የቤት ውስጥ ፍጆታ አነስተኛ በመሆኑ ነው።

### (4) የአብዛኞቹ ጥራጥሬ እህል ምርት ግብይትና ድህረ-ምርት አያያዝ

#### 1) ባቄላ

በደቡብ ክልል ባቄላ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልል በዞንና በልዩ ወረዳ ከዚህ በታች ተመልክቷል። ባቄላ በአሀገሪቱ ዋንኛ ከሚባሉት የግብርና ምርቶች አንዱ ቢሆንም ምርቱ በቂ አይደለም። ዓመታዊ ምርትም 697,801 ቶን ብቻ ነው። ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች አማራና ኦሮሚያ ክልሎች ሲሆን የምርትና የገበያ ድርሻቸውም 82.4% እና 81.5% እንደ ቅደም ተከተላቸው ነው።

በደቡብ ክልል ዓመታዊ ምርቱ 104,056 ቶን ሲሆን ይህም ከሀገር አቀፍ 3ኛ ደረጃ እንዲኖረው ያደርገዋል። የምርት መጠኑ በ2011/12 ከ2008/09 (እ.ኤ.አ) ጋር ሲነፃፀር 1.5 ጊዜ የምርት ጭማሪ አሳይቷል። ዋንኛው የምርት አካባቢ ከፋ ዞን ሲሆን ዓመታዊ ምርቱ 21,151 ቶን ነው። ይኸውም በክልል ደረጃ 20.3% ድርሻ ይኖረዋል። የገበያ ድርሻ ስንመለከት ከፋ 4,484 ቶን ያለው ሲሆን የክልሉን 24.7% ድርሻ ይኖረዋል።

ሠንጠረዥ 3.1-9 የባቄላ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ


| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ton | % |
| 1. ኦሮሚያ | 324,478 | 46.5% | 16.6% | 53,863 | 44.6% |
| 2. አማራ | 250,284 | 35.9% | 17.8% | 44,551 | 36.9% |
| 3. ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ | 104,056 | 14.9% | 18.2% | 18,938 | 15.7% |
| 4. ትግራይ | 17,563 | 2.5% | 18.4% | 3,232 | 2.7% |
| 5. ሌሎች | 1,420 | 0.2% | 18.2% | 258 | 0.2% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 697,801 | 100.0% | 17.3% | 120,842 | 100.0% |
| 10 ዋና የምርት ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች | | | | | |
| 1. ከፋ | 21,151 | 20.3% | 21.2% | 4,484 | 24.7% |
| 2. ሃዲያ | 13,134 | 12.6% | 23.3% | 3,060 | 16.9% |
| 3. ጉራጌ | 10,948 | 10.5% | 6.7% | 734 | 4.0% |
| 4. ሲዳማ | 9,383 | 9.0% | 23.2% | 2,177 | 12.0% |
| 5. ዳውሮ | 7,627 | 7.3% | 19.2% | 1,464 | 8.1% |
| 6. ከምባታ ጠምባሮ | 7,065 | 6.8% | 12.9% | 911 | 5.0% |
| 7ቤንች ማጂ | 6,428 | 6.2% | 32.5% | 2,089 | 11.5% |
| 8. ስልጤ | 5,902 | 5.7% | 8.4% | 496 | 2.7% |

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ton | % |
| 9. ደቡብ ኦሞ | 5,237 | 5.0% | 8.5% | 445 | 2.5% |
| 10. ጋሞ ጎፋ | 4,358 | 4.2% | 15.0% | 654 | 3.6% |
| 11. ሌሎች | 12,823 | 12.3% | 12.7% | 1,629 | 9.0% |
| የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ ድምር | 104,056 | 100.0% | 18.2% | 18,143 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

የባቄላ የሽያጭ ዋጋ በተመለከተ በ100 ኪ.ግራም በቀዬ/ማሣ ላይ 450-500 ብር ሲሆን ጅምላ ሽያጭ በአ/አበባ ላይ 600 ብር ሲሆን ችርቻሮ ዋጋ 620 ብር ነው። በደቡብ ክልል በሀዋሣ ገበያ በአሁኑ ጊዜ 6 ብር በ1ኪ.ግራም ይሸጣል። የጥራት ደረጃ ሲታይ የፍሬ መጠኑ ወጥ አይደለም፣ የተለያዩ ቀለማት ያሉትና የተቀላቀለ ነው።

የባቄላና የአተር የችርቻሮ ዋጋ ከዚህ በታች ተመልክቷል። ይህ አሀዝ የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የችርቻሮ ዋጋ መረጃ ከህዳር 2009 እስከ ሰኔ 2010 (እ.ኤ.አ) ያለው የ6 ዋና ዋና የገበያ ማዕከላት የሚያሣይ ነው። የባቄላ ችርቻሮ ዋጋ በተለያዩ ከተሞች ሲታይ በጣም ሰፊ ልዩነት አለው። ከ400-700 ብር በ100 ኪ.ግራም ይደርሳል። በሌላ አንፃር የአተር ምርት በተለያዩ ከተሞች መካከል በችርቻሮ አማካኝ ዋጋ አነስተኛ ልዩነት ነው ያለው። ከ520-700ብር በ100 ኪ.ግራም ይሆናል።




**ምስል 3.1-5 የባቄላና አተር አማካይ የችርቻሮ ዋጋ**

የባቄላ ድህረምርት አያያዝ ከሌሎች ከዚህ በፊት ከተገለጹት እህሎች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ውቂያውና የቆሻሻ ማበጠር ሥራ በሰው ጉልበት ይከናወናል።

**2) ቦሎቄ**

በደቡብ ክልል የቦሎቄ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልል በዞንና በልዩ ወረዳ ከዚህ በታች ተመልክቷል። ቦሎቄ በሀገሪቱ ዋንኛ ከሚባሉት የግብርና ምርቶች አንዱ ቢሆንም ምርቱ በቂ አይደለም። ዓመታዊ ምርት 340,282 ቶን ነው። ዋንኛው የምርት አካባቢ ኦሮሚያ ክልል ሲሆን 50% የምርትና 50% የገበያ ድርሻ ይሸፍናል። በደቡብ ክልል ሁለተኛው ዋና አምራች ሲሆን 106,279 ቶን ዓመታዊ ምርት አለው። በክልሉ ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ሲዳማ፣ ወላይታ እና ጋሞ ጎፋ ዞኖች ናቸው። የእነዚህ 3 ዞኖች ምርት 76,652 ቶን ሲሆን በክልሉ 71% ድርሻ ይኖራል። ቦሎቄ በክልሉ በብዙ አካባቢዎች ይመረታል። ሆኖም በሌሎች ዞኖች የሚመረተው ከ600 ቶን የማይበልጥ ነው። ይህ የሚያሣየው የሚመረተው ምርት ከቤት ፍጆታ አይበልጥም ማለት ነው።

ቦሎቄ ብዙ ዓይነት የፍሬ መጠንና ቀለም አለው፡፡ ዋና ታዋቂ የሆነው ቀይ ቦሎቄ ሲሆን ወደ ኬኒያና ሌሎችም ሀገሮች ይላካል፡፡ ነጭ ቦሎቄ በሕግ በተደነገገው መሠረት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አማካይነት ብቻ ንግድ ልውውጥ የሚደረግ ሲሆን ለውጭ ሀገር ገበያ ብቻ የሚቀርብ ነው፡፡

የቦሎቄ የሽያጭ ዋጋ በተመለከተ በ100 ኪ.ግራም በቀዬ/ማሣ ላይ 500 ብር፣ ጅምላ ሽያጭ በአ/አበባ 600 ብር እና ችርቻሮ 650 ብር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በደቡብ ክልል በሀዋሣ ገበያ 7.50 ብር በ1 ኪ.ግራም ይሸጣል፡፡

የቦሎቄ ድህረምርት አያያዝ ከሌሎች ሰብሎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ውቂያና ቆሻሻ ማበጠር በሰው ጉልበት ይከናወናል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-10 የቦሎቄ ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ**

| ክልል | ምርት | | ሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. ኦሮሚያ | 169,645 | 49.9% | 18.3% | 31,045 | 49.3% |
| 2. አማራ | 106,279 | 31.2% | 13.9% | 14,773 | 23.5% |
| 3. ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ | 51,056 | 15.0% | 29.8% | 15,215 | 24.2% |
| 4. ትግራይ | 8,903 | 2.6% | 13.4% | 1,193 | 1.9% |
| 5. ሌሎች | 4,399 | 1.3% | 15.9% | 699 | 1.1% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 340,282 | 100.0% | 19.7% | 62,925 | 100.0% |
| 10 ዋና የምርት ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች | | | | | |
| 1. ሲዳማ | 34,292 | 32.3% | 15.1% | 5,178 | 37.2% |
| 2. ወላይታ | 30,360 | 28.6% | 11.1% | 3,370 | 24.2% |
| 3. ጋሞ ጎፋ | 12,000 | 11.3% | 11.0% | 1,320 | 9.5% |
| 4.ከፋ | 5,044 | 4.7% | 11.2% | 565 | 4.1% |
| 5. ቤንች ማጂ | 3,466 | 3.3% | 11.1% | 385 | 2.8% |
| 6. ሃዲያ | 2,933 | 2.8% | 11.1% | 326 | 2.3% |
| 7. ኮንሶ | 2,682 | 2.5% | 4.4% | 118 | 0.8% |
| 8. ቡርጂ | 2,438 | 2.3% | 8.4% | 205 | 1.5% |
| 9. አላባ | 2,380 | 2.2% | 16.3% | 388 | 2.8% |
| 10. ዳውሮ | 2,067 | 1.9% | 15.0% | 310 | 2.2% |
| 11. ሌሎች | 8,617 | 8.1% | 20.5% | 1,766 | 12.7% |
| የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ ድምር | 106,279 | 100.0% | 13.9% | 13,931 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

### 3) አተር

በደቡብ ክልል የአተር ምርትና የገበያ ድርሻ በክልል በዞንና በልዩ ወረዳ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ አተር በሀገሪቱ ዋኝኛ ከሚባሉት የግብርና ምርቶች አንዱ ቢሆንም ምርቱ በቂ አይደለም፡፡ ዓመታዊ ምርት 257,032 ቶን ብቻ ነው፡፡ ዋና ዋና ምርቶች አካባቢዎች አማራና ኦሮሚያ ክልሎች ሲሆን የምርት የገበያ ድርሻቸውም 77% እና 75% እንደ ቅደም ተከተላቸው ነው፡፡ በደቡብ ክልል ዓመታዊ ምርቱ 54,012 ቶን ሲሆን ይህም በሀገር አቀፍ 3ኛ ደረጃ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡

በደቡብ አካባቢ ዋነኛው የምርት አካባቢ ከፋ ዞን ሲሆን በሌሎችም ዞኖች በስፋት ይመረታል፡፡ የከፋ ዞን የገበያ ድርሻ 3,546 ቶን ሲሆን በሌሎች አካባቢዎች ከ2000 ቶን

በታች ነው፡፡ የሽያጭ ዋጋ በ100 ኪ.ግራም በቀዬ/ማሣ ላይ 500 ብር ሲሆን ጅምላ ሽያጭ በአ/አበባ 550 ብር እና ችርቻሮ ዋጋ 570 ብር ነው፡፡ በደቡብ ክልል በሀዋሣ የወቅቱ ገበያ ሽያጭ ዋጋ 7ብር በ1ኪሎ ግራም ነው፡፡ የድህረምርት አያያዝ በተመለከተ ከሌሎች ከዚህ በፊት ከተገለፁት እህሎች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ውቂያና ቆሻሻ ማበጠር ሥራ በሰው ጉልበት ሲሆን በሜካኒካል ዘዴ መጠቀም በጣም ውስን ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-11 የአተር ምርትና የገበያ ድርሻ በክልልና በዞን/ልዩ ወረዳ**

| ክልል | ምርት | | ሽያች | ለገበያ የቀረበ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 1. ኦሮሚያ | 106,648 | 41.5% | 20.2% | 21,543 | 40.6% |
| 2. አማራ | 91,326 | 35.5% | 20.2% | 18,448 | 34.7% |
| 3. ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ | 54,012 | 21.0% | 22.6% | 12,207 | 23.0% |
| 4. ትግራይ | 4,331 | 1.7% | 17.6% | 762 | 1.4% |
| 5. ሌሎች | 715 | 0.3% | 22.6% | 162 | 0.3% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 257,032 | 100.0% | 20.4% | 53,121 | 100.0% |
| 10 ዋና የምርት ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች | | | | | |
| 1. ከፋ | 14,533 | 26.9% | 24.4% | 3,546 | 26.6% |
| 2. ዳውሮ | 6,750 | 12.5% | 27.6% | 1,863 | 14.0% |
| 3. ሃዲያ | 3,723 | 6.9% | 32.4% | 1,206 | 9.0% |
| 4. ስልጤ | 3,530 | 6.5% | 11.2% | 395 | 3.0% |
| 5. ደቡብ ኦሞ | 2,960 | 5.5% | 54.1% | 1,601 | 12.0% |
| 6. ሸካ | 2,823 | 5.2% | 24.2% | 683 | 5.1% |
| 7. ቤንች ማጂ | 2,220 | 4.1% | 34.1% | 757 | 5.7% |
| 8. ወላይታ | 1,629 | 3.0% | 10.1% | 165 | 1.2% |
| 9. የም | 1,464 | 2.7% | 15.0% | 220 | 1.6% |
| 10. ከምባታ ጠምባሮ | 1,090 | 2.0% | 16.3% | 178 | 1.3% |
| 11. ሌሎች | 13,290 | 24.6% | 20.5% | 2,724 | 20.4% |
| የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ ድምር | 54,012 | 100.0% | 22.6% | 13,338 | 100.0% |

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የምርት ትንበያ ናሙና ዳሰሳ 2011/12 (እ.ኤ.አ), (ቡለቲን 532)

### 3.1.3 አትክልት[1]

**(1) የምርትና ፍጆታ አጠቃላይ ሁኔታ**

የአትክልት ፍጆታ በተለይም የተለያዩ ዓይነቶችን ስናይ ከኢትዮያ የምግብ ባሕል አንፃር በጣም ውስን ነው፡፡ ከምግብ ባህል ጋር የማይነጣጠሉ በርበሬ፣ ቃሪያና ሽንኩርት ሲሆኑ እነዚህም እንደ ምግብ ማባያ ያገለግላሉ፤ በመቀጠልም በጣም ታዋቂ የሆኑት አበሻ ጐመንና ቲማቲም ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥቅል ጐመን፣ ካሮት፣ ሽንኩርት፣ ፎሶሊያ፣ ቀይስር እና ዱባ በተለያዩ መጠን ለምግብነት ይውላሉ፡፡ በአ/አበባ በርከት ያሉ የአትክልት ዓይነቶች እንደ የቻይና ጐመን፣ የፈረንጅ ዱባ፣ ፎሶሊያ፣ ወዘተ.. ያሉ ገበያ ላይ አሉ፡፡

ከምግብ እህል ምርት ጋር ሲነፃፀር የአትክልት ምርት በጣም ውስን ነው፡፡ የእርሻ ማሣ በተመለከተ አትክልት የሚመረትበት መሬት በጣም ትንሽ ሲሆን በሀገር ደረጃ ከ1% በታች

1 በርበሬ (ደረቅ ዱቄት ሆኖ ያገለግላል) በዚህ ጥናት የሥራ አድማስ እንደተመለከተው እንደ አትክልት ይመደባል በመሆኑም በኢህ ሪፖርት በአትክልት ክፍል ተመድበዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ እንደ ቅመም ይመደባል፡፡ እርጥብ ዝንጅብል እና የሥራሥር እህሎች እንደ ድቡልቡልና ስኳር ድንች ያሉት በኢትዮጵያ እንደ አትክልት አይመደቡም ካሮት፣ ሽንኩርት እና ቀይ ስር ያሉት እንዳንድ ጊዜ እንደ ሥራሥር እህል ይመደባሉ፡፡

እንደሆነ አንዳንዶች ይናገራሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት አብዛኛው አትክልት የሚመረተው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ነው፡፡ የተወሰነ የቲማትምና ቃሪያ መርት ወደ ጅቡቲ የሚላክ ሲሆን ወደ አውሮፓ አገሮች በአየር ማጓጓዣ የሚላከው በጣም ጥቂት ነው፡፡ ቀይ በርበሬ በድልህና በዱቄት መልክ ወደ ውጭ ይላካል፡፡ የተሻለ ጥራት ያለው አትክልት ለሀገር ውስጥ ያለው ፍላጐት በጣም የተወሰነ ነው፡፡

### (2) የአትክልት ምርት በደቡብ ክልል

ደቡብ ክልል ዋንኛው የአትክልት አምራች ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ 46% የምርትና ገበያ ድርሻ አለው፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-12 በኢትዮጵያ የአትክልት* ምርትና የገበያ ድርሻ መጠን**

| ክልል | ምርት | | ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | 274,158 | 46% | 18.98 | 52,035 | 46% |
| አማራ | 79,354 | 13% | 16.75 | 13,292 | 12% |
| ትግራይ | 16,186 | 3% | 25.79 | 4,174 | 4% |
| ኦሮሚያ | 224,901 | 38% | 18.81 | 42,304 | 38% |
| ጋምቤላ | 841 | 0.1% | 20.31 | 171 | 0.2% |
| አፋር | 486 | 0.1% | 36.17 | 176 | 0.2% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 595,926 | 100% | | 112,152 | 100% |

* የሚያጠቃልለው ሰላጣ፣ አበሻ ጎመን፣ ጥቅል ጎመን፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ በርበሬ፣ ቆስጣ
ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ፣ኤ፣አ), ጥራዝ VII (ብሉቲን 446)

በደቡብ ክልል የአትክልት ምርት በገበያ ድርሻ በቀጣይ ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡ በርበሬና ሽንኩርት ከሌሎች አትክልቶች ከፍ ያለ ሽያጭ ዋጋ አላቸው፡፡ ሌሎች በቶሎ የሚበላሹ አትክልቶች በአብዛኛው ለቤት ውስጥ ፍጆታ ይመረታሉ፡፡ በአጠቃላይ በክልል ደረጃ በገበያ ላይ የዋለው የአትክልት መጠን በጣም አነስተኛ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-13 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የአትክልት ምርትና የገበያ ድርሻ መጠን**


| ዓይነት | ምርት (ቶን) | % ሽያጭ | የተሸጠ መጠን (ቶን) |
|---|---|---|---|
| አበሻ ጎን | 184,232 | 12% | 21,463 |
| ጥቅል ጎመን | 4,003 | 19% | 760 |
| ቲማቲም | 6,539 | 26% | 1,717 |
| ቃሪያ | 11,645 | 20% | 2,289 |
| በርበሬ | 67,412 | 64% | 43,326 |
| ቀይ ሥር | 3,417 | 17% | 575 |
| ካሮት | 946 | 18% | 175 |
| ሽንኩርት | 8,573 | 41% | 3,533 |
| ነጭ ሽንኩርት | 1,870 | 27% | 514 |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ማጠቃለያ)

### (3) በደቡብ ክልል የግብይት ሁኔታ

የሚበላሹ የአትክልት ዓይነቶች የሚመረቱት ለቤት ፍጆታ ሲሆን ግብይቱ የሚከናወነው በአቅራቢያ በሚገኙ ማዕከላት ነው፡፡ በተነፃፃሪ ወደ ራቅ ያሉ አካባቢ አበሻ ጐመንና ቲማቲም ከሲዳማ አካባቢ ጀምሮ በደቡብ አቅጣጫ ሞያሌና ያቬሎ ለገበያ ይሄዳሉ፡፡ ሆኖም የግብይት መጠኑ አነስተኛ ነው፡፡ ቀረብ ወዳሉ አካባቢዎች (አ/አበባ እና ሻሸመኔ ገበያ) የአትክልት

ምርት ከሰሜናዊ የደቡብ ክልል አካባቢዎች የሚመጣ ሲሆን መጠኑም ከፍ ያለ ነው:: አስከአሁን ለሚበላሹ የአትክልት ምርቶች በደቡብ ክልል የገበያ ሥፍራዎች አልተዘጋጁም:: አርሶ አደሮች በአብዛኛው የአትክልት ምርት የሚሸጡት ልክ እንደሌሎች የእህል ዓይነቶች ሁሉ በገበያ ላይ ነው:: ሸማቾች የሚገዙትም በገበያ ነው:: በሀዋሣ ከተማ ተወዳጅ የሆኑ የአትክልት ዓይነቶች (እንደ ድንች፣ ሽንኩርት፣ ጎመን የመሳሰሉት) የሚሸጡባቸው በርከት ያሉ ሱቆች አሉ:: ከዚህ በተጨማሪ 2 የአትክልት መሸጫ ግሮሰሪዎች (የአትክልት ላኪ ድርጅቶች) ያሉ ሲሆን የተለያዩ ዓይነት ጥራት ያላቸው አትክልቶች ለሽያጭ ያቀርባሉ:: በአጠቃላይ የአትክልት ግብይት ፍሰት ከዚህ በታች ተመልክቷል::




ምስል 3.1-6 በደቡብ ክልል የአትክልት የገበያ ስንሰለት

### (4) ምርት፣ ግብይትና ድህረምርት አያያዝ

#### 1) ጎመን (አበሻ ጎመንና ጥቅል ጎመን)

የጐመን ምርትና በገበያ መጠን በዞን/ ልዩ ወረዳ ከዚህ ቀጥሎ ተመልክቷል:: በኢትዮጵያ ደረጃ የአምራቾች የሽያጭ መጠን ሲታይ የሀበሻ ጎመን 12% ሲሆን የጥቅል ጎመን 15% የገበያ ድርሻ አለው:: የደቡብ ክልል የጎመን ገበያ ፍላጎት ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ነው:: አብዛኛው የጎመን ሽያጭ የሚካሄደው በአርሶአደሮች ለአካባቢ ነጋዴዎችና ሸማቾች በገበያ ሥፍራዎች ሲሸጥ ነጋዴዎች ወደ አካባቢ ከተማ ገበያዎች አጓጉዘው ይሸጣሉ:: በተነፃፃሪ የረዥም ርቀት ግብይት በጣም አነስተኛ ነው:: አልፎ አልፎ የሀበሻ ጎመን ከሲዳማ አካባቢ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሞያሌና ያቤሎ ተጓጉዞ ይሸጣል::


ሠንጠረዥ 3.1-14 የጎመን ምርትና የገበያ መጠን በዞን

| | የአበሻ ጎመን | | | ጥቅል ጎመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዞን ልዩ ወረዳ | ምርት (ቶን) | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን (ቶን) | ምርት (ቶን) | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን (ቶን) |
| ሲዳማ | 48,907 | 13% | 6,568 | | | |
| ሃዲያ | 27,178 | 12% | 3,188 | 561 | 14% | 81 |
| ስልጤ | 25,037 | 11% | 2,842 | 1,025 | 18% | 180 |
| ጉራጌ | 17,624 | 8% | 1,403 | 1,195 | 8% | 91 |
| ጌደኦ | 11,138 | 14% | 1,506 | | | |
| አላባ | 9,591 | 7% | 683 | 245 | 4% | 9 |
| ከፋ | 8,977 | 10% | 871 | | | |
| ከምባታ ጠምባሮ | 7,680 | 10% | 752 | 509 | 10% | 49 |
| ወላይታ | 6,645 | 11% | 706 | | | |

| ዞን ልዩ ወረዳ | የአበሻ ጎመን | | | ጥቅል ጎመን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ምርት (ቶን) | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን (ቶን) | ምርት (ቶን) | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን (ቶን) |
| ጋሞ ጎፋ | 5,791 | 13% | 779 | 279 | 40% | 111 |
| ቤንች ናጂ | 4,028 | 11% | 443 | | | |
| ዳውሮ | 3,961 | 7% | 279 | 17 | 7% | 1 |
| አማሮ | 1,831 | 24% | 442 | | | |
| ደቡብ ኦሞ | 1,579 | 19% | 294 | | | |
| ሸካ | 1,232 | 5% | 62 | 156 | 34% | 53 |
| የም | 1,140 | 17% | 196 | | | |
| ደራሼ | 782 | 7% | 58 | | | |
| ቡርጂ | 446 | 21% | 95 | | | |
| ኮንታ | 428 | 13% | 54 | | | |
| ኮንሶ | 124 | 6% | 7 | | | |
| ባስኬቶ | 114 | 19% | 22 | 16 | 45% | 7 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 184,232 | 12% | 21,249 | 4,003 | 15% | 582 |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ብሉቲን 446)

ጎመን የሚመረተው ለቤት ፍጆታ ነው፡፡ ስለሆነም የአቅርቦትና ገበያ ፍላጐት የምርት ዋጋ ይወሰናል፡፡ እንደ ማዕከላዊ አስታቲስትክስ ኤጀንሲ የአምራቾች የ2009 (እ.ኤ.አ) የዋጋ መረጃ እንደሚያሳየው ከዞን ዞን ልዩነት ያሳያል፡፡ በሃዲያ ዞን የነበረው የገበያ ዋጋ ከሌሎች አካባቢ ካለው ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምናልባት ለአ/አበባ ገበያ የሚያቀርብ ስለሆነ ተጽእኖ አድሮ ይሆናል፡፡  በሚያዝያ ወር ዋጋ ከፍ የሚለው ምናልባት የዐብይ ጾም ወራት የአትክልት ፍላጐት ስለሚጨምር ዋጋውም ከፍ ይላል፡፡ በሌላ በኩል የጉራጌ ጎመን የሚባለው ከአባሻ ጎመን ዋጋው በጥቂቱ ከፍ ይላል፡፡




**ምስል 3.1-7  በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ወርሃዊ የአበሻ ጎመን ዋጋ /ጥር-ታህ 2009 (እ.ኤ.አ)**

ጥቅል ጎመን ወደ ገበያ ለማጓጓዝ ምንም ዓይነት የእንጨት ሣጥንም ሆነ ከረጢት ሥራ ላይ አይውሉም፡፡ የመጫንና ማውረድ አያያዝ በጣም ደካማ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሚመረተው ጎመን የመጫንና የማውረድ ችግሮችን የሚቋቋም ጠንካራ ዓይነት ዝሪያ ነው፡፡ የአበሻ ጎመን በተመለከተ የማጠብ፣ የማሠርና በሥርዓት የማስቀመጥ ሥራ የሚከናወነው በገበያ ሥፍራ ባሉ ቸርቻሪዎች ነው፡፡



በሀዋሣ የጎመን ገበያ



በአ/አበባ ጅምላ ሻጭ ሱቅ ሲወርድ



ሀዋሣ ጎመን በደረጃ ሲለይና ሲታሰር

2) *ቃሪያ*

የደቡብ ክልል በቃሪያ ምርት በሀገር ደረጃ 18% እና 22% የገበያ ድርሻ አለው፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-15 በኢትዮጵያ የቃሪያ ምርት የገበያ ድርሻ

| ክልል | ምርት | | ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ኦሮሚያ | 31,900 | 48% | 13% | 4,026 | 39% |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | 11,645 | 18% | 20% | 2,289 | 22% |
| አማራ | 11,573 | 18% | 11% | 1,227 | 12% |
| ትግራይ | 9,623 | 15% | 28% | 2,675 | 26% |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 809 | 1.2% | 10% | 80 | 0.8% |
| ጋምቤላ | 303 | 0.5% | 9% | 27 | 0.3% |
| ሶማሌ | 19 | 0.0% | 33% | 6 | 0.1% |
| የኢትዮጵያ ድምር | 65,873 | 100% | 100% | 10,331 | 61% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446)

የምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና ልዩ ወረዳ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ ሲዳማ፣ ቤንች ማጂ፣ ከፋና ወላይታ ዞን በደቡብ ክልል ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ናቸው፡፡ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ምርት (39%) እና የገበያ ድርሻ (51%) አለው

ሠንጠረዥ 3.1-16 የቃሪያ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና ልዩ ወረዳ

| ዞን/ልዩ ወረዳ | ምርት | | ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ሲዳማ | 4,534 | 39% | 31% | 1,397 | 51% |
| ቤንች ማጂ | 1,729 | 15% | 20% | 342 | 12% |
| ከፋ | 1,546 | 13% | 22% | 339 | 12% |
| ወላይታ | 1,247 | 11% | 20% | 247 | 9% |
| ጌደኦ | 788 | 7% | 9% | 74 | 2.7% |
| ጋሞ ጎፋ | 483 | 4% | 31% | 148 | 5.4% |
| ሃዲያ | 329 | 2.8% | 11% | 35 | 1.3% |
| ሸካ | 247 | 2.1% | 8% | 19 | 0.7% |
| ከምባታ ጠምባሮ | 211 | 1.8% | 16% | 34 | 1.2% |
| ጉራጌ | 148 | 1.3% | 10% | 15 | 0.5% |
| ኮንታ | 135 | 1.2% | 30% | 41 | 1.5% |
| ደቡብ ኦሞ | 106 | 0.9% | 43% | 45 | 1.6% |
| የም | 101 | 0.9% | 14% | 14 | 0.5% |
| ዳውሮ | 42 | 0.4% | 11% | 5 | 0.2% |
| የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 11,645 | 100% | 24% | 2,757 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (በሉቲን 446)

ቃሪያ በኢትዮጵያ ሁሉም ሰው የሚጠቀመው አትክልት ነው። ስለሆነም አብዛኛው አርሶአደሮች በጓሮው ያመርታል። አንዳንድ ጊዜ የቃሪያ ገበያ አነስተኛ ይሆናል። ነግር ግን የቃሪያ ፍላጐት በጣም ከፍ ያሚለው በዐቢይ ጾም ወቅት ሲሆን ዋጋው በዚያው ልክ ከፍ ይላል። የቃሪያ የገበያ ፍሰት ከላይ በተገለፀው መልክ ነው። በድህረምርት አያያዝ ወቅትም የተለየ ችግር የለውም። ከቃሪያ በባህላዊ አሠራር ድልህ (ዳታ) ይዘጋጃል። አንዳንድ ሰዎች ይህንን በአሁኑ ወቅት ለገበያ ማዘጋጀት ጀምረዋል።

### 3) በርበሬ

የደቡብ ክልል በበርበሬ ምርት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃፀር ለገበያ የሚቀርበውም ከፍ ያለ (64%) ነው። ስለሆነም በደቡብ ክልል የበርበሬ ገበያ ድርሻ 60% ይደርሳል።

ሠንጠረዥ 3.1-17 በኢትዮጵያ የበርበሬ ምርትና የገበያ ድርሻ

| ክልል | ምርት | | ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | 67,412 | 37% | 64% | 43,326 | 59% |
| ኦሮሚያ | 58,136 | 32% | 32% | 18,382 | 25% |
| አማራ | 53,047 | 29% | 20% | 10,599 | 14% |
| ትግራይ | 2,543 | 1.4% | 21% | 531 | 0.7% |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 1,893 | 1.0% | 16% | 297 | 0.4% |
| ሌሎች ክልሎች | 373 | 0.2% | 26% | 95 | 0.1% |
| የኢትዮጵ ድምር | 183,403 | 100% | 40% | 73,230 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡሉቲን 446)




**ምስል 3.1-8 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የበርበሬ ምርት የሚካሄድባቸው አካባቢዎች**

የበርበሬ ምርት የገበያ ድርሻ በዞንና ልዩ ወረዳ ከዚህ በታች ተመልክቷል። በክልሉ ጉራጌ፣ ሥልጤ፣ ዞንና አላባ ልዩ ወረዳ ዋና ዋና የበርበሬ ምርት አካባቢዎች ናቸው። 90% የሚሆነው ለገበያ የሚመረተው በርበሬ ከነዚህ አካባቢዎች ነው። ማራቆና አላባ የታወቁ የበርበሬ ምርት የሚገኝባቸው ናቸው። በጉራጌ ዞን ማራቆ ወረዳ ማራቆ ፊና የተባለ በርበሬ ዝሪያ መገኛ እንደሆነ ይገመታል። ማራቆ በርበሬ ከፍተኛ ጥራት ያለውና ብዙ ተፈላጊነት ያለው ሲሆን በገበያ ዋጋም ከሌሎች ዝራያዎች ከፍ ያለ ነው።

**ሠንጠረዥ 3.1-18 የበርበሬ ምርትና ገበያ ድርሻ በዞንና በልዩ ወረዳ**


| ዞን/ልየ ወረዳ | ምርት | | ለሽያጭ % | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | | ቶን | % |
| ስልጤ | 24,685 | 37% | 77% | 19,092 | 40% |
| ጉራጌ | 20,463 | 30% | 61% | 12,402 | 26% |
| አላባ | 13,421 | 20% | 87% | 11,692 | 25% |
| ከፋ | 2,343 | 3% | 55% | 1,296 | 3% |
| ሃዲያ | 1,969 | 3% | 75% | 1,472 | 3% |
| ቤንች ማጂ | 1,761 | 3% | 27% | 479 | 1% |
| ወላይታ | 1,687 | 3% | 51% | 858 | 2% |
| ሌሎች | 1,083 | 2% | 34% | 367 | 1% |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 67,412 | 100% | 71% | 47,660 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446)

በዋና ዋና የበርበሬ ምርት አካባቢዎች ከ4-5 የሚሆኑ የታወቁ የምርት መሰብሰቢያዎች እንደ አላባ ቁሊቶ፣ ዳሎቻ፣ ኢንስኖ፣ ቡታጅራ እና ቆሼ ገበያዎች ይገኛሉ። አርሶአደሮች በርበሬውን አድርቀው ወደ እነዚህ የገበያ ሥፍራዎች ሲያመጡ ከአ./አበባ፣ ናዝሬት፣ መቀሌ/ትግራይ እና ከሌሎችም ዋና ዋና ገበያዎች ለሚመጡ ትላልቅ ነጋዴዎች ይሸጣሉ። እንደ ሌሎች የግብርና ምርቶች የአካባቢ ነጋዴዎች ወደ እርሻ ማሣ ድረስ በመሄድ መግዛት የተለመደ አይደለም። ከዚያ ይልቅ አንስተኛ ነጋዴዎች ብዙ ጊዜ (አርሶአደር ነጋዴዎች) ወደ አካባቢ ገበያዎች በመሄድ በርበሬ በመግዛትና በመሰብሰብ አጠራቅመው ለትላልቅ ነጋዴዎች ይሸጣሉ።

አንዳንድ አርሶአደሮች የሞባይል ቴሌፎን በመጠቀምና ከጅምላ ነጋዴዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የገበያ ዋጋ መረጃ ያገኛሉ፤ ዋጋም ይወስናሉ። እንዲሁም መቼ ምርቱን ገበያ አውጥተው መሸጥ እንዳለባቸው ይወስናሉ። በአላባ ልዩ ወረዳ በርበሬ ንግድ የተሰማራ የአርሶአደር ቡድንም ሆነ ሕ/ሥራ ማህበር የለም። ኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት በስልጢ፣ በማራቆ እና በሀዋሣ 3 የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበራትን በበርበሬ ገበያና ማቀናባበር ሥራ እንዲሠማሩ ይደግፍ ነበር። በሐምሌ 2010 (እ.ኤ.አ) ሁለት ሕ/ሥራ ማህበራት በስልጢና በማራቆ ተጐብኝተው ነበር። ነገር ግን ሁለቱም ሕ/ሥራ

ማህበራት የተባለውን ድጋፍ አግኝተው ራሳቸውን ችለው ለመቆም ብዙ ይቀራቸዋል በተለይ ግብይትን በተመለከተ።




**ምስል 3.1-9 በአላባ ገበያ የበርበሬ ገበያ ሰንሰለት**

በገበያ ሥፍራ ያለውን ግብይት በሚመለከት አላባ ቁሊቶ የሚካሄደው በገበያ ልውውጥ የተለየ ገፅታ አለው። ይኸውም ሀ) ከትላልቅ ከተማዎች የሚመጡ በርካታ ገዥዎች አሉ። ለ) ከፍ ያሉ የገበያ ልውውጦች የሚካሄዱት በምሽት አካባቢ ነው፣ እና ሐ) በገበያ ልውውጡ በርካታ ደላላዎች አሉ። ለዚህ ግብይት ሂደት ልዩ ያደረገው ምናልባት ከአርሶአደሮች የዕውቀት ማነስ ጋር የተያያዘ ወይንም ከአካባቢው የባህል ተጽእኖ የተነሣ ሊሆን ይችላል። በዚህ ዙሪያ ቀጣይ ጥናት ይኖራል።

በርበሬ እንደ ማቅለሚያም ያገለግላል። በርበሬ ተጨምቆ ቅባት በአለው ፈሳሽ መልክ በኢትዮጵያ ቅመማ ቅመም ማቅነባበሪያ ፋብሪካ ተዘጋጅቶ ወደ ውጭ ሀገር ይላክ ነበር። በሀገሪቱ ውስጥ ከአለው የበርበሬ ዝሪያ የተነሳ አሁን ፋብሪካው በዚህ መልክ የሚያዘጋጀው ምርት ዝቅተኛ ጥራት ደረጃ (ዝቅተኛ የቀለም ይዘት) ያለው በመሆኑ ወደ ውጭ ሀገር መላክ አቁሟል።

**ሠንጠረዥ 3.1-19 በድህረምርትና በሽያጭ እንቅስቃሴ የአርሶአደሮች መረጃ ማጠቃለያ**

| ዝርዝር | ዘዴ |
|---|---|
| ዝሪያ | መልካ ዛላ፣ ማራቆ ፋና |
| ምርት (ከደረቀ በኋላ) | በአማካይ 800 ኪ.ግ በሄ/ር፣ ጥልቁ 2000 ኪ.ግ በሄ/ር፣ ግብ 1200 ኪ.ግ በሄ/ር (አላባ) (ወደ 15 ኪ.ግ በከረጢት) |
| ማቅለም | በቀጥታ መሬት ላይ በፀሐይ ብርሃን. ፕላስቲክ ሸራ አይጠቀሙም |
| እርጥበት መቆጣጠር | በእይታና በመነካካት |
| ማከማቸት/ማቆየት | ረዥም ጊዜ: ግለሰብ ከቀርካሃ በተሠራ ጎተራ<br>አጭር ጊዜ: በጆኒያ ተከቶ |
| ሽያጭ | ግለሰቦች ገበያ ቦታ አምጥተው ይሸጣሉ፣ የገቢ ማስገኛ ሥራ፣ የማሰባሰብ ግብይት አይካሄድም |
| ከሽያጭ በፊት ማፅዳትና መለየት | የለም |
| ሌሎች | ምርቱ በብዛት ጨምሯል፣አላባ ልዩ ወረዳ 500 ሄ/ር (ከ10 ዓመት በፊት የነበረው) ወደ 13,500 ሄ/ር በአሁኑ ወቅት ደርሷል። |

ጃይካ የጥናት ቡድን

የበርበሬውን ሙሉ ቅርጽ ለመጠበቅ (እንዳይሰባበር) እና ጥሩ የቀይ ቀለሙን እንዳይለቅ በቂ የእርጥበት መጠን መኖር አለበት። ስለሆነም አርሶአደሮችና ነጋዴዎች አንዳንድ ጊዜ የእርጥበት መጠኑን ለመጠበቅ ውሃ ይረጩበታል። በአላባ ልዩ ወረዳ አርሶአደሮች ከአካባቢ ማቴሪያል የተሠራ መጋዘን ለማጠራቀም ይጠቀማሉ። እነሱ እንደገለፁልን በዚህ ዓይነት መጋዘን በመጠቀም እስከ አንድ ዓመት በርበሬውን ሳይበላሽ ያቆያሉ።

የባህላዊ የበርበሬ የማድረቅያና የማጠራቀምን ዘዴ ለማሻሻል አንዳንድ ጥረቶች ሊደረጉ ይገባል። ይሁን እንጂ የድህረምርት አያያዝን ለማሻሻል እንደ የእርጥበት መጠን በመለየት፣ የበርበሬው ዛላ ቅርጹንና ቀለሙን ወዘተ ሳይለቅ ለማቆየት የምርምር ሥራ መሠራት አለበት።




በአካባቢ ቁሳቁስ የተሠራ የበርበሬ ጎተራ (አላባ ልዩ ወረዳ)



የአካባቢ ነጋዴዎች የማከማቻ ሁኔታ (አላባገበያ)

ከአካባቢው ነጋዴዎች በተገኘው መረጃ መሠረት በአላባ ቁሊቶ ገበያ የሚከተሉት ደረጃዎችን ይጠቀማሉ። ለአካባቢው ነጋዴዎች የግዥ ዋጋ ለየደረጃው ከ2 እስከ 3 ብር በኪ.ግራም ይለያል። ምንም እንኳን የዋጋ ልዩነት ቢስተዋልም በደረጃዎች መካከል ያለው ልዩነት የተረጋጋ ነው።

| | |
|---|---|
| ደረጃ 1፡ | በከረጢቱ ውስጥ ያለው በርበሬ ሙሉ ቅርጽ (ዛላ) ያለውና ቀይ ጥቁር ሆኖ በቂ የእርጥበት መጠን ይኖረዋል። |
| ደረጃ 2፡ | በከረጢቱ ያለው በርበሬ ሙሉ በሙሉ ቅርጽ አለው። የተወሰነ በርበሬ ቀለሙን የለቀቀ ነው። በቂ የእርጥበት መጠንም አለው። |
| ደረጃ 3፡ | የተቀላቀለ ይሆናል |

✶ በሌሎች ከተማዎችና በአ/አበባ ያለው የበርበሬ ገበያ የደረጃ አወጣጥ አልታየም።


በአካባቢ ገበያዎች ነጋዴዎች በርበሬ በሚገዙበት ጊዜ በመጀመሪያ የእርጥበት መጠኑን በመነካካት ያረጋግጣሉ። የክብደት መጠኑ በእያንዳንዱ ከረጢት ይታወቃል፣ ክብደቱ ከፍ ያለ እንደሆነ እንዲበተን ተደርጐ ይታያል። በአሁኑ ጊዜ ማፅዳትና ደረጃ መስጠት ሥራ በነጋዴዎች እንጂ በአርሶአደሮች አይከናወንም።



የማፅዳትና ደረጃ መስጠት ሥራ በአ/አበባ



ጅምላ ሻጭ በሀዋሣ ገበያ




| ጥር | የካቲት | መጋቢ.ት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረ | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | >>>> | >>>> | | | XXXX | XXXX | XXXX | |
| | | >>>> | ተከላ ወቅት | | | XXXX | ምርቱ የሚሰበሰብበት ወቅት | | | | |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ወርሃው የአምራቾች ዋጋ ሪፖርት ጥር-ታህሳስ 2009 (እ.ኤ.አ)፣፡ አላባ ልዩ ወረዳ የግብይት የሥራ ሂደት፣ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት

**ምስል 3.1-10 ወርሃዊ የበርበሬ ዋጋና የምርት ወቅት**

በላይኛው ምስል እንደታየው የበርበሬ ዋጋ እንደ ወቅቱ ሁኔታ ይለዋወጣል፡፡ በአጠቃላይ የበርበሬ ፍላጐት በተለይ በአ./አበባ ገበያ የተረጋጋ ቢሆንም ዋጋው የሚወሰነው በአቅርቦት መጠን ነው፡፡ በአላባ ልዩ ወረዳ የግብይት የሥራ ሂደት መሠረት ከመስከረም እስከ ታህሣሥ የበርበሬ ዋጋው ዝቅ እያለ ይሄዳል፡፡ እነሱ እንደገለፁልን በሌሎች ክልሎች ባለፈው ዓመት በብዛት የተመረተው በርበሬ ምርት የደቡብ ክልል ዋጋ ዝቅ እንዲል አድርጓል፡፡ በመጋቢት 2009 (እ.ኤ.አ) የአምራቾች ዋጋ ከ26-27 ብር በኪ.ግራም ነበር፡፡

### 4) ቲማቲም

የቲማቲም ምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና በልዩ ወረዳ ያለው ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ በክልል የገበያ መጠን አንፃር የቲማቲም የሽያጭ ድርሻ 32% ነበር፡፡ በደቡብ ክልል ጋሞ ጐፋ ዞን ከፍተኛ የገበያ ድርሻ ያለው ሲሆን አብዛኛው ለቤት ፍጆታ ይውላል፡፡ የምርት መጠን በሃዲያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ እና ሲዳማ ዞኖች የተወሰነ ነው፡፡ እንደ አ/አባበ እና ናዝሬት ወዳሉ ትላልቅ ገበያዎች የሚቀርብበት ማጠራቀሚያ ገበያ የለም፡፡ አንዳንዴ የቲማቲም ምርት ከሲዳማ ዞን ወደ ሞያሌና ያቬሎ ይሄዳል፡፡

### ሠንጠረዥ 3.1-20 የቲማቲም ምርትና ገበያ ድርሻ በዞን

| ዞን | ምርት | | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (ቶን) | (%) | | (ቶን) | (%) |
| ጋሞ ጎፋ | 2,716 | 42% | 37% | 1,005 | 48% |
| ሃዲያ | 1,665 | 25% | 29% | 479 | 23% |
| ከምባታ ጠምባሮ | 1,197 | 18% | 23% | 279 | 13% |
| ሲዳማ | 503 | 8% | 55% | 276 | 13% |
| ሌሎች | 460 | 7% | 12% | 55 | 3% |
| የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 6,539 | 100% | 32% | 2,095 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ) ጥራዝ VII (ቡለቲን 446)

ለገበያ የሚደረግ የቲማቲም የማምረት ሥራ በአ/አበባ አካባቢ ይካሄዳል፡፡ የቲማቲምና የሌሎችም አትክልቶች ለገበያ የሚደረግ እርሻ ሥራ በመቂ-ዝዋይ አካባቢ (ኦሮሚያ ክልል) የሚገኝ ሲሆን በመስኖ አማካይነት ይለማል፡፡ የመቂ-ዝዋይ ቲማቲም ለሀዋሣ ገበያ ይቀርባል፡፡ በሲዳማ ዞን ወንዶገነት አካባቢ አንዱ ለሀዋሣ ቲማቲም አቅራቢ አካባቢ ነው፡፡

በመቂ፣ ዝዋይ እና ወንዶገነት አካባቢዎች የተለያዩ ዝሪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ የወንደገነት ቲማቲም ምርት ወፍራም ቆዳ ያለው ሲሆን በአያያዝ ጊዜ ቶሎ አይበላሽም፡፡ በሀዋሣ ገበያ ላይ የወንዶገነት ቲማቲም በኪ.ግራም 3 ብር እና የመቂ-ዝዋይ ምርት በኪ.ግራም 5 ብር ሲሆን በመካከሉ የ2 ብር በኪ.ግራም ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡ ከወንዶገነት ወደ ገበያ የሚደረገው ማጓጓዣ በአህያ ጋሪ ነው፡፡ ጉዞው ከ5-6 ሰዓት የሚፈጅ ሲሆን በሣጥን ተደርጐ የሚጓጓዝ በአንድ ጋሪ 30 ብር ሲሆን በጭነት መኪና ከሆነ ጭነቱን 1,500 ብር ነው፡፡ የማጓጓዣ ዋጋ በኪ.ግራም በጣም የተቀራረበ ነው (0.25 ብር በኪ.ግራም ለጋሪ 120 ኪ.ግራም 30 እና 0.22 ብር በኪ.ግራም ለጭነት መኪና)፡፡ ሆኖም አንድ አርሶአደር ወደ ገበያ የሚያጓጉዘው መጠን በጣም ትንሽ በመሆኑ የጭነት መኪና ለመከራየት አይችልም፡፡ የአርሶአደሮች የጋራ ግብይት ሥራ ገና አልተጀመረም፡፡ በእንጨት ሳጥን ተጓጉዞ ወደ ገበያ ሲደርስ በሣጥን ከመሙላት የተነሣ ተበላሽቶ የሚጣለው በየጊዜው ይስተዋላል፡፡ ይህንን ችግር ለማቃለል የሚደራረቡ ሣጥኖችን መጠቀም ይመረጣል፡፡ በአካባቢ የሚመረቱ ኘላስቲክ ሣጥኖች (በቀኝ በኩል ፎቶ) የሚደራረቡ ናቸው፡፡ ዋጋቸውም (140 ብር በአንድ ሣጥን) ሲሆን ከእንጨት ሣጥን ክፍ ያለ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአውሮፓ የተሠሩ የኘላስቲክ ሣጥኖች 50 ብር በአንድ ሣጥን) በሀዋሣ ከተማ ብዙ የተለያዩ ምርቶችን የሚይዙ ታዋቂ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ እነዚህ ጥቅም ላይ የዋሉ የኘላስቲክ ሣጥኖች የአገልግሎት ዘመናቸው በአካባቢ ከሚሠሩ ሣጥኖች ያነሰ ነው፡፡ ዋጋቸውም 1/3ኛ ያህል ነው፡፡ እነዚህ እርካሽ የሆኑ የኘላስቲክ ሣጥኖች የሚበላሹ የቲማቲም ምርት ወደ ከተማዎች ለማጓጓዝ በስፋት አገልግሎት ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡



ከሚገባው በለያ የተሞላ (ሀዋሣ ገበያ)



የተሻለ አያያዝ (ጅምላ ሽያጭ (አ/አበባ)

### 3.1.4 ፍራፍሬ

#### (1) የምርትና የፎጆታ አጠቃላይ ሁኔታ

የፍራፍሬ ምርት ከምግብ እህል ምርት ጋር ሲነፃፀር በጣም ውስን ነው፡፡ የተሰጠውም ትኩረት በጣም አናሳ ነው፡፡ ምርት ለማሳደግም ሆነ ጥራትን ለማሻሻል (የተሻሻሉ ዝሪያዎችን የማስተዋወቅ ሥራ) የተደረገ ጥረት በጣም ውስን ነው፡፡ በተለይ ለገበያ የሚደረገው የፍራፍሬ ምርት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ምንም እንኳን የመንግሥት እርሻዎች ቢኖሩም የሚያመርቱት ብርቱካን ሆኖ በአብዛኛው ፍራፍሬ የሚመረተው በአነስተኛ ደረጃ በአርሳአደሮች በየጓሮአቸው ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገር ደረጃ የሚመረተው አብዛኛው ፍራፍሬ ለቤት ውስጥ ፍጆታ ይውላል፡፡ የተወሰነ መጠን ያለው እንደ አቮካዶ፣ አናናስ፣ ሙዝ ወዘተ ያሉ ምርቶች ወደ ጅቡቲ ይላካሉ፡፡ ከዚያ ውጪ ወደ ባህር ማዶ ሀገሮች የሚላክ የለም፡፡ ፍራፍሬ ወሳኝ የምግብ ዓይነት ሳይሆን እንደ መዝናኛ በየመደብሩ የሚሸጥ ምርት ነው፡፡ ፍራፍሬ መብላት በከተሞች አካባቢ በጣም የተለመደ ነው፡፡ በከተሞች አካባቢም በርካታ የፍራፍሬ ዛፎች ማየትና በተጨማሪ ትኩስ የፍራፍሬ ጭማቂ ተወዳጅ መጠጥ እየሆነ መጥቷል፡፡ ሆኖም ለተሻለ ጥራት ያለው ፍራፍሬ ፍላጎት (ማለትም ጥራት ላላቸው ፍራፍሬዎች የተሸለ ዋጋ ለመክፈል) በሸማቾች ዘንድ መኖሩ ገና አልተጣራም፡፡

በጃይካ ጥናት ቡድን የተሻለ ፍራፍሬ ምርት እና የግዥ ባህሪይ በሀዋሣ ነሐሴ 2010 (እ.ኤ.አ) በአካሄደው ደሰሳ ጥናት መሠረት 80% ሸማቾች ፍራፍሬ የሚገዙት ከአንድ እስከ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ በሣምንት እንደ ሆነና የሚገዙአቸውም ሙዝ፣ ማንጐ፣ ብርቱካን እና አቮካዶ እንደ ቅደም ተከተላቸው ነው፡፡ በግዥ ወቅት ጥራትን ለመቆጣጠር ሊቶከርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ለማንጐ ቀለምና የብስለት ደረጃ፣ ለአቮካዶ የብስለት ደረጃና ብልሽት መኖር አለመኖር ናቸው፡፡ የሸማቾች ስሜት በተመለከተ 30-40% የሚሆኑት በአቦቡካዶ ጥራት ደስተኞች አይደሉም፡፡ ብዙ ሸማቾች ትልቅና ጥሩ እይታ (ጥራት) ለአለው ማንጐ የተሻለ ክፍያ ለመፈጸም ፍቃደኛ እንደሚሆኑ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው በከተማ ሸማቾች አካባቢ የተሻለ ጥራት ያለውን ፍራፍሬ ለማግኘት ፍላጐት እንዳለ ነው፡፡

#### (2) የፍራፍሬ ምርት በደቡብ ክልል

ደቡብ ክልል በሀገር አቀፍ ደረጃ ዋንኛው ፍራፍሬ አምራች አካባቢ ነው፡፡ እንደ ማዕከላዊ እስታቲስትክስ ኤጀንሲ መረጃ (2008/09 እ.ኤ.አ) በደቡብ ክልል በአቮካዶ፣ ሙዝና አናናስ ከፍተኛ የምርት ድርሻ አለው፡፡ ሙዝ በአ/ምንጭ አካባቢ ለገበያ ይመረታል፡፡ አናናስ ደግሞ በሲዳማ አካባቢ ለገበያ ይመረታል፡፡ የአናናስ መንግሥት እርሻ (ጎጅብ ከፋ ዞን የነበረው) በቅርብ ጊዜ ወደ በቆሎ እርሻ ተቀይሯል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-21 በኢትዮጵያና ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ፍራፍሬ ምርት የገበያ ድርሻ**

| ዝርዝር | የሀገር ምርት (ቶን) | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ምርት (ቶን) | ከሀገሪቱ ምርት ያለው ድርሻ | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን (ቶን) | የተመረጠ ፍራፍሬ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አቮካዶ | 32,452 | 22,986 | 71% | 46% | 10,504 | X |
| ሙዝ | 194,333 | 130,834 | 67% | 50% | 65,208 | X |
| ማንጎ | 44,158 | 13,720 | 31% | 39% | 5,282 | X |
| ፓፓያ | 44,003 | 18,274 | 42% | 18% | 3,202 | X |
| አናናስ | 153 | 128 * | 84% | 53% | 67 * | |
| ዘይቱን | 1,947 | 394 | 20% | 33% | 131 | |


| ዝርዝር | የሀገር ምርት (ቶን) | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | | | | የተመረጠ ፍራፍሬ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምርት (ቶን) | ከሀገሪቱ ምርት ያለው ድርሻ | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን (ቶን) | |
| ሎሚ | 4,871 | 1,494 | 31% | 63% | 943 | |
| ብርቱካን | 29,341 | 8,422 | 29% | 42% | 3,550 | |

* ከሲዳማ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት መመሪያ ከተገኘው መረጃ እጅግ ያነሰ ነው።.

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446)

### (3) በደቡብ ክልል የግብይት ሁኔታ

የፍራፍሬ የገበያ ሰንሰለት ከታች ተገልጿል። አርሶአደሮች ፍራፍሬ ልክ እንደ ሌላ እህል በአቅራቢያ በሚገኘው ገበያ ስፍራ ይሸጣሉ። ከአትክልት ገበያ ሂደት የተለዩ ጉዳዮች ሀ) በማሣ ላይ የተለየ የምርት መሰብሰብያ አሠራር አለ፣ ለ) በትላልቅ ከተሞች አካባቢ ቋሚ የችርቻሮ ንግድ ሱቆች አሉ፣ ሐ) ፍራፍሬ ከሚበላሹ አትክልት ይልቅ ረዥም መንገድ ተጓጉዘው ይሸጣሉ፣ እና መ) በአጠቃላይ የአርሶአደሮች ሽያጭ ድርሻ ከአትክልት ይበልጣል።




**ምስል 3.1-11 የፍራፍሬ የግብይት ሰንሰለት**

በአርባምንጭ አካባቢ ብዙ የሙዝ ምርት በአርሶአደሮች የሚመረት ሲሆን የግብይት ዘዴውም ከሌሎች አካባቢዎችና ሌሎች ፍራፍሬዎች የተለየ ነው።

- የምርት መሰብሰቢያዎች በማሣ ላይ ሳይሆን በመንገድ ዳር ነው።
- የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበራት እና ዩኒየን በሙዝና ማንጉ ገበያ ላይ ይሣተፋሉ።
- የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማበራት ከአባል አርሶአደሮች ፍራፍሬ ይገዙና ቀጥታ ለገዢዎች (ጅምላ ሻጮች) በአ/አበባ፣ ናዝሬት፣ መቀሌ (ትግራይ) ወዘተ ይሸጣሉ።

የሙዝ በጅምላ ነጋዴዎች በፍጆታ አካባቢ የማብሰያ ሂደት ያስፈልገዋል። በሀዋሣ ከተማ የሙዝ ጅምላ ሽያጭ ነጋዴ የለም፤ ሽያጩ የሚካሄደው በፍራፍሬ ሱቅ ነው።

በሚቀጥለው ሠንጠረዥ የፍራፍሬ ብልሽት መጠን (ካልተሸጠ ምርት) ያሣያል። ማንጉ አራት ዓይነት ፍራፍሬዎች ከፍተኛ የብልሽት መጠን አለው። 11 ሱቆች ከታዩት 3 ሱቆች በየቀኑ የማይሸጥ አለ ሲሉ 8 ሱቆች አንዳንድ ጊዜ የማይሸጡ ፍራፍሬዎች እንዳሉ መልሰዋል።

**ሠንጠረዥ 3.1-22 በችርቻሮ ሱቅቆች ያለው ብልሽት**

| | ብልሽት (ያልተሸጠ) መጠን | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0 - 5 % | 6 - 10 % | 11 - 20% | 21 - 30% | 31 - 40% | |
| ማንጎ | 1 | 2 | 1 | 3 | 2 | 9 |
| አቮካዶ | 3 | 4 | 1 | 2 | | 10 |
| ሙዝ | 3 | 5 | 2 | | | 10 |
| አናናስ | | | 3 | 1 | | 4 |

(መለኪያ: የሱቅ ቁጥር)

ምንጭ፡ በሀዋሣ የጥራት ፍላጎትና ለትኩስ ፍራፍሬ የገዥ ባህርይ ዳሰሳ ጥናት ነሐሴ 2010 (እ.ኤ.አ) ጃይካ ጥናት ቡድን

## (4) የተመረጡ ፍራፍሬ ምርቶች ግብይትና ድህረምርት አያያዝ

### 1) አቮካዶ

የአቮካዶ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና ልዩ ወረዳ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡ አብዛኛው የአቮካዶ ምርት በአርሶአደሮች ጓሮ በራሳቸው ማሣ ላይ ይመረታል፡፡ ወንዶገነት በሲዳማ ዞን (ዋነኛው የምርት አካባቢ) ሲሆን በ175 ሄ/ር መሬት የአቮካዶ ዛፍ ተሸፍኗል፤ በዓመት 2800 ቶንም ያመርታሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት አምራች አካባቢ የአንድ አርሶአደር በአማካይ 3-5 የአቮካዶ ዛፎች ያሉት ቢሆንም ከፍተኛ መጠን ከ15-20 ዛፎች ነው፡፡ በወንዶገነት ወረዳ ኤልፎራ የተባለ የግል ድርጅት 9 ሄ/ር የአቮካዶ እርሻ አለው፡፡ ይህ ድርጅት ከአርሶአደሮች ምርት አይገዛም፡፡ በዚህ ወረዳ በአቮካዶ እርሻ ላይ የተለየ ነገር ቢኖር አርሶአደሮች በእርሻቸው መስኖ ይጠቀማሉ፡፡ 32 ሄ/ር ከ175 ሄ/ር ውስጥ በመስኖ ይለማል፡፡ አርሶአደሮች በመስኖ የሚያለሙት ምርት ያለመስኖ ከሚያለሙት እንደሚበልጥ የገለጹ ሲሆን የምርት መሰብሰብያ ወቅት ግን አንድ ወቅት ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-23 የአቮካዶ ምርትና የገበያ መጠን በዞን**

| ዞን/ልዩ ወረዳ | ምርት | | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (ቶን) | (%) | | (ቶን) | (%) |
| ወላይታ | 6,115 | 27% | 48% | 2,946 | 28% |
| ሲዳማ | 4,690 | 20% | 60% | 2,819 | 27% |
| ሃዲያ | 3,613 | 16% | 36% | 1,317 | 13% |
| ጌደኦ | 2,911 | 13% | 42% | 1,212 | 12% |
| ከምባታ ጠምባሮ | 2,430 | 11% | 40% | 975 | 9% |
| ጉራጌ | 831 | 4% | 39% | 326 | 3% |
| ቤንች ማጂ | 540 | 2% | 59% | 320 | 3% |
| ሌሎች | 1,856 | 8% | 31% | 570 | 5% |
| የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 22,986 | 100% | 46% | 10,484 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጄንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (በሉቲን 446)

የግብይት ሰንሰለቱ ላይ እንደተገለፀው ነው፡፡ ለአቮካዶ ምርት ዋና መሰብሰብያ እንደ ቦዲቲ (ወላይታ ዞን)፣ ወንዶገነት እና አለታ ወንዶ (ሲዳማ ዞን) እና ሃዳሮ (በከምባታ ጣምባሮ ዞን) ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ምርት መሰብሰብያ ገበያዎች በጣም የበሰለና በይዘት አነስተኛ የሆነው ተወግዶ ወደ ዋና ዋና ገበያዎች ይጓጓዛል፡፡ ከረጢቶች ምርቱን ለማጓጓዝ ያገለግላሉ፡፡ ምርቱን በመሰብሰብ ሆነ በሚጓጓዝበት ወቅት ምንም ዓይነት ብልሽት ለመከላከል የሚደረግ አሠራርና ጥንቃቄ የለም፡፡ ከዚህ የተነሣ እስከ 50% ድረስ የምርት ብክንት ይከሰታል፡፡ ከብልሽት ለመከላከል አለመቻል ዋናው ምክንያት የአርሶአደሮችና የነጋዴዎች የዕውቀት ማነስ እንደሆነ በተለይም የአርሶአደሮች የጎላ እንደሆነ ይታወቃል፡፡




ትንሽና የበሰሉ ፍሬዎች ሲለዩ (ሃዳሮ ገበያ)



አቮካዶ ማስባሰብ (ሃዳሮ ገበያ)

ለአርሶአደሮች በከፍተኛ የምርት ወቅት የዋጋ መውረድ ከፍተኛው ችግር ነው። ተከታዩ አሃዝ እንደሚያሣየው የአምራቾች የዋጋ ልዩነት ከ2 እስከ 3 ጊዜ ይሆናል።




ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ወርሃው የአምራቾች ዋጋ ሪፖርት ጥር-ታህሳስ 2009 (እ.ኤ.አ)

**ምስል 3.1-12 የአቮካዶ የአምራች ዋጋ (2009 እ.ኤ.አ) እና ምርት መሰብሰቢያ ወቅት**

የፍራፍሬ ዛፎች ፍሬ የሚይዙበትን ወቅት በግብርና ዘዴ መቆጣጠር አይቻልም። ማቀዝቀዣ ያለውን መጋዘን መጠቀም የኢኮኖሚ አዋጭነቱ አይታይም። ይሁን እንጂ ማቀዝቀዣ ያለውን መጋዘን በከተሞች አካባቢ በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ባለበትና በሸማቾች አካባቢ መሆን አለበት እንጂ ገጠር ወይም በአርሶአደር ድርጅት አካባቢ ሊሆን አይገባም። ማቀዝቀዣ ያለውን መጋዘን መሠረት ያለበትም የገንዘብ አቅም ባለውና ለማሠራት በቂ ችሎታና ዕውቀት ባለው አካል መሆን አለበት። አቮካዶን ጥሩ የማቀዝቀዥ ውስጥ የማቆየት ጊዜ ከ30-35 ቀናት ሲሆን የሙቀት መጠኑ 7 ዲግሪ ሴ.ግሬድ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ የቅዝቃዜ መጠን ለተለያዩ የአቮካዶ ዝርያዎች የተለያዩ ባህሪይና በብስለት መጠን ስለሚለያይ ለአካባቢው ዝሪያ የተስተካከለ የቅዝቃሴና የመጋዘን ሁኔታ ለወደፊቱ በምርምር መለየት አለበት።

አቮካዶ ወደ ጅቡቲ ይላካል። የምርት ምርጫ፣ ደረጃ ማውጣትና የማሸግ ሥራዎች በጅቡቲ ይሠራል። ብቃት ያለውና አስተማማኝ የምርት መሰብሰብያ ዘዴ ሊኖር ያስፈልጋል። ወደ አውሮፓ ገበያዎች ለመላክ ቀጥታ ድጋፍ ለነጋዴዎች ሊሰጥ ይገባል።

## 2) ማንጎ

የማንጎ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና በልዩ ወረዳ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ በደቡብ ክልል የጋሞጎፋ ዞንና የወላይታ ዞን ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ናቸው፡፡ ልክ እንደ አቮካዶ የማንጎ ምርትም በአነስተኛ አርሶአደሮች በጓሮአቸው ባሉት የማንጎ ዛፎች አማካይነት ይመረታል፡፡


**ሠንጠረዥ 3.1-24 የማንጎ ምርትና የሽያጭ መጠን በዞን**

| ዞን/ልዩ ወረዳ | ምርት | | % ለሽያጭ | የሽያጭ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (ቶን) | (%) | | (ቶን) | (%) |
| ጋሞ ጎፋ | 6,794 | 50% | 42% | 2,846 | 51% |
| ወላይታ | 3,326 | 24% | 44% | 1,456 | 26% |
| ቤንች ማጂ | 868 | 6% | 31% | 271 | 5% |
| ከምባታ ጠምባሮ | 840 | 6% | 51% | 428 | 8% |
| ሸካ | 711 | 5% | 15% | 105 | 2% |
| ደቡብ ኦሞ | 455 | 3% | 35% | 158 | 3% |
| አማሮ | 214 | 2% | 51% | 109 | 2% |
| ሌሎች | 513 | 4% | 42% | 215 | 4% |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 13,720 | 100% | 41% | 5,586 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446)

የማንጎ የግብይት ሰንሰለት ከዚህ በላይ በሌሎች ምርቶች እንደተገለጸው ነው፡፡ የማንጎ ምርት በአ/ምንጭ አካባቢ የሚሰበሰበው እንደ ሙዝ በመንገድ ዳር ሲሆን ከዚያም ወደ አ/አበባ እና ናዝሬት ይጓጓዛል፡፡ በጋሞ ጎፋ ዞን ላንቴ ቀበሌ የሚገኘው "ኦቾሎ ላንቴ ጠንክር መጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር" ለኢትፍሩት (አ/አበባ እና ናዝሬት) ማንጎ ያቀርብ የነበረ ስሆን ውጤታማ አልነበረም፡፡

ማንጎ "ብጫና ሙሉ ቃጫ" የሆነ ዝሪያ ያለው በብዛት የሚመረት ሲሆን የአምራቾች ዋጋ በከፍተኛ የምርት ወቅት በጣም ርካሽ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ምሳሌ ለ1 ብር 3 ማንጎ (ወደ 1ብር በኪ.ግራም) አርባምንጭ ላይ ነው፤ ከፍተኛ ዋጋ 0.75 ብር ለ1 ማንጎ ፍሬ ይደርሳል፡፡




ምንጭ፡ ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እና ኡሞ ላንቴ ሕ/ሥራ እንደተሰማው

መሰብሰቢያ ወቅት　ከፍተኛ ምርት መሰብሰቢያ ወቅት

**ምስል 3.1-13 የማንጎ የምርት ወቅት**

በሀዋሣ ገበያ ማንጎ የማብሰል ሥራ አረንጓዴ ምርት በእንጨት ሣጥን ሆኖ በፍራፍሬ ሱቆች ይቀመጣል፡፡ የተለየ የማቆያ አሠራር አይጠቀሙም፡፡



የተበላሸ ማንጎ (ሀዋሣ ገበያ)



የእንጨት ሣጥኖች በጭነት መኪና ለማጓጓዝ ይጠቀማሉ፡፡ ሣጥኖቹ በጎን በኩል ከታች ይጫናሉ

በአያያዝ ምክንያትና በጣም ከመብሰል የተነሣ ብዙ ብልሽት ያጋጥማል፡፡ አብዛኛው ብልሽት የሚያጋጥመው በችርቻሮ ደረጃ ነው፡፡ ማንጎ ዛፍ በተፈጥሮ የሚያድግ ሲሆን አይከረከምም፡፡ አርሶአደሮች ምርቱን የሚሰበስቡት በዛፍ ላይ በመውጣትና በበትር በመምታት እንዲወርድ በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የምርት መሰብሰቢያ ዘዴ በኢትዮጵያ የለም፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-25 የማንጎን ምርት አርሶአደሩ የሚሰበስብበት ዘዴ**

| የሚሰበስቡበት ዘዴ | ቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ | | ዲላ ዙሪያ ወረዳ | |
|---|---|---|---|---|
| | መልስ የሰጡ ብዛት | % | መልስ የሰጡ ብዛት | % |
| ዛፍ ላይ ወጥቶ ፍሬውን በመልቀም | 20 | 33% | 31 | 52% |
| ፍሬውን በብትር በመምታት | 16 | 27% | 17 | 28% |
| ዛፍ ላይ ወጥቶ ፍሬውን በመልቀም＋በብትር ፍሬውን በመምታት | 20 | 33% | 10 | 17% |
| የተለየ መሣሪያ በመጠቀም | 2 | 3% | 1 | 2% |
| በአካባቢ የተሠራ መንጠቆ በመጠቀም | 2 | 3% | 1 | 2% |
| ድምር | 60 | 100% | 60 | 100% |

ምንጭ፡ መነሻ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፡ በቦሎሶ ቦምቤና በዲላ ዙሪያ ወረዳ የማንጎ ምርትና የግብይት ችግሮችና አማራጭ ሁኔታዎች፣ ህዳር 2009 (እ.ኤ.አ) ኤስ.ኤ.ቪ.

ለእንደዚህ ያለ በተለይም እርካሽ ለሆኑ ምርቶች በቀዝቃዛ መጋዘን ሳይበላሹ ለረዥም ጊዜ ማቆየት የኢኮኖሚ አዋጪነት ስለሌለው አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በተለይ በእነዚህ እርካሽ ምርቶች ላይ በምርት አያያዝ ላይ ወጪ በመጨመር የሽያጭ ዋጋ ከፍ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ስለሌለ አርሶአደሮች ብዙ ወጪ ማውጣት (መልፋት) የለባቸውም፡፡ አጋጣሚ ሆኖ ይህ የማንጎ ምርት ወደ ውጭ የሚላክበት ጥራት ደረጃ የለውም፡፡ አልፎ አልፎ የሚከሰተውን የምርት መጥለቅለቅ አዳዲስ የገበያ ፍላጐት ወይም የገበያ አማራጮችን በሀገር ውስጥ በማፈላለግ ገበያ የሚያገኝበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

<u>በአፍሪካ ጁውስ የተፈጠረ አዲስ የማንጎ ፍላጎት</u>

የአፍሪካ ጀውስ ቲቢላሼር ካምፓኒ የተባለ በአዋሽ ሸለቆ ኦሮሚያ ክልል አዲስ የጭማቂ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በመስከረም 2010 (እ.ኤ.አ) ተከፈተ፡፡ የአፍሪካ ጁውስ ከዳሞታ ዩኒየንና ጋሞ ጎፋ ዩኒየን ጋር በነሐሴ 2010 (እ.ኤ.አ) "ብጫ ትንሽና ቃጫ የበዛበት" ማናንጎ በብዛት ከአ/ምንጭና ከበሎሶ በምቤ አካባቢዎች ለመግዛት የኮንትራት ውል ገብቶ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የዳሞታ ዩኒየን የኮንትራት ውል መሠረት 1.3 ብር በኪ.ግራም (ለድርድር ክፍት

ሆኖ) በማሣ ላይ ለኩባኒያው የሚገዘበት ሆኖ ዩኒያኑ በተዋረድ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበርሩ 1.10 ብር በኪ.ግራም ሲከፍል ማህበሩ ደግሞ ከአርሶአደሮች የሚረከበው 0.90 ብር በኪ.ግራም ነበር፡፡ የሚፈለገው የጥራት ደረጃ የስኳር ይዘቱ 12% ሆኖ የማንጎ ፍሬ ከ60 ግራም በላይ ክብደትና መልካም እይታ ያለው መሆን አለበት፡፡

በ2010/11 (እ.ኤ.አ) የምርት ዘመን የጋሞ ጎፋ ዩኒየን ለኩባኒያው ያቀረበው ምርት በኩባኒያው የጭነት መኪና ባለማዘጋጀቱና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የብልሽት ችግር የደረሰበት ሲሆን፤ ከዚህም ጋር በተያያዘ የክፍያ ችግር አጋጥሞት ነበር፡፡ ይህ ችግር በኩባንያው የብቃት ማነስ እና የጥራት ደረጃ ፍላጐት (በተለይም የብስለት ደረጃ) በትክክል ለዩኒየንና ለሕ/ሥራ ማህበሩ ወይም አርሶአደሮች ካለመግለጽ የተፈጠረ ችግር ነበር፡፡ ከዚህ የተነሣ ኩባኒያው በቀረበው የማንጐ ምርት ጥራት ደረጃ ደስተኛ አልነበረም፡፡ ምናልባት ከላይ በተገለጸው ችግር መሆኑ በትክክል ባይረጋገጥም በ2011/12 (እ.ኤ.አ) የምርት ዘመን ኩባኒያው ከዩኒየኑ ግዥ አልፈፀመም፡፡ ለማንኛውም የምግብ ማቀነባበሪያ ሥራ የማቴሪያል ግዥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በግድየለሽ ወይም በቂ ባልሆነ መንገድ ማቴሪያል መግዛት በ2010/12 ምርት ዘመን የአፍሪካ ጁውስ የሥራ እንቅስቃሴ ብቁ ነበር ለማለት ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጂ የኩባኒያው የማንጐ ፍላጐት በሀገር ደረጃ ከፍተኛው ነው፡፡ በአቅርቦት በኩል (ዩኒየኖች፣ ሕ/ሥራ ማህበራት፣ ወረዳ የግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶችና የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ) የተረጋጋ የግብይት ግንኙነት ለመፍጠርና የገዢዎችን የጥራትና የምርት መጠን ፍላጐት ለማሟላት ብዙ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

<u>ከፍተኛ ዋጋ ያለው “አፕል ማንጐ”</u>

“አፕል ማንጐ” የተባለው ዝሪያ ከጥቂት ዓመታት በፊት በብዙ ዞኖች ትውውቅ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ምርቱ እስከአሁን ገበያ ላይ አልዋለም፡፡ አፕል ማንጐ ከአዋሽ ስምጥ ሸለቆ ኦሮሚያ ክልል የሚመረት ሲሆን በአ/አበባ በሐምሌ 2010 (እ.ኤ.አ) 1 ኪ.ግራም በ17 ብር (ችርቻሮ ዋጋ) ይሸጥ ነበር፡፡ ከብጫ ትንሽና ቃጫ የበዛበት ማንጐ የተሻለ የምርት የአያያዝና የተለዩ የግብይት ዘዴዎች ሊኖሩና ሊስፋፉ ይገባል፡፡

3) ሙዝ

የሙዝ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና ልዩ ወረዳ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ ሙዝ በክልሉ በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ይመረታል፡፡ በተለይ ጋሞ ጎፋ (አ/ምርጭ) እና ሲዳማ ዞን ዋና ዋና አምራች አካባቢዎች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-26 የሙዝ ምርትና የሽያጭ መጠን በዞን

| ዞን/ልዩ ወረዳ | ምርት | | % ለሽያጭ | የተሸጠ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (ቶን) | (%) | | (ቶን) | (%) |
| ጋሞ ጎፋ | 57,916 | 44% | 58% | 33,533 | 46% |
| ሲዳማ | 22,782 | 17% | 71% | 16,232 | 22% |
| ወላይታ | 8,516 | 7% | 57% | 4,815 | 7% |
| ከምባታ ጠምባሮ | 7,975 | 6% | 54% | 4,289 | 6% |
| ሃዲያ | 7,604 | 6% | 46% | 3,490 | 5% |
| ቤንች ማጂ | 6,300 | 5% | 43% | 2,732 | 4% |
| ከፋ | 4,446 | 3.4% | 33% | 1,478 | 2.0% |
| ዳውሮ | 3,223 | 2.5% | 33% | 1,071 | 1.5% |
| ደቡብ ኦሞ | 3,134 | 2.4% | 43% | 1,358 | 1.9% |
| ጌደኦ | 1,501 | 1.1% | 30% | 445 | 0.6% |
| ሸካ | 1,364 | 1.0% | 40% | 542 | 0.7% |

| ዞን/ልዩ ወረዳ | ምርት | | % ለሽያጭ | የተሸጠ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (ቶን) | (%) | | (ቶን) | (%) |
| ኮንታ | 1,271 | 1.0% | 45% | 572 | 0.8% |
| አማሮ | 1,247 | 1.0% | 64% | 803 | 1.1% |
| ኮንሶ | 989 | 0.8% | 63% | 627 | 0.9% |
| ጉራጌ | 840 | 0.6% | 43% | 360 | 0.5% |
| ባስኬቶ | 651 | 0.5% | 59% | 382 | 0.5% |
| ስልጤ | 460 | 0.4% | 27% | 122 | 0.2% |
| የም | 296 | 0.2% | 50% | 147 | 0.2% |
| አላባ | 151 | 0.1% | 8% | 12 | 0.0% |
| ደራሼ | 90 | 0.1% | 61% | 55 | 0.1% |
| ቡርጂ | 78 | 0.1% | 55% | 43 | 0.1% |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 130,834 | 100% | 56% | 73,110 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446)

ከላይ እንደተገለፀው የምርት የግብይት ዘዴ በአርባምንጭ አካባቢ ያለው ከሌሎች አካባቢዎች የተለየ ነው፡፡ ልዩነቱ እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-27 በምርትና ግብይት መካከል ያለ ልዩነት**

| | አርባምንጭ | ሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|
| ምርት | በመስኖና በዝናብ<br>ለንግድ አገልግሎት | በዝናብ<br>የቤት ውስጥ ፍጆታ፣ ትርፍ ምርት ሽያጭ |
| ዝሪያ | ካቨንዲሽ፣ አጭሩ ካቨንዲሽ | በአብዛኛው የአካባቢ ነው |
| የአርሶአደሩ ማሽጫ ቦታ | መንገድ ዳር በመሰብሰብ<br>የሕ/ሥራ መጋዘን | ገበያ ቦታ |
| በሽያጭ ላይ ያሉ ሕ/ሥራ ማሕበራት | ዩኒያንና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት | የለም |



መንገድ ዳር መሰብሰቢያ ቦታ (አርባ ምንጭ)



የሙዝ ገበያ (ሃዳሮ)

የአርባምንጭ ሙዝ በሕ/ሥራ ማህበራትና በነጋዴዎች በአ/አበባ፣ ናዝሬት፣ መቀሌ ወዘተ.. ገበያዎች ይሸጣል፡፡ በአ/አባባ ገበያ ምርቱን ለመሸጥ ወኪሎችን የሚያሰማራ ሕ/ሥራ ማህበር አሉ፡፡ በአ/አበባ ያለው የጅምላ ነጋዴ ወኪሉን በአ/ምንጭ አስቀምጦ ምርቱን ይሰበስባል፡፡

አረንጓዴ ሙዝ ሰብስቦ በመጋዘን ለ2 ቀን በማስቀመጥ እንዲበስል ይደረግል፡፡ ወይንም በእንጨት ሣጥን በጋዜጣ በመሸፈን እንዲበስል ማድረግ ይቻላል፡፡ በማሰባሰብ ሂደት፣ በአያያዝና በማጓጓዝ ወቅት ብዙ የምርት ብልሽት ይከሰታል፡፡



በክፍል ውስጥ ማብሰል (አ/አበባ)




በእንጨት ሣጥን መብሰል (ሃዳሮ)

የአርባምንጭና የአ/አበባ ንግድ የዋጋ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ 50 ኩንታል በሚጭነው አይሱዙ የጭነት መኪና የትራንስፖርት ዋጋ 0.30 ብር በኪ.ግራም ነው፡፡ ከማንጎና ከአቮካዶ አምራቾች ዋጋ ጋር ሲነፃፀርና የዋጋ ልዩነት ዝቅ ያለ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-28 የሙዝ የዋጋ ሁኔታ (ከአርባምንጭ ወደ አ/አበባ)

| የንግድ ልውውጥ | ቦታ | ዋጋ | መለኪያ |
|---|---|---|---|
| አርሶአደር➔ ጅማላ ነጋዴ | በአ/ምንጭ መሰብሰቢያ ጣቢያ | 2.40 ብር በኪ.ግ | የሙዝ ዘለላ |
| ጅምላ ነጋዴ➔ ቸርቻሪዎች | አ/አበባ ጅምላ ነጋዴዎች | 3.10 ብር በኪ.ግ | የሙዝ ዘለላ |
| ቸርቻሪ ➔ ሸማቾች | አ/አበባ ችርቻሮ ሱቅ | 6- 7 ብር በኪ.ግ | ኪ.ግራም |

ምንጭ፡ የጃይካ ጥናት ቡድን፣ ከአ/አበባ ጅምላ ነጋዴዎች የተገኘው መረጃ መሠረት መጋቢት 12/ 2010 (እ.ኤ.አ)




| | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረ | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የዝናብ ሁኔታ በአርባ ምንጭ አካባቢ | | + | +++ | +++ | +++ | +++ | | ++ | ++ | +++ | +++ | |
| የዝናብ ሁኔታ ከጠ፣ ወላይታ፣ ሃዲያና ሲዳማ አከባቢ | | | +++ | +++ | +++ | ++ | +++ | +++ | +++ | +++ | + | |
| ጋሞ ጎፋ ዞን (አርባ ምንጭ) ( መስኖ፣ ካቨንዲሽ) | | | | | | | | | | | | |
| ከጠ፣ ወላይታ፣ ሃዲያና ሲዳማ ዞን (በዝናብ፣ የአካባቢ/ካቨንዲሽ) | | | | | | | | | | | | |

ምንጭ፡ ከወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እንደተሰማው

መሰብሰቢያ ወቅት | ከፍተኛ መሰብሰቢያ ወቅት

ምስል 3.1-14 የአምራቾች የሙዝ ዋጋ (2009 እ.ኤ.አ) እና ምርትመሰብሰቢያ ወቅት

አግሪ ቢዝነስና ንግድ ማስፋፊያ ኘሮግራም

አግሪ ቢዝነስና ንግድ ማስፋፊያ ኘሮግራም የግብርና ምርት የውጭ ንግድ ማስፋፋትና ለገበያ የሚያመርቱ አምራቾችና ላኪዎች እንዲሆኑ ይደግፋል። በደቡብ ክልል የአ/ምንጭ አካባቢ ከተመረጡ አካባቢዎችና አምራቾች አንዱ ነው። የሚከተሉት ድጋፎች በ2010 (እ.ኤ.አ) ተሰጥተው ነበር።

- ለገበያ አምራቾች የጠብታ መስኖ ቁሳቁሶች ተሠጥቷል።
- የገበያ ትስስር (ኢንቨስትመንት ማስፋፋት) ቺኩይታ የተባለ ዓለም አቀፍ የፍራፍሬ ኩባኒያ ወደ አ/ምንጭ አካባቢ የሙዝ እርሻ እንዲጎበኙ ተደርጉል።
- ትምህርታዊ ጉዞ፡ ወደ ካሜሩን፡ የሙዝ አምራቾችን ወደ ካሜሩን ሀገር በመላክ የውጭ ንግድ ሥራ እንዲጎበኙ ተደርጓል።

በቺኩይታ ኩባኒያ አማካይነት የመጀመሪያ የሙከራ (4-6 የሚደርስ ኮንቴነር) ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች ለመላክ በጥቅምት 2010 (እ.ኤ.አ) ታቅዶ ነበር። ነገር ግን አንዳንድ ተሣታፊ አምራቾችን ከመምረጥ ባለፈ ምንም የተሠራ ሪፖርት አልተሰማም።

በኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኤጀንሲ አማካይኝነት የጋሞ ጎፋ ዩኒየን ያደረገው ሙዝ ወደ ውጭ ሀገር መላክ እንቅስቃሴ

በኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኤጀንሲ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት በ2008 (እ.ኤ.አ) የተቋቋመ ሲሆን አትክልትና ፍራፍሬ ወደ ውጭ የሚልኩ ኩባኒያዎችን የውጭ ምንዛሪ ለማሣደግ እንዲያስችል ይደግፋል። የአ/ምንጭ አምራቾች ዩኒየን ሙዝ ወደ ሳውድ ዐረብያ ለመላክ በ2011 እና መጋቢት 2012 (እ.ኤ.አ) ድጋፍ አድርጉ ነበር። የሙዝ የውጭ ገበያ ውጤት በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል። የክልሉ የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ እንዚህን ላኪዮች በማስተባበርና በማሸግ ሥራ ዩኒየኑንና ሕ/ሥራ ማህበሩን በማሣ ላይ ድጋፍ ሰጥቷል።

**ሠንጠረዥ 3.1-29 የጋሞ ጎፋ የሙዝ ኤክስፖርት ውጤት**

| | ጊዜ | ሙዝ አቅራቢ | ውጪ ሀገር ላኪ | የተላከ መጠን | የተላከበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ታህሳስ 2011 (እ.ኤ.አ) | ጋሞ ጎፋ ዩኒያን | ጋሞ ጎፋ ዩኒያን | 1 ኮንቴነር (200 ኩንታል) | ሳውዲ አረቢያ |
| 2 | መጋቢት 2012 (እ.ኤ.አ) | ካንቻማ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማሕበር | ጋሞ ጎፋ ዩኒያን | 10 ኮንቴነር (2000 ኩንታል) | ሳውዲ አረቢያ |

ምንጭ: ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ እንደተሰማው

የማሸግ ሥራዎች በአ/ምንጭ ይከናወናሉ። የማሸግ ሥራ ሂደት 1) መጀመሪያ ማጠብ (ሙዝ በውሃ መንከር) 2) ሁለተኛ ማጠብ (በማጠራቀሚያ ውስጥ በእጅ ማጠብ)፣ 3) እንዲደርቅ ለተወሰኑ ደቂቃዎች መስቀል፣ እና 4) በኘላስቲክ ከረጢትና በካርቱን ማሸግ ናቸው። ምንም ዓይነት የፀረ-ፈንገስ ኬሚካል አይጠቀሙም። የማሸጊያ ማቴሪያል (ካርቱን ሣጥንና ኘላስቲክ ከረጢት) እና ሌሎችም መሣሪያዎች በኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኤጀንሲ የተደረጉ ድጋፎች ናቸው።

4) ፓፓዬ

የፓፓዬ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞንና በልዩ ወረዳ በሚከተለው ሁኔታ ተመልክቷል። ፓፓዬ በብዙ የክልሉ አካባቢዎች ይመረታል። ሆኖም የምርትና የገበያ ድርሻ አነስተኛ ነው። የአርሶአደሮች የሽያጭ መጠን ከሌሎች ፍራፍሬ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው።

ሠንጠረዥ 3.1-30 የፓፓያ ምርትና የገበያ ድርሻ በዞን

| ዞን/ልዩ ወረዳ | ምርት | | % ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (ቶን) | (%) | | (ቶን) | (%) |
| ኮንሶ | 2,937 | 16% | 29% | 853 | 22% |
| ቤንች ማጂ | 2,716 | 15% | 11% | 307 | 8% |
| ወላይታ | 1,993 | 11% | 21% | 413 | 11% |
| ጋሞ ጎፋ | 1,960 | 11% | 21% | 403 | 10% |
| ጉራጌ | 1,792 | 10% | 29% | 524 | 14% |
| ሲዳማ | 1,109 | 6% | 43% | 478 | 12% |
| ደቡብ ኦሞ | 984 | 5% | 24% | 238 | 6% |
| ስልጤ | 789 | 4.3% | 13% | 99 | 2.6% |
| ከፋ | 758 | 4.1% | 12% | 87 | 2.3% |
| ዳውሮ | 705 | 3.9% | 5% | 33 | 0.9% |
| ኮንታ | 675 | 3.7% | 16% | 108 | 2.8% |
| ሸካ | 630 | 3.4% | 1.3% | 8 | 0.2% |
| ከምባታ ጠምባሮ | 467 | 2.6% | 27% | 125 | 3.2% |
| አማሮ | 390 | 2.1% | 29% | 115 | 3.0% |
| ሃዲያ | 242 | 1.3% | 15% | 36 | 0.9% |
| ሌሎች | 128 | 0.7% | 23% | 30 | 0.8% |
| የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 18,274 | 100% | 21% | 3,858 | 100% |

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446)

የግብይት ዘዴ ከሌሎች የሚበላሹ አትክልቶች ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በወንዶ ገነት ሲዳማ ዞን የእንጨት ሣጥንና ከረጢት ምርት ለማጓጓዝ ያገለግላል፡፡

## 3.1.5 ሥራሥር እህሎች

### (1) እንሰት

ከታች ያለው ሠንጠረዥ እንደሚያሣየው የእንሰት ምርት በሁለት ክልሎች ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ እንሰት ድርቅ የመቋቋም ችሎታ አለው፤ በተጨማሪም ከፍተኛ ምርት አለው፡፡ የእንሰት ምርት በደቡብ ክልል በአብዛኛው ዞኖች ያለ ሲሆን ሲዳማ ዞን ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ የሽያጭ መጠኑም ቢሆን በሲዳማና በጌዲኦ ከፍተኛ ሲሆን ከ10% ይበልጣል፡፡ በአብዛኛው አርሶአደሮች ከሲዳማና ጌዲኦ ዞኖች በስተቀር እንሰት ለቤት ፍጆታ ይውላል፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-31 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የእንሰት ክልላዊና የዞን ምርት

| | ምርት | | ለሽያች | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ኢትዮጵያ | 825,350 | 100.0 | 8.75 | 72,218 | 100.0 |
| ትግራይ | የለም | -- | የለም | የለም | -- |
| አማራ | የለም | -- | የለም | የለም | -- |
| ኦሮሚያ | 229,748 | 27.30 | 8.88 | 20,401 | 28.25 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | 595,602 | 72.59 | 8.61 | 51,281 | 71.75 |
| በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ 9 ዋና አምራች ዞን/ል ወረዳ | | | | | |
| 1. ሲዳማ | 335,338 | 56.3 | 11.11 | 37,256 | 67.81 |
| 2. ከፋ | 89,377 | 15.0 | 7.02 | 6,274 | 11.42 |
| 3. ጌደኦ | 30,283 | 5.1 | 11.55 | 3,497 | 6.37 |

| | ምርት | | ለሽያች | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| 4. ሃዲያ | 29,007 | 4.9 | 7.21 | 2,091 | 3.81 |
| 5. ጋሞ ጎፋ | 16,473 | 2.8 | 8.03 | 1,322 | 2.41 |
| 6. ዳሮ | 16,040 | 2.7 | 5.53 | 887 | 1.61 |
| 7. ሸካ | 15,220 | 2.6 | 8.67 | 1,319 | 2.40 |
| 8. ከምባታ ጠምባሮ | 12,386 | 2.1 | 10.0 | 1,238 | 2.25 |
| 9. ጉራጌ | 10,800 | 1.8 | 4.98 | 537 | 0.98 |
| 10. ወላይታ | 10,257 | 1.7 | 5.00 | 512 | 0.93 |

ማስታወሻ: የ2004 ዓ/ም የሽያጭ መረጃ ስላለተገኘ የ2001 ዓ/ም ተውስዷል፡፡
ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2011/12 (እ.ኤ.አ), ቡለቲን 532

የእንሰት አብዛኛው ክፍል አግልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ቅጠሉ ዕቃ ለመጠቅለል ያገለግላል፡፡ ዋናው የእንሰት ክፍል ቆጮ ለመሥራት ሲጠቅም ቃንጫው ሥጋጃ ይሠራበታል፡፡ ሥሩ ይበላል አለያም ቆጮ ለመሥራት እንደጥሬ ዕቃ ያገለግላል፡፡ ቡልአ የሚባለው በእስታርች የበለፀገ ምግብ ከሥሩ ይሠራል፡፡ ቆጮ የሚሠራው የእንሰት ዋናው ክፍልና ሥሩ ተጨቅጭቆ በጉድጓድ ተቀብሮ እንዲብላላ ከ2-8 ሣምንት ከተቀመጠ በኂላ ነው፡፡ የጊዜ መርዘሙ በመሬት ላይ ካለው የአየር ፀባይና ከበላተኛው ጣዕም ጋር የተያይዞ ይወሰናል፡፡

እንሰት የማዘጋጀት ሂደት ሙሉ በሙሉ በሰው ጉልበት ይከናወናል፡፡ ዲራም የሚባል የእንሰት መላጫ ተሠርቶ ለሙከራ ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ማሽኑ በሚልጥበት ወቅት ቃጫው በጥርሱ ውስጥ በመግባት ሥራውን አስቸጋሪ እያደረገው ነው፡፡ እስክራፐር የሚባል ማሽን በሙከራ የቀረበ ሲሆን ከዲራም የተሻለ ቢመስልም ዋጋው ለአርሶአደሮች የሚቻል አይመስልም፡፡ የቡልአ መሸጫ ዋጋ ከፍ ያለ ነው፡፡ በሰው ጉልበት የሚሠራ የቡልአ መጭመቂያ የተሠራ ቢሆንም እስካሁን በአርሶአደሮች ተቀባይነት ያገኘ አይመስልም፡፡



እጅና እግር በመጠቀም የመፋቅ ሥራ ይሠራል፡፡ በእግር ቅጠሉ ሲያዝ ምግብ የሚሆነው ክፍል ይፋቃል፡፡ የውጭ ክፍሉ ቃጫ ይሆንና ለስገጃ ሥራ ያገለግላል፡፡



በሞተር የሚሠራ የታምቡር ዓይነት ማሽን ሆኖም ይህ ማሽን የሚበላውን የቆጮ ከፍልና ቃጫን አይለይም፡፡



ከሽያጭ በፊት የቆጮ ችርቻሪ ነጋዴዎች በትልቅ ቢላዋ ከቆጮ ጋር ያለውን ቃጫ ደጋግሞ በመቁረጥ ያለሰልሳሉ፡፡



ሀዋሣ ዩኒቨርስቲ የሚሽከረከር ብዙ መቁረጫ ቢላዋ ያለው ሠርተዋል፡፡ነገር ግን ተጠናቆ ሥራ ላይ አልዋለም፡፡

አርሶአደሮች ትርፍ ቆጮ ያመረቱትን ወደ አካባቢ ገበያ በአህያ በመጫን ወይም በሰው ትከሻ ያጓጉዛሉ፡፡ አብዛኛው የቆጮና የቡልአ ምርት ለቤት ፍጆታ የሚውል ሲሆን በተለይም ከሲዳማና ከጌዲኦ ዞን የሚመረተው በአ/አበባ ትልቅ ገበያ አለው፡፡ የእነዚህ አካባቢ ነጋዴዎች ቆጮና ቡልአ ከአካባቢ ገበያ በመሰብሰብ ወደ ከተሞች አካባቢ በጭነት መኪና ያጓጉዛሉ፡፡

የገበያ ዋጋ በተመለከተ ቆጮ ከመለኪያ 50 ኪ.ግራም ነው፡፡ በቀዬ/ማሣ ላይ 170 ብር፣ ጅምላ ሽያጭ 180 ብር፣ የችርቻሮ ዋጋ 200 ብር በሲዳማ አካባቢ (4 ብር በኪ.ግራም) ሲሆን የሚወሰነውም በቆጮው ጥራትና ጣዕም ላይ ተመስርቶ ነው፡፡

የቆጮና ቡልአ ዝግጅትና ግብይት ሂደቱ በባህላዊ የሰው ጉልበትና በማሽን ወይም መሣሪያ የሚከናወን ሲሆን እርካሽና ለአፈፃፀም ቀላል የሆነ ማሽኖች ገና አልተሠሩም፡፡ የእንሰት ማምረትና መሰብሰብ የተረጋጋ ሲሆን የቆጮና የቡልአ ገበያ ዋጋ ብዙ መዋዠቅ አይታይበትም፡፡

### (2) ስኳር ድንች

በኢትዮጵያ ደረጃ ኦሮሚያና ደቡብ ክልል ከፍተኛውን የስኳር ድንች አምራች አካባቢዎች ናቸው፡፡ በደቡብ ክልል ደረጃ ጋሞ ጎፋና ወላይታ ዞን ከፍተኛ አምራች አካባቢዎች ሲሆኑ አብዛኛው ምርት ለቤት ፍጆታ ይውላል፡፡ የሽያጭ መጠኑ በሲዳማና በባስኬቶ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ነው፡፡ የሽያጭ ዋጋ ዝቅተኛ መሆንና የትራንስፖርት ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ወደ አ./አበባ ገበያ ከደቡብ ክልል የሚቀርብ ምርት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በአርሶአደሮች የሚሸጠው ምርት በአካባቢው ለቤት ፍጆታ ይውላል፡፡ ምርቱ ከማሣ ወደ አካባቢ ገበያ የሚጓጓዘው በአህያ ወይንም በአህያ ጋሪ ሲሆን ወደ ከተሞች አካባቢ የሚጓጓዘው በጭነት መኪናዎች ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-32 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የስኳር ድንች ክልላዊና ዞናዊ ምርት**

| | ምርት | | ለሽያጭ | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ኢትዮጵያ | 682,281 | 100.00 | 11.27 | 76,893 | 100.0 |
| ትግራይ | የለም | - | - | - | - |
| አማራ | 2,136 | 0.31 | 19.20 | 410 | 1.0 |
| ኦሮሚያ | 248,114 | 36.37 | 12.05 | 29,898 | 39.0 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | 421,935 | 61.83 | 10.86 | 45,822 | 60.0 |
| ሌሎች | 10,096 | 1.47 | -- | -- | -- |

| | ምርት | | ለሽያች | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ 9 ዋና አምራች ዞን/ልዩ ወረዳ | | | | | |
| 1. ወላይታ | 136,952 | 33.20 | 1.46 | 1,999 | 4.0 |
| 2. ሲዳማ | 133,045 | 32.25 | 25.26 | 33,607 | 70.0 |
| 3. ጋሞመጎፋ | 108,551 | 26.31 | 8.08 | 8,771.0 | 18.0 |
| 4. ከምባታ ጠምባሮ | 9,218 | 2.23 | 4.24 | 391 | 1.0 |
| 5. ደቡብ ኦሞ | 7,206 | 1.75 | 17.61 | 1,269 | 3.0 |
| 6. ባስኬቶt | 5,844 | 1.42 | 20.28 | 1,185 | 2.0 |
| 7. ጌደኦ | 3,387 | 0.82 | 8.32 | 867 | 2.0 |
| 8. ከፋ | 2,406 | 0.58 | 8.30 | 200 | 0.1 |
| 9. አማሮ | 2,315 | 0.56 | 8.30 | 192 | 0.1 |
| 10. ሌሎች | 3,636 | 0.86 | 2.0 | 72 | 0 |

ማስታወሻ: የ2004 ዓ/ም የሽያጭ መረጃ ስላለተገኘ የ2001 ዓ/ም ተውስዷል፡፡

ምንጭ: ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2011/12 (እ.ኤ.አ), ቡለቲን 532

ድንች የሚዘጋጀው በመቀቀል ነው፡፡ ከረሜላ ወይንም ሌሎች ጣፋጭ ነገሮችን በመሥራት ዋጋ የመጨመር ሥራ በኢትዮጵያ አልታወቀም፡፡ ለምርት ከደረሰ በኂላ ለተወሰነ ጊዜ በአፈር ውስጥ እንደ ማከማቻ ይቆያል፡፡ የገበያ ዋጋ በተመለከተ 1.ኪ.ግራም በማሣ ላይ 0.70 ብር፣ ጅምላ ሽያጭ 0.80-0.90 ብር እና ብር 1.99 በሲዳማ ሸማቾች ዋጋ ነው፡፡ ከላይ የተገለፀው ዋጋ በምርት ጥራትና በምርት ወቅት ይወሰናል፡፡

(3) ጎደሬ

ጎደሬ የሚመረተው በደቡብ ክልል በተለይም በምዕራባዊ አካባቢ ነው፡፡ ለጎደሬ ምርት ምቹ አካባቢ ሞቃታማና እርጥበት ያለበት አካባቢ ነው፡፡ ቆላማ አካባቢ በምዕራብ ዞን ያሉ ሥፍራዎች ምቹ የምርት አካባቢዎች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-33 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የጎዳሬ ክልላዊና የዞን ምርት

| | ምርት | | ለሽያች | የገበያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ኢትዮጵያ | 300,324 | 100.00 | 4.89 | 14,686 | 100.00 |
| ትግራይ | - | | - | - | -- |
| አማራ | - | | - | - | -- |
| ኦሮሚያ | 36,983 | 12.3 | 2.8 | 1,036 | 7.0 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ | 263,136 | 87.6 | 5.36 | 14,104 | 93.0 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ 10 ዋና አምራች ዞን/ልዩ ወረዳ | | | | | |
| 1. ወላይታ | 62,295 | 23.8 | 4.91 | 3,059 | 24.3 |
| 2. ቤንች ማጂ | 35,167 | 13.4 | 6.78 | 2,384 | 18.9 |
| 3. ዳውሮ | 27,462 | 10.5 | 2.51 | 689 | 5.5 |
| 4. ጋሞ ጎፋ | 25,153 | 9.6 | 6.5 | 1,635 | 13.0 |
| 5. ከፋ | 22,954 | 8.8 | 4.56 | 1,047 | 8.3 |
| 6. ከምባታ ጠምባሮ | 21,579 | 8.2 | 5.47 | 1,180 | 9.4 |
| 7. ኮንታ | 19,299 | 7.4 | 5.01 | 967 | 7.7 |
| 8. ሃዲያ | 14,238 | 5.4 | 5.0 | 712 | 5.7 |
| 9. ደቡብ ኦሞ | 10,989 | 4.2 | 5.0 | 549 | 4.4 |
| 10. ሌሎች | 22,739 | 8.7 | 5.0 | 1,137 | 8.1 |

ማስታወሻ: የ2004 ዓ/ም የሽያጭ መረጃ ስላለተገኘ የ2001 ዓ/ም ተውስዷል፡፡

ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (በለቲን 446)

ከስኳር ድንች ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ የጎዳሬ የሽያጭ ዋጋ ዝቅተኛ በመሆኑና የትራንስፖርት ዋጋ ከፍተኛ ስለሆነ በአብዛኛው ለቤት ፍጆታ ይውላል፡፡ ርቀት ወደላቸው ትላልቅ ገበያዎች አይጓጓዝም፡፡ የምግብ ዝግጅቱ በመቀቀል ብቻ ሲሆን የሚጨምር ምንም ሌላ የሚሠራ ነገር የለም፡፡ የገበያ ዋጋ በተመለከተ በተመሳሳይ እንደ ስኳር ድንች 1 ኪ.ግ በማሣ 0.70 ብር፣ ጅምላ ሽያጭ 0.80-0.90 ብር እና ብር 1.00 በሲዳማ የሸማቾች ዋጋ ነው፡፡ ሆኖም ዋጋው ከምርት ጥራትና ከምርት ወቅት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

(4) ካሳቫ

ካሳቫ በዚህ ጥናት የሥራ አድማስ ስምምነት ላይ እንደተገለፀው ከተመረጡ ሰበሰሎች አንዱ ነው፡፡ ሆኖም በማዕከላዊ እስታትስትክስ ኤጀንሲ የተመዘገበ ምንም መረጃ አልተገኘም፡፡ እንደ ግብርና ቢሮ ባለሙያዎች ገለፃ የምርት አካባቢው ከስኳር ድንች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የገበያ ዋጋው ለቤት ፈጆታ 1 ኪ.ግራም 1.00 ብር ነው፡፡ የካሳቫ ምርትና አመጋገብ ሁኔታ ከሌሎች አጎራባች ሀገሮች ጋር ሲነፃር እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የካሳቫ ዱቄት ከጤፍ ዱቄት ጋር ተዋህዶ እንጀራ ስለሚሠራበትና ጣዕሙንም እየተገነዘቡ ስለመጡ ካሳቫ ማምረት ሥራ እየጨመረ መጥቷል፡፡

በደቡብ ክልል የግብርና ቢሮ መረጃ መሠረት በ2009 (እ.ኤ.አ) የካሳቫ ምርት 184348 ቶን ሲሆን ከዚህ ውስጥ የ94858 ቶን ወይም 51% በወላይታ ዞን የተመረተ ነው፡፡ አብዛኛው የካሳቫ ምርት ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚውል ሲሆን ከ10-20% የሚሆነው ለገበያ ይቀርባል፡፡ ደረቅ ካሳቫ በከተሞች አካባቢ ተፈጭቶና ከጤፍ ጋር ተቀላቅሎ እንጀራ የጋገርበታል፡፡ በእንጀራ ውስጥ ከ10-20% የካሳቫ ዱቄት ሲሆን በአንዳንድ ገቢያቸው ዝቅ ያሉ ቤተሰብ እስከ 50% ካሳቫና 50% ጤፍ ተደርጉ ይሠራል፡፡ ይህም የሚሆንበት የካሳቫ ዱቄት ዋጋ ከጤፍ ዋጋ ከሁለት ዕጥፍ በላይ ስለሚቀንስ ነው፡፡

የካሳቫ ምርት ከመጀመሪያው ማለት ማምረት፣ ማድረቅ፣ መፍጨትና ማብሰል ሂደት ውስጥ የአሴት መፍጠር ሥራ የሚከተሉት ጉዳዮች መሻሻል አለባቸው፡፡

1) አርሶአደሮች አግባብ ያላቸው ካሳቫ ማድረቂያ ዕቃዎች ስለሌሏቸው ጥሬ ካሳቫውን በረዥሙ (በግምት 3 ሴንቲ ሜትር) በመክተፍ የላይኛውን ቆዳ ልጦ በመሬት ላይ በመዘርጋት በፀሐይ ያደርቁታል፡፡ በዚህ ዓይነት የደረቀው ካሳቫ የጥራት ደረጃ በጣም የተለያየ ነው፡፡ ምክንያቱም በመሬት ላይ በሚደርቅበት ጊዜ ብዙ የተለያዩ ጥራት የሚያጓድሉ ነገሮች ስለሚነካካና ሻጋታ ስለሚፈጥር ማለት ነው፡፡
2) በምርት አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች ከንፅህና ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ስለሚያውቁ ደረቅ ካሳቫ የመመገብ ልምዳቸው በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ዝቅተኛ ጥራት ያለው የደረቀ ካሳቫ ወደ አ/አበባ ገበያ ይጓጓዛል፣ ከዚያም ተፈጭቶ ከጤፍ ዱቄት ጋር እንጀራ ይሠራበታል፡፡
3) በሶዶ ከተማ የሚገኙ የካሳቫ ነጋዴዎች በወር እስከ 50 ቶን የሚደርስ ምርት ያገኛሉ፡፡ ነገር ግን የተጠቀሰውን ፍላጐት የሚያሟላ የጥራት ደረጃን ለማምጣት ቁጥጥር አያደርጉም፡፡ ስለዚህ በነዚህ ነጋዴዎች የሚታየው የገበያ እድገት ዝቅተኛ ነው፡፡ የደረቅ ካሳቫ ገበያ ጀማሪ እንደመሆናቸው የነዚህን ነጋዴዎች ጥቅም ሁኔታ ለማሻሻል የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡ በተለይም በቅርብ ምርት ከጀመሩ ክልሎች ለምሳሌ አማራ እና ትግራይ ጋር ሲነፃሩ፡፡
4) የደረቅ ካሳቫ ምርት በሚገኙባቸው አካባቢዎች በተለይም በወላይታ ዞን ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ ተጠቃሚዎች ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚገዙዋቸው የደረቅ ካሳቫ ነው፡፡
5) ገበሬዎች (አምራቾች) የደረቅ ካሳቫ በመሸከም ወደ አካባቢ ገበያዎች ይወስዳሉ፡፡ ከዛም ለነጋዴዎችና ለተጠቃሚዎች በቀጥታ ይሸጣሉ፡፡ የደረቅ ካሳቫ የዋጋ ሁኔታ የጤፍ እና የበቆሎ ዋጋን ተከትሎ በየጊዜው ይለዋወጣል፡፡

6) የደረቅ ካሳቫ የሚሸጡ በሶዶ ከተማ የሚገኙ ነጋዴዎች እስከ 50 ቶን የሚደርስ የደረቀ ካሳቫ በየወሩ ይይዛሉ። በሶዶ ከተማ 10 የደረቀ ካሳቫ ነጋዴዎ ይገኛሉ። የጥራት ደረጃን በምንም መንገድ ቁጥጥር ስለማያደርጉ አዳዲስ የደረቀ ካሳቫ ገበያዎችን ለህብረተሰቡ ጥቅም እንዲውል ከማድረግ አንፃር እድገት እንዲኖር አስተዋፅኦ አላደረጉም።
7) ከጐረቤት ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር የኢትዮጵያ የካሳቫ መጠን በጣም አነስተኛ ነው። በተጨማሪም ተጠቃሚዎች የደረቀ ካሳቫ ለእንጀራ ግብአት መሆን እንደሚችል ያላቸው ግንዛቤ ትንሽ ነው። ንፅህናው የተጠበቀን የደረቀ ካሳቫ ለማግኘት ያለው የገበያ ፍላጐት ደግሞ ከፍተኛ ነው።
8) የላይኛው ቆዳ ከተላጠና ከተከተፈ በኋላ በፍጥነት ይደርቃል፤ ጥራቱ ይሻሻላል እንዲሁም የመሸጫ ዋጋው ይጨምራል። ነገር ግን አነስተኛና ንፁህ የደረቀ ካሳቫ የሚያመርቱ ነጋዴዎች ቁጥር አነስተኛ ነው። ይህም የሆነው ካሳቫውን በቢለዋ ለመክተፍ ለአርሶአደሮቹ አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ነው።
9) አርሶአደሮቹ ቀላል የካሳቫ መክተፊያ ማሽንና የኘላስቲክ ማሸጊያዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ይፈልጋሉ። በመሆኑም ለዚህ ሁኔታ የአመራር አካላት ድጋፍ አስፈላጊ ነው።



በትልቅ ተከተፎ በፀሐይ እንዲደርቅ በፕላስቲክ ሸራ የተዘረጋ ካሳቫ



አርሶአደሮች ወደ አካባቢ ገበያ በአህያ ገሪ ሲያጓጉዙ



ከአካባቢ ገበያ የተሰበሰበ የካሳቫ ምርት በኦፋ ወረዳ ወላይታ ዞን



ለጥራቱ ምንም ሳይታሰብበት በመጋዘን ውስጥ የተቀመጠ ካሳቫ

ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ በግብርና ቢሮ ኤክስቴንሽን ዋና የሥራ ሂደት የተዘጋጀ የካሳቫ ምርት መረጃ ነው። ሆኖም የሽያጭና የገበያ ድርሻ አልተገኘም።

**ሠንጠረዥ 3.1-34 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የካሳቫ ምርት**

| | የምርት የሸፈነው መሬት (ሄ/ር) | ምርት (ቶን) | ምርት (%) | በአንድ ሄ/ር የተገኘ ምርት |
|---|---|---|---|---|
| 1. ወላይታ | 8,042 | 94,858 | 51.43 | 11.8 |
| 2. ጋሞ ጎፋ | 4,283 | 33,373 | 18.09 | 7.8 |
| 3. ዳውሮ | 1,374 | 28,717 | 15.57 | 20.9 |
| 4. ቤንች ማጂ | 754 | 14,307 | 7.76 | 19.0 |
| 5. ደቡብ ኦሞ | 676 | 5,408 | 2.93 | 8.0 |
| 6. ጉራጌ | 471 | 4,239 | 2.30 | 9.0 |
| 7. ባስኬቶ | 210 | 3,150 | 1.71 | 15.9 |
| 8. ከምባታ ጠምባሮ | 21 | 406 | 0.22 | 19.3 |
| 9. ሌሎች | 0 | 0 | 0.00 | 0 |
| የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ድምር | 15,831 | 184,348 | 100.00 | 15.96 |

ማስታወሻ: በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የተዘጋጀው የምርት መረጃ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲከሚያዘጋጀው አሀዝ ከፍ ያለ ነው።
ምንጭ፡ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

### 3.1.6 ሌሎች ሰብሎች

#### (1) ሸንኮራ አገዳ

3 ትላልቅ የስኳር ፋብሪካዎች በኢትዮጵያ ስኳር ያመርታሉ። እነዚህ ቀደም ሲል በመንግሥት የተያዙ ፋብሪካዎች ወንጂ፣ ማታሃራና ፊንጫ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ናቸው። የጥሬ ዕቃዎች የሚቀርቡት በአቅራቢያቸው ካለው ስፋፊ የሸንኮራ አገዳ እርሻዎች ነው።

በአርሶአደሮች የተመረተው ሸንኮራ አገዳ ለቤት ተጠቀሚዎች ይውላል እንጂ ወደ ፋብሪካዎች አይሄድም። በኢትዮጵያ የሸንኮራ ጭማቂ አይሠራበትም። ሸንኮራ መጭመቂያ ተሽከርካሪ ማሽን በሌሎች ሸንኮራ አገዳ ባለባቸው እሲያ ሀገሮች የተለመደው በኢትዮጵያ የለም። የሸንኮራ አገዳ ጭማቂ በመቀቀል ቡኒ ስኳር (ጃጋሪ) መሥራት አልተለመደም። በኢትዮጵያ የተለመደው የሸንኮራ አገዳ አመጋገብ አኘኮ መምጠጥ ብቻ ነው።

**ሠንጠረዥ 3.1-35 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የሸንኮራ አገዳ ክልላዊ ምርት**

| | ምርት | | ለሽያጭ | የሽያጭ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | % | % | ቶን | % |
| ኢትዮጵያ | 559,404 | 100 | 39.44 | 220,629 | 100.00 |
| ትግራይ | - | | - | - | -- |
| አማራ | 102,338 | 18.29 | 60.13 | 61,536 | 27.89 |
| ኦሮሚያ | 212,991 | 38.07 | 42.38 | 90,266 | 40.91 |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ | 243,047 | 43.45 | 38.63 | 93,889 | 42.56 |
| በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ 9ኙ ዋና አምራች ዞን/ልዩ ወረዳ | | | | | |
| 1. ሲዳማ | 108,891 | 47.45 | 57.6% | 62,721 | 57.20 |
| 2. ሃዲያ | 28,653 | 12.49 | 42.3% | 12,106 | 11.04 |
| 3. ወለይታ | 19,160 | 8.35 | 32.6% | 6,254 | 5.70 |
| 4. ጌደኦ | 14,413 | 6.28 | 54.1% | 7,792 | 7.11 |
| 5. ካፋ | 13,903 | 6.06 | 16.9% | 2,355 | 2.15 |
| 6. ቡርጂ | 13,846 | 6.03 | 36.0% | 4,986 | 4.55 |
| 7. ምንባታ ጠምባሮ | 12,034 | 5.24 | 39.6% | 4,765 | 4.35 |
| 8. ጋሞ ጎፋ | 8,213 | 3.58 | 54.1% | 4,440 | 4.05 |
| 9. አማሮ | 5,455 | 2.38 | 58.7% | 3,202 | 2.92 |
| 10. ሌሎች | | 5.91 | -- | -- | -- |

ማስታወሻ: በሰፋፊ የመንግሥት እርሻዎች ተመርቶ ለፋብሪካዎች የሚቀርብ የሸንኮራ አገዳ ምርት አልተካተተም
ምንጭ፡ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ አጀንሲ፣ የግብርና ናሙና ደሰሳ ጥናት 2008/09 (እ.ኤ.አ), ጥራዝ VII (ቡለቲን 446

የሸንኮራ አገዳ ምርት ከሌሎች የሰብል ዓይነቶች ልዩ የሚያደርገው ሸንኮራ አገዳ ለገበያ ተብሎ የሚመረትና የሚቀርብ መሆኑ ነው። ሲዳማ ዞን ከፍተኛ የሸንኮራ አገዳ አምራች አካባቢ ሲሆን የሽያጭ ድርሻውም ከጠቅላላ ምርት ከ50% በላይ ነው።

በሲዳማ ዞን ወንዶ ገነት ወረዳ ዋነኛው የሸንኮራ አገዳ አምራች አካባቢ ሲሆን የማያቋርጥ የመስኖ ውሃ ስላለ ዓመቱን በሙሉ ያመርታሉ። አርሶአደሮች ከአንድ የሸንኮራ አገዳ ግንድ 3 ጊዜ ይቆርጣሉ። የምርት ወቅት ተብሎ የሚታወቅ ጊዜ የለም። ምርቱ ከተሰበሰበ በኂላ ለቀጣዩ ጊዜ አስኪደርስ ከ11 እስከ 12 ወር ይቆያል።

አነስተኛ አርሶአደሮች ከቤት ውስጥ ፍጆታ በላይ የሆነውን ምርት ወደ አካባቢ ገበያ ወስደው ይሸጣሉ። ለገበያ ሸንኮራ አገዳ የሚያመርቱ አርሶአደሮች ለነጋዴ የሚሸጡት ከመቆረጡ በፊት በቁሙ ነው። ነጋዴዎች ከአርሶአደሮቹ ጋር ከተስማሙ በኂላ ከአርሶአደሩ መሬት ምርቱን ለመሠብሰብ ሠራተኞችን ያዘጋጃሉ። ከተሰበሰበም በኂላ የሸንኮራ እገዳው ይከመርና በመንገድ ዳር ይከማቻል። ከዛም በጭነት መኪናዎች ላይ ይጫንና ወደ አ/አበባ፣ ናዝሬት፣ ሞያሌና ሌሎች አካባቢዎች ይጓጓዛል።

አርሶአደሮች በእርሻው ያለውን የሸንኮራ አገዳ የስሩን ቁጥርና ደረጃ ነጋዴዎች ለግዥ ስምምነት ከመምጣታቸው በፊት ያውቁታል። ነጋዴዎች በእርሻ ያለውን የሸንኮራ አገዳ ከስምምነት በፊት ይቆጥራሉ። የመሸጭያ ጥራት ላይ ተመስርቶ የሚለያይ ሲሆን ከ2-3 ብር ለአንድ ትልቅ ሸንኮራ አገዳ ይሆናል። ጥራቱ ጥሩ ከሆነ አርሶአደሩ ከአንደ ሄክታር ማሣ 150000 ብር ያገኛል።
ከነጋዴው የተራረፈውን የሸንኮራ አገዳ ቅጠል አርሶአደሩ ለእንስሳት መኖነት ይጠቀምበታል።

በሀዋሣ አካባቢ የተለመደው ለአንድ 2.5 ሜትር ርዝመት ለአለው የሸንኮራ አገዳ በማሣ ውስጥ አንድ ብር ሲሆን፤ በጅምላ እስከ ሁለት ብር ይሸጣል። በ25 ሳንቲ ሜትር የተቆራረጠ የሸንኮራ አገዳ ደግሞ ሀዋሣ ከተማ በጐዳና ላይ ሻጮች አሉ።



የሸንኳራ አገዳ መሰብሰቢያ ቦታ። ነጋዴዎች መጓጓዣ ያዘጋጃሉ።



አርሶአደሮች ከማሣ ወደ አካባቢ ገበያ በአህያ ጋሪ ያጓጉዛሉ።

(2) **ቅመማ ቅመም፡ ዝንጅብል**

የተለያዩ የቅመማ ቅመም አይነቶች ለምሳሌ በርበሬ[2]፣ ዝንጅብል፣ እርድ፣ በርበሬ፣ ኮረሪማ፣ እና የመሳሰሉት በደቡብ ክልል ይመረታሉ። ከነዚህም ቅመማ ቅመሞች መካከል ዝንጅብልና በርበሬ ከአርሶአደሩ የገቢ ምንጭ እና ካለው የምርት መጠን አንፃር ሲታዩ ከፍተኛ ቦታ ይይዛሉ።

[2] የበሰለ ምጥሚጣ በጥናት ቡድኑ የሥራ አድማስ ስምምነት መሠረት በአትክልት ክፍል ይመደባል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የደቡብ ክልል 99% የምርት ድርሻ (እንደ ወጪ ምርቶች ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ የደቡብ ክልል የቅመማ ቅመም የውጭ ገበያ 2004 እ.ኤ.አ) አለው፡፡ የ2008/09 (እ.ኤ.አ) የዞኖች የምርት ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ዝንጅብል በከምባታ ጠምባሮ እና በወላይታ ዞኖች ይመረታል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-36 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የዝንጅብል ምርት (2008/2009 እ.ኤ.አ)**

| ዞን | ምርት | | ምርት |
|---|---|---|---|
| | ሄ/ር | ቶን | ቶን/ሄ/ር |
| ወላይታ | 9,783 | 90,833 | 9.3 |
| ከምባታ ጠምባሮ | 6,494 | 93,376 | 14.4 |
| ዳውሮ | 2,331 | 34,140 | 14.6 |
| ሃዲያ | 270 | 3,240 | 12.0 |
| ሸካ | 520 | 7,800 | 15.0 |
| ጋሞ ጎፋ | 148 | 1,407 | 9.5 |
| ድምር | 19,546 | 230,796 | 11.8 |

ምንጭ : የኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

የሚከተለው ሠንጠረዥ በከምባታ ጠምባሮ ዞን በ3 የምርት ወቅቶች (/2006-2009 እ.ኤ.አ) ያለውን የዝንጅብል ምርት ያሳያል፡፡ የማሣ ስፋት ተመሳሳይ ቢሆንም በየዓመቱ የምርት መጠን መቀነስ ታይቷል፡፡ ለምርቱ መቀነስ ምክንያት ምን እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡

**ሠንጠረዥ 3.1-37 በከምባታ ጠምባሮ ዞን የዝንጅብል ምርት (2006/07- 2008/09 እ.ኤ.አ)**


| | የታረሰ መሬት (ሄ/ር) | | | ዓመታዊ ምርት (ቶን | | | ምርት (ቶን በሄ/ር) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወረዳ | 2006/07 | 2007/08 | 2008/09 | 2006/07 | 2007/08 | 2008/09 | 2006/07 | 2007/08 | 2008/09 |
| ቃጫ ቢራ | 2,306 | 2,233 | 2,360 | 59,956 | 52,694 | 33,040 | 26.0 | 23.6 | 14.0 |
| ሃዳሮ ጡንጦ | 3,812 | 3,790 | 3,986 | 71,436 | 53,060 | 51,021 | 18.7 | 14.0 | 12.8 |
| ጠምባሮ | 2,149 | 2,200 | 1,913 | 25,788 | 27,500 | 20,081 | 12.0 | 12.5 | 10.5 |
| ድምር | 8,267 | 8,223 | 8,259 | 157,180 | 133,254 | 104,141 | 19.0 | 16.2 | 12.6 |

* ዓመታዊ ምርቱ የእርጥብ ዝንጅብል ነው፡፡
ምንጭ፡ የከምባታ ጠምባሮ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ፡፡

በከምባታ ጠምብሮና ወላይታ ዞኖች የዝንጅብል ተከላ በታህሣሥ ወር ይጀመራል፡፡ አርሶአደሮች ዝንጅብል እርጥብ እያለ ወይም አድርቀው ለገበያ ያቀርባሉ፡፡ የምርት መሰብሰቢያውም በዚያው ዓይነት የተለያየ ነው፡፡ ለእርጥብ ዝንጅብል ሽያጭ ምርቱ የሚሰበሰበው ከተከላ በኂላ በ7 ወር ነው፡፡ ለደረቅ ዝንጅብል አርሶአደሮች የተሻለ ምርት መጠን ለማግኘት ከ9-12 ወር ከተከላ በኂላ አቆይተው ለገበያ ያቀርባሉ፡፡ ምርቱን የዋጋ ሁኔታ እየተከታተሉ ከማሣቸው ይሰበስባሉ፡፡ ሁለት ዓይነት ዝሪያዎች "ሶልቮ" እና አርጌማ" የተባሉት በእነዚህ አካባቢዎች ይመረታሉ፡፡ ቮልቮ የተባለው አዲስ ዝሪያ ሲሆን መጠኑ ትላልቅና ምርቱም ከአርጌማ ዝሪያ የበለጠ ነው፡፡ "አርጌማ" የተባለው ዝሪያ በአካባቢው ለረዥም ጊዜ የሚታወቅና በመጠኑ አነስተኛና በምርቱም ዝቅተኛ ነው፡፡ ሆኖም የአካባቢው ህ/ሰብ ለቤት ፍጆታ ይህንኑ ይመርጣሉ፡፡ ምርቱ ሲደርቅ ክብደቱ "ቮልቮና" 25% ሲሆን የአርጌማ 33% ነው፡፡

የአርሶአደሮች በግብይት ዘዴ በተለምዶ የሚታወቀው ለደረቅና ለእርጥብ ዝንጅብል መሸጫ ቦታ በገበያ ውስጥ ተሰጥቶ ነው፡፡ የሃዳሮ ገበያ ማዕከል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ቁልፍ የእርጥብና ደረቅ ዝንጅብል መሰብሰብያ ቦታ ነው፡፡ አልፎ አልፎ የተወሰነ በወላይታ ዞን የሚመረተው ዝንጅብል ወደ ሃዳሮ መሰብሰቢያ ማዕከል ይመጣል፡፡ ሌሎች የዝንጅብል መሰብሰብያ ማዕከላት እንደ ሺንሺቾ፣ ሙዱላ እና ጡንጦ በከምባታ ጠምባሮ ዞን አሉ፡፡ ሺንሽቾ ቁልፍ የእርጥብ ዝንጅብል መሰብሰቢያ ማዕከል ነው፡፡ በወላይታ ዞን አርካ ገበያ አንዱ የምርት መሰብሰብያ ማዕከል ነው፡፡

በሃዳሮ ከተማ እስከ 10 የሚደርሱ የተመዘገቡ ምርት ሰብሳቢዎች የደረቅ ዝንጅብል ከአርሶአደሮችና ከአንስተኛ ሰብሳቢዎች ገዝተው ለአ.አበባ ገበያ ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ በታች በፎቶግራፉ (በስተቀኝ) እንደሚታየው ብዙ አርሶአደሮች ጥቂት ዝንጅብል ለቤት ውስጥ ቁሳቁስ ለመግዛት ገንዘብ ለማግኘት ይሸጣሉ፡፡ እነዚህ አነስተኛ ምርት ሰብሰሳቢዎች ከአርሶ አደሮች ገዝተው የስበሰቡትን ለትላልቅ ሰብሳቢዎች ይሸጣሉ፡፡ የገበያ ፍሰቱ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡




**ምስል 3.1-15 በከምባታ ጠምባሮ ዞን የዝንጅብል (እርጥብ/ደረቅ ምርት) የግብይት ሰንሰለት**



በአካባቢ ነጋዴዎች ምርት ሲሰበሰብ (ሃዳሮ ገበያ)


አርሶአደሮች አነስተኛ መጠን ለሽያጭ ሲያቀርቡ (ሃዳሮ ገበያ)

በከምባታ ጠምባሮ ዞን አምባሪቾ የሕ/ሥራ ዩኒየን እና 11 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት በዝንጅብል ግብይት ለመሣተፍ በ2010 (እ.ኤ.አ) መክረው/ለመሞከር አስበው ነበር፡፡ ሆኖም እስከ አሁን ሪፖርት የተደረገ ነገር የለም፡፡ ምንም የተመዘገበ የደረቀ ዝንጅብል የአህዝ መረጃ ባለመኖሩ የፍጆታ ወይንም የፍላጐት መጠን ለማወቅ አልተቻለም፡፡ በሀገሪቱ የዝንጅቢል ገበያ መሸጫ መስመሮች ሀ) እንደ ምግብ የሀገር ውስጥ ፍጆታ (ለሻይ፤ ከቅመም

ጋር በማቀላቀል)፣ ለ) ለመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች በውጭ መላክ፣ እና ሐ) እንደ የኢትዮጵያ ቅመማቅመም መጭመቂያ ፋብሪካና ቅመማ ቅመምና መድሃንነት ያላቸው ቅጠላቅጠል መጭመቂያ ፋብሪካ ናቸው፡፡ በደቡብ ክልል ትላልቅ የደረቀ ዝንጅብል ነጋዴዎች የሉም፡፡ ትላልቅ ነጋዴዎች ያሉት በአ.አበባ ነው፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ 10 ደረቅ ዝንጅብል ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች አሉ፡፡ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች ከፍ ያለ የጥራት ደረጃ ያለውን ምርት ይፈልጋሉ ይባላል፡፡ (የውጭ ላኪዎችና የዝንጅብል አስፈላጊ ዘይትና ራይዘን ጭማቂ ፋብሪካዎች በሚመለከት በጥናቱ ቡድን ቀጣይ ጥናት መካሄድ አለበት)፡፡

የእርጥብ ዝንጅብል ዓመታዊ የዋጋ መወዠቅ በ2009 (እ.ኤ.አ) ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ በ2009 ዋጋው በመጠኑ እያደገ ሄዶ ከፍተኛ የደረሰው በህዳር ወር ነው፡፡ የምርት መጠንና የዋጋ ሁኔታ ግንኙነት ለማየት ስንፈልግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ይህም የሚሆንበት የዋጋ ሆኔታ በፍላጐት መጠን የሚወሰን ይመስላል፤ የደረቀ ዝንጅብል በተመለከተ ተከታታይ የዋጋ መረጃ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ የዋጋ ከፍ ዝቅ ማለትና ለዚህ ምክንያቱ ምንድር ነው የሚለውን ለማወቅ እርግጠኛ መሆን አንችልም፡፡ ሆኖም አንዳንድ የሃዳሮ ከተማ ዝንጅብል ነጋዴዎች እንደገለፁልን የደረቀ ዝንጅብል የዋጋ ሁኔታ በፍላጐት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ነው፡፡ ምናልባት የውጭ መላክ ሥራ በአብዛኛው የአምራቾች ዋጋ የሚወሰን ይመስላል፡፡




ምንጭ ማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጄንሲ፣ ወርሃዊ የአምራቾች ዋጋ ሪፖርት ጥር-ታሕሳስ 2009 (እ.ኤ.አ)

| ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| >>>> | | | | | | | | | | | >>> |
| XXXX | XXXX | XX | | | | | | XXX | XXXX | XXXX | XXXX |

>>>> ተከላ/መዝራት xxxxx ምርት መሰብሰብ

**ምስል 3.1-16 የአምራቾች የእርጥብ ዝንጅብል ዋጋና የተከላ ወቅት (2009 እ.ኤ.አ)**

የረዥም ጊዜ የዋጋ ሁኔታ ሲታዩ ለእርጥብና ለደረቀ ዝንጅብል ከ2003/04 ጀምሮ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ በ2006/07 (እ.ኤ.አ) ዋጋው በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል፡፡

ሠንጠረዥ 3.1-38 የሃዶሮ ገበያ የዝንጅብል ዋጋ ከ2003/04-2007/08 (እ.ኤ.አ)

| ዓመት (እ.ኤ.አ) | ደረቅ | እርጥብ | የደረቅ ዝንጅብል የተሰላ ዋጋr | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 25% * | 33% * |
| 2003/2004 | 130 — 180 | 27 — 30 | 108 — 120 | 82 — 91 |
| 2004/2005 | 100 — 130 | 20 — 25 | 80 — 100 | 61 — 76 |
| 2005/2006 | 80 — 110 | 15 — 20 | 60 — 80 | 45 — 61 |
| 2006/2007 | 40 — 60 | 10 — 15 | 40 — 60 | 30 — 45 |
| 2007/2008 | 45 — 75 | 12 — 17 | 48 — 68 | 36 — 52 |

መለኪያ: ብር ለ17 ኪ.ግራም (ፈረሱላ) * 25% ለ"ቮልቮ" እና 33% ለ"አርጋሜ" ደረቅ ዝንጅብልን ለመገመት መጠቀም ይቻላል፡፡

ምንጭ: ከምባታ ጠምባሮ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ፣ የዝንጅብል ምርትና ግብይት መጋቢት 2010 (እ.ኤ.አ)

<u>የደረቅ ዝንጅብል ድህረምርት ሥራ ሂደት</u>

ሙሉ በሙሉ ለማየት ይቻላል ዝንጅብል የሚደርቀው በመሬት ላይ በማስጣት ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢ በአውራጐዳና ላይ ሲሰጣ እንስሳትና ሰዉ እየረጋገጠው ያልፋል፡፡ ከንፅህና አኳያ አሁን እየተሠራ ያለው የማድረቅ ሥራ ለሰው ፍጆታ/ለምግብነት የሚደገፍ አይደለም፡፡

በከምባታ ጠምባሮ ዞን አሚፕ የዝንጅብል ድህረምርት አያያዝ ለማሻሻል የሥልጠና ኘሮግራም በ2009/10 (እ.ኤ.አ) አካሂዶ ነበር፡፡ የአመፐ ሥልጠና ኘሮግራም አርሶአደሮችን ቀለል ያለ በእንጨት የሚሠራ ቆጥ ዝንጅብል ለማጠብና ለማድረቅ እንዲጠቀሙ አስተምሯቸዋል፡፡ ሆኖም አሚፐ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የማጠቢያ ዘዴ በሥልጠናው አቅርቦ አላሳየም፡፡ ከታች በፎቶግራፍ የታየው የወረዳ ግብርና ልማት ባለሙያዎች ዝንጅብል ለማጠብ የሚያስችል የሙከራ ቁሳቁስ ያዘጋጁት ሲሆን ብዙ መሻሻል ያለባቸው ነገሮች አሉ፡፡ የማጠቢያ ዘዴ ሊቀርብ ከሚችለው የውሃ መጠንና ባህሪይ ጋር ተያይዞ ዲዛይን መደረግ አለበት፡፡ እንዲሁም ቁሳቁሱ የሚሠራበት ለአርሶአደሮች ማዕከላዊ በሆነ ቦታ ሲፈልጉ መጠቀም በሚችሉበት ዓይነትና በቀላሉ መጠቀም እንዲችሉ ዲዛይን መደረግ አለበት፡፡



በከተማ አካባቢ በመንገድ ላይ የተሰጣ ዝንጅብል



በወረዳ ግብርና ባለሙያዎች ለአርሶአደሮች የተዘጋጀ ዝንጅብል ማጠቢያ ቁሳቁስ

ንፁህና የደረቅ ዝንጅብል ለማዘጋጀት ችግሩ በትንሽ ደረጃ ይጀምራል፡፡ እንደ ከምባታ ጠምባሮ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ ለታጠበ ዝንጅብል ዋጋ እጥፍ በማደግ (90-100 ብር በ17 ኪ.ግራም ለታጠበ ሲሆን 45-50 ብር በ17 ኪ.ግራም ላልታጠበ ዝንጅብል) ባለፈው የምርት ዘመን ተሸጧል፡፡

ከትላልቅ ገዢዎች በአ/አበባ ካሉት ጋር ያለው ግንኙነት በጣም ደካማ አልያም የለም ማለት ይቻላል፡፡ የከምባታ ጠምባሮ ዞን ባለሙያዎች በሪፖርታቸው እንደገለፁልን በእርግጥ የዝንጅብል ምርት የሚረከቡን ማን እንደሆኑ አናውቃቸውም (መጋቢት 2010 እ.ኤ.አ.የዝንጅብል ምርትና ገበያ ሪፖርታቸው) ብለዋል፡፡ አሁን ያለውን የዝንጅብል ማድረቂያ አሠራር ለመቀየር ለአምራቾች የተሻለ ዋጋ ለሚሠሩት ሥራ መክፈል ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አገላለጽ አስተማማኝ የሆነ የንግድ ግንኙነት በአምራቾችና በአካባቢ ነጋዴዎች/ላኪዎችና ለፋብሪካዎች ጋር መፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡
በሃደሮ ጡንጦ ወረዳ የወረዳ አስተዳደር ዝንጅብል በመሬት ላይ ያለ ምንም ከሥር የተደረገ ንጣፍ ሳይጠቀሙ ማድረቅን አግዷል፡፡ ከዚህ የተነሣ በሃዳሮና አካባቢው ያሉ አርሶአደሮችና የአካባቢው ነጋዴዎች የቀርከሃ ቅርጬ እና ኘላስቲክ ሸራ መጠቀም ጀምረዋል፡፡

አንድ የግል ኩባንያ (ወደ የመን ሀገር ዝንጅብል የሚልክ) በሃዳሮ ከተማ ዝንጅብል ማጠቢያና አርትፊሻል ማድረቂያ አቋቁሞ ነበር፡፡ ሆኖም በ2010/11 እና 2011/12 (እ.ኤ.አ) የምርት ወቅት ምንም ሥራ አልጀመረም፡፡


አዲስ የተቋቋመ ማጠቢያ


ማድረቂያ (በጥቅል ዓይነት)

## 3.2 ድህረምርት ማቀነባበርና እሴት መጨመር

### 3.2.1 ብርዕና ጥራጥሬ

በደቡብ ክልል የእርሻ ምርቶች እሴት መጨመርና የጥራት ማሻሻል በሚነሳበት ጊዜ “የጥራት ደረጃ” “የዱቄት ፋብሪካ” እና “የምግብ ማቀነባበር” ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባው ሶስት ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በአሁኑ ወቅት ያለው እሴት መጨመርና የጥራት ማሻሻል አፈፃፀምና ግንዛቤ እንደ ሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### (1) የአሁኑ ጊዜ ያለው የጥራት ቁጥጥር ሁኔታ

አርሶአደሩ ምርቱን ከሰበሰበ በኂላ የማድረቅ፣ የመወቃት እና የማበጠር ተግባር ያከናወናል፡፡ አብዛኛው አርሶአደር ምርቱን ከመወቃቱ በፊት በፀሐይ ያደርቀል በማሳ ውስጥ ወይንም በመኖሪያ ቤቱ አባባቢ ምርቱን ሳይወቃ መሬት ላይ ይከምራል ወይንም አስጥቶ ያቆያል፡፡ ከዚያ በኂላ በበሬ፣ በአህያ ወይንም በእንጨት ወይንም በቀርካሃ ብትር በመምት ምርቱ የመወቃት ሥራ ይሠራል፡፡ የበቆሎ ምርትን በተመለከተ በሰው ጉልበት በእጅ የቀርከሃ አንጓዋ በመጠቀም አልያም የገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከል በሠራው በቆሎ በወቃያ መሣሪያ ይወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የተሠራ በቤንዚን ኃይል የሚሠራ የበቆሎ መውቂያ መሣሪያ በብዛት ይገኛል፡፡

አርሶአደሩ፣ የአካባቢ ምርት ሰብሳቢዎችና ነጋዴዎች ስለምርት ጥራት ቁጥጥር የላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው ይባላል፡፡ “ ጥራት” የሚለው ቃል ከማወቅ በዘለለ የጥራት ቁጥጥር ምን እንደሆነ የሚያውቁ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የጥራት ማሻሻያ ዘዴን እና ተፈላጊ የጥራት ደረጃን ማሟላት የሚችልበትን ሁኔታ የሚገነዘቡ ነጋዴችና አርሶአደሮች ውስን ናቸው፡፡

አርሶአደሩ የተወሰነ ባዕድ ነገር እና የጥራት ጉድለት ቢኖርም የተቻላቸውን ያህል ምርት መሸጥ ይፈልጋል፡፡ አርሶአደሩ ባዕድ ነገሮች፣ የጥራት ጉድለቶችን፣ ያልበሰሉ የእህል ዘርና እብቅ በማስወገድ ንፁሁ ምርት ተመሳሳይ መጠንና ጥሩ እይታ ይለውን ሰብል ቢያዘጋጁም በደህና ዋጋ የሚገዛው የለም፡፡ ስለሆነም ባዕድ ነገር የተደባለቀበት፣ በደንብ ያልደረሰ፣ እብቅና የተለያየ ከለር ያለውን እህል እንዲሸጡ ይገደዳሉ፡፡

ነጋዴዎችና የአባባቢ ሰብሳቢዎች በአብዛኛው ተመሳሳይ የሆነ ዋጋ ጥራቱም ለአልተጠበቀ ምርት ይከፍላሉና አንዳንድ ጊዜ የተለያየ ዝሪያ ያላቸው ሰብሎችን በደንብ ያልደረቁና ከፈተኛ አርጥበት ያላቸው ሰብሎችን ለጥራት ተገቢውን ትኩረት ሳይሰጡ ይገዛሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የገዙበትን ምርት በአንድ ላይ በመደባለቅ በፀሐይ በማድረቅ እንጥበቱ ያስወግዳሉ፡፡ በመቀጠልም እህሉን በጆንያ ከተው በመመዘን ለከፍተኛ ነጋዴዎችና እክስፖርተሮች ለመሸጥ ያዘጋጃሉ፡፡

አርሶአደሩ የአግሮ ኬሚካል ቅሪት የሚያስከትለውን ጉዳት በአግባቡ ስለማይረዱ ምርቶቻቸውን ከኬሚካል ንክኪ አርቀው አይጠብቱም፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖችም የእህል ምርቱን ከማዳበሪያ ኬሚካል ሳይለዩ በአንድ መጋዘን ያከማቻሉ፡፡

ትልቅ አቅም ያለው የዱቄት ፋብሪካ ሁለት ዓይነት ምርት ነው የሚያመርተው፤ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ዱቄት፡፡ በአሁኑ ወቅት እነዚህ የዱቄት ፋብሪካዎች ምርት የሚፈልግ ሸማች ቁጥር በደንብ አላደገም፡፡ የዱቄት ፋብሪካዎችን የተሻለ ጥራት ያለው ምርት ቢያመርቱም ይህ ሁኔታ ወደፊት እንደሚቀጥል ይገመታል፡፡ ከፍተኛ ጥራት ላለው ምርት ፍላጐት ከሌላ ጠንካራ የጥራት ቁጥጥር አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ፋብሪካዎች በቤት ውስጥ ፍጆታ ለማሟላት

ይሠራሉ፤ የተገዛው እህል ከአበጠሩ በኋላ አይደለም የሚፈጩት፡፡ ለቤት ውስጥ ፍጆታ ስለሆነ የሚያመርቱ የጥሬ ዕቃ ጥራት ቁጥጥርን አይፈልጉም፡፡

(2) አዲሱ የጥራት ቁጥጥር እንቅስቃሴ

በግብርና ምርት ግብይት ሥርዓት ውስጥ የምርት ጥራት ደረጃን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ግብይቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ የውጭ ሀገር ንግድ እና የዓለም ምግብ ፕሮግራም የሚካሄዱት ግብይቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ የንግድ ልውውጥ ሥራ የምርት ጥራት ቁጥጥር ማካሄድ የግድ ይሆናል፡፡ የጥራት ደረጃ ቁጥጥር በመስፈርትነት ከሚያያቸው የእርጥበት መጠን፣ የተሠባበረ ዘር፣የተደባለቀ ሌላ እህል ዘር፣ ባዕድ ነገር፣ የእህል መልክ፣ በበሽታና ተባይ የተጠቃ፣ የሻገተ የብዕር ሰብልና ጥራጥሬ፣ እና የስንዴ ዘር ልስላሳ/ጠንካራ በማለት መለየት ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የድቄት ፋብሪካ በእይታ ብቻ ከሚያካሄዱት የጥሬ ዕቃ ቁጥጥር ውጪ ስንዴ ሲገዙ የሚያደርጉት ሌላ ነገር የለም፡፡

1) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግብይት

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቡና ብቻ ሳይሆን ከበጨረታ ሂደቱ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ቦሎቄ፣ አተርና ሰሊጥን ያገበያያል፡፡ በመሣሪያና በእይታ የሁሉም ምርት ናሙና በመውሰድ ደረጃ ቁጥጥር ያደረጋሉ፡፡

2) የውጭ ሀገር ግብይት

በኢትዮጵያ የብዙ የግብርና ምርት ውጤቶች የጥራት ደረጃ መቆጣጠሪያ መስፈርቶች አሉ፡፡ የውጭ ሀገር ግብይትን በተመለከተ የግብርና ምርት ውጤቶች የጥራት ደረጃ ግልጽ መሆን አለበት፡፡ የውጭ ሀገር ላክ ነጋዴዎች ዓለም አቀፍ የግብርና ምርቶች የጥራት ደረጃ እና የክብደት መለኪያ ሚዛን ጡጥጥር ግንዛቤና ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

የግብርና ምርት ውጤቶች ወደ ውጭ ሀገር በሚላኩበት ወቅት ከኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃ ባለስልጣን የተሠጠ የጥራት ደረጃ ሴርቴፍኪት ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ የወጪ ግብይት ደንብ የግብርና ምርቶችን የኢትዮጵያ ደረጃ ሴርቴፍኬትና የፋብሪካው የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃ ባለሥልጣን ሴርቴፍኬት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የግብርና ምርቶች የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃ ባለሥልጣን በየዓመቱ ቁጥጥር አድርጐ ፈቃድ በሰጣቸው ፋብሪካዎች በሚገኝ ማበጠሪያ/ማጣሪያ ማሣሪያ ተበጥሮ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ የጥራት ደረጃ እና ለምርቱ የተጠውን ደረጃ ለማሟላት ይህ ሁኔታ እንዲሟላ ይፈለጋል፡፡ ስለዚህ የውጭ ሀገር ላኪዎች የኢትየጵያ እህል ገበያ ድርጅትን ጨምሮ ከፍተኛ አቅም ያለው የምርት ማበጠሪያና ማቀነባበሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ወደ ኬንያ ጥራጥሬ የሚልኩ ነጋዴዎች በተመለከተ የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃ ባለሥልጣን ሰርቴፍኬት ከእህል በራሳቸው ማበጠሪያ ከበጠሩ በኋላ ማግኘት ይችላሉ፡፡

3) የዓለም የምግብ ፕሮግራም ግብይት

በምዕራፍ 2 ቁጥር 2.4.2 እንደተመለከተው የዓለም የምግብ ፕሮገራም አካል የሆነው ግዥ ለዕድገት የእህል ምርቶች ከአንስተኛ አርሶአደሮች ከታህሣሥ 2009 (እ.ኢ.አ) ጀምሮ በቀጥታ እየገዛ ነው፡፡ ይህንኑ ተግባር በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በሐምሌ 2010 (እ.ኢ.አ) ጀምሯል፡፡

በግዥ ለዕድገት የግዥ ኮንትራት ውል ስምምነት ሠነድ የግብርና ምርት ጥራት ቁጥጥር ተመልክቷል፡፡ የሕ/ሥራ ዩኒያኖች የዓለም ምግብ ፕሮግራም የጥራት ደረጃን ለማሟላት ምርታቸውን በተገቢው መንገድ ማበጠር ይኖርባቸዋል፡፡ የዓለም ምግብ ፕሮግራም የግዥ

መጠኑ ከፍተኛ ስለሆነ ተፈላጊውን የምርት ጥራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሟላት የማበጠሪያ ማሣሪያ በመጠቀም የመለየትና ጥራቱን የማስጠበቅ ሥራ ሊካሄድ ይገባል።

ለዚሁ ተግባር በኢትዮጵያ 15 ሕ/ሥራ ዩኒየኖች የተመረጡ ሲሆን ከነዚሁ 8 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ይገኛሉ። የዓለም ምግብ ፕሮግራም/ግዥ ለዕድገት ተፈላጊው የጥራት ደረጃ እንዲጠበቅ ለእነዚህ 15 የሕ/ሥራ ዩኒየኖች የተለያዩ ማሽንና መሣሪያዎች እንደ በቆሎ መፈልፈያ፣ እህል ማበጠሪያ፣ ተንቀሳቃሽ ጆንያ ማሸጊያ፣ ማጠቢያ ሽራ፣ የተባይ መከላከያ መርጫ እና የጥራት መቆጣጠሪያ መሣሪያ በጥቅምት 2011 (እ.ኢ.አ) ሰጥቷል።

### (3) የዱቄት ፋብሪካ እንቅስቃሴ

ቀደም ሲል ለብዙሀኑ ሸማቾችን የሚያቀርቡ ትላልቅ የዱቄት ፋብሪካዎች መንግሥት ያስተዳድራቸው ነበር። በአሁኑ ጊዜ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚሠሩ ለንገድ ሥራ የተዘጋጁ ትላልቅ የዱቄት ፋብሪካዎች በትላልቅ ከተሞች አካባቢ እየተስፋፉ ነው። በሌላ በኩል በገጠሩ አካባቢ ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚሆን ስንዴ ገብስ የሚፈጩ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ወፍጮ ቤቶች የገኛሉ። እነዚህ ወፍጮ ቤቶች ለሚሰጡት አገልግሎት ክፍያ ይጠይቃሉ። እንደ ማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት 2828 ወፍጮ ቤቶች በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ይገኛሉ።

በሀዋሣ ከተማ ወደ 20 የሚሆኑ ወፍጮ ቤቶች ገበያ በሚገኝባቸው ሁለት አካባቢዎች እህል የመፍጨት ሥራ ይሠራሉ። ከእነዚህም አንዳንዶቹ ጥራጥሬና በርበሬ ይፈጫሉ። የሚፈጨው እንደ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ገብስ የመሳሰሉት ሰብሎች ከወፍጮ ቤቶች ወይንም ከአካባቢ ገበያዎች ይሸመታሉ። የእህል ሰብሉ የተገዛው ከወፍጮ ቤቶችና ማህበራት ከሆነ የወፍጮ አገልግሎት ክፍያ ብር 15.00 በኩንታል ሲሆን ከግል ነጋዴዎች ከሆነ ብር 30 ብር በኩንታል ነው። ጥራጥሬ ከመፍጨት በፊት የማበጠር ሥራ ይህንኑ በሚያከናውኑ ሠራተኞች ይከናወናል። ለዚሁ ሥራ ለጤፍ ብር 10 በኩንታል ይከፈላል። ጤፍን በተመለከተ በአንድ ኩንታል 10-15 ኪ.ግ ሩዝና ሌሎች ሰብሎች ይደባለቃሉ። በኤልክትሪክ ኃይል የሚሠራ ወፍጮ አንድ ኩንታል ጤፍ 10-30 ደቂቃ በአለው ጊዜ ይፈጫሉ። የአንድ ወፍጮ ቤት (/2-3 መፍጫ ያላቸው) የመፍጨት አቅም በአማካይ 3-5 ቶን በቀን ሲሆን እንደ አህል ወፍጮ ብዛትና የሥራ ሰዓት ሊለያይ ይችላል።

የዚህ አይነት ወፍጮ ቤት በየትኛውም የኢትዮጵያ የገጠር ከተሞች ይገኛል። የጤፍ ዱቄት እያንዳንዱ ቤተሰብ በሚፈልገው ሁኔታ ከጤፍ ጋር በሚደባለቀው የእህል ዓይነትና መጠን ይለያያል። ከስንዴ በስተቀር ለሌሎች የእህል ዓይነት በስፋት የሚሠራ የዱቄት ፋብርካ የለም።

ስንዴን በተመለከተ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/፣ ኦሮሚያ ክልል አርሲና ባሌ ለሚገኙ የዱቄት ፋብሪካዎች የሚያስፈልገው ጥሬ የዕቃ (ስንዴ) የሚሸመተው ከነጋዴዎች፣ ጅምላ ሻጮችና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ነው። የተመረተው ዱቄት ለዳቦ፣ ማኮሮኒ/ፓስታ እና ቡስኩት ለመሥራት በጥሬ ዕቃነት የዱቄት ፋብሪካዎች ይሸጣል። በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የተወሰኑ የግል ትላልቅና አንድ የመንግሥት የዱቄት ፋብሪካዎች እየሠሩ ይገኛሉ። የእነዚህ ፋብሪካዎች ምርት ለሰፊው ሸማች የሚቀርቡ ከመሆኑም ባሻገር አንዳንድ የዱቄት ፋብሪካዎች ለራሳቸው ሞኮኖሪና ፓስታ እንዲሁም ብስኩት ለሚያመርቱ ፋብሪካዎች በጥሬ ዕቃነት ይቀርባሉ። የሚቀጥለው ምስል በሀዋሣ የሚገኘው የብስኩት ፋብሪካን ያሳያል።


ብስኩት የመፈረክነት መስመር


የብስረኩት ማብሰያ ታናል

የግብርና ምርት ውጤቶች የእሴት መጨመርና የጥራት ቁጥጥር ተግባራዊ በማድረግ ምሳሌ የሚሆን እንተርኘራዝ እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡ ሆሳዕና ከተማ ከሚገኙት ሕ/ሥራ ዩኒየኖች አንዱ የሆነው "ሊቻ ሃዲያ ሕ/ሥራ ዩኒየን በቀን 80 ቶን የማምረት አቅም ያለው የተሟላ የዱቄት ፋብሪካ አቋቁሟል፡፡ ፋብሪካው ቻይና ሠራሽ የሆኑ 8 ወፍጮ እና 2 ትልቅ መጠን ያላቸው ገይሮ-ሺፍተስ አሉት፡፡ የዱቄት ፊብሪካው ሥራውን ከግንቦት 2009 (እ.ኢ.አ) ጀምሯል፡፡ የሚከተለው ምስል የሊቻ ሃዲያ ሕ/ሥራ የኒየን የዱቄት ፋብሪካ የማምረቻ አካላትን ያሳያል፡፡


ትልቅ መጠን ያለው ተሽከርካሪ ወፍጮ


ትልቅ መጠን ያለው ገይሮ-ሺፍተስ

የዱቄት ፋብሪካ 2 ዓይነት (ደረጃ 1 እና 2) እንዲሁም የስንዴ ፉርሽካ ያመርታል፡፡ ዱቄቱ በ5, 10, 25 እና 50 ኪ.ግራም ከታጀገ በኂላ በቀጥታ ሆሳዕና ከተማ አ/አበባ፣ ጅማ እና ናዝሬት ለሚገኙ የችርቻሮ ነጋዴዎች በእርካሽ ዋጋ ይሸጣል፡፡ የስንዴ ፉርሽካ በመኖነት ለወተት ላሞች እርባታ ይሸጣል፡፡ ዩኒየኑ ለዳቦ መጋገሪያ ቤቶች፣ ለዩኒቨርስቲዎች፣ ለሆስፒታሎችና ማረሚያ ቤቶች በቀጥታ ዱቄቱን በዝቅተኛ ዋጋ ያቀርባል፡፡ ዩኒየኑ የራሱ የሆነ የምግብ ማቀናበሪያ እና የእንስሳት መኖ ማዘጋጃ ለመሥራት ዕቅድ አለው፡፡

### (4) ፋሚክስ/ሲኤ.ቢ እና ሩተፊ

በኢትዮጵያ ውስጥ ገይሮ-ሺፍተስ የግል አምራቾች አሉ፡፡ ገይሮ-ሺፍተስ ከተቆላ በቆሎ እና አኩሪ አተር እንዲሁም ቫይታሚን ሚኒራል በመደባለቅ የተዘጋጀ ነው፡፡ እነዚህ አምራቾች ገበያውን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር ለዓለም የምግብ ፕሮግራምና ለዩኒስኤፍ ይሸጣሉ፡፡ ቀጥሎ የተመለከተው ምስል በአዲስ አበባ የሚገኘው ገይሮ-ሺፍተስ ማምረቻ የግል ኩባንያ ያሳያል፡፡



*መቀበያ /ማበጥሪያ/መቁያ መሥመር*



*መፍጨት/ መደባለቂያ/ማሸጊያ መስመር*

ከነዚህ አምራቾች መካከል አንዱ አዲስ አበባ በሚገኘው የግል ኩባንያ ተጨማሪ ኢንቨስትሜንት በማድረግ ትቅም ላይ ለመዋል ዝግጁ የሆነ አልሚ ምግብ (ሩተፈ) ማምረት ጀምሯል፡፡ ለፋብካው የሚያስፈልገው መሣሪያ ሙሉ በሙሉ የተገዛው ከውጪ ሀገር ሲሆን ማሸጊያ ቁሳቁስ፣ ባይታሚንና ሚኔራሎች ከውጪ ሀገር የገባሉ፡፡ በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግለው ኦቾሎኒ ብቻ ነው ከሀገር ውስጥ የሚቀርበው፡፡

የፋብሪካ ግንባታ፣ አቀማመጥና መገልገያዎቹ የኤችሲሲፒ ዝርዝር መስፈርት ያሟላ ነው፡፡ ይህም የሆነ አልሚ ምግቡ በተለየ ሁኔታ የሚቀነባበር ምግብ ሲሆን የንፀህናና ሃይጅን ደረጃው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ በመሆኑ ነው፡፡ ከዓለም የምግብ ፕሮግራም እና ዩኒሴፍን ከመሳሰሉ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ድጋፍ ምግብ የማቀነባበር ሥራ ለማካሄድ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡

የግሉ ዘርፍ ድህረምርት አያያዝ በምግብ ማቀነባበር እየተሠማሩ በሄዱ ቁጥር ቀስ በቀስ የነጋዴዎች የአርሶአደሮች የጥራት ደረጃ ማሻሻል ላይ ተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳል፡፡ በመሆኑም የግብርና ምርት የጥራት ማሻሻል በመስፋፋት የሀገር ውስጥ የውጪ ሀገር ምግብ አቀነባባሪዎች ፍላጐት ማርካት ይቻላል፡፡

### 3.2.2 የፍራፍሬና አትክልት ዘርፍ

#### (1) በኢንድስትሪ ደረጃ የፍራፍሬና አትክልት ማቀነባበር

በሀገሪቱ በባህላዊ መንገድ የተቀነባበረ ፍራፍሬና አትክልት ምርት እጥረት አለ፡፡ በሀገሪቱ የፍራፍሬና አትክልት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ በደንብ አልዳበረም፡፡ እስከ 2007 /እ.ኢ.አ/ በሀገሪቱ ውሰጥ 5 የፍራፍሬና አትክልት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ነበሩ፡፡ ከጥሎ የተመለከተው ሠንጠረዥ የ5ቱን ፋብሪካዎችንና በጥናቱ ወቅት የተገኙ የሌሎች ፋብሪካዎች ስም፣ አድራሻና ዋና ዋና የምርት ውጤቶቻቸውን ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.2-1 የታወቁ የፍራፍሬና አትክልት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች/ቢዝነስ**

| የፋብሪካው ስም | አድራሻ | ባለቤትነት | ምርት | ሎሎች |
|---|---|---|---|---|
| በ2007 (እ.ኤ.አ) 5 ፋብሪካዎች ነበሩ | | | | |
| ኤልፎራ መልጌ ወንዶ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ *1 | መልጌ ወንዶ ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ | የግል (አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ) | ቲማቲም ድልህ፣ የተላጠ ቲማቲም ለጦር ኃይል | 25 ቶን በቀን (24 ሰዓት.) |
| ማርቲ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | መርቲ ኦሮሚያ | የመንግሥት (የላይኛው አዋሽ (አግሮ ኢንዱስትሪ) | ቲማቲም ድልህ፣ የብርቱካን ማልማላት | |

| የፋብሪካው ስም | አድራሻ | ባለቤትነት | ምርት | ሎሎች |
|---|---|---|---|---|
| የአዋሽ ወይን ፋብሪካ *2 | አዲስ አበባ | የመንግሥት | ወይን | 5.2 ሚሊዮን ሊትር በዓመት (2007/08 እ.ኤ.አ) |
| ግሪን ስታር የምግብ ኮባኒያ | ደብረዘይት ኦሮሚያ | የግል | በቆርቆሮ የታሸገ አትክልት | |
| ጎንደር ምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ | ጎንደር አማራ | የግል | የቲማቲም ድልህ | |
| በጥናቱ 6 ፋብሪካዎች/ቢዝነስ ተገኝተዋል | | | | |
| እስጢፋኖስ ሀይሉ መላኩ | አዲስ አበባ | የግል | | |
| ግሪነር ኃ/የተ/የገ/ማህበር | አዲስ አበባ | የግል | የተቀነባባረ አትክልትና ፍራፍሬ | |
| ናስር ግራኝ ብርቱካን ፋብሪካ | አዲስ አበባ | የግል | ብርቱካን ጭማቂ | |
| | አዲስ አበባ | የግል | ብርቱካን ጭማቂ | |
| ሪኪያ ነጋሽ ብርቱካን ጅውስ ፋብሪካ | አዲስ አበባ | የግል | ብርቱካን ጭማቂ | |
| ሽልካን ምግብና መጠጥ | | የግል | የተቀነባባረ አትክልትና ፍራፍሬ | |

*1: መልጌ ወንዶ ምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ቀደም ሲል በመንግሥት ባለቤትነት ሥር ነበረ፡፡
*2: 3 የወይን ፋብሪካዎችን ያጠቃልላል፡ ስማቸውም ልደታ፣ መካኒሳ እና አዲስ ከተማ ይባላል፡፡
ምንጭ: ኤልያስ አበበ፣ በኢትዮጵያ የተቀናጀ የፍራፍሬ ማቀነባበር አዋጭት ቅንት፣ ሐምሌ 2007 (እ.ኤ.አ)

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በሲዳማ ዞን መልጌ ወንዶ በሚባል ቦታ ብቸኛው ኤልፎራ መልጌ ወንዶ የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ይገኛል፡፡ ፋብሪካም ቀደም ሲል በመንግሥት ይዞታሥር ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ፋብሪካው ለጦር ኃይል የሚሆን የቲማቲም ድልህና ቲማቲም ያመርታል፡፡ ፋብሪካውን ሲያጋጥሙት ከነበሩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የብረት ጣሳ አቅርቦት በሀገሪቱ ውስጥ ባለመኖሩ ከወጪ ሀገር የሚመጡ ውድ መሆን
- በተረጋጋ ዋጋ ትኩስ ቲማቲም ዓመቱን በሙሉ የማግኘት ችግር፡፡ ቲማቲም ማቀነባበር ብዙን ጊዜ ከታህሣሥ እስከ ግንቦት በአለው ጊዜ ይቋረጣል፡፡ ይህም የሚሆነው በዚህ ወቅት የቲማቲም ዋጋ ማቀነባበሪ ፋብሪካው አትራፊ ሊሆን ከሚችልበት ዋጋ (ብር 1.60 በ1 ኪ.ግ) በላይ ስለሚሆን ነው፡፡ የተረጋጋ ዋጋ እንዲኖር ፋብሪካው በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን ዱሮ ላንጋኖ አርሶአደሮች ሕ/ሥራ ዩኒየን ጋር ውል ገብቶ እየሠራ ይገኛል፡፡
- የፋብሪካው የጥራት ፍላጐት ከነጋዴዎች ፋላጐት ያተለየ ነው፡፡ ፋብሪካው ቀይ የበሰለ ቲማቲም ሲገዛ ነጋዴዎት ቀይ የበሰለ ቲማቲም አይገዙም፡፡

### (2) በጐጃ ኢንድስትሪ ደረጃ የሚካሄድ የፍራፍሬና አትክልት ማቀነባበር

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከፍራፍሬና አትክልት ምግብ የማቀነባበር ልምድ በኢትዮጵያ የተለመደ አይደለም፡፡ ስለሆነም አነስተኛ የምግብ ማቀነባበሪያ በደንብ አላደገም፡፡ በጥናቱ ወቅት ሀዋሣና ወላይታ የሚንቀሳቀስ አንድ የአርንጓዴ በርበሬ ዳታ የሚያዘጋጅ አነስተኛ የምግብ ማቀነባበሪያ ተገኝቷል፡፡

አነስተኛ ፍራፍሬ ማቀነባበርን በተመለከተ ኢኮፒያ (የኢትየጵያ ምርት ኢትዮጵያ) የሚባል ኩባንያ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ እየሠራ ይገኛል፡፡ የኢኮፒያ ዝርዝር ሥራና ተግባር እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

ኢኮፒያ ኃ/የተ/የግል ማህበር የተቋቋመውም በ2005 (እ.ኤ.አ) ሲሆን ዋናው መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ይገኛል። የበላይ ኃላፊና ሥራ አስኪያጅ በጀርመን ነዋሪ ይሆኑ ኢትዮጵያዊ ሴት ናቸው። ኢኮፒያ በኦርጋኒክ ምርቶች ላይ ይሠራል። ኢኮፒያ የግል ድርጅትም ሲሆን ራሱን እንደ ማህበራዊ ድርጅት ይቆጥራል። በኩባኒያው ድህረገጽ ለ2 ሚሊዮን የኢትዮጵያ አርሶአደሮች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ምግብ በማቀነባበር የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥና በኢትዮጵያ ልማት በመሳተፍ እንዲችሉ ያግዛል።

በአሁኑ ጊዜ በአጠቃላይ የ54 ዓይነት የምርት መስመር ይገኛል። ፍራፍሬና አትክልት ላይ የተመሠረቱ የምርት ውጤቶች እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

- ኦርጋኒክ ማልማላት፡ ከማንጎ፣ ዘይቱን፣ አናናስ፣ ፕላም፣ ፓፓያ፣ ብርቱካን፣ ወዘተ እና ድብልቅ የሚዘጋጅ
- የደረቀ ፍራፍሬ (በፀሐይ የደረቀ)፡ አናናስ፣ ፕላም
- ጭማቂ፡ አናናስ፣አፕል፣ ወዘተ ..
- ከሱካር በተዘጋጀ ጣፋጭ ሽሮፕ የተዘፈዘፈ የፍራፍሬ ቁርጥራጭ፡ አፕል፣ ማንጎ፣ አናናስ፣ ፕላም
- ጣፋጭ ሽሮፕ /መጠጥ/፡ አፕል፣ ማንጎ፣ አናናስ፣ ፕላም
- ወይን፡ ገና በምርት ዝግጅት ላይ ያለ
- ፒክልስ፡ አረንጓዴ አተር፣ ካሮት
- ሌሎች፡ ማር፣ የታሸጉ ቅመማ ቅመምና ዕፅ፣ ሻይ ቅጠል /ነጭ ሣርና ጦስኝ ወዘተ ../
  - ኦርጋኒክ ይሁንና ማረጋገጫ ሴርቲኬት ያልተሰጠው
  - የምርት መነሻ ኮድ (ለእያንዳንዱ ምርት በእጅ የተጻፈ) በቅርቡ እየተዋወቀ ይገኛል።

ከተቀነባበረ ምርት በተጨማሪ ኢኮፒያ የፍራፍሬ ሽያጭም ያካሄዳል። ዋነኛ የመሸጫ ቦታ ሱፐር ማርኬትና ሁቴሎች ናቸው።

<u>የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ዘዴ</u>

የኢኮፒያ ጨንቻ እና ጩኮ በተከራየው ቤት የራሱ የሆነ የምግብ ማቀነባበሪያ መገልገያዎች አሉት። ይህ ማቀነባበሪያ መገልገያ በአሰቡት አካባቢ የኢኮፒያ ለብዙ አርሶአደሮች ስለምግብ ማቀነባበር ሥልጠና ይሰጣል። በመቀጠልም ፍራፍሬ ማቀነባበር ሥራ እንዲሠሩ የተወሰነ ጉበዝ ሰዎችን ይቀጥራል።

የፍራፍሬ ማቀነባበር ዘዴውም ቀላል ሲሆን ለቤት ውስጥ ምግብ በሚዘጋጅበት ሁኔታ በአነስተኛ ደረጃ የሚካሄድ ሲሆን ምንም አይነት ማሽን ጥቅም ላይ አይውልም።

ጨንቻና ጭኮ የሚገኙ ማቀነባበሪያ ቦታዎች ተለይተው ለዚሁ ተግባር የተሠሩ ቤቶች አይደሉም። ስለሆነም ወደፊት የምግብ ደህንነትና ንፅህና ከማረጋገጥ አኳያ ተገቢው ዲዛይን ተሠርቶ የማሻሻያ ሊደረግባቸው ይገባል።

በጥሬ ዕቃነት ለፍራፍሬ ማቀነባበር የሚያስፈልጉ ወይንም ለሽያጭ የሚውሉ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን ኢኮፒያ ከሕ/ሥራ ማህበራት ጋር ውል በመግባት ግዥ ይፈጽማል። ስልጠና በተመለከተ ኢኮፒያ ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንደ ወርልድ ቪዥንና ኤስ.ኦን.ቪ እንዲሁም በየአካባቢ ያሉትን ዩኒቨርስቲዎችን ይጠቀማል።

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የሥራ ቦታ (እስከ 2010 እ.ኤ.አ)

| ቦታ | የፍራፍሬ ዓይነት | የሥራው ድርሻ/የተፈጠረ እሴት ሰንሰለት |
|---|---|---|
| ጨንቻ ጋሞ ጉፋ ዞን | አፕል ፕላም | የማቀነባበሪያ መገልገያዎችና ሠራተኞች ተሟልተው ይገኛሉ። ከጨንቻ የደጋ ፍራፍሬ አምራቾች ሕ/ሥራ ማህበር ጋር የሥራ አጋርነት ተመሥርቷል። |
| ጩኮ ሲዳማ ዞን | አናናስ | የማቀነባበሪያ መገልገያዎችና ሠራተኞች ተሟልተው ይገኛሉ። ከቱሶ፣ ጋሞቤላ እና ደቢቾ አናናስ ሕ/ሥራ ማህበራት ጋር የሥራ አጋርነት መፍጠር በሂደት ላይ ነው። |
| ላንቴ ጋሞጉፋ | ማንጎ | ፍራፍሬ ማቀነባበር ሥልጠና ለአርሶአደሮች ተሰጥቷል። በዚህ ሥልጠና 25 አርሶአደሮች የተሳተፉ ሲሆን ተጨማሪ ሥልጠና እንደሚሰጥ ይጠበቃል። |

* አሶሳና ቤንሻንጉል ጉሙዝ በማንጎ ላይ የሚንቀሳቀስ የሥራ ቦታ ይገኛል

አነስተኛ የምግብ ማቀነባበሪያ ሥራ ላይ ከሚገጥሙ ችግሮች ዋነኛው የምርት ማሸጊያ ቁሳቁስ የሚያመርት ፋብሪካ በሀገር ውስጥ አለመኖሩ ነው። በሀገሪቱ አንድ የጠርሙስ የሚያምርት ፋብሪካ ይገኛል። ፋብሪካው አንድ ዓይነት ጠርሙስ ወይንም ብልቀጥ

ለማምረት የሚፈልገው አነስተኛ የብዛት መጠን አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ከሚፈልጉት እጅግ የበዛ ነው፡፡

ከውጭ ሀገር ጠርሙሶችን/ብልቃጦችን በማስገባት መጠቀም የሀገር ውስጥ ዋጋን የሚያንር በመሆኑ ኢኮፒያ የማልማላት ብልቃጦችን የእያዟዛረ ይጠቀማል፡፡

<u>አንድ መንደር አንድ ምርት ማስፋፊያ ኘሮጀክት/ በጃይካ እገዛ የሚካሄድ</u>
አንድ መንደር አንድ ምርት ኘሮጀክት ከ2010 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በመካሂድ ላይ ይገኛል፡፡ ኘሮጀክቱም የግብርና ምርት እሴት መጨመር ላይ የቴክኒዮሎጂ (ገንዘብ) መረጃ ለማግኘት ችግር ያለባቸውን አርሶአደሮች መደገፍ ዋና ዓላማው ነው፡፡ ለመንደር/ገጥ ዕድገት የሚሆ ሞዴል የየመንደሩን ምርት በማሳደግ መፍጠር ፈታኝ ነው፡፡ ይሁንና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ይህንኑ ሞዴል ለመፍጠር ተመርጧል፡፡ የየመንደሩን ምርት የገበያ አማራጭ መስመሮችን ለመፍጠር አንድ መንደር አንድ ምርት ኘሮጀክት አርሶአደር ቡድኖችና አንድ ሌላ አካል ("ግለሰብ ወይንም ኩባኒያ አንድ መንደር አንድ ምርት ፕሮጀክት አጋር የሚባል") ጋር የሥራ ግንኙነት በመፍጠር ለአርሶአደር ቡድኖች የቴክኒክና የገበያ አማራጭ የማፈላላግ ድጋፍ እንደ አቅጣጫ ተይዟል፡፡

ፍራፍሬና አትክልትን በተመለከተ አንድ መንደር አንድ ምርት ኘሮጀክት ማንጐ፣ አቮካዶ ማቀነባበር (ማልማላታና ጭማቂ ዝግጅት) ሥራ ላይ ከበርካታ አርሶአደር ቡድኖች እና ኢኮፒያ (የአንድ መንደር አንድ ምርት ኘሮጀክት አጋር ድርጅት) ጋር አርባምንጭ፣ ጋሞጐፋ ዞን እና በሎሶ ቦምቤ (ወላይታ ዞን) በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

### (3) በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የሚካሄድ የአግሮ ኘሮሰሲንግ ማሻሻል

ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ደህነትና ሥራ አጥነትን ለማቃለል ክልላዊ የኢንተርኘራይስ ልማት ኘሮግራም በተለይ በከተሞች አካባቢ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ኘሮግራም በአራቱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እነርሱም፡ 1) ጨርቃጨርቅ አገልግሎት፣ 2) ብርታብረትና እንጨት ሥራ፣ 3) አግሮ ፕሮስስንግ፣ እና 4) ዕደጥበብ ናቸው፡፡

በክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሥር ያለው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይስ ልማት ኤጀንሲ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራስ ልማትን ያካሄዳል፡፡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዝ ልማት ኤጀንሲ በክልሉ ውስጥ ባሉ 22 ኢፎርም ከተሞች በእያንዳንዱ 4 ባለሙያዎች በማስማራት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ማስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ባለሙያዎች አንዱ የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ ያለው ሲሆን አግሮ ፕሮሰስንግ የማስፊፊት የሥራ ድርሻ አላቸው፡፡ የዚሁ ባለሙያ ዋነኛ ኃላፊነት የተለያዩ ቡድኖች ማቋቋም፣ ማሰልጠንና ከአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ብድር እንዲያገኙ ማመቻቸት ነው፡፡

<u>በአግሮ ኘሮሰስንግ ዙሪያ የተካሄደ ተግባር</u>
ከቅርብ ጊዜ በኋላ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይስ ልማት ኤጀንሲ አነስተኛ ኢንተርኘራዞችን የማስፋፋትና የመደገፍ ሥራ እየሠራ ነው፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘይዞች ቡድን የማደራጀት ሥራ በተወሰነ ደረጃ ተካሂዷል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጠና በሀዋሣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ በኩል ተሠጥቷል፡፡ በኢኮፒያ፣ ኤስ.ኤን.ቪ. እና ሀዋሣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ለ65 ሰዎች በፍራፍሬ ማቀነባበር (ጭማቂ፣ ወይን፣ማልማላት) የንድፈ ሀሣብና የተግባር ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ የአግሮ ፕሮሰስንግ ሥልጠና አርባምንጭ ከተማ ለመስጠት ታቅዷል፡፡

ከላይ ከተመለከተው በተጨማሪ በአንድ አካባቢ እጅብ ያለ ልማት በክልሉ ውስጥ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በ12 የሪፎርም ከተሞች በሀዋሣ፣ አለታወንዶ፣ ይርጋለም፣ ወልቂጤ፣ ቡታጅራ፣ ሆሳዕና፣ አርባምንጭ፣ ሶዶ፣ ቦዲቲ፣ አላባ፣ ሚዛን ተፈሪ እና ቴፒ የአንድ አካባቢ የልማት ማዕከሎች እየተገነቡ ነው፡፡ በማዕከላቱ ለአምስት ዓመታት ያህል ኢንተርፕራይዞችን የመፈልፈልና የማብቃት ሥራ የሚያከናወንባቸው ሲሆን ለሥራ የሚያስፈልግ ቦታና ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

### 3.2.3 የአካባቢ የአግሮ ፕሮሰስንግ ማሽን የሚፈርኩ ተቋማት

#### (1) አጠቃላይ ገጽታ

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ አርሶአደሮች መጥረቢያ፣ መቆፈሪያ፣ በበሬ የሚጐተት ማረሻ የመሳሰሉ ለእርሻ ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች አሉዋቸው፡፡ የማንንዝ አገልግሎት የሚሰጥ የአህያ ጋሪ ያለው አርሶአደር በቁጥር ውስን ነው፡፡ በአንዳንድ ጥቂት አርሶአደሮች የውሃ ፖምፕ እና መርጫ መሣሪያዎች በግል ወይንም በጋራ የሚጠቀሙበት ሁኔታ አለ፡፡ በአንዳንድ የእርሻ ተግባራት ተሪዳድቶ የመሥራት ልምድ በስፋት የተለመደ ነው፡፡ ይህም የሆነው ምናልባት ገጠር አካባቢ አንጥረኛ ባለመኖሩ ወይንም ያሉትም አንጥረኞች የተሻሻሉና የተወሳሰቡ መገልገያ መሣሪያዎችን ጥገናና ዕድሳት ለማድረግ ያላቸው ክህሎት ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ያላመቻላቸው ነው፡፡ በመሆኑም የተሻሻለ የእርሻ መሣሪያዎች በኢትዮጵያ ለማስተዋወቅና ለማስረዳት የተሻሻሉ መገልገያዎች ልማት ሊደገፍ ይገባል፡፡

የእርሻ መገልገያዎች ማምረት የተጠቃሚ አርሶአደሩን በመሣሪያው የመጠቀም፣ የማስተዳደርና የመጠገን ዕውቀትን የሚፈልግ ሲሆን የመንግሥት የገንዘብ ድጋፍንም ይሻል፡፡ ተከታታይነት በአለው እንደ ማረስ፣ መዝራት፣ ማዳበሪያ መርጨት፣ ሰብል መሰብሰብ እና ድህረምርት ሥራ በመሳሰሉ የእርሻ ተግባራት በሬ በመጠቀም ማረስ በኢትዮጵያ በስፋት ተግባራዊ እየሆነ ነው፡፡ ከሰፋፊ እርሻዎች በስተቀር ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን መጠቀም እምብዛም የተለመደ አይደለም፡፡ ምርቱ ከተወቃ በኂላ የማበጠሩ ተግባር በሰው ኃይል ወይንም ለንፋስ በመስጠት/በማዝራት ይሆናል፡፡

#### (2) የገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከል

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በግብርና ቢሮ በግብዓት አቅርቦት የሥራ ሂደት ሥር በሚተዳደሩ ሁለት የገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከላት በሚዛንና ወላይታ ሶዶ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ማዕከላት ዋነኛ ተግባር አዳዲስ ቴክኖሎጂን የእርሻ መሣሪያዎች የማስተዋወቅ፣ አጠቃቀምን የመከታተል፣ የመገምገምና ማሻሻል እንዲሁም የእርሻ መሣሪያዎችን አምርቶ መሸጥን ያካትታል፡፡ እነዚህ ማዕከላት ዓመታዊ በጀታቸው ላይ የተመሠረተ የድርጊት መርሐ ግብር አላቸው፡፡ የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችን ዲዛይን የሚያደርጉ ባለሙያዎች ለዚሁ ተግባር የሚሆን የተለየ ቢሮ ሲኖራቸው መሣሪያዎችንም ለመፍብረክ የሚረዱ የብረታ ብረትና እንጨት ሥራ ወርክሾፖች ይገኛሉ፡፡ በግብዓት አቅርቦት የሥራ ሂደት መመሪያ መሠረት የተወሰኑ የእርሻ መሣሪያዎችን ለማምረትና ሙከራ ለማካሄድ የተያዘው ዕቅድ አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.2-2 ዓመታዊ የምርምር ልማት ዕቅድና አፈጻጸም**

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የድህረምርት መቀነባበሪያ ማሽን የኤክስቴንሽን ሁኔታ | አንዱ ክፍል አልቋል |
| 2 | የእንስት መቀነባበሪያ ማሽን የምርምርና ልማት ኤክስቴንሽን | አልቋል (ሶደ፣ ሚዛን) |
| 3 | በበሬ፣ ፈረስ፣ አህያ ወዘተ የሚጎተት ጋሪ ማሻሻያ ቴክኖሎጂ. | አልቋል (ሶደ፣ ሚዛን) |
| 4 | የእርድ በፀሐይ ለማድረቅ መላጫ ማሽን ለመሥራትና ቅልጥፍና መለኪያ ሙከራ | አልቋል (ሶደ፣ ሚዛን) |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | የበቆሎ መፈልፈያ ቅልጥፍና መለኪያ ሙከራ | በሙከራ ላይ (ሚዛን) |
| 6 | ለፍራፍሬ ድህረምርት ብክነት መቀነሻ ዘዴ | ገና ነው |
| 7 | የመጋዘን የተሸሻለ ቴክኖሎጂና | ገና ነው |
| 8 | የማሸግያ ማቴሪያል ማሻሻልና ኤክስቴንሽን | ገና ነው |
| 9 | የካሳቫ መቁረጫ ለመፈብረክና ቅልጥፍና ለማየት የሚደረግ ሙከራ | ገና ነው |
| 10 | የማንጎ ማውረጃ ቁሳቁስ ለመፈብረክና ቅልጥፍና ለማየት የሚደረግ ሙከራ | ገና ነው |

## ሠንጠረዥ 3.2-3 ብረታ ብርት ድርጅት (ሶዶ)

| መገልገያ | ብዛት | መገልገያ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| ትልቅ ቅርጻረ ማውጫ | 2 | የኤክትሪክ መፈግፈጊያ | 1 |
| መቁረጫ ማሽን (በሞተር/በእጅ የሚሠራ) | 1 | ከፍተኛ ፍጥነት ያለው መቁረጫ | 1 |
| መቆልመሚያ | 1 | አርክ መበየጃ | 2 |
| መጠቅለያ ማሽን | 2 | መበየጃ | 1 |
| የኤሌክትሪክ መብሻ | 2 | የኤሌክትሪክ መሮድ | 2 |
| የኤክትሪክ መጋዝ (ለብረት) | 1 | በናፍጣ የሚሠራ ጀነሬተር | 3 |
| ቅርጽ ማውጫ | 1 | | |

## ሠንጠረዥ 3.2-4 የእንጨት ሥራ ድርጅት (ሶዶ)

| መገልገያ | ብዛት | መገልገያ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| የኤሌክትሪክ መጋዝ (ለእንጨት) | 1 | የኤሌክትሪክ መብሻ | 1 |
| የኤሌክትሪክ መላጊያ | 1 | የኤሌክትሪክ ቦይ ማውጫ | 1 |
| የኤሌክትሪክ መፈግፈጊያ | 1 | ቅርጽ መውጫ | 1 |

የሶዶ ገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከል በአሁኑ ጊዜ ማረሻ፣ የውሃ ፓምኘ፣ የእንስት መጭመቂያ፣ የንብ ቀፎ፣ ቅቤ መናጫ እና የውሃ መዝግያ በማምረት ላይ ይገኛል፡፡ የሚዛን ገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከል የእንስት መጭመቂያ፣ በእጅ የሚሠራ በቆሎ መፈልፈያዎች፣ ቅቤ መናጫ ያመርታል፡፡ በመጋዘኖቻቸው በዙ ክምችት ያለ ሲሆን 20 የበቆሎ መፈልፈያ፣ 500 ማረሻ 20 የውሃ ፓምኘ፣ 50 የንብ ቀፎ እና ከወጪ ሀገር የገቡ ለሠርቶ ማሳያና የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ማዕከላት አስፈላጊ በሆነ ቁሳቁሶችና የሰው ኃይል ቢሟላ ቀለል ያሉ የድህረምርት ማሰብሰቢያ ማሣሪያዎች ሊያመርቱ ይችላሉ፡፡ በሰው ኃይልና በበጀት እጥረት ምክንያት በአሁኑ ወቅት ሁለቱ ማዕከላት የእርሻ መሣሪያዎችን ብቻ በማመረት ተወስነዋል፡፡ ማዕከለቱም ምርቶቻቸውን በትዕዛዝና ውል ላይ በመመሥረት ያመርታሉ፡፡ ይሁንና በማዕከሉ የሚሠራው የጤፍ መውቂያና የእንስት መጭመቂያ በሽያጭ ላይ ውሎ በደንብ ከተተዋወቀ እነዚህ የድህረምርት ቴክኖሎጂዎች ለሕ/ሥራ ማህበራትና ለአርሶአደሩ እንደሚደርሱ ይጠበቃል፡፡

### (3) የአካባቢ የእርሻ መሣሪያ

በሀዋሣ ከተማ የሚገኘው አንድ የግል ድህረምርት መገልገያ መሣሪያዎች የሚያመርት ድርጅት ምን ምን መሣሪያ እንደሚያመርት፣ የአሠራር ሁኔታና ዋጋ ለማወቅ ተጐብኝቶ ነበር፡፡ አዲስ አበባ የሚገኘው ሠላም የሚባል የሙያ መሠልጠኛ የእርሻ መሣሪያዎችን በማመረት ተሠማርቷል፡፡ በሀዋሣ ቅርንጫፍ እህት ድርጅት አለው፡፡ በሀዋሣ የሚገኘው ሠላም ሙያና ቴክኒክ ማሠልጠኛ እንደ ጤፍ መውቂያ፣ የተለያዩ ሰብሎች መፈልፈል፣ በቆሎ መፍልፈያ፣ ሩዝ መወቂያ ወዘተ ያመርታል፡፡ በተጨማሪ ድርጅቱ እንደ ድንጋይ

መፍጫ፣ ስሚንቶ መደባለቂያና ታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂዎችን (አነስተኛ የውሃ ኃይል) ያመርታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጠቅላላ መካኒክስና ኤሌክትሪክ ሥራ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ይሠራል፡፡
የሚቀጥለው ምስል ሠላም ሀዋሣ የውስጥ ይዘት ያሳያል፡፡


የተላያዩ መፈልፈያዎች መፈብረክ


የቦቆሎ መፈልፈያ

በናፍጣ የሚሠራ ሞተር የተገጠመለት የጤፍ መውቂያ ዋጋ ብር 30,000 ነው፡፡ የመውቃት አቅሙም በሰዓት 300 ኪ.ግ ነው፡፡ ይህም 6-8 የሚሆኑ በሬዎች በአንድ ቀን የሚወቁትን ያክላል፡፡ ይህ መውቂያ ድህረምርት ሥራን በማሻሻል፤ ከአፈር ከእርጥበትና ባዕድ ነገሮች የነፃ ምርት ለማምረት ተስማሚ ነው፡፡ የበቆሎ መውቂያ፣ የኦቾሎኒ ቅቤ መሥሪያ እና የእንስት መፋቂያ ሥራ በሙከራ ደረጃ ይገኛል፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ከሠላም ሀዋሣ ውጪ የተወሰኑ በአነስተኛ ደረጃ የእርሻ መሣሪያዎችን የሚያመርቱ ድርጅቶች አሉ፡፡ በእርሻ መሣሪያዎች ያለው ፍላጐት የተወሰነ በመሆኑ በትዕዛዝ ላይ ተመሥርተው ያመርታሉ፡፡ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ከገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከላት ጋር በመቀናጀት ቀስ በቀስ የእርሻ መሣሪያዎች አጠቃቀም በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ተመሥርቶ እንደገና እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

የድርጅቱ ሽያጭ በሚከተለው ሠንጠረዥ ተጠቃሏል፡፡ በሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው የሠላም ሀዋሣ የእርሻ መሣሪያ አቅርቦት አነስተኛ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 3.2-5 የሠላም ሀዋሣ የሽያጭ ምዝገባ

| ተ.ቁ | መገልገያ መሣሪያ | አቅም (ኩ/ል በሰዓት) | የሽያጭ ዋጋ (ብር) | Features | የተሸጠ/የቀረበ (ቀጥር) | ደንበኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በቆሎ መፈልፈያ (ከነቆሮቆንዳ) | 50 | የለም | | | |
| 2 | በቆሎ መፈልፈያ (ያለቆሮቆንዳ) | 25 | 27,600 | | 9 | * ባኮ አካባቢ |
| 3 | በቆሎ መፈልፈያ (ያለቆሮቆንዳ) | 50 | የለም | | 1 | * ግል |
| 4 | ጤፍ መውቂያ | 3 | 27,600 | 9 የፈረስ ጉልበት ባለው ሞተር የሚሠራ | 7 | * ባስኬቶ ልዩ ወረዳ |
| 5 | በእጅ የሚሠራ ብዙ ዓይነት ሰብል መውቂያ | | 27,600 | ለጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ሩዝ | 7 | * ግል |
| 6 | የእጅ መፈልፈያ (የበቆሎ) | | የለም | የተለያያ ዓይነትና መጠን | | |
| 7 | የሩዝ መውቂያ | | 10,300 | 3.5 የፈረስ ጉልበት ባለው ሞተር የሚሠራ | 9 | * ግል |
| 8 | የኦቾሎኒ ቅቤ መሥሪያ መሽን | | የለም | | | |
| 9 | የበቆሎ ወፍጮ | | የለም | | | |
| 10 | የሩዝ ወፈጮ | | 25,000 | | | * ሶማሌ ክልል |
| 11 | ፒን መውቂያ | | 9,000 | | 1 | * ግል |
| 12 | እንሰት መፋቂያ | | የለም | | | |
| 13 | ኦቾሎኒ መፈልፈያ | | የለም | | | |
| 14 | በቆሎ ማበጠሪያ/ መዝሪያ | | የለም | | | |

በተጨማሪ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ አንድ በጐጆ ኢንድስትሪ ደረጃ ብርዕና ጥራጥሬ ማበጠሪያ የሚሠራ ድርጅት አለ፡፡ ምርቶቻቸውን ለማስተዋዋቅ እየሠሩ ቢሆንም ያለው ፍላጐት አነስተኛ ነው፡፡ ለአለፉት 6 ዓመታት የጤፍ ማበጠሪያ በመሥራት ላይ ያለ ድርጅት ሻሸመኔ ይገኛል፡፡ የምርቶቹም ተጠቃሚ የእህል ወፍጮ ቤቶች ናቸው፡፡ ድርጅቱም በተከታታይ የጤፍ ማበጠሪያ መሣሪያውን አቅም የማሻሻልና በቀላሉ መጠቀም የሚያስችል ሁኔታን የመፍጠር ሥራ ሠርቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ድርጅቱ ጥሩ ስም አትርፏል፡፡ በተጨማሪ በቀን 80 ቶን ቦሎቄ ማበጠር የሚችል የማበጠሪያ ማሣሪያ ለውጪ ሀገር ላኪ ነጋዴዎች በትዕዛዝ ሠርቷል፡፡ ይህ መሣሪያ አሜሪካ ሠራሽ የሆነ ማበጠሪያ ቅጂ ሲሆን የተወሰኑ ማሻሻያዎች ሊደረጉለት ይገባል፡፡

የማበጠሪያ መሣሪያ ፍላጐት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ እንደሚጨመር ይገመታል፡፡ ይህም በመሆኑ የማበጠሪያ ማሣሪያውን ማመረት ቴክኒካዊ ዕውቀትና ክህሎት መሻሻልና ተወዳዳሪ መሆን ይገባዋል፡፡

## 3.3 የግብርና የገበያ መረጃ አገልግሎት

### 3.3.1 የሀገሪቱ የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት

ቁጥሩ በዛ ያለ እንደ ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተዳደር፣ የዓለም ምግብ ፕሮግራም፣ የእንስሳት መረጃ አውታርና እውቀት ሥርዓት፣ የኢትዮጵያ እህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት የገበያ መረጃ በመሰብሰብ ያሰራጫሉ፡፡ ማዕከላዊ የእስታቲስቲክስ ኤጀንሲና ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተዳደር ሀገሪቱ በሙሉ የሚሸፍን የተለያዩ ምርቶች የገበያ ዋጋ መረጃ ይሰበስባሉ፡፡ የእንስሳት መረጃ አውታርና እውቀት ስርዓት የእንስሳት ዋጋና ብዛት መረጃ በሀገር ውስጥ በተመረጡ አካባቢዎች ይሰበሰባሉ፡፡ የዓለም ምግብ ፕሮግራም/የተጎጂነት መተንተኛና በካርታ ማሳያ[1] በሀገሪቱ ውስጥ በአሉት የዓለም ምግብ ፕሮግራም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት የዋና ዋና ምርቶችን ዋጋ ይሰበሰባል፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተመረጡ ምርቶች (በዋናነት የቡና) የገበያ ማዕከሉ የጨረታ ዋጋ የኤሌክትሮኒክስ ማሳያ፣ ድህረገጽ፣ ብዙሃን መገናኛ እና የሞባይል አጭር የጹሑፍና የድምፅ መልዕክት በመጠቀም ያሰራጫል፡፡

በሞባይል አጭር የጹሑፍና የድምፅ መልዕክት ከታህሳስ 2010 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በማሰራጨት ላይ ከአለው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በስተቀር ለአርሶአደሩ ወይንም ለሌሎች የገበያ ተዋኒያኖች የዋጋ መረጃ የሚያሰራጭ የለም በሀገሪቱ ውስጥ በዋናነት የገበያ መረጃ ላይ የሚሠሩ ድርጅቶች አንቅስቃሴ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### (1) ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

ማዕከላዊ የእሰታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሁለት ዓይነት የዋጋ ያሰባስባል፡፡ እነርሱም የዕቃዎችና አገልግሎቶች ወርሃዊ የችርቻሮ ዋጋ እና የግብርና ምርት አምራቾች ዋጋ ናቸው፡፡

1) ወርሃዊ አማካይ የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ

የወርሃዊ ችርቻሮ ዋጋ መሰብሰብ በ1963 (እ.ኤ.አ) በአዲስ አበባ ነው የተጀመረው፡፡ ዋጋ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ከ1986/87 እስከ 1986/97 (እ.ኤ.አ) በአለው ጊዜ ውስጥ ወደ 760 ደርሶ ነበር፡፡ በመቀጠልም በ1997/98 (እ.ኤ.አ) ወደ 1420 ከፍ ብሏል፡፡ በ1998 ደግሞ ወደ 446 ዝቅ ብሏል፡፡ የመረጃ አሰባሰብን ለማሻሻል ሲባል በ2001 (እ.ኤ.አ) የዋጋ መረጃ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ለውጥ ተደርጓል፡፡ ከዚህም የተነሳ 105 ከተሞችን የሚወክሉ 119 የዋጋ መሰብሰቢያ ቦታዎች ተመርጠዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የዋጋ ደሰሳው ወደ 400 የሚሆን የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶችንና አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡

ብዙውን ጊዜ አንድ መረጃ ሰብሳቢ ለአንድ የገበያ ቦታ ይመደባል፡፡ የብዙ ዕቃዎች ዋጋ የሚሰበሰብ በመሆኑ የመረጃ አሰባሰቡ ወርሃዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ወር በገባ 1-15 (እ.ኤ.አ) ባሉት ቀናት ውስጥ ይካሄዳል፡፡ የችርቻሮ ዋጋ ከተለያዩ መሸጫ ቦታዎች (ከገበያ፣ ሱቆች፣ ግሮሰሪ፣ ሥጋ ቤቶች ወ.ዘ.ተ) ይሰበሰባል፡፡ ለአንድ ዕቃ ከሶስት ችርቻሮ ሻጮች ዋጋ ይሰበሰባል፡፡ የመረጃ ሰብሳቢው ፒዲኤ እና ትንሽ ሚዛን (10ኪ ግራም የሚመዘን) ይጠቀማል፡፡ ፒዲኤ መረጃ ለማስገባትና ለመላክ ያገለግላል፡፡

[1] የተጎጂነት መተንተኛና በካርታ ማሳያ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ምግብ ዋስትና መተንተኛ ሥራ ሲሆን በዓለም ውስጥ በአሉ 120 መተንተኛ ቦታዎች ይካሄዳል፡፡ የተጎጂነት መተንተኛና በካርታ ማሳያ ምግብ ዋስትና እጥረት ያለባቸውን አካባቢዎች በመለየት በካርታ የሚያስቀምጥ ሲሆን ለአደጋ ተጋላጭ የሚሆኑ አካባቢዎችንም ያመላክታል፡፡ ይህንንም ለማድርግ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ዘመናዊ የሆኑትን ቴክኖሎጂዎች እንደ ሳታላይት መስል፣ ጂኦግራፋያዊ መረጃ ሥርዓት ወይንም የግለሰብ ዲጂታል አጋዥ ይጠቀማል፡፡

ፒዲኤ (የግል ዲጅታል አጋዥ) ኢዩ/ፋኦ በሚያካሄደው "በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና መረጃ ሥርዓት" ፕሮጀክት አማካኝነት ነው ወደ ኢትዮጵያ የገባው ይሁን እንጂ የተለመደው በወረቀት ላይ በመረጃ ቋት መሙላት ስህተት ለመቆጣጠር ሲባል ጐን ለጐን ይካሄዳል፡፡



ፒዲኤ በእጅ መዳፍ ውስጥ የሚያዝ የኮምፒውተር ሙሉ ኪቦርድ አለው፡፡ መረጃ ታች (መነካካት) አስክሪንን በመጠቀም ይመዘግባል፡፡ ፋይሎች እንደ ማንኛውም ኮምፒውተር ይከፈታል፣ ይከማቻል፣ እንደገና ይከፍታል፡፡ የመጠቁ ቅጽ (ፎርማት ቀደም ብሎ በፒዲኤ ላይ ተጭኗል፡፡ በኤክስኤል ሶፍትዌር የተዘጋጀ መረጃ ማስገቢያ ቋት የዋጋ መረጃ ለመመዝገብ ያገለግላል፡፡ ስህተትን ለመቀነስ ሲባል አነስተኛና ከፍተኛ ዋጋ ጣሪያ ተቀምጧል፡፡ በአጠቃላይ 138 ፒዲኤ በኢዩ/ፋኦ ፕሮጀክት አማካኝነት ተሠራጭቷል፡፡.

የተሰበሰበው የዋጋ መረጃ በየአካባቢው ለሚገኙ ለማዕከላዊ እስታቲክስ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይሰጣል፡፡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱም መረጃው በዞን ደረጃ ያስገባና ለማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃውን በመተንተንና በማቀነባበር አትሞ እንዲያወጡ ይላካል፡፡ ወርሃዊ ሪፓርቱ "ወርሃዊ አማካይ የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ" በሚል መረጃ ከተሰበሰበ 3 ወር በኋላ ታትሞ ይወጣል፡፡

2) ወርሃዊ የአምራቾች የግብርና ምርቶች ዋጋ

ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ከ1981 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ የአምራቶች የግብርና ምርቶች ዋጋ ሲሰበስብ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት የዋጋ መረጃ አሰባሰቡ ወደ 99 የሚሆኑ የተመረጡ የግብርና ምርት ውጤቶችን ያካትታል፡፡

በመሆኑም ብርዕ ሰብል፣ ጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ቅመማ ቅመም፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ እና ሌሎችንም ይሸፍናል፡፡ መረጃው በወር አንድ ጊዜ (ወር በገባ 1-15 /እ.ኤ.አ/ ባለው ጊዜ) ከተመረጡ ከአርሶአደር ቤተሰቦች ወይንም ከሕ/ሥራ ማህበራት ይሰበሰባል፡፡ በታህሳስ ወር 2009 (እ.ኤ.አ) በተገኘው መረጃ መሠረት የአምራቶች ዋጋ መሰብሰቢያ ቦታዎች በአጠቃላይ 438 ደርሷል፡፡

ለእያንዳንዱ የግብርና ምርት ሶስት ሶስት የዋጋ መረጃ ከተለያዩ ሶስት አርሶአደሮች ወይንም ሕ/ሥራ ማህበራት ይሰበሰባል፡፡ መረጃ ሰብሳቢው ትንሽ ሚዛን (10 ኪ.ግራም የሚመዝን) ይጠቀማል፡፡ የመረጃ ማስተላለፍ፣ መረጃ ማስገባትና መተንተን እንዲሁም የሪፓርት ሕትመት ሥራ ሂደት ከወርሃዊ የችርቻሮ ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የማዕከላዊ እስታቲስቲክ ኤጀንሲ ከ1997 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ዞናዊ የአምራቶች ዋጋ መረጃ እየሰጠ ይገኛል፡፡

3) የዋጋ መረጃ ስርጭት

ከወርሃዊ የዋጋ መረጃ በተጨማሪ የገበያ ዋጋ መረጃ በማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ድህረገጽ (www.esa.govet consumer price) ይገኛል፡፡ የ2007/08 እና 2009/10 (እ.ኤ.አ) የዋጋ መረጃ ከማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ድህረገጽ በመጋቢት 2010 (እ.ኤ.አ) ለማውረድ ሲሞከር በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡


4) በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የማዕከላዊ እሰታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ

አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማለትም ሀዋሣ፣ አርባምንጭ፣ ሆሳዕና፣ ሶዶና ሚዛን ተፈሪ በክልል ውስጥ በአሉ የተመረጡ የገበያ ቦታዎች መረጃ ያሰባስባሉ፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታ ብዛት፣ አድራሻና የገበያ ቦታዎች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ 3.3-1 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የአምራች ዋጋ መሰብሰቢያ ቦታ ብዛት

| | ዞን/ልዩ ወረዳ | መረጃ የሚሰበሰብባቸው አካባቢዎች | | ዞን/ልዩ ወረዳ | መረጃ የሚሰበሰብባቸው አካባቢዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከምባታ ጠምባሮ | 5 | 12 | ሸካ | 3 |
| 2 | ሃዲያ | 4 | 13 | ከፋ | 8 |
| 3 | ወላይታ | 7 | 14 | አላባ ልዩ ወረዳ | 2 |
| 4 | ሲዳማ | 9 | 15 | የም ልዩ ወረዳ | 2 |
| 5 | ጋሞ ጎፋ | 11 | 16 | ደራሼ ልዩ ወረዳ | 2 |
| 6 | ዳውሮ | 5 | 17 | አማሮ ልዩ ወረዳ | 2 |
| 7 | ጉራጌ | 8 | 18 | ቡርጂ ልዩ ወረዳ | 2 |
| 8 | ስልጤ | 6 | 19 | ኮንሶ ልዩ ወረዳ | 2 |
| 9 | ቤንች ማጂ | 8 | 20 | ኮንታ ልዩ ወረዳ | 2 |
| 10 | ጌዲኦ | 4 | 21 | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | 2 |
| 11 | ደቡብ ኦሞ | 5 | | ድምር | 99 |

ምንጭ፡ የማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ,የበዞን ደረጃ አምራቹ የግብርና ምርት ሂደት፣ ታህሳስ 2009 እ.ኤ.አ (ቡለቲን 474)




* በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በጠቅላላው 31 የገበያ ቦታዎች አሉ።
የተርጫ ማንኛውም የዋጋ መረጃ በጥቅምት 2009 (እ.ኤ.አ) ወርሃዊ ሪፖርት አልቀረበም።.

**ምስል 3.3-1 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የችርቻሮ ዋጋ መሰብሰቢያ የገበያ ቦታዎች አቀማመጥ**

### (2) የኢትዮጵያ የእህል ገበያ ኢንተርፕራይዝ

የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ የእህል ሰብል፣ ጥራጥሬና የቅባት አህሎች የዋጋ መረጃ መደበኛና ወቅታዊ በሆነ መንገድ ያሰባስባል፡፡ በቅርንጫፍና ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤታቸው አማካኝነት ሀገሪቱ ውስጥ ከአሉ 22 የገበያ ቦታዎች የዋጋ መረጃ ይሰበስባል፡፡ መረጃው 15 ሰብሎችን የሚሸፍን ሲሆን በየሳምንቱ በገበያ ቀን ይሰበሰባል፡፡ ምርት እንደተሰበሰበ ወቅታዊ የዋጋ መሰብሰቢያ ሥራ በ60 የገበያ ቦታዎች ምርት አንደተሰበሰበ ይካሄዳል፡፡

የተሰበሰበው መረጃ ወደ ዋና መ/ቤቱ የሚላክ ሲሆን የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ መረጃው ለራስ ውሳኔ አሰጣጥ ይጠቀማል፡፡ መረጃውም በኢንተርፕራይዙ ድህረገጽ (www.egtemis.com/priceone.asp) ይገኛል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.3-2 የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ መደበኛ የዋጋ መረጃ መሰብሰቢያ የገበያ ማዕከላት**

| ክልል | የገበያ ማዕከል |
|---|---|
| አዲስ አበባ | አዲስ አበባ፣ አድስ አበባ ዙሪያ |
| ድሬዳዋ | ድሬዳዋ |
| ትግራይ ክልል | መቀሌ |
| አማራ ክልል | ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ቢጠና፣ ቡሬ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደጀን፣ ደሴ |
| ኦሮሚያ ክልል | አምቦ፣ ናዝሬት፣ አሰላ፣ ሻሸመኔ፣ ጂማ፣ ባሌ ሮቤ፣ ፍቼ፣ ነቀምት፣ ወልሶ |
| ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | ሆሳዕና |
| ሐራሪ | ሐረር |

ምንጭ: ግብርናና ገጠር ልማት ሚስቴር "ረቂቅ ኢትዮጵያ ብርሔራዊ የገበያ መረጃ አገልግሎት ማቋቋሚያ ሰነድ (ሰኔ 2008 እ.ኤ.አ)፣ የትዮጵያ እህል ሰብል ንግድ ኢንተርፕራይዝ ድህረገጽ

**ሠንጠረዥ 3.3-3 በኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ ድህረገጽ ዋጋ መረጃ የሚሰጥባቸው ሰብሎች**

| ብርዕባ አገዳ ሰብል | ጥራጥሬ | የቅባት ሰብል |
|---|---|---|
| ጤፍ (ድብልቅ፣ ቀይ፣ ነጭ)<br>ስንዴ (ደብልቅ፣ ነጭ)<br>ገብስ (ደብልቅ፣ ነጭ)<br>ማሽላ (ድብልቅ፣ ቀይ፣ ነጭ)<br>በቆሎ<br>ነጭ በቆሎ | ሽምቡራ<br>አተር ድብልቅ<br>ነጭ አተር<br>ቦሎቄ<br>ባቄላ<br>ምስር<br>ቀይ ቦሎቄ | የጥጥ ዘር<br>ጥቁር ሰፍ<br>ሰልጥ |

ምንጭ: የትዮጵያ እህል ሰብል ገበያ ኢንተርፕራዝ ድህረገጽ

### (3) የኢትዮጵየ ምርት ገበያ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተመረጡ ምርቶችን ማለትም የቡና፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ነጭ ቦሎቄ እና ሰሊጥ ያገበያያል፡፡ በአሁኑ ወቅት ቡና 90% የሚሆነው የገበያ ማዕከሉ ሥራ ይሸፍናል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወቅታዊና የረዥም ጊዜ የዋጋ መረጃ በድህረገጹ (http:/www.ecx.com.et) ያቀርባል፡፡ የዋጋ ማስታወቂያ ቦርዶች በ2008 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን በድህረገጹም ተመልክተዋል፡፡ አልፎ አልፎ ከምርት ገበያ ማዕከሉ ድህረገጽ መረጃ ማግኘት ያስቸግራል፡፡ የዋጋ ማስታወቂያ ቦርዱ በእንግሊዘኛና በአማርኛ

ቋንቋዎች ሀ) የአንድ ቦታ፣ ለ) የምርት ገበያ ዋጋ በአካባቢ ዋጋ ንጽጽር፣ ሐ) የምርት ገበያ ዋጋ ከዓለም ዋጋ ንጽጽር፣ እና መ) የገበያ ሐተታ ያሰራጫል፡፡

በኤሌክትሮኒክስ ማሳያ በገበያ ቦታዎች የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋጋ ይሰራጫሉ፡፡ በተጨማሪ የምርት ገበያው ከታህሳስ 2009 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ የሞባይል አጭር የጹሑፍና የድምፅ መልዕክት ዘዴ በመጠቀም የዋጋ መረጃ ያሠራጫል፡፡ እስከ መጋቢት 2011 (እ.ኤ.አ) ድረስ የሞባይል አጭር የጹሑፍና የድምፅ መልዕክት የቡና ዋጋ መረጃ ብቻ ነበር የሚያሰራጨው፡፡ የአጭር መልዕክት ተጠቃሚዎች በአግባቡ መረጃ ለማግኘት የምርቶችን ኮድ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁንና ኮዶቹን ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ በመሆኑም ይህ መረጃ ማግኛ መንገድ ለገበሬው ተስማሚ አይደለም፡፡

#### (4) ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተዳደር

ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተዳደር ከ1998 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በሀገሪቱ ውስጥ የዋጋ መረጃን እያሰባሰበ ይገኛል፡፡ የቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተዳደር በ2008/09 (እ.ኤ.አ) በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር በአለው የአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ጽ/ቤት ሥር ተደራጅቷል፡፡ በክልል ደረጃ የዋጋ መረጃ ይሰበሰብ የነበረው በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ስር በተደራጀው በቅድመ ማስጠንቀቂያና የምግብ ዋስትና ዋና የሥራ ሂደት ነው፡፡

የዋጋ መረጃ ለቅድመ ማስጠንቀቂያ የሚሰበሰበው እንደማንኛውም ሌሎች መረጃዎች ነው፡፡ የዋጋ መረጃው በወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ሥር በአለው ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሥራ ሂደት አማካኝነት በየሳምንቱ ከተመረጡ የገበያ ቦታዎች ይሰበሰባል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ ወደ ዞን ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተልዕኮ ይጠናቀርና ቅድመ ትንተና ተደርጐ ከሌሎች መረጃዎች ጋር ተጠቃሎ ለበለጠ ትንታኔ ለክልሉ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሥራ ሂደት በዶክመንት ደረጃ ይላካል፡፡ ሁሉም መረጃዎች ተጠናቅረው በወርሃዊ ሪፖርት (የወርሃዊ አማካይ ዋጋ ጨምሮ) በክልሉ የሥራ ሂደት ይዘጋጃል፡፡ ሪፖርቱም ለፌዴራል ጽ/ቤት እንዲሁም ለክልሉ ትምህርት፣ ጤና፣ ወዘተ ይላካል፡፡

እንደ ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት [2] "የዋጋና ገበያ ማከታተያ ስርዓት" የኮምፒውተር ፕሮግራም ለቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ተዘጋጅቷል፡፡ የዓለም ምግብ ፕሮግራም/የተጉጅነትን መተንተኛ በካርታ ማሳያ የተዘጋጀውን የኮምፒውተር ፕሮግራም ከመረመረ በኂላ በ2007 (እ.ኤ.አ) የአደጋ መከላከያና ዝግጁነት ጽ/ቤትን አቅም መገንባት ጀምሯል፡፡ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ድህረገጽ እስካሁን ያለ ቢሆንም ወቅታዊ መረጃዎች አይጨመሩበትም፡፡

<u>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ</u>

- መረጃና የመሰብሰብ ኃላፊነት ያለበት የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስትና ዋና የሥራ ሂደት ሥር የሚገኘው የቅድመ ማስጠንቀቂያ የሥራ ክፍል ነው፡፡
- ሳምንታዊ የገበያ መረጃ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች የሚሰበሰብ ሲሆን በአብዛኛው ከየወረዳው ከተመረጠ አንድ ወካይ የገበያ ቦታ ይሰበሰባል፡፡
- የገበያ ቦታ መረጣ በወረዳ ይካሄዳል
- የሚሰበሰበው የችርቻሮ ዋጋ ነው
- በወር በገባ በመጀመሪያ ሳምንት ወርሃዊ ሪፖርት ከዞን የግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ ወደ ክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይገባል

[2] ግብርናና ገጠር ልማት ሚስቴር "ረቂቅ ኢትዮጵያ ብርሔራዊ የገበያ መረጃ አገልግሎት ማቋቋሚያ ሰነድ (ሰኔ 2008 እ.ኤ.አ)

– በወረዳ ደረጃ 6-7 የሚሆን ሠራተኛ ሲኖር በዞን ደረጃም 6-7 ሠራተኛ ነው የሚገኘው
– የገበያ መረጃ ልውውጥ ከግብይት የሥራ ሂደት ጋር አይካሄድም፡፡ (በዞንና በወረዳ ደረጃ አሁን ያለው ሁኔታ ሊጣራ ይገባል)
– የዋጋ መረጃ የሚሰበሰብባቸው ሰብሎች የሚከተሉት ሲሆን ምንም አይነት የጥራት ደረጃ ስርዓት የለም፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ብርዕና አገዳ | : ጤፍ፣ (ነጭ፣ ድብልቅ)፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ዘንጋዳ፣ በቆሎ፣ ማሽላ |
| 2. ጥራጥሬ | : ምስር፣ አተር፣ ባቄላ፣ ሽምቡራ |
| 3. ሥራሥርና ሌሎች | : ስኳር ድንች፣ ድንች፣ ጎዳሬ፣ ቆጮ |
| 4. ገቢ. መስገኛ ሰብሎች | : አልተዘረዘሩም |
| 5. እንስሳት | : በሬ፣ ላም፣ ፍየል፣ በግ፣ ግመል፣ አህያ፣ በቅሎ፣ ፈረስ፣ ዶሮ |

### (5) የዓለም ምግብ ፕሮግራም /የተጉጂነት መተንተኛና በካርታ ማሳያ

የዓለም ምግብ ፕሮግራም ተጉጅነት መተንተኛና በሰርቶ ማሳያ በክልሉ ከአሉ 50 የገበያ ቦታዎች ከሚያዝያ 2006 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በዓለም ምግብ ፕሮግራም ቅርንጫፍና ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት የምግብ ሰብል፣ የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ዋጋ ይሰበስባል፡፡ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ወርሃዊ መጽሔት "የኢትዮጵያ ወርሃዊ የገበያ ቅኝት" በሚል ርዕስ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካላት ያሰራጫል፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ሀዋሣ የሚገኘው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከ14 የገበያ ማዕከላት የዋጋ መረጃ ያሰባስባል፡፡ መረጃውን የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባልደረባ የሆኑት 9 ሠራተኞች ነጋዴዎችንና ወረዳ ጽ/ቤት ወዘተ በማነጋገር ይሰበስባሉ፡፡ መረጃው በአንድ ወር ውስጥ ከ1 እስከ 4 ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ምንም ዓይነት የጥራት ደረጃ ስርዓት የለም፡፡ አንፃራዊ ዋጋ (ዝቅተኛ ወይንም ከፍተኛ) በማለት ይሰበስባል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.3-4 በዓለም የምግብ ፕሮግራም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የዋጋ መረጃ የሚሰበሰብባቸው ወረዳዎች**

| ዞን | ወረዳ | ገበያ ማዕከል | ዝርዝር * |
|---|---|---|---|
| ዳውሮ | ሎማ | ገሳ | ገብስ፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ጋሞ ጎፋ | አ/ምንጭ ዙሪያ | ሲቃላ | በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ሙዝ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| | ከምባ | ኦቶሎ | ገብስ፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ኮሮሪማ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| | ጎፋ ዙሪያ | ሳውላ | በቆሎ፣ ጤፍ፣ ቦሎቄ፣ ዝንጅብል፣ ቡና፣ ፍየል፣ በግ |
| ጌዲኦ | ወናጎ | ዲላ | በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ቡና፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ጉራጌ | መስቃን | ኢንሴኖ | በቆሎ፣ ስንዴ፣ ቦሎቄ፣ በርበሬ፣ ፍየል፣ ቅቤ |
| ሃዲያ | ሌሞ | ሆሳዕና | በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ቡና፣ በርበሬ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ከምባታ ጠምባሮ | ቃጫ ቢራ | ሃዳሮ | በቆሎ፣ ጤፍ፣ ዝንጅብል፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ደቡብ ኦሞ | ሀመር | ቱርሚ | በቆሎ፣ ማሽላ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ሲዳማ | አለታ ወንዶ | አለታ ወንዶ | በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| | ሀዋሣ ዙሪያ | ሀዋሣ ከተማ | በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ቡና፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ስልጤ | ዳሎቻ | ዳሎቻ | በቆሎ፣ ስንዴ፣ ቦሎቄ፣ በርበሬ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ኮንሶ | | ካራት | በቆሎ፣ ማሽላ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |
| ወላይታ | ሶዶ ዙሪያ | ሶዶ | በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ቡና፣ አቮካዶ፣ ፍየል፣ በግ፣ ቅቤ |

* በሚያዝያ 2008 እ.ኤ.አ የተሰበሰበ መረጃ ውጤት ምንጭ: የዓለም ምግብ ፕሮግራም ሀዋሣ ቅ/ ጽ/ቤት

### (6) የእንስሳት መረጃ አውታር እና እውቀት ሥርዓት

የእንስሳት መረጃ አውታርና እውቀት ሥርዓት በዓለም የእንስሳት ትብብር ምርምር አጋዥ ፕሮግራም የሚካሄድ የምስራቅ አፍሪካ አርብቶ አደር የኑሮ መተዳደሪያ ማስፋፊያ ፕሮጀክት አካል ነው፡፡ የሚካሄደው በቴክሳስ ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት ሲሆን በአሜሪካ ተርአዶ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ ይታገዛል፡፡

የእንስሳት መረጃ አውታርና የእውቀት ሥርዓት በኢትዩጵያ የአርብቶ አደር አካባቢ ክልሎች፣ በኬንያና በታንዛኒያ የእንስሳት ዋጋና መጠን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመኖ ሁኔታ፣ የእንስሳት የበሽታ ክስተቶች፣ የውሃ አቅርቦትና ግጭቶችን በሚመለከት ዘወትር መረጃ ያቀርባል፡፡

በኢትዮጵያ በጠቅላላው 27፣ በአፋር (3)፣ በሶማሌ (3)፣ በአማራ (4)፣ በትግራይ (3)፣ በደቡብ ክልል (4)፣ በኦሮሚያ (6)፣ በድሬደዋ (1)፣ እና በአዲስ አበባ (3) የቁጥጥር ሥፍራዎች አሉ፡፡ የእንስሳት ዋጋ በየሳምንቱ የገበያ ቀን በሠለጠኑ የእንስሳት ገበያ ተቆጣጣሪዎች አማካይነት ይመዘገባል፡፡ የእንስሳት የመረጃ አውታርና የእውቀት ሥርዓት በዓይን እይታ የቁመናና የክብደት መጠን (የሰውነት ክብደት %) በማየት ደረጃ የማውጣት ሥርዓት አለው፡፡

መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ መለያ ኮድ ተሰጥቶ ወዲያው በአጭር የጹሑፍ መልእክት ወደ ብሔራዊ የመረጃ ቋት ይተላለፋል፡፡ አብዛኛው የተሰበሰበው መረጃ በድህረገጽ (http://links.tamu.edu/pages/public/Home.aspx) እንዲገባ ይደረጋል፡፡

ሠንጠረዥ 3.3-5 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የእንስሳት መረጃ አውታርና የእውቀት ስርዓት የተሸፈኑ የገበያ ማዕከላት

| ዞን | የገበያ ማዕከል |
|---|---|
| ወላይታ | ቦዲቲ |
| ቤንች ማጂ | ሚዘን |
| ደቡብ ኦሞ | ጂንካ |
| ሃዲያ | ሆሳዕና |

ምንጭ: ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር "ረቂቅ ኢትዮጵያ ብርሔራዊ የገበያ መረጃ አገልግሎት ማቋቋሚያ ሰነድ (ሰኔ 2008 እ.ኤ.አ)

### (7) ሌሎች ክልላዊ መንግስታት

የመንግስት የሥልጣን ክፍፍል ወደ ታች ከወረደ በኋላ ክልሎች የግብርና የገበያ መረጃ አገልግሎት ሥራዎችን መሥራት ጀምረዋል፡፡

#### 1) የትግራይ ክልል

የትግራይ የመረጃ አገልግሎት በትግራይ የግብርና ግብይት ማስፋፊያ ኤጀንሲና በኢፋድ ድጋፍ የሚንቀሳቀሰው በክልሎች ደረጃ በደንብ የተደራጀና ሥርዓት ያለው ሆኖ ከየካቲት 2011 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ሆኖ የተቋቋመ ነው፡፡

በትግራይ ክልል በተለያዩ ገበያዎች ያለው የእህልና የእንስሳት ሳምንታዊ ዋጋ፣ የረዥም ጊዜ ዋጋና በግራፍ የታገዘ የዋጋና የአቅርቦት መረጃ በ (http://www.agrimartg.org) መረጃ መረብ ይገባል፡፡ ገበያ ትግራይ ትስስር ከጽሔት በወር ሁለት ጊዜ ይታተማል፡፡ እንደ የትግራይ የግብርና ማስፋፊያ ኤጀንሲ የመረጃ አጠናቃሪዎች የመረጃ ቋት መሠረት በጠቅላላው የ56 ዓይነት የግብርና ምርቶች መረጃ ይሰበስባል፡፡

በሚያዝያ 2012 (እ.ኤ.አ) ትግራይ የግብርና ግብይት ማስፋፊያ ኤጀንሲ መረጃ መረብ (http://www.agrimart.org) ተደራሽ አልነበረም ወይም አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን ትክክለኛ ምክንያቱ ባይታወቅም የአገልግሎት ማደሻው ጊዜ በመጋቢት 2012 (እ.ኤ.አ) የመጣና እንዲቀጥል ያልተደረገ ይመስላል፡፡

**2) የኦሮሚያ ክልል**

የኦሮሚያ ክልል በተመለከተ የግብርና ግብይት ኤጀንሲ ሙሉ ኃላፊነት ያለው አካል ነው፡፡ እስከ የካቲት 2011 (እ.ኤ.አ) የገበያ መረጃ አገልግሎት የዋና ዋና ተግባራት ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- 19 የገበያ ቦታዎች 4 የገበያ በአ/አበባ ጨምሮ ተመርጠዋል፤ በ14 የገበያ ቦታዎች ዋጋ ይሰበሰባል፡፡ የዋጋ መሰብሰብ ሥራ በ5 የገበያ ቦታዎች በቅርብ ጊዜ ይጀመራል፡፡
- ዋጋ መሰብሰቡ በአጠቃላይ 81 የግብርና ምርቶችን ያጠቃልላል፡፡ በሳምንት ሁለት ጊዜ ዋጋ ይሰበስባል፡፡
- የግብርና ምርቶች በየዓይነቱ ትንታኔ በዝርዝር ይካሄል፡፡ ብርዕና አገዳ ሰብልና ጥራጥሬ በዓይነት ሲተነተኑ፣ አንዳንድ አትክልትና ቅመማቅመም በምርት መነሻ ሁኔታ ይተነተናሉ፡፡
- የተሰበሰበ ዋጋ ዓይነት እንደሚከተለው ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| የጅምላ ሽያጭ ዋጋ (ዋጋ በ100 ኪ.ግ (ኩን)) | X | ዋጋዎች<br>(ዝቅተኛ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ) |
| የችርቻሮ ዋጋ በጭነት መኪና ላይ | | |
| የችርቻሮ ዋጋ በገበያ ቦታ | | |

- ምንም የጥራት መመዘኛ/ደረጃ ሥርዓት አልተጠቀሙም
- አንድ የመረጃ ሠራተኛ በአንድ የገበያ ሥፍራ ይመደባል፡፡ የመረጃ ሠራተኞች የወረዳ አስተዳደር ሠራተኞች ናቸው፡፡
- የተሰበሰበው መረጃ በሞባይል ስልክ (ከክልል ቢሮ ለመረጃ ሠራተኞች በሚደወል ስልክ) ይተላለፋል፡፡ መረጃው በኤክስኤል ሠንጠረዥ ይጠራቀማል፡፡ ሌላ ምንም ዓይነት ሶፍትዌር ጥቅም ላይ አይውልም፡፡
- የመረጃውን ተዓማንነት ለማረጋገጥ የክልሉ ቢሮ ሠራተኞች የገበያ ቦታውን (ወረዳውን) በየጊዜው ይጎበኛሉ፡፡
- ወረዳ ኔት ለመረጃ ማስተላለፊያ ሥራ ላይ ውሎ ነበር፡፡ ሆኖም ወጪው ስለናረ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡
- የመረጃ መረብ ለመረጃ ማስተላለፊያና ማሰራጫ በመስራት ላይ ነው፡፡

የመረጃ መረብ (www.oromiyaa.gov.et) በ2011 (እ.ኤ.አ) አጋማሽ ላይ ተደራሽ ነበር፡፡ ሆኖም ከሚያዝያ 2011 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ተቋርጧል፡፡

### 3.3.2 ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒሰቴር የግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት

የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት በመጋቢት 2011 (እ.ኤ.አ) የተለያዩ የገበያ መረጀ ሥርዓቶችን በብሔራዊ ሥርዓት ውስጥ ለማካተት ለማስተሳሰር ሃሣብ ነበረው፡፡ ይህንን ሃሣብ ተግባራዊ ለማድረግ ተስማሚ የሆነ ዲዛይንና ይዘት ያለው ብሔራዊ መረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት ሚኒስቴሩ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም፡- ከማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ ከኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፕራይዝ፣ ከእንስሳት የመረጃ አውታርና የእውቀት ሥርዓት፣ ከዓለም የምግብ ፕሮግራምና ከሕ/ሥራ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ጥናት አካሂዶ ነበር፡፡

እንደ ግብርና ግብይት ሥርዓት ልማት የቅርብ ጊዜ መረጃ መሠረት "በኢትዮጵያ የብሔራዊ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ለማቋቋም የሥራ ዶክመንት ጥር 2008 እ.ኤ.አ" ተዘጋጅቷል፡፡ ተቋማዊ የብሔራዊ ግብርና መረጃ አገልግሎት አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

(1) ሥርዓቱ በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሲመራ የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ የአማካሪነትና እስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማተም ሚና ይኖረዋል፡፡

(2) የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ባለድርሻ አካላት ሚና እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ/ የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት፡ የገበያ ተቆጣጣሪ ቡድን ከሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ጋር የመረጃ መሰብሰብ፣ ማስተላለፍ፣ ማጠራቀምና የዋጋ መረጃ ማሠራጨትና የአቅርቦትና ፍላጐት መረጃ በቋሚነት ይሠራል፡፡

ለ/ የክልሉ የግብርና ግብይት ኤጀንሲ/ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፡ የገበያ መረጃ ሥርዓት ደንቦች/መመሪያዎች የማውጣት፣ የማስተባበርና የመቆጣጠር፣ ወጥ የሆኑ የምርት ደረጃ፣ መለኪያ/ክብደት መመዘኛ ቅጾችን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡ የመረጃ ቋት የመክፈትና ከፌዴራል የመረጃ ቋት ጋር የማገናኘት ሥራ ይሠራል፡፡ ለክልሉ ተጠቃሚዎች መረጃ ያስተላልፋል፡፡ የገበያ ተቆጣጣሪዎችና የመረጃ አጠናቃሪዎች ሥልጠና መስጠትና በመስክ ላይ ክትትል የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡

ሐ/ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በፌዴራል ደረጃ የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት ያቋቁማል፡፡ የገበያ መረጃ ያጠራቅማል፣ ይተነትናል፣ ለሀገር ውስጥና ለዓለምአቀፍ የገበያ መረጃ ያሠራጫል፡፡ የደንበኛን ፍላጐት ይዳሰሳል፣ የገበያ መረጃ ለአርሶአደሮች፣ ለነጋዴዎች፣ ለአቀነባባሪዎች፣ ለአስመጪዎችና ላኪዎች ያቀርባል፡፡ የገበያ ዕምቅ ኃይል ያለበትን ይቃኛል፡፡ የገበያ ድርሻ፣ የሥርጭት መስመሮች፣ ፍላጐትና አቀርቦትን፣ ሽያጭንና የገበያ ልማት ይተነትናል፡፡

መ/ ተባባሪዎች፡- የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ኢንተርፐራይዝ፣ ማዕከላዊ የእስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ፣ ፋኦ፣ የእንስሳት መረጃ አውታርና የእውቀት ሥርዓት ወዘተ ናቸው፡፡

ኢፋድ/አሚፕ የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴርን በግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ልማት ይደግፋል፡፡ እንደ መጋቢት 2010 (እ.ኤ.አ) የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር መረጃ የገበያ መረጃ ቡድን በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ውስጥ ተቋቁሟል፡፡ ሚኒስቴሩም የተጀመረውን የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ይኸውም የኮድ አሰጣጥ ሥርዓት፣ የጥራት ደረጃና መመዘኛ ሥርዓት ለማጠቃለል ዓለምአቀፍ አማካሪ በዚያው በ2010 (እ.ኤ.አ) ይቀጥራል፡፡ የግብርና ገጠር ልማት ማኒስቴር የግብርና ግብይት ዳይሬክቶሬት በጥቅምት 2010 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ወደ ንግድ ሚኒስቴር እንዲዞር ተደርጓል፡፡

### 3.3.3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግስት የግብርና የገበያ መረጃ ሥርዓት አሠራር

#### (1) ከጥናቱ ጊዜ በፊት የነበረው የግብርና ገበያ መረጃ ሥርዓት ታሪካዊ ሁኔታ

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ (የግብይት ኤጀንሲ) ከ32 ዋና ዋና የገበያ ቦታዎች የዋጋ መረጃ የሚሰበሰቡና የተሰበሰበውን የዋጋ መረጃ በሬዲዮ፣ በፋክስና በመረጃ መረብ የሚያሠራጩ የገበያ መረጃ አገልግሎት ለማቋቋም ሃሣብ ነበረው፡፡ ሆኖም የአፈፃፀም ጊዜና አሠራር የሚያሣይ መሠረታዊ ዕቅድ አልተዘጋጀም፡፡ የበለጠ ግልጽ ለመሆን በወረቀት ላይ የተፃፈ ዕቅድና ዝርዝር የአሠራር ደንቦች አልተዘጋጁም፡፡ ይሁን

እንጂ የቀድሞው የግብይትና ግብዓት የሥራ ሂደት ባለቤት የአገልግሎትና የአጠቃቀም ሥርዓት ለመዘርጋት የሚከተለው ሃሣብ ነበረው፡፡

- ያለፈው ሳምንት የዋጋ መረጃ ከተለያዩ የገበያ ሥፍራዎች (ከክልሉ ውጭ ያሉትን እንደ አ/አበባ ጭምር) የተሰበሰበውን የመረጃ መረብ በመጠቀም ለእያንዳንዱ ወረዳ በፋክስ በቴሌፎን፣ በሬዲዮ ማሰራጨት፤ በገበያ ቦታም ማሳየት፡፡
- ወቅታዊ የዋጋ መረጃ በሞባይል ማሰራጭት፣ አጭር የጽሑፍ ምልክትና በገበያ ቦታ ማስተዋወቅ፡፡
- የመረጃ ቋት ሥርዓት በፋኦ ሶፍትዌር "ፋኦ አግሪ ገበያ" (ማይክሮ ሶፍት አክሰስ)
- የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የገበያ ትንተና ሪፓርት ማቅረብ፡፡

ሃሣቡን ተግባራዊ ለማድረግ በ2008 (እ.ኤ.አ) ሳምንታዊ የችርቻሮ ዋጋ መረጃ ለመሰብሰብና የሙከራ ሥራ ለመጀመር 15 የገበያ ሥፍራዎች ተመርጠው ነበር፡፡ በመረጃ የማሰባሰብ ዘዴና መመሪያ የተለያዩ ቅጾች ተዘጋጅተው ሥልጠና በግንቦት 2008 (እ.ኤ.አ) ለዞንና ለወረዳ ባለሙያዎች ተሠጥቷል፡፡ ለእያንዳንዱ ወረዳዎች የፋክስ ማሽን ተሠጥቷል፡፡ በክልሉ ም/ቤት በተቋቋመው የግብይት ኤጀንሲ ጽ/ቤት የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት እንዲገባ ተደርጓል፡

**ሠንጠረዥ 3.3-6 በ2008 የተመረጡ 15 የገበያ ሥፍራዎች**

| ዞን/ልዩ ወረዳ | | የገበያ ቦታ | ዞን/ልዩ ወረዳ | | የገበያ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከምባታ ጠምባሮ | ዱራሜ | 12 | ሸካ | ቴፒ |
| 2 | ሃዲያ | ሆሳዕና | 13 | ከፋ | ቦንጋ |
| 3 | ወላይታ | ሶዶ | 14 | አላባ ልዩ ወረዳ | አላባ |
| 4 | ሲዳማ | ሀዋሣ፣ ዳዬ (በንሳ) | 15 | የም ልዩ ወረዳ | --- |
| 5 | ጋሞ ጎፋ | አርባ ምንጭ | 16 | ደራሼ ልዩ ወረዳ | --- |
| 6 | ዳውሮ | --- | 17 | አማሮ ልዩ ወረዳ | --- |
| 7 | ጉራጌ | ቡታጅራ | 18 | ቡርጂ ልዩ ወረዳ | --- |
| 8 | ስልጤ | ወራቤ | 19 | ኮንሶ ልዩ ወረዳ | --- |
| 9 | ቤንች ማጂ | ሚዛን | 20 | ኮንታ ልዩ ወረዳ | --- |
| 10 | ጌዲኦ | ዲላ፣ ወናጎ | 21 | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | --- |
| 11 | ደቡብ ኦሞ | ጅንካ | | | |

ምንጭ፡ ጃይካ የመጀመሪያ ጥናት ሪፖርት 2009 (እ.ኤ.አ)

ቢ.ፒ.አር በ2008 (እ.ኤ.አ) ተጀምሯል፡፡ የግብይት ኤጀንሲ የግብይትና ግብዓት አቅራቢ የሥራ ሂደት ሆኖ ወደታች ዝቅ ብሎ በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሥር እንዲሆን ተደረገ፡፡ ብዙዎች የሠለጠኑ በዞንና ወረዳ ደረጃ ያሉ ባለሙያዎች ቦታቸውን ቀይረዋል ወይምን እንደገና ተመድበዋል፡፡ ስለሆነም ቀደም ሲል የተጀመረው ሳምንታዊ የችርቻሮ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ በ15 ገበያ ሥፍራዎች የተጀመረው አልቀጠለም፡፡

የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በ2009 (እ.ኤ.አ) ሁለት አዳዲስ ተመራቂ ባለሙያዎች ቀጥሮ ለመረጃ ቋት አስተዳደርና ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት እንዲሠሩ አደረገ፡፡ የፋኦ አዲስ የመረጃ ቋት ሶፍትዌር "ፋኦ አግሪ ገበያ" በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር አማካይነት በ2009 (እ.ኤ.አ) ለግብይት ሥራ ሂደት እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ የአንድ ስዓት የሶፍትዌሩ አሠራር በፋኦ ባለሙያ እንዲታይ ከተደረገው ውጭ ተግባራዊ የሶፍትዌር የአጠቃቀም ሥልጠና ለግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ባለሙያዎች አልተሰጠም፡፡ ከተቀጠሩት አንዱ ባለሙያ በ2009 ()እ.ኤ.አ) ወደ ትግራይ ክልል ሄዶ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት አሠራር እንዲያይ ተደርጓል፡፡

### (2) በጥር 2010 (እ.ኤ.አ) ጥናቱ በተጀመረበት ወቅት የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት አሠራርና የአመራር ሥርዓት ያለበት ሁኔታ

የግብይትና የግብዓት አቅራቢ ዋና የሥራ ሂደት ተብሎ በህዳር 2009 (እ.ኤ.አ) በሁለት የሥራ ሂደቶች ተከፍሏል፡፡ እነርሱም የግብይት ዋና የሥራ ሂደትና የግብዓት ዋና የስራ ሂደት ናቸዉ፡፡ የግብይት ዋና የሥራ ሂደት በአጠቃላይ 8 ባለሙያዎች ያሉት ሲሆን 1 በዋጋ መረጃ ማሰባሰብ ሙሉ ጊዜ የሚሠራ ባለሙያ በ2009 ተቀጥሯል፡፡ ሌሎች 2 ባለሙያዎች ከዞን ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ በግማሽ ጊዜ እንዲያግዙ የተመደቡ በዋጋ መረጃ ማሰባሰብ ይሠራሉ፡፡

በገበያ መረጃ አገልግሎት ተግባራት የሚከተሉት ናቸው

- ሳምንታዊ የዋጋ መረጃ ከ14 ዞን/ልዩ ወረዳ ማሰባሰብ
- የዋጋ መረጃ ለክልሉ ቢሮ በፋክስ፣ በቴሌፎን ወይም በሰው መላክ
- የተሰበሰበውን መረጃ (በእህል ምርት ብቻ) በሠንጠረዥ (ማይክሮ ሶፍት ኤክስኤል) ይጠቃለላል፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ ተግባራዊ ባይሆንም እንኳን ለሁሉም ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች በየወቅቱ ለማሠራጨት ታቅዶ ነበር፡፡

#### ሠንጠረዥ 3.3-7 መረጃ የሚሰበስቡ ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች

| ዞን/ልዩ ወረዳ | | መረጃ አሰባሰብ | ዞን/ልዩ ወረዳ | | መረጃ አሰባሰብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከምባታ ጠምባሮ | X | 12 | ሸካ | X |
| 2 | ሃዲያ | X | 13 | ከፋ | X |
| 3 | ወላይታ | X | 14 | አላባ ልዩ ወረዳ | X |
| 4 | ሲዳማ | X | 15 | የም ልዩ ወረዳ | |
| 5 | ጋሞ ጎፋ | X | 16 | ደራሼ ልዩ ወረዳ | |
| 6 | ዳውሮ | | 17 | አማሮ ልዩ ወረዳ | X |
| 7 | ጉራጌ | X | 18 | ቡርጂ ልዩ ወረዳ | |
| 8 | ስልጤ | X | 19 | ኮንሶ ልዩ ወረዳ | |
| 9 | ቤንች ማጂ | X | 20 | ኮንታ ልዩ ወረዳ | |
| 10 | ጌዲኦ | X | 21 | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | |
| 11 | ደቡብ ኦሞ | X | | | |

#### ሠንጠረዥ 3.3-8 የመረጃ ማሰባሰቢያ ምርቶችሰብልና ሌሎች

| | | |
|---|---|---|
| ሰብልና ሌሎች | ብርዕና አገዳ | ጤፍ፣ (ነጭ፣ ድብልቅ፣ ቀይ)፣ ስንዴ፣ ነጭ፣ ቀይ)፣ በቆሎ |
| | ጥራጥሬ | ቦሎቄ (ነጭ፣ቀይ) ባቄላ፣ አተር |
| | ፍራፍሬ | ሙዝ፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ አናናስ፣ አፕል |
| | ቅመም | በርበሬ፣ ኮሮርማ፣ ዝንጅብል |
| | ሌሎች | ማር |
| እንስሳት | በሬ | በሬ (ትልቅ፣ መካከለኛ)፣ የእርሻ በሬ፣ ኮርማ፣ ጥጃ |
| | ላም | የምትታለብ ላም፣ ያነጠፈች ላም፣ ግደር፣ ጥጃ |
| | ፍየል | ሴት ፍየል፣ ወንድ ፍየል፣ የደለበ ፍየል፣ ግልገል |
| | በግ | ሴት በግ፣ ወንድ ፣ የደለበ በግ፣ ጠቦት |
| | ዶሮ | አውራ ዶሮ፣ እንቁላል ጣይ ዶሮ፣ ቄብ |

ምንጭ፡ : ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

### (3) በመጀመሪያ ዓመት (ከጥር-ሚያዚያ እና ከሐምሌ-መስከረም 2010 እ.ኤ.አ) በመስክ ሥራ የታዩ ችግሮች

በቀላሉ ለማስቀመጥ የግብርና ገበያ ግብይት መረጃ አገልግሎት (የመረጃ ማሰባሰቢያ ሥርዓት) በአስተዳደር ሰንሰለት የገበያ ሂደት በሥርዓት የተደራጀ ካለመሆኑም በላይ በሕግና ደንብ የሚሠራ አይደለም፡፡ የዚህ ዋና ምክንያቱ የተፃፈ ደንብና መመሪያ ያለመኖር እና የባለሙያ እጥረት ናቸው፡፡

1) ዋና ዋና ችግሮች

- ለግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ከአንዳንድ ዞን ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያ የሚተላለፈው መረጃ ወቅታዊ አለመሆን፡፡ አንዳንድ ዞኖች እንደ ሃዲያ፣ ከፋና ካምባታ ጣምባሮ ያሉት መረጃ ወደ ክልል የሚልኩት አንዳንድ ጊዜ ነው፡፡ ከምባታ ጠምባሮ ዞን በግብይት ዋና የሥራ ሂደት 2 ባለሙያዎች ብቻ ያሉት ሲሆን እነርሱም ተጨማሪ ባለሙያ ካልተመደበ የዋጋ መረጃ የሚሰበስቡትን እንደሚያቁሙ ገልፀዋል፡፡
- የምርት ዓይነቶች እንዲሁም የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾችና ማጠቃለያ ቋት በቅርብ ጊዜ ተከልሰዋል፡፡ ሆኖም አሁንም ብዙ ዞኖችና ወረደዎች አሮጌውን ቅጾች ወይንም የራሳቸውን ቅጾች ይጠቀማሉ፡፡ ስለሆነም በመረጃ ቋት ላይ አንድ ዓይነት ወይም ወጥ አሠራር የለም፡፡
- በመረጃ አሰባሰብ ታሣቢ የተደረገው በአንዱ የምርት ዓይነት ከ5 የተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ሲሆን ይህ ሕግ በሁሉም አካባቢ በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ የሆነ አይመስልም፡፡
- የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች የዞን ግብርናና ገጠር ልማት መምሪያዎች ከወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤቶች አንድ ዓይነት አይደለም፡፡ አንዳንድ ዞኖች ለምሳሌ እንደ ሲዳማ ዞን ያሉት መረጃውን ከየወረዳዎች በወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የግብይት ዋና የሥራ ሂደት አማካይነት ይሰበስባሉ፡፡ በሊላ በኩል እንደ ካምባታ ጣምባሮ ዞን ያሉት የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ለመረጃ ማሰባሰብ አይጠቀሙም፡፡ ከዚህ ይልቅ የዞን ባለሙያዎች ቀጥታ ከገበያ ሥፍራ በዞን ዋና ከተማ መረጃውን ይሰበስባሉ፡፡
- በወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተሰበሰበው መረጃ በአብዛኛው ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውለም፡፡ እንዲሁም ፋይል ተደርጎ ይቀመጣል፡፡
- የተሰበሰበው መረጃ ተዓማንነት ለማረጋገጥ ምንም ወቅታዊ ክትትል ሥራ አይሠራም፡

2) የተገለጹ ችግሮች መንስኤዎች

- የተሰበሰበው የዋጋ መረጃ አገልግሎት (የቅድሚያ የሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች) ግልፅ አይደለም፡፡ የተሰበሰበውን ዋጋ መረጃ በምን መልክ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የጋራ የሆነ ግንዛቤ የለም፡፡
- የግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎት የተዘጋጀ በጽሑፍ የተቀመጠ መመሪያ የለም፡፡ ከዚህ የተነሣ የሥራ ዝርዝረና የአሠራር ሥርዓታዊ የሆነ አደረጃጀት የለም፡፡
- የባለሙያ እጥረት

የግብይትና ግብዓት አቅራቢ የሥራ ሂደት በግብይት ሥራ ሂደትና የግብዐት ሥራ ሂደት በመባል በህዳር 2009 (እ.ኤ.አ) ለሁለት ተከፍለዋል፡፡ በዚህ መሠረት በዞን ደረጃ ይኖራሉ ተብሎ የተገመተው የባለሙያ መጠን ከ5-8 ሲሆን ከ6-7 በወረዳ ደረጃና 18 በክልል ደረጃ ነበር፡፡ ሆኖም ትክክለኛ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ከ2-3 በአብዛኛው ዞኖችና ወረዳ ደረጃ ሲሆን በክልል ያሉት 8 ብቻ ናቸው፡፡ ብዙ ዞኖች/ወረዳዎች በተለይ ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት የተመደቡ ባለሙያዎች የሉም፡፡

## ሠንጠረዥ 3.3-9 የባለሙያዎች ቁጥር በዞን/ልዩ ወረዳ የግብይት ሥራ ሂደት (ሰኔ 2010 እ.ኤአ)

| ዞን/ልዩ ወረዳ | ግብያት የሥራ ሂደት ባለሙያዎች | የወረዳ ብዛት | የዋጋ መረጃ በሚሰበስብ ዞን.ስር ያለ ወረዳ ብዛት *1 | በግብይት የሥራ ሂደት ባለሙያ ያለው ወረዳ ብዛት * 1 | የዋጋ መረጃ ኃላፊነት ያው በለሙያ ያለው ወረዳ ብዛት | ገበያ ቦታ ያለ በመሙያ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | አማካይ. | ዝቅተኛ | ከፍተኛ. |
| 1 ጉራጌ | 3 | 13 | 12 | 13 | 12 | 3.6 | 3 | 6 |
| 2 ስልጠየ | 2 | 8 | 5 | 5 | 2 | 2.2 | 2 | 3 |
| 3 ሃዲያ *2 | | 10 | | | | | | |
| 4 ከምባታ ጠምባሮ | 3 | 7 | 7 | 7 | 7 | 2.9 | 3 | 4 |
| 5 ወላይታ | 3 | 12 | 9 | 10 | 8 | 3.5 | 3 | 5 |
| 6 ሲዳማ | 4 | 19 | 16 | 17 | 15 | 3.6 | 3 | 6 |
| 7 ጌዲኦ | 3 | 6 | 6 | 6 | 5 | 3.2 | 2.5 | 6 |
| 8 ጋሞ ጎፋ | 4 | 15 | 3 | 4 | 2 | 2.3 | 1.5 | 5 |
| 9 ዳውሮ | 2 | 5 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 10 ከፋ | 1 | 10 | 3 | 3 | 1 | 2.3 | 2 | 4 |
| 11 ሸካ | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 12 ቤንች ማጂ | 3 | 10 | 8 | 8 | 5 | 2.3 | 2 | 4 |
| 13 ደቡብ ኦሞ | 3 | 8 | 4 | 4 | 2 | 1.5 | 1 | 3 |
| 14 አላባ ልዩ ወረዳ | 3 | | | | 1 | | | |
| 15 የም ልዩ ወረዳ | 2 | | | | 1 | | | |
| 16 ኮንታ ልዩ ወረዳ | 3 | | | | 1 | | | |
| 17 ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | 1 | | | | 0 | | | |
| 18 አማሮ ልዩ ወረዳ | 3 | | | | 1 | | | |
| 19 ቡርጂ ልዩ ወረዳ | 3 | | | | 1 | | | |
| 20 ደራሼ ልዩ ወረዳ | 3 | | | | 1 | | | |
| 21 ኮንሶ ልዩ ወረዳ | 4 | | | | 0 | | | |
| ድምር | 55 | 126 | 78 | 81 | 68 | | | |

*1፡ የከተማ አስተዳዳር አይጨምርም *2: ከሃዲያ ዞን ምላሽ አልተገኘም

ምንጭ፡ የግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ዳሰሳ ጥናት (ሰኔ-ሐምሌ 2010 እ.ኤ.አ), ግርናና ገጠር ልማት ቢሮ/ ጃይካ ጥናት ቡድን

- *የዕቃዎች ውስንነት*

  *ለሥራ የሚያስፈለጉ ሀብቶች (ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር፣ ፋክስ የቢሮ ሥፍራ) በቂ አይደሉም በተለይ በአዲስ መልክ የተዋቀሩ ወረዳዎች፡-*

  *የግብርናና ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ተሻሽሎ የግብርና ቢሮና የግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በመባል በጥቅምት 2010 (እ.ኤ.አ) ሲደራጅ በወረዳም በተመሳሳይ መልክ ተደራጅተዋል፡፡ ብዙ ቁጥር ያላቸው የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ወደ አዳዲስ ጽ/ቤቶች ገብተዋል፡፡ በዚህ መሠረት ቀድመውንም ደካማ የነበሩ የጽ/ቤት ዕቃዎች ወደ ባሰ ሁኔታ /ወንበርና ጠረጴዛ ብቻ/ ይዘው ይገኛሉ፡፡*

- *የሥራ ማስኬጃ በጀት እጥረት ወይም አለመኖር፡-*

  *የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች/ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች (ደስጣ ወረቀት፣ የፕሪንተር ቀለም ወዘተ) ለግንኙነት (ሞባይል ካርድ) እና ለትራንስፖረት (የአውቶቡስ ክፍያ፣ ለነዳጅ) በቂ የሥራ ማስኬጃ በጀት የላቸውም፡፡ 14 ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 እንደገለፁት ለአላቂ ዕቃዎች እንደ ወረቀትና እስፒል ያሉ የዋጋ መረጃ በማስታወቂያ ቦርድ ለመለጠፍ የበጀት እጥረት እንዳጋጠማቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡*

<u>ሌሎች ችግሮች</u>

- የገበያ ቀናት ተመሳሳይ አለመሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች የገበያ ቀን ቅዳሜ ነው፡፡
- የዞንና የወረዳ ወደ ወጭ የሚልኩትን በሚመለከት የክልል ባለሙያዎች ለማዘዝ ምንም ሥልጣን የላቸውም፡፡

## 3.3.4 ለግብርና ገበያ መረጃ አገልግሎትና የመረጃ ልማት ያሉ ሀብቶች

### (1) የሞባይል ቴሌፎን አገልግሎትና የመረጃ ግንኙነት አገልግሎት

ሞባይል ቴሌፎን ለማንኛውም የንግድ እንቅስቃሴ ወሳኝ መሣሪያ ነው፡፡ እንደሚባለው የግብርና ምርት ጋር የተያያዙ ነጋዴዎች በሙሉ የሞባይል ቴሌፎን አሏቸው፡፡ በሌላ አንፃር የሞባይል ቴሌፎን ያሏቸው አርሶአደሮች በጣም ውሱን ናቸው፡፡ ሆኖም ብዙ የዩኒየን/የመጀመሪያ ደረጃ የሕ/ሥራ ማህበራትና የቀበሌ አመራር አርሶአደሮች ሞባይል ይጠቀማሉ፡፡ በኢትዮጵያ የሞባይል ቴሌፎን አገልግሎት በሞኖፓል የተያዘው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፓሬሽን ሀዋሣ ቅርንጫፍና ወላይታ ቅርንጫፍ የደቡብ ክልል አካባቢ ይሸፍናሉ፡፡ የሞባይል ኔትወርክ በዋና ዋና መንገዶች በሚተላለፉበት አካባቢ በአብዛኛው በደቡብ ክልል ሸፍኗል፡፡ የገጠር አካባቢ የሆኑት እንደ ሸካ ዞን፣ የም ልዩ ወረዳ፣ አማሮ ልዩ ወረዳ፣ እና ባስኬቶ ልዩ ወረዳ እስከ ታህሣስ 2009 (እ.ኤ.አ) የክልሉ የአቅም ግንባታ ቢሮ መረጃ መሠረት በኔትወርክ አልተሸፈኑም፡፡

ሁለት ዓይነት የሞባይል ኢንተርኔት አገልግሎት አሉ፡፡ ሲዲኤምኤ እና ኢቪዲዮ የሚባሉ ሲሆን ተጠቃሚዎችም እየጨመሩ ይገኛሉ፡፡ የሲዲኤምኤ ፍጥነት 3 ሜጋ ባይት ነው፡፡ የሲዲኤምኤ የመረጃ ማስተላለፊያ በጣም ፈጣን ባይሆንም (ከመደበኛ የስልክ መደወል ትንሽ የሚሻል ነው) የአገልግሎት ክፍያ እርካሽ ነው፡፡ (6ብር በሰዓት) እና የሲዲኤምኤ አገልግሎት ከኢቪዲዮ አገልግሎት ይልቅ ሰፋ ያለ አካባቢ ይሸፍናል፡፡ ኢቪድዮ ሞዲየም (ዩኤስቢ ዓይነት) አገልግሎቱን ለማግኘት ያስፈልጋል፡፡ የኢቪድዮ አገልግሎት ክፍያ እርካሽ አይደለም፡፡ ከ300 - 500 ብር በወር ለ1 ጂቢ-2 ጂቢ መረጃ ለማስተላለፍ ያስከፍላል፡፡ የኢቪዲዮ አገልግሎት በአብዛኛው የገጠር አካባቢ የለም፡፡

በጥቅም ላይ የሚውሉ የግንኙነት ዕቃዎች በ14 የወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 የተሳተፉ ከዚህ በታች ተጠቃለዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.3-10 ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 የዝንጅብል ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በጥቅም ላይ የሚውሉ የግንኙነት ዕቃዎች (መጋቢት 2011 እ.ኤ.አ)**

| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | መብራት ኃይል | መደበኛ ስልክ | የኢንተርኔት ተደራሽነት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዳይ አፕ | ሞባይል ኢንተርኔት | ሲዲሜኤ |
| ቦሎሶ ሶሬ | አለ | አለ | አለ | (አለ) | አለ |
| ቦሎሶ ቦምቤ | አለ | የለም | የለም | አለ | የለም |
| ኪንዶ ኮይሻ | አለ | አለ | አለ | (አለ) | የለም |
| ሀዳሮ ጡንጦ | አለ | ?? | ?? | (አለ) | የለም |
| ጠምባሮ | የለም | የለም | የለም | (አለ) | የለም |

(አለ) በሞባይል ተሞክሮ ያልተረጋገጠ ግን በወረዳ አቻ ባለሙያ አለ ተብሎ የተገመተ

* የጃይካ ጥናት ቡድን አንድሮድ ሞባይል ስለሌለው የሞባይል ኢንቴርነት መቦሩን መፈተሽ አልቻለም (የኢትጵያ እህል ሰብል ገበያ እንተርፕራዝ አገልግሎት) በመጋቢት 2011 (እ.ኤ.አ)

**ሠንጠረዥ 3.3-11 ለሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 በሎቄ ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች በጥቅም ላይ የሚውሉ የግንኙነት ዕቃዎች (ሰኔ 2011 እ.ኤ.አ)**

| ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት | መብራት | መደበኛ ስልክ | | የኢንተርኔት ተደራሽነት | | ፋክስ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጽ/ቤት | በግቢ ውስጥ | ሞባይል ኢንተርኔት | ሲዲሜኤ | |
| ምስራቅ ባድዋቾ | አለ | አለ | | አለ | የለም | በግቢ ውስጥ ያለ ግን የማይሠራ |
| ምዕራብ ባድዋቾ | የለም ግን የታቀደ | የለም | የለም | ? | አለ | የለም |
| ዳሞት ጋሌ | አለ | አለ ግን የተቋረጠ | የለም | አለ | የለም | የለም |
| ሶዶ ዙሪያ | አለ | አለ | | አለ | አለ | የለም |
| አላባ | አለ | አለ | | አለ | ? | የለም |
| ሎኮ አባያ | አለ | ሽቦ አልባ ግን የማይሠራ | የለም | የለም | የለም | የለም |
| ቦርቻ | አለ | የለም | የለም | አለ | የለም | የለም |
| ቡርጂ | አለ | አለ | | ? | አለ | የለም |
| አማሮ | አለ | አለ | | ? | አለ | የለም |

ሞባይል አገልግሎት = የኢትጵያ እህል ሰብል ንግድ እንተርፕራይዝ አገልግሎት

የግንኙነት አገልግሎት በብዙ ወረዳዎች በጣም ውሱን ነው፡፡ የግብርናና ግብይት መረጃ አገልግሎት ኢንተርኔት በደቡብ ክልል ጥቅም ላይ እየዋለ አይደለም፡፡ የሞባይል ቴሌፎን አገልግሎት የድምፅና የአጭር መልእክት ለመረጃ ልውውጥ በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤቶች መካከል አሁን አገልግሎት እየሰጠ ያለ ብቸኛ መሣሪያ ነው፡፡

ሆኖም የሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01 ግልጽ እንዳደረገው አሁን ያለው የሞባይል ኔትወርክ የአጭር መልእክት አገልግሎት አስተማማኝ አይደለም ምክንያቱም የኔትወርክ መቋረጥ የአስቸኳይ መልእክት መቀበልና መላክ የዋጋ መረጃ ማስተላለፍ ሲያደናቅፍ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ መረጃው ተላልፎ እያለ የአጭር መልእክት የሚጠፋበት ሁኔታዎች ነበሩ፡፡፡

### (2) የሬዲዮ ጣቢያዎች

ደቡብ ኤፍ ኤም 100.9

ክልላዊ ኤፍ ኤም ሬዲዮ (ደቡብ ኤፍ ኤም 100.9) በደቡብ ክልል የብዙኃን መገናኛ ድርጅት (የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ) ሥር የሚሠራ ነው፡፡ ደቡብ ኤፍ ኤም 100.9 ዋና ጣቢያ በሀዋሣ ከተማ ያለው ሲሆን ሌሎች 7 ንዑስ ጣቢያዎች (ወልቂጤ፣ ቦንጋ፣ ሚዛን፣ ዋካ፣ አ/ምንጭ፣ጂንካና ደዬ) ሶገኙ የደቡብ ክልልን ይሸፍናሉ፡፡ ደቡብ ኤፍ ኤም 100.9 የዋጋ መረጃ የግብርና ምርቶችን ጨምሮ ከሰዓት በኂላ በ7:00 እና በ10:00 ይሠራጫል፡፡ እያንዳንዱ የሥርጭት ጊዜ 3 ደቂቃ ሲሆን በሣምንት 2 ጊዜ (3 ደቂቃ x 2ጊዜ በቀን x2ቀን በሣምንት) ይሠራጫል፡፡ የዋጋ መረጃ በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ (የንግድ ማስፋፊያ ዋና የሥራ ሂደት) ይቀርባል፡፡ የሌሎች ክልሎችና የአ/አበባ ዋጋ መረጃ በአሁኑ ጊዜ የሚሸፈን አይደለም፡፡ እነርሱ እንደሚሉት የንግድና ኢንድስትሪ ቢሮ የዋጋ መረጃ የሚያገኘው ከሸማቾች ሕ/ሥራ ማህበራትና ከሌሎችም ነው፡፡

አሁን ያለውን ፕሮግራም ለማሳደግ ከፍተኛ እድል እንዳለ ይኸውም የዋጋ መረጃ በተጨማሪ ምርት/ የገበያ ሥፍራና የሥርጭት ድግግሞሽ መጨመር እንደሚቻል ተገምቷል፡፡ እያንዳንዱ አካባቢም የገበያ መረጃ ማስረጫት ይገባል፡፡

<u>የማህበረሰብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች</u>

በደቡብ ክልል 3 የማህበረሰብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች አሉ። ስማቸውም ከምባታ ማህበረሰብ ሬዲዮ (ከምባታ ጠምባሮ ዞን) ፣ አማሮ ማህበረሰብ ሬዲዮ (ሰገን ዞን)፣ ሲዳማ ማህበረሰብ ሬዲዮ (ሲዳማ ዞን) ናቸው። የከምባታ ማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ የገበያ መረጃ በነፃ ለማሠራጨት መስማማቱን ለማረጋገጥ ችለናል። በሌላ በኩል የአመሮ ማህበረሰብ ሬዲዮ የገበያ መረጃ ለማሠራጨት በተወሰነ ክፍያ ሊያሠራጭ ተስማምቷል፡ የዞን ግብይትና ሕ/ሥራ መምሪያ ለካምባታ ማህበረሰብ ሬዲዮና የሲዳማ ማህበረሰብ ሬዲዮ የዋጋ መረጃ የሚያቀርበው መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ነው።

<u>ኤ.ኤም ሬዲዮ ጣቢያ</u>

የትምህርት በሬዲዮ ጣቢያ በወላይታ ሶደ ከተማ ይገኛል። ይህ የሬዲዮ ጣቢያ የኤ.ኤም ሞገድ ይጠቀማል። ከትምህርት ሥርጭት ፕሮግራም መካከል ባለው ትርፍ ሰዓት የዋጋ መረጃ በጥቂት ክፍያ ለማሠራጨት እንደሚቻል ለማረጋገጥ ችለናል።

### (3) ወረዳኔት (የኢትዮጵያ መንግስት ኔትወርክ)

ወረዳኔት የመንግስት ኔትወርክ ሲሆን ሁሉንም ወረዳዎች፣ ዞኖች፣ ክልሎችና ፌደራል መንግስታዊ መ/ቤቶች በአጠቃላይ የሚያገናኝ ነው። ወረዳኔት ለመሬትና ለሳተላይት ኔትወርክ ዲዛይን ተደርጎ የተሠራ ነው። ዋናው ዓላማ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት እንደ ቪዲዮ ኮንፍራንሲንግ፣ ዳይሬክተሪ፣ መልእክትና ድምፅ እንዲሁም የኢንተርኔት ግንኙነት ለፌዴራል፣ ክልላዊና ወረዳ ደረጃ መንግስት አካላት ማስተላለፍ ነው። የወረዳ ኔት ዋና ዋና ዓላማዎች እንደሚከተለው ነው።

- በከተማና ገጠር ከሚኒቲዎች መካከል መሸጋገሪያ ለመፍጠር፣
- ለሕዝቦች ዕውቀትንና መረጃን ለማቅረብ፣
- በሁሉም መንግስታዊ አካላት ዘንድ ድርጅታዊ አቅም ለመገንባት፣
- ለአነስተኛ ደረጃ የመንግስት አካላት ትክክለኛ መረጃ ለማድረስ ነው።

ወረዳ ኔት ቪሳት እና የመሬት ላይ ግንኙነት በመጠቀም ኢንተርኔትና ከሌሎች ወረዳኔት ር ለማገናኘት ይጠቀማል። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ተከላና ኮሚሽን እንዲሁም ለሥራው ኢንጂነሮች ምደባ በአቅም ግንባታ ሚኒስቴርና። የመብራት ኃይል በሌሉባቸው አካባቢዎች የዲዚል ጄኔሬተሮች ተተክለዋል።

በክልል ውስጥ ካሉት 134 ወረዳዎች 104 (80%) የሚሆነው በመጋቢት 2010 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ወረዳኔት ሽፋን አግኝቷል። ወረዳኔት የመንግስት ኔትወርክ ሲሆን የገበያ መረጃ ለማሠራጨትና ለመቀበል የሚያገለግል ሲሆን በመሠረቱ በጣም አጥጋቢ አገልግሎት ይሰጣል።

ሆኖም በሐምሌ 2010 (እ.ኤ.አ) በተደረገው የመስክ እይታ ብዙ ችግሮች ተስተውለዋል። ከእነዚህም:-

- የኢንተርኔት አጠቃቀም ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በኋላና በፊት በጣም የተወሰነ ነው። ይሁንና በመበደኛ ሥራ ሰዓት ለመጠቀም ከሚመለከታቸው ቢሮዎች ጋር በመነጋገር ማስተካከል ይቻላል።

- ለወረዳኤት ሥራ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው በሌለበት ጊዜ ኔትወርኩ ለመጠቀም አይቻልም፡፡
- ለግብርና ግብይት መረጃ አገልግሎት ኮምፒውተር ለመትከል የሚኖረው ቦታ በወረዳኤት ከቦታ ቦታ የተለያየ ነው፡፡

የክልሉ ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የወረዳኔት በመጠቀም ከወረዳዎች የፋይናንስ መረጃ ወደ መረጃ ቋታቸው እንዲያስተላልፉ ኮምፒውተር በችያንዳዱ ወረደኔት በማስቀመጥ መጠቀም ጅምሮ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ አሠራር በአጭር ጊዜ እንዲቋርጢልል፡፡ ይህም የሆነበት በርካታ ወረቀት በየእለቱ ወደ ወረዳኔት በመሸከም በተፈጠረው ችግር ምክንያት ነው፡፡ እስከ አሁን መጋቢት 2012 (እ.ኤ.አ) ድረስ በደቡብ ክልል የግብርና አስተዳደር ይህንን ሥርዓት የተጠቀመ የለም፡፡

## 3.4 በአሁኑ ወቅት ያለው የግብርና ግብይት መሠረተልማት

### 3.4.1 የመንገድ ሁኔታ

በባለቤትነትንና አስተዳዳርን መሠረት በማደርግ የመንገድ አውታሮች የክልልና የፌዴራል መንግሥት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ በተጨማሪ የክልል መንገዶች ጠጠር የለበሰና ያልለበሰ ተብለው ይለያሉ፡፡ ክረምት ከበጋ ወይንም የማህበረሰብ መንገድ ይባላሉ፡፡ የመንገድ አውታር ደረጃና የማስተዳደር ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.4-1 የመንገድ አውታር ደረጃና ኃላፊነት**

| የመንገድ አይነት | | ኃላፊነት/ አስፈጻሚ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ፌዴራል መንግሥት | ገጠር መንገድ ባለሥልጣን | ወረዳ | ቀበሌ | ሌሎች |
| ክረምት ከበጋ ምንገድ | አስፋልት ንጣፍ(ዲኤስ1, ዲኤስ2) | ◎ | ◎ | | | |
| | የፌዴራል መንግሥት ጠጠር መንገድ (ዲኤስ6-ዲኤስ8) | ◎ | | | | |
| | የክልል መንግሥት ጠጠር መንገድ (ዲኤስ6-ዲኤስ8) | | ◎ | ◎ | | |
| የበጋ መንገድ | ጠጠር ያልለበሰ መንገድ (ዲ.ኤስ9) | | | ◎ | | |
| | መንገድ (ዲኤስ10) | | | ◎ | | |
| | የማህበረሰብ መንገድ (ዲኤስ 10) | | | ◎ | ◎ | |

ምንጭ : የጥናት ቡድን

የመንገድ ደረጃ በ10 ዓይነት ሊከፋፈል ይችላል፡፡ ከዲኤስ 1 እስከ ዲኤስ10 የመንገድ ስፋት፣ የመንገድ ንጣፍ እንደ አስፋልት፤ ጠጠር ንጣፍ እና ምንም ያልተነጠፈበት ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡ ዲኤስ 1 እና ዲኤስ 2 አስፋልት ንጣፍ የለበሱ ሲሆን ዲኤስ 3 እስከ ዲኤስ 8 ያሉት የጠጠር ንጣፍ አላቸው፡፡ የተቀሩት ምንም ንጣፍ ያልለበሱ ናቸው፡፡

**(1) የፌደራል መንግሥት የመንገድ/ የትራስፖርት ልማት ዕቅድ**

በ1990 (እ/ኤ.አ) መጀመሪያዎቹ አካባቢ የኢትዮጰጵያ መንገድ አውታር ወደ 23,000 ኪ.ሜትር የነበረ ሲሆን ወደ 75% የሚሆነው በመጥፎ ደረጃ ላይ ይገኝ ነበር፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍና ተጨማሪ መንገዶችን በክልሎች ውስጥ በመገንባት ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኖሚያዊ ዕድገትን ለማምጣት መንገድ ልማት ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርጓል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያው ምዕራፍ የመንገድ ዘርፍ ፕሮግራም በ1997 )እ.ኤ.አ) ተጀምሯል፡፡.

የመጀመሪያው ምዕራፍ ፕሮግራም (1997-2002 እ.ኤ.አ) የመንገድ ንኡስ ዘርፍ አቅም ከማጎልበቱም በላይ የኢኮኖሚ ዕድገቱን በማፋጠንና አስፈላጊ የሆኑ የመንገድ አውታሮችን በተፈለገው ሁኔታ እንዲሻሻል ተገርጓል፡፡

ሁለተኛው ምዕራፍ የመንገድ ሴክትር ልማት ፕሮግራም በመጋቢት 2003 (እ.ኤ.አ) የተጀመረ ሲሆን አሁንም ተግባራዊ እየሆነ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የገጠር ጉዞና ትራንስፖርት ፕሮግራም ገጠሩን ክፍል ለማልማት የተቀመጠው እስትራቴጂ አስመልክቶ የመንገድ አውታርን መስፋፋትና በተለይም የግብርና ምርት አምራች በሆኑ አካባቢዎች ያለውን የመንገድ እጥረት በማስወገድና እንቅስቃሴን ሰፋ ባለ ሁኔታ ማካሄድ እንዲያስችል የአገናኝ መንገዶችን ግንባታና ደረጃቸውን ማሻሻል የመንግሥትንም ትኩረት አግኝቷል፡፡

ሦስተኛው ምዕራፍ የመንገድ ሴክተር ልማት ፕሮግራም ድህነት ማስወገጃ የተፋጠነ ልማት ዕቅድን መሠረት አድርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ በሁለት ምዕራፎች የማሻሻያ ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም መንገድ/ትራንስፖርት ያለበት ሁኔታ ዝቅተኛ በመሆኑ ቀጥሎ የተመለከቱ ሊሻሻሉ የሚገቡ ችግሮች ይታያሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች የገጠሩን ልማት ወደኋላ ከመጎተት በአለፈ የመጓጓዣ ወጪንና ጊዜን ከፍ አድርጓል፡፡

- የገጠሩ ማህበረሰብ ለክረምት ከበጋ መንገድ ያለው ተደራሽነት አነስተኛ በመሆኑ በዓመት ውስጥ ለበርካታ ጊዜያት ተለይቶ ይቆያል፡፡ ይህም ሁኔታ በተዘዋዋሪ መንገድ በግብርና ምርት አመራረትና ግብይት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡
- ህዝቡ ወደ እርሻ ማሳው የሚሄደው በእግሩ ሲሆን በአማካይ ከ5 እስከ 6 ኪ.ሜትር ይጓዛል፡፡ በመንገድ መጥፎነት የተነሳ ህዝቡ ውሃ ለመቅዳት፣ የማገዶ እንጨት ለመሰብሰብ፣ የግብርና ምርቶቻቸውን ገበያ ለማውጣት፣ የሚፈልጉት ዕቃ ለመግዛት እና ወደ ጤና ተቋምና ትምህርት ቤት ለመሄድ ይቸገራሉ፡፡
- አርሶአደሩ በአካባቢ ገበያ ምርቱን በትንሹ እየከፋፈለ በእርካሽ ዋጋ በመሸጥ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን ይገዛል፡፡
- በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መጓጓዣ ብዙውን ጊዜ በከተሞች መካካል በአሉ መንገዶችና የትራንስፖርት መስመሮች ብቻ ነው፡፡ አገልግሎት የሚሰጡት አልፎ አልፎ ከመሆኑም በላይ ክፍያቸውም ከፍተኛ ነው፡፡
- በገጠሩ አካባቢ በእግር መጓዝና በሞተር በማይንቀሳቀስ መጓጓዣ (በጭንቅላት መሸከም፣ በጀርባ ማዘል፣ በጋማ ከብት መጫን) መጠቀም ዋንኛ የተለመደ ነው፡፡

በዚህ መሠረት በድህነት ማስወገጃ የተፋጠነ ልማት ፕሮግራም በ2009/10 (እ.ኤ.አ) የሚከተለው ግብ ተጥሏል፡፡

- ከ5 ኪ.ሜትር ርቀት በላይ ያለውን መኖሪያ አካባቢ ወደ 59% መቀነስ
- ከ2 ኪ.ሜትር ርቀት በላይ ያለውን መኖሪያ አካባቢ ወደ 81% መቀነስ
- በአማካይ መንገድ ያለበት ቦታ ለመድረስ በእግር የሚደረገውን ጉዞ ወደ 3፡20 ሰዓት መቀነስ
- የመንገድ ጥጊጊትን ወደ 54.1 ኪሜትር በl,000 ስስኩዌር ኪ.ሜትር ማሳደግ ወይንም ወደ 0.72 ኪ.ሜትር በ1000 ሰው ማሳደግ (ዝቅተኛ ደረጃ መንገዶችን ጨምሮ)
- ለሁሉም የመንገድ ዓይነቶች አንፃራዊ ደረጃ (ጥሩ + መካከለኛ መንገድ) ማሻሻልና ማሳደግ


**(2) በጥናቱ አካባቢ አሁን ያለው የመንገድ አውታር ሁኔታ**

ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት ሀገር በመሆንዋ ወደ 100% የሚጠጋ የሀገር ውስጥ ምርት የሚጓጓዘው በመንገድ ነው፡፡ መንገድ ማሻሻል ማለት የግብርናው ምርት ግብይት ሁኔታ ማሻሻል ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት (2007/2008 እ.ኤ.አ)[1] በደ/ብ/ብ/ሕ/ ያለው የመነገድ ርዝመት 16,574 ኪሜትር ነው፡፡ ይህም የመንገድ ጥጊጊቱ 1.1 ኪ.ሜትር በ1000 ሰው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ የመንገድ ዕቅድ (2010/11-2014/15 እ.ኤ.አ) መሠረት ከዲኤስ 1 እስከ ዲኤስ 7 ያለ መንገዶች የክልሉን የመንገድ ጥጊጊት 66 ኪ.ሜትር በ1000 እስኩዌር ኪ.ሜትር ወይንም 0.63 ኪ.ሜትር በ1000 ሰው እንደሚሆን ነው፡፡ ይህ ፌዴራል መንግሥት ከአስቀመጠው 54.1 ኪ.ሜትር እስኩዌር ኪ.ሜትር እና 0.72 ኪ.ሜትር በ1000 ሰው ግብ እንደየቅድመ ተከተሉ ያንሳል፡፡

ይሁን እንጂ የመንገድ ጥጊጊቱ ከወረዳ ወረዳ ይለያያል፡፡ ከፍተኛና ዝቅተኛ የመንገድ ጥጊጊት ያላቸው ቦታዎች የተደበላለቁ ሲሆኑ አንዳንዶችም ይህን ግብ ሊደርሱ አይችሉም፡፡ በምስል 3.4-1 የተመለከተው ቻርት ይህንን ልዩነት ያሳያል፡፡


---

[1] የክልሉ እስታቲስቲክስ አብስትራክት 2000 ዓም




ምንጭ : የጥናት ቡድን (በክልሉ የመንገድ ዕቅድ 2010/11-2014/15 እ.ኤ.አ. መሠረት)

**ምስል 3.4-1 ዞናዊ የመንገድ ጥጊት በእስኩዌር ኪ.ሜትር**




ምንጭ : የጥናት ቡድን (በክልሉ የመንገድ ዕቅድ 2010/11-2014/15 እ.ኤ.አ. መሠረት)

**ምስል 3.4-2 የየዞኑ የመንገድ ጥጊት በ1000 ሰው**


በአጠቃላይ 6550 ኪ.ሜትር መንገድ ክረምት ከበጋ መንገድ 40% ይሆናል፡፡ በክልሉ መንገድ ባለሥልጣን 2010 (እ.ኤ.አ) በተደረገው የመንገድ አውታር ጥናት 50% በላይ የሚሆነው መንገድ ሁኔታ መጥፎ ሲሆን ከዚህ በታች በሠንጠዥ ተመልክቷል፡፡ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንገድ ባለሥልጣን የመንገድ ልማት ዕቅድ ከ2010 እስከ 2014 (እ.ኤ.አ) ያለውን ጊዜ የሚሸፍን አዘጋጅቷል፡፡

**ሠኝጠረዥ 3.4-2 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የመንገድ ሁኔታ**

| ጥሩ | መካከለኛ | መጥፎ | በጣም መጥፎ |
|---|---|---|---|
| 4% | 34% | 35% | 27% |

በክልሉ 14 ዞኖችና 4 ልዩ ወረዳዎች ያሉት ሲሆን በአጠቃላይ 134 ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ ሠንጠረዥ 3.4-3 በወረዳ ከተማና ከዞን ማዕከል ተማ መካካል ያውን ርቀት ያሳያል፡፡ ወደ 56% የሚሆኑት ከ50 ኪ.ሜትር ባልበለጠ ርቀት ሲገኙ 80% የሚሆኑት ከ100 ኪ.ሜትር በአነሰ ርቀት ይገኛሉ፡፡

ይህም በዞንና ወረዳ መካካል ያለው ርቀት በመካከላቸው በሚደረገው ግብይት ላይ የጎላ ችግር እንደማያስከትል ነው የሚያሳየው፡፡




ምንጭ : የጥናት ቡድን (በክልሉ የመንገድ ዕቅድ 2010/11-2014/15 እ.ኤ.አ. መሠረት)

**ምስል 3.4-3 ከወረዳና ዞን ዋና ከተማ መካካል ያለው እርቀት**

ይሁን እንጂ ከ134 ወረዳዎች 26 ህዘብ ትራንፖርት (አውቶቢስ) ከዞን ከተማ ወደ ወረዳ ከተማ አይገባም፡፡ 9 መስመሮች ከ200 ኪ.ሜትር በላይ ርቀት አላቸው፡፡ ከጂንካ የደቡብ ኦሞ ርሰ ከተማ እስከ ገሊላ ደርስ 603 ኪሜትር ርቀት ያለ ሲሆን የህዝብ መጓጓዣ የለም፡፡

ከዚህም በመነሳት የገጠር ማንገድ ባለሥልጣን የመነገድ ልማቱን በክልሉ መንገድ ልማት ዕቅድ 2010/11-2014/15 (እ.ኤ.አ) መሠረት ተመስርቶ በአለው ውስን በጀት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆጥቷል፡፡

**(3) የክልሉ የመንገድ ልማት ዕቅድ 2010/11 -2014/15 (እ/ኤ.አ)**

የደ/ብብ/ሕ/ክ/ ገጠር መንገድ ባለሥልጣን የክልሉን መንገድ ልማት የክልሉ የመንገድ ልማት ዕቅድ በ2010/11 -2014/15 (እ/ኤ.አ) መሠረት ያካሂዳል፡፡ በዚሁ መሠረት 57 አዳደስ መንገዶችና ሲገነቡ 11 ነባር መንገዶች ዕድሳት በድምሩ የ1,578 ኪ.ሜትር መንገድ ሥራ በሠንጠረዥ 3.4-3 እንደተመልተው ይከናወናል፡፡ የመንገድ ጥጊጊት ግብ 0.075 ኪ.ሜትር በእስኩዌር ኪ.ሜትር ነው፡፡


ዕቅዱ በ2009/10 (እ.ኤ.አ) የተጀመረውን መንገድ ማስቀጠል ትኩረት የሰጠ ሲሆን አዳዲስ መንገዶች ከዚህ በታች በተመለከው መስፈርት መሠረት ቅድመ ተከተል ወጥቶላቸዋል፡፡

(1) የወረዳ ህዝብ ብዛት (40%)
(2) የግብርን ምርት የማምረት እምቅ አቅም (20%)
(3) የኢኮኖሚ እድገት (15%)
(4) ቀበሌ የሚያገናኝ መሆኑና የመንገዱ ጠቃሚነት (10%)
(5) ሌሎች (15%)

ሠንጠረዥ 3.4-3 የደ/ብ/ሕ/ክ/ የመንገድ ዕቅድ 2010/11-2014/15 (እ.ኤ.አ)

| ዞን/ ልዩ ወረዳ | የታቀደ መንገድ | | | ዞን/ ልዩ ወረዳ | የታቀደ መንገድ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ርዝመት (ኪ.ሜ) | የመንገድ ዓይነት | በጀት (ሚ.ሊ. ብር) | | ርዝመት (ኪ.ሜ) | የመንገድ ዓይነት | በጀት (ሚ.ሊ. ብር) |
| 1. ቤንች ማጂ | 163.0 | ዲኤሰ 6 | 207.3 | 10. ሸካ | 26.0 | ዲኤሰ6 | 16.4 |
| 2. ዳውሮ | 32.0 | ዲኤሰ 6 | 17.0 | 11. ሲዳማ | 103.5 | ዲኤሰ6 | 89.3 |
| 3. ደቡብ ኦሞ | 251.0 | ዲኤሰ6<br>ዲኤሰ7 | 284.4 | 12. ሲልጢ | 88.0 | ዲኤሰ6 | 66.3 |
| 4. ጋሞ ጎፋ | 286.5 | ዲኤሰ6<br>ዲኤሰ7 | 288.6 | 13. ወላይታ | 68.0 | ዲኤሰ6<br>ዲኤሰ7 | 77.7 |
| 5. ጌደኦ | 97.0 | ዲኤሰ6 | 98.2 | 14. ሰገን አካባቢ | 50.0 | ዲኤሰ6 | 26.6 |
| 6. ጉራጌ | 76.0 | ዲኤሰ6 | 65.7 | 15. አላባ ልዩ ወረዳ | 0.0 | - | 0.0 |
| 7. ሃዲያ | 120.5 | ዲኤሰ6<br>ዲኤሰ7 | 119.1 | 16. ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | 0.0 | - | 0.0 |
| 8. ከፋ | 132.5 | ዲኤሰ6<br>ዲኤሰ7 | 95.5 | 17. ኮንታ ልዩ ወረዳ | 45.0 | ዲኤሰ6 | 63.0 |
| 9. ከምባታ ጠመባሮ | 20.0 | ዲኤሰ7 | 12.6 | 18. የም ልዩ ወረዳ | 19.5 | ዲኤሰ6 | 27.3 |
| | | | | ድምር | 1,578.5 | | 1,554.8 |

ካርታ ላይ አቀማመጥ




ምንጭ: የክልሉ የመንገድ ዕቅድ 2010/11-2014/15 (እ.ኤ.አ), የክልል ገጠር መንገድ ባለሥልጣን

## 3.4.2 የግብርና መጋዘን

### (1) በጥናቱ አካባቢ ያለው የመጋዘን ሁኔታ

በደ/ብ/ብ/ሕክ/ በመንግሥት፣ በግልና በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ (የምግብ ዋሰት እና ግብአት ለማከማቸት) ባለቤትነት ሥር ያሉ መጋዘኖች ብዛትና የመያዝ አቅማቸው እንደሚከተለው ቀርቧል[2]፡ በዞንና በወረዳ ውስጥ የመጋዘኖች የሚገኙበት ስርጭት ወጥ አይደለም፡፡

ከግብይት የሥራ ሂደት እና በግብርና ቢሮ ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስት የሥራ ሂደት በተገኘው መረጃ መሠረት በሕ/ሥራ ማህበራት የሚተዳደሩ መጋዘኖች ያሉበት ሁኔታ ጥሩ ኤደለም፡፡ በተጨማሪ በእንደዚህ ያለ ደረጃው ዝቅተኛ በሆነ መጋዘን በጊዜያዊነት ወይንም ለአጥር ጊዜ እንኳን የተቀመጠ የግርና ምርት ውጤት ቶሎ ይበላሻል፡፡ በቁጥር አነስተኛ መጋዘን ከመኖሩም ሌላ የመጋዘን አሰተዳዳር እና አሠራር በመሠረታዊነት ሊሻሻል ስለሚገባ ለሕ/ሥራ ማህበራት ሠራተኞች የክህሎት ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

2 በሕ/ሥራ ማህበራት፣ በኢትዮጵያ እህል ገበያ ኢንተርፕራይዝ የሚተዳደር መጋዘኖች አልተካተቱም.

## ሠንጠረዥ 3.4-4 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የመጋዘን ሁኔታ

| ዞን/ ልዩ ወረዳ | የተለያዩ ድርጅቶች | | የግል ድርጅት | | ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስትና | | | | ግብርና. | | ንዑስ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | የመያዝ አቅም (ቶን) | ቁጥር | የመያዝ አቅም (ቶን) | የመጋዘን ቀጥር | የመያዝ አቅም (ቶን) | የሸራ መጋዘን ቀጥር | የመያዝ አቅም (ቶን) | ቁጥር. | የመያዝ አቅም (ቶን) | ቁጥር. | የመያዝ አቅም (ቶን) |
| ጉራጌ | 1 | 2,500 | | | 2 | 8,000 | 2 | 6,000 | | | 5 | 16,500 |
| ስልጤ | | | | | | | 2 | 3,000 | | | 2 | 3,000 |
| ሃዲያ | 4 | 8,700 | | | 2 | 20,000 | 3 | 12,500 | 2 | 3,500 | 11 | 44,700 |
| ከምባታ ጠምባሮ | | | 6 | 6,900 | 3 | 15,000 | 1 | | | | 10 | 21,900 |
| ወላይታ | 3 | 13,000 | | | 4 | 16,000 | 2 | | 25 | 117,000 | 34 | 146,000 |
| ሲዳማ | 5 | 67,000 | 15 | 60,500 | 1 | 41,000 | 7 | 28,000 | 3 | 18,000 | 31 | 214,500 |
| ጌዲኦ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| ጋሞ ጎፋ | 8 | 51,000 | | | 10 | 59,000 | 4 | | 7 | 39,000 | 29 | 149,000 |
| ዳውሮ | | | | | 1 | 3,000 | 2 | | 1 | 1,500 | 4 | 4,500 |
| ከፋ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| ሸካ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| ቤንች ማጂ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| ደቡብ ኦሞ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| አላባ ልዩ ወረዳ | 3 | 3,800 | | | | | 1 | | | | 4 | 3,800 |
| የም ልዩ ወረዳ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| ኮንታ ልዩ ወረዳ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | | | | | | | | | | | 0 | 0 |
| አማሮ ልዩ ወረዳ | | | | | | | 1 | | | | 1 | 0 |
| ቡርጂ ልዩ ወረዳ | | | | | | | 1 | | | | 1 | 0 |
| ደራሼ ልዩ ወረዳ | | | | | | | 1 | | | | 1 | 0 |
| ኮንሶ ልየ ወረዳ | | | | | | | 2 | | | | 2 | 0 |
| ድምር | 24 | 146,000 | 21 | 67,400 | 23 | 162,000 | 29 | 49,500 | 38 | 179,000 | 135 | 603,900 |

ምንጫ: የተለያዩ ድርጅቶች የአካቢ ምንግሥት/ማዘጋጃ ቤት ጭምር.
የጥናት ቡድን ከግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ከአገኘው መረጃ የተጠናቀረ፡፡

### (2) የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘን ሁኔታ

የሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘን አጠቃቀምና ያሉበትንሁኔታ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ነበር፡፡ ለዚሁ ጥናት በሲዳማ ኤልቶ ዩኒያን ሥር 62 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት 8 ተመርጠዋል፡፡ ምርጫውም ሕ/ሥራ ማህበራት ያሉበትን አካባቢ መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላ አካባቢዎች ተካሂዷል፡፡

በሠንጠረዥ 3.4-5 በሲዳማ ዞን የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የመጋዘን ዳሰሳ ውጤት ቀርቧል፡፡ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘኖቻቸውን የሚጠቀሙት በዋናነት ማዳበሪያና ዘር ለማከማቸት ነው፡፡ ብዙ ማህበራት ጽ/ቤታቸውን ወይንም የአባሎቻቸውን መኖሪያ ቤት በመጋዘንነት ይጠቀማሉ፡፡ ከዚህ በታች በፎቶ እንደተመለከተው አብዛኛው የማህበራት መጋዘን የተሠራው ከጭቃ ግድግዳ ሲሆን አንድ በር ብቻ አለው፡፡ የመያዝ አቅማቸው 35 - 200 ቶን ነው፡፡ አንዳንድ ማህበራት የራሳቸው መጋዘን ሲኖራቸው አንዳንዶችም ለአጭር ጊዜ ያከራያሉ፡፡

**ሠንጠረዥ 3.4-5 በሲዳማ ኤልቶ ዩኒያን ሥር ያሉ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘን**

| ወረዳ | መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር | ቁጥር | ዓይነት | ስፋት ርxስxከ (ሜ) | የመያዝ አቅም (ቶን) | የበር ስፋት (ሜ) | ዋንኛ ምርት | ንፋስ ማስገቢያ +/- |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሁላ (ከፍተኛ ቦታ) | ጭሮኒ | I | WM | 6 x 5 x 2.65 | 50 | 0.8 x 1.7 | ስነዴ ገብስ በቆሎ ባቄላ አተር | + |
| | | II | WM | 7 x 8 x 2.7 | 90 | 1.2 x 1.9 | > > | + |
| | ሀንኮ ሞልቾሆ | I | WM | 6 x 15 x 2.9 | 160 | 1.1 x 1.8 | > > | + |
| | | II | WM | 5 x 5 x 2.8 | 40 | 0.9 x 1.7 | > > | + |
| | አበላ | I | HB | 12 x 7 x 4 | 200 | 1.8 x 2.5 | > > | + |
| | | II | HB | 12 x 7 x 4 | 200 | 1.8 x 2.5 | > > | + |
| | | III | CS+MW | 12 x 6 x 2.7 | 115 | 1.3 x 1.8 | ድንች | + |
| ቦረቻ (መካከለኛ ቦታ) | ኮንሶሬ | I | WM | 4 x 6 x 2.8 | 40 | 1.9 x 1.0 | በቆሎ፣ ቦሎቄ | - |
| | | II | WM | 6 x 6 x 2.8 | 60 | 1.9 x 1.0 | > > | - |
| | | III | WM | 6 x 6 x 2.8 | 60 | 1.9 x 0.9 | > > | - |
| | ቦኖያ ጭሬ | I | WM | 4 x 6 x 2.6 | 35 | 1.0 x 2.0 | በቆሎ፣ ቦሎቄ | + |
| | | II | WM | 5 x 6 x 2.6 | 45 | 1.0 x 2.0 | > > | + |
| | | III | WM | 5 x 6 x 2.6 | 45 | 1.0 x 1.9 | > > | + |
| | ሻሎ በሊላ | I | WM | 8 x 8 x 3 | 140 | 0.8 x 1.7 | በቆሎ፣ ቦሎቄ | - |
| ሎኮ አባያ (ዝቅተኛ ቦታ) | ሀንጣጤና አካባቢው | I | WM | 9 x 6 x 3 | 100 | 1.9 x 1.9 | ጤፍ | + |
| | | II | WM | 9 x 6 x 3 | 100 | 1.9 x 1.9 | > > | + |
| | ሀንጣጤና አካባቢው | I | WM | 3 x 7 x 3 | 35 | 1.0 x 1.8 | > > | - |

WM= እንጨትና ጭቃ HB= ብሎኬት CS= ቆርቆሮ, MW= የሽቦ ወንፊት

ንፋስ ማስገቢያ +/-.= + (ንፋስ ማስገቢያ ያለው), - ((ንፋስ ማስገቢያ የሌለው)

ምንጭ : የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማግበራት መጋዘን ዳሰሳ ጥናት፣ ጃይካ ጥናት ቤድን



አባላ ሕ/ሥራ ማህበር፣ ሁላ ወረዳ ንፋስ ማስገቢያ ያለውመጋዘን፣ ከተሠራ 20 ዓመት ይሆናል፣ በሥራ ላይ ይገኛል። 200 ቶን እያንዳዱ ይይዛል.



ቦኖያ ጭሬ ሕ/ሥራ ማህበር፣ ቦረቻ ወረዳ በማህበሩ ባለቤትነት ሥር ያለ የበቆሎና ቦሎቄ መከማቻ መጋዘን



ሻሎ በሊላ ሕ/ሥራ፣ ቦረቻ ወረዳ ከግለሰብ የተከራየው መጋዘን.



ሀንጣጤና ሕ/ሥራ፣ ሎኮ አባያ ወረዳ፣ ከቀበሌ የተከራየው 2 መጋዘን 1 በርና 6 መስኮት ያለው

**ፎቶ : በሲዳማ ኤልቶ ዩኒያን ሥራ ያሉ ሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘን**

### (3) ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

የሕ/ሥራ ማህበራት ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች እንሚቀጥለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡

- አብዛኛው የሕ/ሥራ ማህበራት መጋዘን ከእንጨትና ጭቃ የተሠሩት ረዘም ለአለ ጊዜ ምርትን ለማከማቸት ጥሩ አይደሉም
- አብዛኛው መጋዘን አንድ በር ብቻ ያለው በመሆኑ ቀድሞ የገባው ቀድሞ ማውጣት የሚለውን የመጋዘን ስርዓት በመጋዘኑ ውስጥ በተከማቹ የግብርና ምርት ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ አያስችልም
- ጥቂት መጋዝኖች ንፋስ መስገቢያ ያላቸው ሲሆን ቢሮና መኖሪያ ቤትም ለግብርና ምርት መከማቻ መጋዘን በመሆን ጥቅም ላይ እየዋለ ነው፡፡
- የግብርና ምርት በመጋዘን ውስጥ የኩንታል መደርደሪያ ወይንም ፕላስቲክ ሸራ ተጠቅሞ አለመደርደር
- አንዱ መጋዘን ሳይከፋፈል ማደበሪያ/የግብርና ኬሚካሎች እና ምርት ለማከማቸት ጥቅም ላይ ይውላሉ
- የመጋዘን አስተዳደር እውቀት ውስንነት
- በመጋዘኑ ውስጥ እንደ ነፍሳት፣ ወፍ፣ ቆርጣሚ እንስሳትና ፈንገስ የመሳሰሉ ተባዮችን የመከላከልና የመቆጣጠር በቂ ያለመሆን
- እህል በማጠን የማከም እውቀት ያለመኖር
- በመጋዘኑ ውስጥ እህሉን ለማጠን በቂ ቦታ ያለመኖር
- ምንም እንኳን የሕ/ሥራ ዩኒያኖች ከብሎኬት የሚያስገነቡት መጋዘን ቁጥር እየጨመረ ቢሆንም የመጋዘን አስተዳዳር ስልጠና ደረጃው የጠበቀ አለመሆኑ፡፡

## 3.4.3 የገበያ ቦታ

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የተለያዩ ብዙ የገበያ ቦታዎች ያሉ ሲሆን አብዛኛዎቹ ሜዳ/ክፍት ቦታ መደበኛ ግብይት በሣምንት አንድ ወይንም ሁለት ቀን ያካሂዳሉ፡፡ መሠረተልማትና መገልገያን በተመለከተ የትልልቅ ከተሞች (የዞንና የወረዳ ርዕሰ ከተማ) ቋሚ/በከፊል ቋሚ በሆነ እንደ ሹቅና መጋዘን አላቸው፡፡ የአካባቢ ገበያዎች ክፍት ቦታ ላይ የሚካሄዱ ሲሆን ምንም ዓይነት መሠረተልማትና መገልገያዎች የሉዋቸውም፡፡ ተንቀሳቃሽ የመገበያያ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ፡፡ ይሁንና በክልሉ ውስጥ ያሉ ገበያ ቦታዎች በሙሉ የመሠረተልማት እጥረት በተመሳሳይነት አለባቸው፡፡

የገበያ ቦተዎች አረርሶአደሩ ምርቱን በመሸጥ ገቢ እንዲያገኝ ጠቃሚ ሚና ያላቸው ሲሆን ማህበራዊ መስተጋብርም በህብተሰቡ መካከል እንዲኖር ያዳርጋሉ፡፡ በዋና አምራች አካባቢ ያሉ የገበያ ቦታዎች ምርት የማሰባሰብ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ ወደ ከተማ መሰራጨትም የመጀመርበት ቦታ ነው፡፡


አብዛኛው ገበያ የሚተዳድረው በመንግሥት አካል ሲሆን እነርሱም በዋናነት ቀረጥ የመሰበስቡና የገበያ መደብ ለነጋዴዎች የሚሰጡ ናቸው፡፡ የገበያ ቦታን ንፅህና መጠበቅ አልፎ አልፎ የመካሄድ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ በብቃት አይከናወንም፡፡

### (1) በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአሁኑ ወቅት ያለው የገበያ ሁኔታ

<u>የገበያ ቦታ ቆጠራ ደሰሳ ውጤት</u>

የጥናት ቡድኑ በክልሉ ውስጥ የገበያ ገበያዎች ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት የገበያ ቦታ ቆጠራ ዳሰሳ ሚያዝያ 2010 (እ.ኤ.አ) አካሂዷል፡፡ የጥናቱም ውጤት በሚቀጥለው ሠንጠረዥ 3.4-6. እና በምስል 3.4-4 እንደሚከተው ቀርቧል፡፡ በደሰሳ ጥናት ወቅት በሚከተለው መልኩ የገበያ ቦታ ተከፋፍለዋል፡፡

| የገበያ መጠን | የገበያ መጠን መግለጫ |
|---|---|
| ዞን (ጥልቅ) | : ከሰባት ወረዳ በላይ የሚገበያዩበት የገበያ ቦታ |
| ወረዳ (መካከለኛ) | : ከሰባት ወረዳ በታች የሚገበያዩበት የገበያ ቦታ |
| ቀበሌ (አነስተኛ) | : ጥንሽ ገበያ በወረዳ ውስጥ ያለ 3-6 ቀበሌቶች የሚጠቀሙት ገበያ |




ምስል 3.4-4 የገበያ ቦታ ብዛት፣ በገበያ መጠንና በዞን

## ሠንጠረዥ 3.4-6 የገበያ ቦታ ቆጠራ ደሰሳ ውጤት

| ዞን/ል ወረዳ | | የገበያ መጠን ዞን | ወረዳ | አካባቢ | ድምር | ዋና ወደ ሌላ አካባቢ/ዞን ውስጥ የሚሸጡ ሰብሎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምሥራቃዊ የክክሉ አካባቢ | | | | | | | | | | |
| 1 | ጉራጌ | 10 | 21 | 21 | 52 | ስንዴ | በቆሎ | ድንች | አትልትና ፍራፍሬ. | ገብስ |
| 2 | ስልጤ | 7 | 4 | 4 | 15 | ስንዴ | ጤፍ | ገብስ | ድንች | በርበሬ |
| 3 | ሃዲያ | 5 | 9 | 13 | 27 | ስንዴ | በቆሎ | አትልትና ፍራፍሬ | ገብስ | ጤፍ |
| 4 | አላባ ል ወረዳ | 1 | 3 | 4 | 8 | በርበሬ | በቆሎ | በሎቄ | ጤፍ | |
| 5 | ከምባታ ጠምራሮ | 1 | 7 | 26 | 35 | ስንዴ | በቆሎ | ዝንጅብል | አትልትና ፍራፍሬ | ገብስ |
| 6 | ዳውሮ | 4 | 10 | 15 | 29 | በቆሎ | ዝንጅብል | ጥራጥሬ | ስንዴ | ሥራሥር |
| 7 | ወላይታ | 3 | 13 | 24 | 40 | በቆሎ | ዝንጅብል | ጥራጥሬ | ፍራፍሬ | ካሳቫ |
| 8 | ሲዳማ | 1 | 33 | 125 | 159 | ገብስ | ስንዴ | በቆሎ | ቆጮ | አትልትና ፍራፍሬ |
| 9 | ጎዴኦ | 2 | 5 | 24 | 31 | ቆጮ | አትልትና ፍራፍሬ | በቆሎ | | |
| 10 | ጋሞ ጎፋ | 2 | 14 | 113 | 129 | በቆሎ | ፍራፍሬ | ሥራሥር | ጤፍ | ጥራጥሬ |
| 11 | አማሮ ልዩ ወረዳ | | 2 | 9 | 11 | በቆሎ | ጤፍ | ጥራጥሬ | | |
| 12 | ቡርጂ ልዩ ወረዳ | | 2 | 5 | 7 | ጤፍ | ጥራጥሬ | በቆሎ | | |
| 13 | ደራሼ ልዩ ወረዳ | | 2 | 6 | 8 | ማሽላ | ጤፍ | በቆሎ | | |
| 14 | ኮንሶ ልዩ ወረዳ | | 1 | 4 | 5 | በቆሎ | ጤፍ | ጥራጥሬ | | |

| | ዞን/ል ወረዳ | የገበያ መጠን | | | | ዋና ወደ ሌላ አካባቢ/ዞን ውስጥ የሚሸጡ ሰብሎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዞን | ወረዳ | አካባቢ | ድምር | | | | | |
| **ምዕራባዊ የክልሉ አካባቢ** | | | | | | | | | | |
| 15 | ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | | 1 | 5 | 6 | ጤፍ | በቆሎ | ቅመም | | |
| 16 | ሸካ | 1 | 7 | 13 | 21 | በቆሎ | ቆጮ | ጥራጥሬ | ፍራፍሬ | ማር |
| 17 | ከፋ | 4 | 15 | 17 | 36 | በቆሎ | ስንዴ | ጥራጥሬ | ጤፍ | ማር |
| 18 | ኮንታ ልዩ ወረዳ | 1 | 1 | 4 | 6 | በቆሎ | ጥራትሬ | ጤፍ | ስንዴ | |
| 19 | ቤንች ማጂ | 6 | 15 | 13 | 34 | በቆሎ | ሩዝ | ሥራሥር | ቅመም | ጥራጥሬ |
| 20 | ደቡብ ኦሞ | 1 | 2 | 11 | 13 | በቆሎ | ስንዴ | ማሽላ | ፍራፍሬ | |
| **የክልል ድምር** | | **49** | **167** | **456** | **672** | | | | | |

ምንጭ፡ የገበያ ቦታ ቆጠራ ዳሰሳ ሚያዝያ 2012 (እ.ኤአ) ጃይካ ጥናት ቡድን

## የሚከተሉት ግኝቶች በገበያ ቆጠራ ዳሰሳ ግልጽ ሆነዋል

1) ከለሰይ እንደተመለከተው 672 የገበያ ቦታዎች በክልሉ ይገኛሉ፡፡ ከእነርሱም ውሰጥ 49 የዞን (ትልቅ) የገበያ ቦታዎች፣ 167 የወረዳ (መካከለኛ) የገበያ ቦታ እና 456 የአካባቢ (አነስተኛ) የገበያ ቦታ ናቸው፡፡ የገበያ ቦታዎች ብዛት ከዞን ዞን ይለያያል፡፡ ሁለቱ ዞኖች (ሲዳማና ጋሞ ጎፋ) በተለይ ብዙ የአካባቢ (አነስተኛ) ገበያዎች ያሉዋቸው ሲሆን ከአጠቃላዩ 42% ይሆናል፡፡
2) በዞንና በወረዳ ርዕሰ ከተሞች የሚገኙ የገበያ ቦታዎች በማዘጋጃ ቤት የሚተዳዱ ሲሆን በገጠሪ የሚገኘው ገበያ የሚያስተዳደረው የቀበሌ አሰተዳደር ነው፡፡
3) በአብዛኛው በክልሉ ውስጥ በአሉ የዞንና የወረዳ ከተማ የሚገኘው ገበያ ቦታዎች መሠረተልማት ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡
   - ሁሉም የገበያ ቦታዎች ለእያንዳዱ ምርት መሸጫ የተከለለ/የተመደበ ቦታ አላቸው፡፡ በዘህ መሠረት ለልብስ፣ ኢንዱስትሪ ምርቶች፣ አትክልት፣ እህል እና ሌሎች ምርቶች የተለየ ቦታ ተመድቦላቸዋል፡፡
   - በሁሉም የገበያ ቦታዎች ማለት ይቻላል ከዝናብና ፀሐይ ተጠልሎ መግዛትና መሸጥ የሚቻልበት ቋሚ የሆነ መጠለያ በበቂ ማጠን የለም
   - በቱላና ሀዋሣ የገበያ ቦታ ብቻ ነው ማዘጋጃ ቤት እንደዚሀ ያለ ቋሚ መጠለያ በመገንባት የጀመረው፡፡
   - በገበያ ቦታዎች አካባቢ የተወሰነ መጋዘኖች ይገኛሉ፡፡ አብዛኛው መጋዘን የግል ሲሆን ያሉበት ሁኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡ በመጠን ትንሽ ሲሆኑ፣ የንፋስ መግቢያ የሌላቸውና ለመጫንና መውረድ ምቹ አይደሉም፡፡
   - ሁሉም የገበያ ቦታዎች የውሃ ፍሳሽ ማስወገጃ የላቸውም፡፡ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና መጸዳጃ ቤት የላቸውም፡፡
   - በወረዳና ዞን የገበያ ቦታዎች ወፍጮ አገልግሎት ሲኖር በተወሰኑ ገጠር አካባቢ በአሉት የገበያ ቦዎችም ይገኛሉ፡፡
   - ሁሉም የዞን ገበያዎች በክረምት ከበጋ መንገዶች ተደራሽ ናቸው፡፡ የወረዳ ገበያን በተመለከተ አብዛኛው ከዞንና ሌሎች ወረዳዎች ክረምት ከበጋ በሆነ መንገድ ተደራሽ ናቸው፡፡ ይሁንና ሁሉም የአካባቢ ገበያዎች በበጋ መንገድ ብቻ ተደረሽ ናቸው፡፡
3) የብዙዎቹ አነስተኛ ነጋዴዎች ገቢ አነስተኛ ነው፡፡ ቶሎ የሚበላሹ ምርቶች ብዙውን ጊዜ በሴት አነስተኛ ነጋዴዎች ነው የሚሸጠው፡፡
4) በዞንና ልዩ ወረዳ ባለሙያዎች እንዲሻሻሉ የቀረቡ ሀሳቦች፡- የገበያ መሠረተልማት ግንባታ፣ ደህረምርት አያያዝና እሴት መጨመር፣ የጥራት ቁጥጥርና ማሻሻል፣ የገበያ ማዕከል መቋቋም፣ የገበያ መረጃ ስርዓትን መሻሻል፣ የገበያ ትስስርን ማሻሻልና ማስፋፋት፣ የገበያ ጥናት ማካሄድ፣ አቅም ግንባታና ግንዛቤ ማስጨበጥ

የየገበያ ቦታ ህዝብ ብዛት

እንደማዕከላው እስታስቲክስ ባለሥልጣን የዳሰሳ ጥናት መረጃ (ረቂቅ የኢትዮጵያ ገጠር መሥረተልማትና አገልግሎት 2007/08 እ.ኤ.አ) የገበያ ቦታዎች የህዝብ ብዛት ተሰልቷል። ውጤቱም እንደሚያሳያው በክልሉ በሚገኙት የገበያ ቦታዎችን በአማካይ 8000 ሰው ይጠቀማል።

ሠንጠረዥ 3.4-7 የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የህዝብ ብዛት በገበያ ቦታ (2000 ዓ/ም 2007-08 እ.ኤ.አ)

| ዞን/ ልዩ ወረዳ | ዋና ከተማ | የህዝብ ብዛት በገበያ ቦታ |
|---|---|---|
| ጉራጌ | ወልቂጤ | 6,000 |
| ስልጤ | ወራቤ | 16,000 |
| ሃዲያ | ሆሳዕና | 17,000 |
| ከምባታ ጠምባሮ | ደራሜ | 17,000 |
| ወላይታ | ሶዶ | 6,000 |
| ሲዳማ | ሀዋሣ | 6,000 |
| ጌዲኦ | ዲላ | 10,000 |
| ጋሞ ጎፋ | አርባምንጭ | 10,000 |
| ዳውሮ | ተርጫ | 8,000 |
| ከፋ | ቦንጋ | 12,000 |
| ሸካ | ማሻ | 2,000 |
| ቤንች ማጂ | ሚዛን ተፈሪ | 16,000 |
| ደቡብ ኦሞ | ጂንካ | 22,000 |
| አላባ ልዩ ወረዳ | አላባ ቁሊቶ | NA |
| የም ልዩ ወረዳ | ፎፋ | 12,000 |
| ኮንታ ልዩ ወረዳ | አማያ | 14,000 |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | ላስካ | 10,000 |
| አማሮ ልዩ ወረዳ | ከሴ | 4,000 |
| ቡርጂ ልዩ ወረዳ | ሶያማ | 8,000 |
| ደራሼ ልዩ ወረዳ | ጊዶሌ | 16,000 |
| ኮንሶ ልየ ወረዳ | ካራት | 32,000 |
| አማካይ | | 8,000 |

ምንጭ: ከመጀመሪያ የኢትዮጵያ የገጠር መሠረተልማትና አገልግሎት ረቂቅ የተወሰደ

## (2) ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ዋና ችግሮች እንሚቀጥለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡

- የገበያ ቦታ ንፅህና ጉድለት በተለይ በዝናብ ወቅት ያለ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ
- በገበያ ላይ ያሉት መሠረታዊ የሆኑ መሠረተልማቶችና አገልግሎቶች በጣም ዝቅተኛ መሆን
- እንደ ዝናብ በአለ የአየር ፀባይ በቀላሉ መቸገር
- በቂ መጠለያ፣ መጋዘን እና ውሃ በለመኖሩ ከፍተኛ የሆነ በቀላሉ የሚበላሹ ምርቶች ብክነት.
- በቂ መንገድ ተደራሽነት (ከእርሻ ቦታ ወደ ገበያ) እንዲሁም ክረምት ከበጋ መንገድ ያለመኖር



የሃዳሮ ገበያ ቦታ፡ ከፀሐይና ዝናብ ለመጠልል ፕላስቲክ ሸራ ሲጠቀሙ.



በስተግራ ከአለው ጋር ይመሳሰል: በጣም በሰው የተጨናነቀ ነው። የመፀዳጃኛ የውሃ አገልግሎት የለም/ ዝቅተኛ ነው።



የአካባቢ ገበያ ጥሩ የአየር ፀባይ ሲኖር፡ አንዳንድ መደቦች የዕቃ መስቀመጫ ቆጥ ሲኖራቸው አብዛኛው መሬት ላይ ያሰጣሉ



የገበያ ቦታ በክረምት ወቅት፡ ጭቃ እና ፍሳሽ የሌለው ሜዳማ ቦታ

### 3.4.4 ቴሌኮሚኒኬሽን

ዘመናዊ ግብይትና የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሻሻል የክልልን ዕድገትና የገጠር ኢኮኖሚን ለማሳደግ የቴሌኮሚኒኬሽን አውታርና አገልግሎት ማሻሻል አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ አርሶአደሩ በአካባቢው መሠረታዊ የስልክ አገልግሎት ተደራሽነት ከኖረ የዋጋ መረጃና ለሰብልና እንስሳት ምርቶቹ የገበያ ፍላጎትን ማወቅ ያስችለዋል፡፡

ከዚህ ሰፋ ብሎ እርካሽና አስተማማኝ የሀገር ውስጥና የውጪ ግንኙነት የኢንቴርኔት ተደራሽነትን ጨምሮ መኖሩ በንግድ ሥራ ለተሰማሩ ሰዎችና ወደ ውጪ ሀገር ላኪዎች ብቻ ሳይሆን የመንግሥት ሥራ ለማከናወን፣ የመስተማርና መማር ሥራ ለማገዝ እንዲሁም በቤተሰብ መካካል ያለው ቁርኝት ለማጠናከር ይረዳል፡፡

#### (1) በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን ሁኔታ

በኢትዮጵያ የቴሌኮሚኒኬሽን ሽፋን በዓለም ስጥ አነስተኛ ከሚባሉት ተርታ ነው የሚመደበው፡፡ በመሆኑም 5 የስልክ መስመር በ1000 ሰው ያለ ሲሆን ወደ 87% የሚሆነው የገጠሩ ህዝብ ከ5 ኪ.ሜትር በላይ ከስልክ አገልግሎት ርቆ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በአለፉት ጥቂት ዓመታት ከፍተኛ መሻሻል ከታየባቸው ሥራዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ገንዝብ በማውጣት ማልቲሚድያ፣ ፋይበር ኦፕቲክ መስመር መዘርጋት፣ ሳታላይትና ራዲዮ ግንኙት አስፋፍቷል፡፡ ባለፉት 3 ዓመታት የትምህርትና የወረዳ ኔት ፕሮግራም ተመቻችተዋል፡፡ ከላይ በተገለጸው መሠረት ድህነት ማስወገጃ የተፋጠነ ዘላቂ ልማት ዕቅድ እስከ 2009/10 (እ/ኤ.አ) መጨረሻ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተመለከተውን ለመድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

ሠንጠረዥ 3.4-8 የቴሌኮሚኒኬሽን ግብ

| ዝርዝር | መነሻ (2004/05) | ግብ (2009/10) |
|---|---|---|
| በ5 ኪ.ሜትር ውስጥ ቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት የሚያገኙት ህብረተሰብ ሽፋን (%) | 13% | 100% |
| ቀጥታ መስመር መጠቀም ያለው የቴሌ ጫና | 0.85 | 3.87 |
| ሞባይል መጠቀም ያለው የቴሌ ጫና | 0.56 | 8.1 |
| የኢንተር ኔት ተጠቃሚ ቁጥር | 17,375 | 193,100 |
| የስልክ መስመር ያላቸው ቀበሌዎች (ቢያንስ 5 መስመር) | 3,000 | 15,000 |

### (2) በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአሁኑ ወቅት ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን ሁኔታ

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በአሁኑ ወቅት ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን ሁኔታ ከዘህ በታች ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 3.4-9 የደ/ብ/ብሕ/ክ/ የቴሌኮሚኒኬሽን ሁኔታ (ታህሣስ 2009 እ፣ኤ.አ)

| ዞን/ ልዩ ወረዳ | የዞን ከተማ | ቀጥታ መስመር (የደንበኛ ብዛት) | ሞባይል (የደንበኛ ብዛት) | ቀጥታ መስመር መጠቀም ያለው የቴሌ ጫና በመቶኛ | ሞባይል መጠቀም ያለው የቴሌ ጫና በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ጉራጌ | ወልቂጤ | 9,703 | 7,096 | 0.76 | 0.55 |
| ስልጤ | ወራቤ | 1,924 | 1,150 | 0.26 | 0.15 |
| ሃዲያ | ሆሳዕና | 6,593 | 974 | 0.53 | 0.08 |
| ከምባታ ጠምባሮ | ደራሜ | 3,811 | 1,000 | 0.56 | 0.15 |
| ወላይታ | ሶዶ | 10,091 | 2,914 | 0.66 | 0.19 |
| ሲዳማ | ሀዋሣ | 18,291 | 35,279 | 0.57 | 1.09 |
| ጌዲኦ | ዲላ | 4,320 | 662 | 0.49 | 0.08 |
| ጋሞ ጎፋ | አርባምንጭ | 7,544 | 6,550 | 0.47 | 0.41 |
| ዳውሮ | ተርጫ | 500 | 2,000 | 0.10 | 0.41 |
| ከፋ | ቦንጋ | 2,384 | 1,500 | 0.27 | 0.17 |
| ሸካ | ማሻ | 2,541 | 0 | 1.27 | 0.00 |
| ቤንች ማጂ | ሚዛን ተፈሪ | 2,516 | 1,500 | 0.38 | 0.23 |
| ደቡብ ኦሞ | ጂንካ | 1,980 | 2,800 | 0.34 | 0.48 |
| አላባ ልዩ ወረዳ | አላባ ቁሊቶ | 1,444 | 906 | 0.62 | 0.39 |
| የም ልዩ ወረዳ | ፎፋ | 363 | 0 | 0.45 | 0.00 |
| ኮንታ ልዩ ወረዳ | አማያ | 355 | 1,400 | 0.39 | 1.53 |
| ባስኬቶ ልዩ ወረዳ | ላስካ | 0 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| አማሮ ልዩ ወረዳ | ከሌ | 436 | 0 | 0.29 | 0.00 |
| ቡርጂ ልዩ ወረዳ | ሶያማ | 426 | 768 | 0.75 | 1.36 |
| ደራሼ ልዩ ወረዳ | ጊዶሌ | 360 | 680 | 0.25 | 0.48 |
| ኮንሶ ልየ ወረዳ | ካራት | 355 | 370 | 0.15 | 0.16 |
| አማካይ | | 75,937 | 67,549 | 0.50 | 0.45 |

ምንጭ: የአቅም ግንባታመምሪያ

### 3.4.5 በመንገድ ዳር የሚደረግ ግብይት

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ከአዲስ አበባ ጋር የሚገኛኝበት 3 ዋና መስመሮች አሉ፡፡ እነርሱም የሀዋሣ መስምር፣ ሆሳዕና አርባምንጫ መስመር እና የጂማ ማስመር ናቸው፡፡ በትራንስፖረት መስመር የሚያልፍባቸው አካባቢዎች የምርት ዓይነት ተመርኩዞ እንደሙዝ፣ ማንጎ፣ ሎሚና አቮካዶ የመሳሰሉ ፍራፍሬዎች በቀጥታ አርሶአደር ቤተሰቦች መንገድ ዳር ይሰጥሉ፡፡ በመንገድ ዳር የመሸጡ ሁኔታ የተማቻቸ ባለመሆኑ የተነሳ ሽያጩ የተረጋጋ አይደለም፡፡ በሌላ አባባል አነስተኛ ሻጮች በመንገድ ዳር ተበታትነው የሚሸጡ ከመሆኑም በላይ በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታ የለም፡፡ የሚሸጡ ፍራፍሬች ጥራት ደረጃ ወጥነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል በእነዚህ መስመሮች ለተጓዦች የተዘጋጀ ማረፍያ የሚሆን የተሸሻለ ቦታ አመለኖሩ ለተጓዡ ምቾትን አይሰጥም፡፡ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የመንገድ ዳር የገበያ ቦታ እንዲኖር ፍላጎት አለው፡፡ ይሁንና ቦታውን የሚያስተዳደር አካል ባለመኖሩ እቅዱ ተፈጻሚ አልሆነም፡፡

## 3.5 የሕ/ሥራ ማህበራት ወቅታዊ እንቅስቃሴ

### 3.5.1 በኢትዮጵያ የሕ/ሥራ ማህበራት ወቅታዊ ሁኔታ

የሕ/ሥራ ማህበር የራሱ ህልውና ያለው ሰዎች የጋራ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ፍላጐታቸውን ለማሟላት በፍቃደኝነት ተሰባስበው በጋራ ባለቤትነትና በዲሞክራሲያዊ አመራር ያቋቋሙት የግል ድርጅት[1] ነው፡፡ የዘመናዊ ቅርጽ ያለው የሕ/ሥራ ማህበር በኢትዮጵያ የተቋቋመው በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ ከዚያ ወዲህ ብዙ ለውጦችን ሲያደርግ ቆይቶ አሁን ያለበትን ትርጉምና አሠራር ይዞ በአዋጅ ቁጥር 147/1998 ታህሣስ 29 ቀን 1998 (እ.ኤ.አ) ሲቋቋም የዓለም አቀፍ የሕ/ሥራ ማህበራት መርሆችና የዓለም አቀፍ የሠራተኛ ድርጅት ማሳሰቢያ 193 ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ተቋቋመ፡፡

በኢትዮጵያ ከ85% በላይ ሕዝቡ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን የግብርና ሴክተር 43% የሚሆነውን አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ይሸፍናል፡፡ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠን የግብርና ሴክተር ማልማት ጠቃሚና ወሳኝ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት እስትራቴጂ ለዚህ ዓላማ አሁን ያለው መንግስት ስልጣን ላይ ከወጣ ወዲህ በርካታ እስትራቴጂዎችና ፓሊሲዎች ወጥተው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ እነዚህም ግብርና መሪ ኢንድስትሪ ልማት እስትራቴጂ፣ ዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሣ ፕሮግራም፣ የምግብ ዋስትና እስትራቴጂ፣ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ድህነትን ለማጥፋት ዕቅድ፣ እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ናቸው፡፡ እነዚህን እስትራቴጂዎችንና ፓሊሲዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሕ/ሥራ ማህበራት የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ምርታማነት በማሳደግ የገበያ ሥርዓት በማስፋፋትና የሥራ ዕድል በመፍጠር ውጤታማ በመሆን መሪ ሚና እንደሚጫወት ይገመታል፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራት ሚና በኢኮኖሚ ልማት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ይልቁንም ለማህበራዊና ለህ/ሠብ ልማትና መሻሻል ማዕከላዊ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

#### (1) ብሔራዊ ሁኔታ

ከታች በሠንጠረዥ እንደታየው በሰኔ 2009 (እ.ኤ.አ) ጠቅላላ የሕ/ሥራ ማህበራት አባላት ብዛት 5 ሚሊዮን ነበር፡፡ ይህ ቁጥር ከሀገሪቱ ሕዝብ ብዛት 7% የሚሆን ነው፡፡ እንደ ፌደራል ሕ/ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ[2] ከሀገሪቱ ሕዝብ 33% የሚሆነው የሕ/ሥራ ማህበራት ከእንቅስቃሴያቸው ወይም ከአገልግሎታቸው በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ እንደሆኑ ግምት ያስቀምጣል፡፡ ከአባላት መካከል 16.46% የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡ ላለፉት 3 ዓመታት የተመዘገቡ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና የአባላት ቁጥር በ1.2 እጥፍ በየዓመቱ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

ሠንጠረዥ 3.5-1 ሀገር አቀፍ የሕ/ሥራ ማህበራት እውነታ

| ዝርዝር | በ2005/2006 (እ.ኤ.አ) | በ2007/2008 (እ.ኤ.አ) | ሰኔ 2009 (እ.ኤ.አ) |
|---|---|---|---|
| የተመዘገቡ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት | 19,146 | 23,167 | 26,672 |
| የአባላት ብዛት (በአጠቃላይ) | 3,911,934 | 4,668,564 | 5,899,761 |
| የሴት አባላት ንፅፅር (%) | 11 | 18 | 16.46 |
| የግብርና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት | 5,974 | 6,825 | 8,747 |
| የግብርና ሕ/ሥራ ማህበር ያልሆኑ ብዛት | 13,172 | 16,342 | 17,925 |
| የሸማቾች ሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት | 82 | 230 | 1,058 |

[1] በኢትዮጵያ የሕ/ሥራ ማህበራት ሁኔታ፣ ፌዴራል ሕ/ሥራ ኤጀንሲ፣ ሚያዝያ 2009 (እ.ኤ.አ)

[2] ፌዴራል ሕ/ሥራ ኤጀንሲ የሀገሪቱን የሕ/ሥራ እንቅስቃሴ የሚጠበቀውን ልማት በማሰብ ግንቦት 2002 (እ.ኤ.አ) በሀገሩቱ ሕገመንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የተቋቋማል፡፡.

| ዝርዝር | በ2005/2006 (እ.ኤ.አ) | በ2007/2008 (እ.ኤ.አ) | ሰኔ 2009 (እ.ኤ.አ) |
|---|---|---|---|
| የብድርና ቁጠባ ሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት | 4,178 | 5,235 | 5,845 |
| የህ/ሥራ ዩኒያኖች ብዛት | 121 | 162 | 174 |
| ሁለገብ የሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት | 91 | 102 | 107 |
| የብድርና ቁጠባ ሕ/ሥራ ዩኒያኖች ብዛት | 6 | 33 | 38 |
| የዩኒያኖች ካፒታል ብዛት (ብር) | | 156,327,436 | 208,909,493 |
| ከሕ/ሥራ ማህበራት ቅጥር የተገኘ ዓመታዊ ገቢ (ብር) | | 451,766,500 | |
| ከሕ/ሥራ ዩኒያን ቅጥር የተገኘ ዓመታዊ ገቢ (ብር) | | 81,152,500 | |
| ከሕ/ሥራ ባንክ የተገኘ ገቢ (ቅጥር፣ ብር) | | 9,300,000 | |
| ለሕ/ሥራ ማህበራት አባላት የትርፍ ክፍፍል (ከየዓመታዊ ትርፍ የተወሰነ ክፍል፣ ብር) | 10,000,000 | 15,000,000 | |
| የሕ/ሥራ ማህበራት አጠቃላይ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ (በብር ግምት) | | 542,209,000 | |

ምንጭe: በኢትዮጵያ የሕ/ሥራ ማህበራት ያሉበት ሁኔታ፡ ፌዴራል የሕ/ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ፣ ሚያዝያ 2009 (እ.ኤ.አ)

በሚቀጥለው ሠንጠረዝ እንደተመለከተው ከአጠቃላዩ ቁጥር የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች አባላት ብዛት አብዛኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ግብርና ነክ ያልሆኑ ሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት 41.6% በመያዝ አንደኛ ሲሆኑ በአባላት ብዛት ከጠቅላላው 80% ድርሻ በመያዝ የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት አብዛኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

**ሠንጠረዥ 3.5-2 የሕ/ሥራ ማህበራትና የአባላት ብዛት**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. የሕብረት ሥራ ማህበራት: | | | | | |
| | የሕ/ሥራ ማህበር ደረጃ | ብዛት | ንፅፅር | አባላት | ንፅፅር |
| | መሠረታዊ | 8,747 | 32.8% | 3,997,568 | 83.8% |
| | ዩኒያን | 131 | 75.3% | 2,788 | 72.4% |
| 2. የግብርና ሕ/ሥራ ማህበር ያለሆኑ: | | | | | |
| | የሕ/ሥራ ማህበር ደረጃ | ብዛት | ንፅፅር | አባላት | ንፅፅር |
| | መሠረታዊ | 11,098 | 41.6% | 292,570 | 6.1% |
| | ዩኒያን | 5 | 2.9% | 163 | 4.2% |
| 3. Financial Cooperatives: | | | | | |
| | የሕ/ሥራ ማህበር ደረጃ | ብዛት | ንፅፅር | አባላት | ንፅፅር |
| | መሠረታዊ | 6,827 | 25.6% | 477,817 | 10.0% |
| | ዩኒያን | 38 | 21.8% | 898 | 23.3% |
| | መሠረታዊ (ድምር) | 26,672 | 100% | 4,767,955 | 100% |
| | ዩኒያን (ድምር) | 174 | 100% | 3,849 | 100% |
| | ጠቅላላ ድምር | 26,846 | | 4,771,804 | |

ምንጭ: ፌዴራል የሕ/ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ፣ ሚያዝያ 2009 (እ.ኤ.አ)

### (2) ከገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራት የሚጠበቁ ሚናዎች

የሕ/ሥራ ማህበራት በኢትዮጵያ በገጠርና በከተማ አካባቢዎች [3] ብዙ (የሁለገብ) አገልግሎቶችን በማቅረብ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራት በጋራ እርምጃ የመደራደር አቅም በማሣደግ ለአነስተኛ አርሶአደሮች የውድድር አሠራር በመፍጠር፣ የቢዝነስ ዕድል በመፍጠር፣ ለፋይናንስ ምንጮች ተደራሽ በማድረግ፣ እና ዕውቀትና አቅም በማሣደግ ለአባሎቻቸውና ለህ/ሰቡ በአጠቃላይ የኑሮ መሻሻል ለማምጣት ያስችላል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሕ/ሥራ ማህበራት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ ተብሎ ይገመታል፡

[3] በኢትዮጵያ የሕ/ሥራ ማህበራት ሁኔታ፣ ፌዴራል ሕ/ሥራ ኤጀንሲ፣ ሚያዝያ 2009 (እ.ኤ.አ) ገጽ 8

1. የግብአት አቅርቦት አገልግሎቶች
2. ምርት
3. የምርት ግብይት
4. የብድር አቅርቦት አገልግሎቶች
5. የተጨማሪ እሴት መፍጠር
6. የፋይናንስ አገልግሎቶች
7. የማህበራዊ አገልግሎቶች

ለግብአት አቅርቦት አገልግሎት ሁለገብ ሕ/ሥራ ማህበራት ይህንን አገልግሎት በመስጠት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። የግብርና ግብአቶች በአብዛኛው ማዳበሪያ ለአርሶአደሮች የሚሠራጨው በሕ/ሥራ ማህበራት ኔትዎርክ ነው። የተጨማሪ እሴት መፍጠር በተመለከተ አንዳንድ ሕ/ሥራ ማህበራት በአንዳንድ ሥራዎች እንደ ማር በማሸግ፣ አቾሎኒ በማሸግ፣ በእህል ወፍጮ፣ ሰሊጥ በማበጠር እንዲሁም የምግብ ዘይት በማጣራት ተሠማርተዋል።

ከሁለገብ አገልግሎት ሕ/ሥራ ማህበራት በተጨማሪ ቁጠባና ብድር ሕ/ሥራ ማህበራት በቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት ጨምሯል። እንደ ፌደራል ሕ/ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ በቁጠባና ብድር ሕ/ሥራ ማህበራት በጥቅል የተንቀሳቀሰው ቁጠባ በ2006 (እ.ኤ.አ) በገጠርና ከተማ 986 ሚሊዮን ብር ሲሆን በ2008 (እ.ኤ.አ) በአማካይ በአንድ የማህበር አባል የተንቀሳቀሰው ቁጠባ ብር 176.33 ሲሆን በገጠር መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የተንቀሳቀሰው ቁጠባ ብር 12,171 ነበር።

### (3) የገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራትን ያጋጠሙ ችግሮች

በሕ/ሥራ ማህበራት አማካይነት ለገጠር ልማት ከፍተኛ ግምት የተሰጠ ቢሆንም አብዛኛዎቹ በውስጣዊ ችግሮቻቸው ምክንያት ግዴታና ኃላፊነታቸውን ሊወጡ አልቻሉም። የሚከተሉት የፌደራል ሕ/ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ የለያቸው ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።

- ሕ/ሥራ ማህበሩ በትክክል ችግሮቻቸውንና ፍላጐታቸውን መድረስ ባለመቻሉ አባሎቻቸው እምነት ማጣት /ዝቅተኛ ተሣትፎ መኖር/
- የካፒታል አለመኖር
- ደካማ የንግድ ሥራ ዕውቀት /ኢንተርፕሩነርሺፕ/
- የሕ/ሥራ ማህበራት የጎንዮሽና የአግድሞሽ ግንኙነት አለመኖር
- ተወዳዳሪ ሥ/አስኪያጆች፣ የማስፋፋት ስራ የሚሠሩና የዳይሬክተሮች ቦርድ አለመኖር
- በተጨማሪ እሴት መፍጠር ደካማ የቢዝነስ ልማት ድጋፍ
- ደካማ የሕግ፣ የኦዲትና የቁጥጥር ድጋፍ
- የወቅታዊና አስተማማኝ የገበያ መረጃ አለመኖርና የኔትዎርክ ግንኙነት ችግር ከተባባሪ አካላት ጋር መኖር

እነዚህ አብዛኛዎቹ የተለዩት ችግሮች የተያያዙ ሲሆን ለማያቋርጥ የሕ/ሥራ ማህበራት ልማት ሁሉአቀፍ የሆነ አቀራረብ የሕጋዊነት፣ የፓሊሲ እና የፊዚካል ማዕቀፍ ያካተተ ለድርጅት ልማት ምቹ የሆነ ሁኔታ ሊፈጥር ይገባል።

## 3.5.2 ወቅታዊ የሕ/ሥራ ማህበራት ሁኔታ በደቡብ ክልል

ከፌደራል ፓሊሲ ጋር በተመሳሳይ መልክ የደቡብ ክልል መንግስት በ2007 (እ.ኤ.አ) አዋጅ 111/2007 (ከዚህ በኋላ አዋጅ እየተባለ የሚጠራ) የፌደራል አዋጅ 147/1998 የሚያብራራ አወጣ። ከብዙ የማስተካከያ ሥራዎች በኋላ በ2010 (እ.ኤ.አ) የገበያ ተኮር ግብርና ማስፋፋት ዓላማ ያለውንና የሕ/ሥራ ማህበራትን አቅም በማሣደግ የልማትና የቁጥጥር

ማዕቀፍ በማዘጋጀት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር የክልል የግብይትና ሕ/ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ አቋቋመ።

## (1) የሕ/ሥራ ማህበራት ቁጥጥር በደቡብ ክልል

በሕ/ሥራ ማህበራት ብዛት የደቡብ ክልል ከኦሮሚያ ቀጥሎ 2ኛ ደረጃ ይይዛል። ከታች በሠንጠረዥ እንደተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ የሕ/ሥራ ማህበራት ቁጥር 6000 ይደርሳል። ከእነዚህ ውስጥ የሁለገብ ሕ/ሥራ ማህበራት ቁጥር 1000 ይሆናል። የእነርሱ ዋና ሥራቸው የግብርና ግብአት ማሰራጨት ሲሆን ጥቂቶቹ የግብርና ምርቶች በአብዛኛው በእህል ሽያጭ የተሠማሩ አሉ።።


**ሠንጠረዥ 3.5-3 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ሁኔታ (2007 እ/ኤ/አ)**

| የሕ/ሥራ ማህበራት ዓይነት | ማህበራት ብዛት | የአባላት ብዛት | | | ካፒታል (ብር) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | ወንድ | ሴት | |
| ሁለገብ | 1,025 | 835,100 | 752,773 | 82,327 | 157,074,040 |
| የወተት ላሞች እርባታ የሕ/ሥራ ማህበራት | 59 | 4,541 | 4,011 | 530 | 1,323,201 |
| ብድርና ቁጠባ | 869 | 63,244 | 37,010 | 26,234 | 24,177,404 |
| የሸማቾች የሕ/ሥራ ማህበራት | 52 | 3,444 | 2,562 | 882 | 1,512,278 |
| የማዕድን ሥራ ሕ/ሥራ ማህበራት | 9 | 467 | 445 | 22 | 150,636 |
| የገጠር ኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች የሕ/ሥራ ማህበር | 7 | 789 | 669 | 120 | 212,045 |
| የዕደጥበብ የሕ/ሥራ ማህበራት | 24 | 690 | 330 | 360 | 482,114 |
| የቤት ሥራ ሕ/ሥራ ማህበር | 119 | 3,900 | 3,313 | 587 | 12,507,616 |
| የአገልግሎት የሕ/ሥራ ማህበራት | 20 | 818 | 509 | 309 | 643,972 |
| የትምህርትና ሥልጠና ሕ/ሥራ ማህበራት | 5 | 289 | 218 | 71 | 257,373 |
| የወጣቶች ማህበር | 3,310 | 105,347 | 90,669 | 14,678 | 2,473,540 |
| የግንባታ ሕ/ሥራ ማህበራት | 13 | 290 | 279 | 11 | 265,688 |
| ድምር | 5,512 | 1,018,919 | 892,788 | 126,131 | 201,079,907 |

ምንጭ: ፌዴራል የሕ/ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ

የሁለተኛ ደረጃ የሕ/ሥራ ማህበራት የሆኑ 34 ሕ/ሥራ ማህበር ዩኒያኖች በክልሉ ሥራ ላይ ናቸው። ከእነዚህ 34 ዩኒያኖች 41% የእህል ዩኒየኖች፣ 32% የቁጠባና ብድር ሕ/ሥራ ማህበር ዩኒየኖች 15% የቡና ዩኒያኖች ከተቀሩት (1) የማር ዩኒያን (1) የአትክልትና ፍራፍሬ ዩኒያን፣ (1) የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ዩኒያን እና (1) የዘር ብዜት ዩኒያን ናቸው። የሚገኙበት ቦታ በሚመለከት ከ6 ልዩ ወረዳዎች አማሮ፣ ቡርጂ፣ ኮንታ፣ ባስኬቶ፣ ኮንሶና ደራሼ ልዩ ወረዳዎች ዩኒያን ለማቋቋም በቂ የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበራት[4] የሌላቸው በስተቀር በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ተቋቁመዋል። ሠንጠረዥ 3.5-4 የግብርና ግብይት ማጠናከሪያ የጥናት ፕሮጀክት የተመረጡ በግብርና ምርትና ግብይት የሚሣተፉ የሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያኖች ማጠቃለያ የኢንቬንተሪ ጥናት ያሣያል።

[4] ዩኒያያንን ለመቋቋም ብያንስ ሁለት መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ያስፈልጋሉ




**ምስል 3.5-1 በደቡብ ክልል ዩኒየኖችና ፌደሬሽን ያሉበት ሥፍራ**

የደቡብ ክልል 3ኛ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር በማቋቋም በሀገሪቱ የመጀመሪያው ነው፡፡ የክልሉ የገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን የተቋቋመውና ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው በ2008 (እ.ኤ.አ) ነው፡፡ በሠንጠረዥ 3.5-4 እንደተመለከተው 13 ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያኖች አባላቱ ናቸው፡፡ የፌደሬሽን የቅድሚያ ሥራው የግብርና ግብአቶችን በማዕከላዊነት ከውጪ በሚያስገባው በግብርና ግብአቶች አቅራቢያ ኮርፖሬሽን ለመረጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበራት ወይም ለወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ከውጪ የሚያስገባውን ተቀብሎ ማሰራጨት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአባል ዩኒያኖች የሥልጠና ፕሮግራም በጊዜያዊ ሁኔታ ያዘጋጃል፡፡ ለወደፊት ፌደሬሽኑ የግብርና ምርቶችን እንዳ በሎቄ፣ ሰሊጥና ዝንጅብል በተለይ ወደ መካከለኛው ምስራቅ እሲያ ሀገሮች ለመላክ ዕቅድ አለው፡፡


## ሠንጠረዥ 3.5-4 የሕ/ሥራ ዩኒያን ቆጠራ ውጤት


| Name | Type | Town | Zone | Estab. | No. of Staff | No. of Members (M/F) | No. of PC | Capital (million birr) | Latest Sales Volume (unit: Qt) | | | Federation Membership |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | Wheat | Maize | Teff | |
| Walta Farmers Cooperative Union | Grain | Butajira | Guraghe | May 2003 | 9 | 7765 (M/6,747 F/1,018) | 23 | 1.6 | 4,000 | 2,000 | 1,300 | ★ |
| Admass Farmers Cooperative Union | Grain | Welkite | Guraghe | May 2003 | 12 | 24596 (M/21,827, F/2,769) | 55 | 3.6 | 287 | 3,564 | 2,980 | ★ |
| Melik Silite's Farmers Cooperative Union | Grain | Werabe | Silitie | March 2004 | 10 | 29960 (M/26,950, F/3,010) | 54 | 3.6 | 4,451 | 2,000 | NA | ★ |
| Licha Hediya's Farmers Cooperative Union | Grain | Hosana | Hadiya | May 2002 | 30 | 89657 (M/73,268, F/16,389) | 32 | 18 | 52,505 | 667 | 750 | ★ |
| Matteiyoma Badewacho Farmers Cooperative Union | Grain | Shonei | Hadiya | February 2008 | 5 | 12374 (M/11,724, F/650) | 10 | 0.6 | NA | NA | 105 | |
| Ambericho Farmers Cooperative Union | Grain | Durame | Kembata Tembaro | June 2005 | 6 | 7113 (M/5,893, F/1,220) | 21 | 1.7 | 7,000 | 5,000 | 2,500 | ★ |
| Angacha Farmers Cooperative Union | Grain | Doyogena | Kembata Tembaro | May 2002 | 6 | 7944 (M/7,261, F/683) | 9 | 1.5 | 10,000 | 3,000 | NA | ★ |
| Damota Wolayta's Farmers Cooperative Union | Grain | Wolayita Sodo | Wolayita | February 2004 | 11 | 22780 (M/18,241, F/4,539) | 63 | 5.3 | NA | 3,000 | NA | ★ |
| Sidama Ealto Farmers Cooperative Union | Grain | Hawassa | Sidama | October 2003 | 11 | 8930 (M/8,444, F/486) | 62 | 5.5 | 400 | 6,100 | 1,200 | ★ |
| Eseipie Dicha Farmesrs Crop Marketign Union | Grain | Sewula | Gamo Gofa | October 2007 | 2 | 2611 (M/2,157, F/454) | 15 | 2 | No Sales | 3,000 | 2,000 | |
| Godefo Kaffa Farmers Cooperative Union | Grain | Bonga | Keffa | December 2007 | 3 | 5131 (M/4,139, F/892) | 18 | 0.1 | 584 | 1,271 | 114 | ★ |
| South Omo Grain | Grain | Jinka | South Omo | April 2005 | 4 | 12944 (M/12,834, F/110) | 21 | 1.9 | No Sales | 4,500 | NA | ★ |
| Manecheno Crop Producers Farmers Coopeartive Union | Grain | Alaba Kulito | Alaba special woreda | December 2004 | 5 | 5580 (M/5,300, F/280) | 17 | 1.5 | NA | 5,000 | 2,000 | ★ |
| Ediget Farmers Seed Multiplication Marketing Cooperative Union | Seed Multiplication | Butajira | Guraghe | November 2009 | 9 | 875 (M/835, F/40) | 13 | 0.3 | NA | NA | NA | |
| Gamo Gofa Farmers Fruit & Vegetable Marketing Cooperative Union | Fruit & Vegetable | Arba Minch | Gamo Gofa | June 2005 | 13 | 1,329 (M/1,226 F/104) | 15 | 0.5 | Banana (37,000), Mango, Lemon, Apple, Pear, Plum, etc. | | | ★ |
| Oyissa Grain, Livestock & Livestock Products Marketing Cooperative Union | Grain & Livestock | Tercha | Dawro | September 2009 | 2 | 3,546 (M/3,273 F/273) | 31 | 0.1 | NA | NA | No Sales | |
| Kaffa Forest Honey Production & Marketing Cooperative Union | Honey | Bonga | Keffa | February 2007 | 4 | 1,658 (M/1,422 F/236) | 7 | 0.2 | Honey | | | ★ |

ምንጭ: በቆጠራ ዳሰሳ መሠረት በጥናት ቡድኑ የተዘጋጀ (መጋቢት 2010 እ.ኤ.አ)

### (2) የሕ/ሥራ ማህበራት የአሠራርና የአመራር አደረጃጀት

የሕ/ሥራ ማህበራት ሕጋዊ ሰውነት ያለውና በሚመለከተው ባለሥልጣን በሕጋዊ አሠራር የተመዘገበ እንደመሆኑ፣ ድርጅታዊ መዋቅሩ፣ ለአባልነት የሚያስፈልገው መስፈርት፣ መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች በግልጽ በአዋጅ የተቀመጠ ነው፡፡ የድርጅታዊ መዋቅርና የውስጥ አደረጃጀትና ግዴታዎች በአዋጁ በዝርዝር ከተገለፁት መካከል ጥቂቶች ናቸው፡፡ የሚቀጥለው ምስል የሕ/ሥራ ማህበር ድርጅታዊ መዋቅር ያሣያል፡፡ ከታች እንደተመለከተው በውስጣዊ አደረጃጀት ሥራ አስኪያጅ ቀጥረው ከሚያሠሩና ሥራ አስኪያጅ ከሌላቸው ሕ/ሥራ ማህበራት መካከል ልዩነት አለ፡፡ ብዙ ጊዜ ሕ/ሥራ ዩኒያኖች ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራሉ፡፡ በሌላ በኩል የመጀመሪያ ሕ/ሥራ ማህበራት ከፋይናንስ እጥረት የተነሣ ሥራ አስኪያጅ አይቀጥሩም፡፡




**ምስል 3.5-2 በአዋጅ የተገለፀው ድርጅታዊ ቻርት**

በማንኛውም ሕ/ሥራ ማህበር ሁሉም አባላት የሚሣተፉበት ጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን የሕ/ሥራ ማህበር የበላይ አካል በማንኛውም ድርጅቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች የመጨረሻ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልና በሁሉም እምነት የተጣለበት ነው፡፡ የሥራ አመራር ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤ ሥር ይሆናል፡፡ የኮሚቴው አባላት በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ ሲሆን ለተከታታይ ሁለት ጊዜ ለ6 ዓመታት በአመራር ተመርጦ ሊሠራ ይችላል፡፡ የሥራ አመራር ኮሚቴ በቁጥጥር ኮሚቴ (በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ) በቅርብ እይታ የሥራ ክንውኑን ይከታተላል፡፡ የጠቅላላ ጉባኤው በማናቸውም ጉዳዮች የሥራ አመራር ኮሚቴ ጭምር የሚቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡

የሥራ አስኪያጅ የተቀጠረ እንደሆነ የዕለት ዕለት የሕ/ሥራ ማህበሩ ሥራዎች በሥራ አመራር ኮሚቴ ሥር ሆኖ ይመራል፡፡ በሌላ በኩል የተቀጠረ ሥራ አስኪያጅ ከሌለ የዕለት ዕለት ሥራዎች በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚመራ ሲሆን ከሥራ አመራር ኮሚቴ በተወጣጡና በንዑሳን ኮሚቴዎች እንደ ግዢ ኮሚቴ፣ የግብይት ኮሚቴ፣ የብድር ኮሚቴ እና ለሌሎች ድጋፍ እየተደረገ ሥራዎችን ያካሂዳሉ፡፡ ከሥራ አስኪያጅ ሌላ ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያኖች ሥራ አስኪያጁን የሚረዱ ጥቂት የሰው ኃይል በመቅጠር የዕለት ዕለት ሥራዎችን ያከናውናል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ፀሐፊ፣ የሂሣብ ባለሙያ፣ ገንዘብ ያዥ ንብረት ያዥና ሌሎችም እንደሥራው መጠንና የሥራው ዓይነት ተቀጥረው ይሠራሉ፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ከሂሣብ ባለሙያ በስተቀር የአስተዳደር ሠራተኞችን አይቀጥሩም፡፡

የጠቅላላ ጉባኤና የስራ አመራር ኮሚቴ በሁሉም የሕ/ሥራ ማህበር ሥራዎች ውሳኔ ለመስጠት ሙሉ ኃላፊነት ያላቸው ቢሆንም የማህበሩ ድርጅታዊ ስኬታማነት የሚወሰነው

የዕለት ቢዝነስ ሥራዎችን በሚመሩት ብቃት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አብዛኛዎች ማህበራት የሚመሩት በድርጅታዊና በቢዝነስ ማኔጅመንት ብዙ ልምድ በሌላቸው ተመራጭ አባላት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ የሚለው የሥራ አመራር ኮሚቴዎች የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ጨምሮ በየ3 ዓመት ምርጫ ተደርጐ የሚመጡ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ ሌላ ማንም ከሁለት ጊዜ ተከታታይ የምርጫ ጊዜ በላይ ማገልገል አይችልም፡፡ ይህ ማለት አብዛኛው ማህበራት በመሠረታዊ ክህሎትና ሥራቸውን ለመምራት ለሚያስፈልገው ዕውቀት በየጊዜው ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡ ማለት ነው፡፡ የሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያኖች በተመለከተ ሁሉም ስራ አስኪያጅ የሚቀጥረው ሲሆን ሁሉም ተወዳዳሪ የሆኑ ፕሮፌሽናል ባለሙያዎችን በፋይናንስ እጥረት ምክንያት ሊቀጥሩ አይችሉም፡፡ በአንዳንድ ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያኖች የማበረታቻ አሠራር መጀመራቸው ምናልባት ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ለማቆየት ወርሃዊ ደመወዝ መክፈል ባይችሉ እንኳን ጥሩ ጅምር ሆኖ ሊታይ ይችላል፡፡

አዋጁ ከዚህ በተጨማሪ የፋይናንስ ጉዳዮችን ከሕ/ሥራ ማህበር አመራር ጋር በተያያዘ የሚያነሣው ጥያቄ አለ፡፡ አዋጁ ማንኛውም ሕ/ሥራ ማህበር ከትርፉ 30% ወደ ካፒታሉ እንዲጨምሩ ያስገድዳል፡፡ የቀሪው 70% አጠቃቀም በጠቅላላው ጉባኤ ይወሰናል፡፡ ከፍ ያለ የትርፍ ክፍፍል አባላቱ በማህበሩ ውስጥ እንዲቆዩ የሚያበረታታ ከመሆኑም በላይ ሌሎች ወደ ማህበሩ እንዲገቡ ይስባል፡፡ ይሁንና ሕ/ሥራ ማህበራት በትርፍ ክፍያና ለማህበሩ ልማት በረዥም ጊዜ ኢንቨስትመንት መካከል ማመዛዘን ይጠበቅባቸዋል፡፡


### (3) የሕ/ሥራ ማህበራት አባልነት

በደቡብ ክልል መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ቁጥር ከዓመት ዓመት እያደገ መጥቷል፡፡ ከገጠር ቤተሰቦች ወደ 30% የሚክለው የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት አባላት እንደሆኑ ይገመታል፡፡ [5] የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በቀበሌ ደረጃ በወረዳው ግብይት ጽ/ቤት ተቆጣጣሪነት የሚሠሩ አደራጆችን ይመድባል፡፡ እነዚህ አደራጆች ለሕ/ሥራ ማህበራት የዕለት ዕለት ድጋፍ በተመደቡበት አከባቢ የሚሰጡ ሲሆን አደራጆቹ በሕ/ሥራ ማህበር ሥራና ጥቅሙን በሚመለከት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሰራሉ፡፡ አንድ የህ/ሠብ አደራጅ በሲዳማ ዞን በልበ ሙሉነት ያረጋገጠው አንድ ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ 80 የሕ/ሥራ ማህበር አባላትን በመጨመር የአባላት ቁጥር ከ420 ወደ 500 እንደደረሰ ተናግረዋል፡፡

ሆኖም አብዛኛዎች አርሶአደሮች በሕ/ሥራ ማህበራት የመሳተፍ ጥቅም የተረዱ አይመስልም፡፡ ከታች ያለው ቁጥር የሚያሳየው የአርሶአደሮች በሕ/ሥራ ማህበራት ያለውን አሉታዊ እይታ ያሳያል፡፡ በጃይካ የጥናት ቡድን በተደረገው መነሻ ዳሰሳ ጥናት በ2011 (እ.ኤ.አ) መጀመሪያ 600 አባወራዎች ተጠይቀዋል፡፡ ስለ ሕ/ሥራ ማህበራት ጥቅም ተጠይቀው ምስል 3.5-3 እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ ወደ አሉታዊ አቅጣጫ ነበሩ፡፡

በአሁኑ ወቅት ብዙዎች መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ማዳበሪያ በማሠራጨት ስራ ብቻ የሚሣተፉ ሲሆን በግብርና ምርት ሽያጭ የሚሣተፉ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ከጠቅላላ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላ እንደ አንድ ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያን ስራ አስኪያጅ እነዚያ በግብርና ምርት በጋራ ሽያጭ የሚሳተፉ

[5] ምንጭ፡ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ግብይት ስርዓት ማጠናከሪያ ጥናት ጥቅምት 2010 (እ.ኤ.አ)




**ምስል 3.5-3 በግብርና ህ/ሥራ ማህበራት ጥቅሞች እይታ**

*መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ምርቱን ሊገዙ የሚችሉት ከፋይናንስ የከፋ እጥረት የተነሣ ከጥቂት አባላት ብቻ እንደሆነ ገልፀዋል። ምንም እንኳን የሕ/ሥራ ማህበራት አባላት ቁጥር እያደገ እንደመጣ ሪፖርቶች ቢገልፁም የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አብዛኞቹ አባላት ጥቅሙን እንዲረዱ በማድረግ ረገድ የተሰራው ስራ አነስተኛ ነው። ስለሆነም የጥናቱ ውጤት እንደሚያሣየው ብዙ አርሶአደሮች የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ኑሮአቸውን ሊያሻሽል እንደሚችል አድርገው አይቀበሉትም።*

*<u>በሕ/ሥራ ማህበራት የሴቶች ተሳትፎ:</u>*
*በደቡብ ክልል የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ውስጥ የሴቶች ተሣትፎ 12% ብቻ ነው።*[6] *ከዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ ምክንያት አብዛኞቹ ሕ/ሥራ ማህበራት አባላትን ሲመዘግቡ ከአንድ ቤተሰብ አንድ ሰው ብቻ ይመዘግባሉ። በኢትዮጵያ ወንዶች እንደ ቤተሰብ ኃላፊ ስለሚቆጠሩ እነሱ ናቸው በምዝገባ ወቅት በሕ/ሥራ ማህበር የሚመዘገቡት።*

*አንድ የተለየ ያጋጠመ ነገር በሶዶ ዙሪያ በወላይታ ዞን ነው። የወረዳ ጽ/ቤት በመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሴት አባላትን ቁጥር ለማሣደግ ዘመቻ በ2005/2006 (እ.ኤ.አ) ጀመረ። መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ዘመቻ በአውንታዊ ምላሽ ሰጡ። አንዳንዶች መተዳደሪያ ደንባቸው ለሴቶች አባላት ቁጥር ዝቅተኛው 25% እንዲሆን ማሻሻያ አደረጉ። በጉልጉላ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በዘመቻው ወቅት በአባላት ምዝገባ ባልና ሚስት ከአንድ ቤተሰብ የተሻሻለውን መተዳደሪያ ደንባቸውን በመጠበቅ መዘገቡ። ሁለቱም ባልና ሚስት የአባልነት መዋጮአቸውን በየራሳቸው መክፈልና የግብርና ምርትም ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበሩ በየራሳቸው ወይም በጋራ መሸጥ ጀመሩ። የጃይካ ጥናት ቡድን ጥቂት አባላትን ለውይይት ባገኘ ጊዜ ሁለቱም ባልና ሚስት ሀሣባቸውንና አመለካከታቸውን በንቃት አቀረቡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ በገጠር ኢትዮጵያ በጣም ውሱንና የተለየ ነው። በውይይት ወቅት አንዱ አባል የሴቶች መሣተፍ ጥቅሙን በመቀበል እንዲህ በማለት "ሁለታችንም ለአንድ ዓላማ እንሠራለን። ስለዚህ የሴቶች አባላት መኖር ጥሩ ነው" አለ።*

*የወረዳው ጽ/ቤት ጥረት የዳሞታ ወላይታ ገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያን በአባልነት ላይ ተንፀባርቋል። የሴቶች ቁጥር ከጠቅላላ አባላት ብዛት 20% ሲሆን ይህ ማለት ከክልሉ ቁጥር 12% በጣም ከፍ ያለ ነው።*


[6] ምንጭ፡ በኢትዮጵያ የሕ/ሥራ ማህበራት ሁኔታ፣ ፌዴራል ሕ/ሥራ ኤጀንሲ፣ ሚያዝያ 2009 (እ.ኤ.አ)

### 3.5.3 የሕ/ሥራ ማህበራት ዋና ዋና ስራዎች

የሕ/ሥራ ማህበራት ዋና ዋና ሥራዎች 2 እጥፍ ናቸው፡፡ አንዱ የግብርና ምርት ልውውጥ የግብርና ምርቶች ግዥና ሽያጭ ሲሆን ሌላው የማዳበሪያ ስርጭት ማመቻቸት ነው፡፡

#### (1) የግብርና ምርቶች

1) የእህል ግብይት
በደቡብ ክልል ወደ 40% የሚሆኑ የሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያኖች በዋናነት የእህል ስብል ግብይት የሚያካሂዱ ናቸው፡፡ በሕ/ሥራ ማህበራት አማካይነት የሚካሄደው የእህል ግብይት ፍሰት በሚቀጥለው ምስል 3.5-4 ተገልጿል፡፡




**ምስል 3.5-4 በሕ/ሥራ ማህበራት አማካይነት የሚካሄደው የእህል ግብይት**

የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አባላት እንዲሁም አባል ያልሆኑ ምርታቸውን ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ይሸጣሉ፡፡ ከነጋዴዎች ይልቅ ብዙ ጊዜ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ጥቂት ብር[7] በኩንታል አስበልጠው ይከፍላሉ፡፡ እህል ሰብል በአርሶአደሮች ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሚቀርበውን በተመለከተ ዩኒያኖች፣ የመንግስት ኃላፊዎች እንዲሁም መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት እራሳቸው የተስማሙት አርሶአደሮች በእህል ጥራት በተሰጣቸው ምክርና ስልጠና መሠረት የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም ከዚህ ጋር በተያያዘ የእህል ጥራት የበለጠ መሻሻል እንዳለበት ተቀብለዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት በአርሶአደሮች የቀረበውን እህል በጥራት ጉድለት ምክንያት አለመቀበል እንዳለባቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል የአካባቢው ነጋዴዎች የጥራት ጉዳይ ምንም ቦታ ሳይሰጡ እህሉን ይቀበላሉ፡፡ ጥራቱ ዝቅተኛ ከሆነ ዋጋውን ዝቅ አድርገው ይገዛሉ፡፡ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ኃላፊዎች ለምን አርሶአደሮች ከአካባቢ ነጋዴዎች ይልቅ እንደሚመርጡ የሚከለተለውን ምክንያት ያስቀምጣሉ፡፡

- መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ብዙ ጊዜ የተሻለ ዋጋ ለአርሶአደሮች ከአከባቢ ነጋዴዎች ይልቅ ይከፍላሉ፡፡
- የአከባቢ ነጋዴዎች ብዙ ጊዜ ትክክል ያልሆነ ሚዛን መጠኑን ለማጭበርበር ይጠቀማሉ፡፡ ለዚህ ምክንያት ነው የአከባቢው ነጋዴዎች እምነት የማይጣልባቸው፡፡

[7] የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የጥናት ቡድኑ ያነጋገራቸው ብዙ ጊዜ ለአርሶአደሮች የሚከፍሉት ከ5 እስከ 10 ብር በላይ በኩንታል ከአከባቢው ነጋዴዎች አስበልጠው ነው፡፡

- አባላትን በሚመለከት በዓመቱ መጨረሻ የትርፍ ክፍያ ባላቸው የአባልነት ድርሻ መጠን ይቀበላሉ፤ እንዲሁም ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በሸጡት የምርት መጠን ይቀበላሉ፡፡

አብዛኛዎቹ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ብድር አባል ከሆኑበት የሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒየን ይቀበላሉ፡፡ የገዙትን እህል ለሕ/ሥራ ማህበር ዩኒየኖች ይሸጣሉ፡፡ የምርት ምልልስ ጊዜ ከመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ወደ ዩኒየኖች ከአንዱ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ከሌላው ይለያያል፡፡ የመጋዘን መገኘትና ሁኔታ ለማጓጓዙ ወይም ለምልልሱ መጠን ዋናው ወሣኝ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሣሌ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በሲዳማ ዞን መጋዘን ስለሌላቸው መበሣጨታቸውን ገልፀዋል፡፡ ምክንያቱም በምርት ወቅት በየ3 ወይም በየ4 ቀን ምርታቸውን ለዩኒያኑ ማስረከብ እንዳለባቸው ህጉ ቢኖርም የመጋዘን አለመኖር መቸገራቸውን ተናግረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተሻለ ዋጋ ተደራድረው ለመሸጥ እንዳላስቻላቸው ወይም አጠራቅመው የምርቱን መጠን ጨምረው እንዳይሸጡ እንቅፋት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ዮኒየኖች ከአካባቢ ነጋዴዎች ይልቅ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ትንሽ የተሻለ ዋጋ እንደሚከፍሉ በተለይ ከመሥረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የመጣው እህል ጥራቱ ጥሩ ከሆነ ማለት ነው፡፡ አንድ የዩኒየን ሥራ አስኪያጅ እንደገለፀው ዩኒየናቸው ከ30-40 ብር ጭማሪ በ1 ኩንታል ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ጥራቱ የተሻለ ከሆነ በአካባቢው ካለው የገበያ ዋጋ በላይ እንደሚከፍላቸው ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ሌላ ዩኒየን ሥራ አስኪያጅ እንዳረጋገጠው የተሻለ ጥራት ያለውንና በመጠኑ ብዙ የሆነ ምርት ማቅረብ ከቻልን ገዢዎችን ለማግኘት ምንም አንቸገርም ብሏል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሥራ አስኪያጁ እንደገለፀው ገዢዎች የተሻለ ዋጋ እንደሚከፍሉና ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የከፈሉትን እንደሚሸፍን አብራርቷል፡፡

የእህል ሕ/ሥራ ማህበራት ሥራቸውን ቀስ በቀስ አሳድገዋል፡፡ ሆኖም የእነርሱ በክልሉ ገበያ ተሣትፎ እምነት ነው፡፡ ሠንጠረዥ 3.5-5 ከታች ዋና ዋና የእህል ዓይነት ገበያ ዝውውር በደቡብ ክልል በዩኒያኖች ያሣያል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.5-5 በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/ የተሸጠ እህል መጠን**

| የእህል ዓይነት | በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የተሸጠ መጠን(ቶን)* | በዩኒያን | % |
|---|---|---|---|
| በቆሎ | 67,828 | 3,910 | 5.8% |
| ጤፍ | 88,288 | 1,395 | 1.6% |
| ስንዴ | 61,477 | 7,923 | 12.9% |


* ማዕከላዊ እስታቲስቲክስ ኤጀንሲ, የግብርና ናሙና ዳሰሳ ጥናት 2008/2009 ጥራዝ VII (ቡልቲን 446)
** በኢንቨንቴሪ ተመስርቶ በጥናት ቡድኑ የተዘጋጀ6 (መጋቢት 2010 እ.ኤ.አ)

የበቂ ካፒታል አለመኖርና የአስተዳዳር አቅም ደካማ መሆን በመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትም ሆነ በዩኒያኖች የገበያ ልውውጥ መጠን እንዳያሣድጉ ትልቅ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሆኖም ስንዴን በተመለከተ 7923 ቶን በዩኒየኖች ግብይት ከተደረገው 5250 ቶን በአንድ ዩኒያን የተካሄደ ነው፡፡ ይህ የሚያሣየው ዩኒየኖች በክልሉ እህል ግብይት ለመሣተፍ እምቅ ኃይል እንዳላቸው ነው፡፡

2) የፍራፍሬ ግብይት

በደቡብ ክልል አንድ ብቻ የፍራፍሬ ህ/ሥራ ዩኒየን አለ፡፡ የሚገኘውም በብሔራዊ ደረጃ በሙዝ ምርት ታዋቂ በሆነው በጋሙ ጎፋ ዞን ነው፡፡ በዩኒያኑ የሚገበየው ሙዝ ሲሆን

በሌሎች ፍራፍሬዎችም እንደ ማንጎና አፕል ገበያ ለማስፋፋት ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ እንደ ሌሎቹ ዩኒያኖች በክልል ውስጥ በእህል ንግድ እንደሚሠማሩ፣ የጋሞ ጎፋ ዩኒያን እህል ከመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ይገዛል፡፡ የሙዝ ግዢ ፍሰት ከመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በሚቀጥለው ምስል 3.5-5 ተብራርቷል፡፡




**ምስል 3.5-5 የሙዝ ግብይት በሕ/ሥራ ማህበራት አማካይነት**

በጃይካ የጥናት ቡድን በተደረገው የቆጠራ ጥናት በ2010 (እ.ኤ.አ) መሠረት ዩኒያኑ ሪፓርት እንዳደረገው በዩኒያኑ አማካይነት በዓመት የተደረገው የሙዝ ግብይት 37,000 ኩንታል ሲሆን ይህም በዞኑ የተደረገው የሙዝ ግብይት 10% ነው፡፡[8] በሌሎችም በክልሉ አካባቢዎች እንደታየው ብዙ አርሶአደሮች በጋሞ ጎፋ ዞን የሚያነሱት፣ ችግር የአካባቢው ነጋዴዎች የሚያደርጉት የቢዝነስ ሥራ ነው፡፡ የአካባቢው ነጋዴዎች ትክክል ያልሆነ ሚዛን በጉልበት እንደሚጠቀሙና የአርሶአደሮችን ደካማ የመደራደር አቅም ጋር አያይዘው ይጠቀሙበታል፡፡

በክልሉ ካሉት ተመሳሳይ አባሎቻቸው በተለየ ሁኔታ በጋሞ ጎፋ ዞን ያሉት የሙዝ አርሶአደሮች በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የተለየ ልምምድ አላቸው፡፡ እነርሱ በሙዝ ማምረትና የንግድ እንቅስቃሴ ከ20 እስከ 30 ዓመት ልምድ አላቸው፡፡ ከመንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ እየተሰጣቸው በአ/አ ካሉት ነጋዴዎች ጋር የቀጥታ ግንኙነት ለመፍጠር ችለዋል፡፡ አንድ የወረዳ ባለሙያ እንደገለፀው የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በመቋቋም አርሶአደሮች ቀጥታ ግንኙነት አ/አ ካሉት ነጋዴዎች ጋር በማድረግ የአካባቢው ነጋዴዎች ከማያቀርቡት የተሻለ ዋጋ ለማግኘት ችለዋል ብሏል፡፡ ከዚህ ሌላ በ2010 ዓ/ም ዩኒየኑ በአ/አ መጋዘን ስለተከራዩ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ቀጥታ ምርታቸውን ወደ አ/አ የዩኒየን መጋዘን መላክ ጀመሩ አንድ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር 54 አባላት ያሉት በየሣምንቱ ከ2-3 ሙሉ ጭነት መኪና ወደ አ/አበባ ይልካል፡፡ በቅርብ ቀን የችርቻሮ ሱቅ በአ/አባበ የራሳቸውን ምርት ለመሸጥ ከፍተዋል፡፡ ሆኖም የማህበሩ አባላት በቢዝነስ ዕቅድ ማውጣት የዕውቀትና የልምድ ማነስ ሥራዎችን ለማስፋፋትና እንደፍላጐታቸው ትርፋቸውን ለማሻሻል አላስቻላቸውም፡፡ ዩኒያኑ በአሁኑ ስዓት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያና ወደ ውጭ ሀገርም በተለይም ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ገበያውን ለማስፋፋት አማራጮችን እያፈላለገ ይገኛል፡፡

በዚህ አካባቢ የሚመረተው ሌላኛው ፍራፍሬ ማንጎ ነው፡፡ ሆኖም የጋሞ ጎፋ ዩኒያንና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የማንጎ ግብይት እንደ ሙዝ ግብይት በጣም የጠነከረ አይደለም፡፡

[8] ምንጭ፡ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ግብይት ስርዓት ማጠናከሪያ ጥናት መሸጋገሪያ ሪፖርት (2) 2011 (እ.ኤ.አ)

3) የዝንጅብል ግብይት

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በዝንጅብል ምርት በሀገር አቀፍ ደረጃ 99% ድርሻ አለው ካምባታ ጠምባሮና ወላይታ ዞኖች በክልሉ ከፍተኛውን መጠን የሚያመርቱ ናቸው።[9] ዝንጅብል እንደ ውጭ አገር የሚላክ ሸቀጥ ቢገመትም በጣም ዝቅተኛ ከሆነው የድህረ ምርት አያያዝ የተነሣ የጥራት ደረጃ በአገር ውስጥ ያለው ግብይት በዓለም ካለው የገበያ ደረጃ እጅግ ዝቅ ያለ ነው። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የሚመረተው የዝንጅብል ምርት በአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ የሚውል ይመስላል።

በሁለቱ ዞኖች ከፍተኛ የምርት መጠን ቢኖርም በሕ/ሥራ ማህበራት በተለይም በዩኒየኖች አማካይነት የሚደረገው የዝንጅብል ግብይት በጣም አነስተኛ ነው፤ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ዩኒየን ሥራ አስኪያጅ በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ የዝንጅብል ገበያ መዋዠቅ እንዳለና ጥራቱ የወረደ ዝንጅብል በመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት እንደሚቀርቡ የእነርሱም በዝንጅብል ምርት ገበያ ያለው ተሣትፎ ደካማ እንደሆነ አብራርቷል። ከእነዚህ ችግሮች የተነሣ ከ4 ዓመት በፊት የደረቅ ዝንጅብል ግብይት ከመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ጋር የነበረውን ጥረት እንዳቋረጡ ገልፆል።

ሆኖም በ2010/2011 (እ.ኤ.አ) ከተመዘገበው በጣም ከፍተኛ የገበያ ዋጋ የተነሣ የህ/ሥራ ዩኒየን በከምባታ ጠምባሮና ዳሞታ ወላይታ ሕ/ሥራ ዩኒየን ወደ ዝንጅብል ገበያ መግባት ጀመሩ። በ2010 የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ባካሄደው የጋራ የውይይት ስብሰባ ላኪዎች፣ ነጋዴዎችና ሕ/ሥራ ማህበራት እንዲሣተፉ ተጋብዘው ነበር። ሁለቱም የአምብርቾና የዳሞታ ወላይታ ዩኑየኖች ከአንድ ወደ ውጭ ላኪ ድርጅት ጋር የጋራ ስምምነት ሰነድ ፈርመው ነበር እንዳጋጣሚ ላኪ ድርጅቱ ከሁለቱም ዩኒያኖች ጋር የስምምነት ሠነድ የፈረመው ከሁለቱም ዩኒያኖች የቀረበው ዝንጅብል በጥራትም በመጠንም ዝቅ ያለ በመሆኑ አልተቀበለውም። ዩኒየኖቹ ሊሰበስቡና ለድርጅቱ ሊያቀርቡ የቻሉት ከታዘዙት ጥቂቱን ብቻ ነበር። በአምበርቾ ዩኒየን በኩል የታዘዙት 1000 ኩንታል ሲሆን ድርጅቱ ሊቀበል የቻለው 200 ኩንታል ብቻ ነው። አርሶአደሮች በጥራቱ ቁጥጥር ግንዛቤ የተነሣ ዝንጅብል በአግባቡ አልደረቀም፣ ከዚህ የተነሣ ፈንገስ መውጣትና የዋጋ ዝቅ ማለት ተከሰተ። ከዚህ ሌላ አርሶአደሮች የቀረበው ዋጋ ለሚያደርጉት ጥረት ተመጣጣኝ ነው ብለው ሊያሳምናቸው አልቻለም። ከዩኒያንና ከመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር እንዲሁም መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር አስተዳደርና ከአባላት መካከል ያለው ደካማ የግንኙነት ሁኔታ አዲሱን ሥራ በጊዜ ገብተው እንዳይሠሩ እንቅፋት ሆኖባቸዋል።

(2) **የማዳበሪያ ሥርጭት**


ሌላው የሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያን ዋና ስራ የማዳበሪያ ስርጭት ነው። የማዳበሪያ ግዢና ሥርጭት በሚመለከተ የፌደራል ፓሊሲ ላለፉት 20 ዓመታት ለብዙ ጊዜ ተከልሷል። በ2000 አጋማሽ ዩኒየኖች በዓለም ዓቀፍ የማዳበሪያ ግዢ ጨረታ እንዲሣተፉ ተፈቅዶ ነበር። በዚህ መሠረት ከደቡብ ክልል ሁለት ዩኒያኖች በወቅቱ በነበረው የሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒየን 551992 ኩንታል ማዳበሪያ በ183 ሚሊዮን ብር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በብድር ዋስትና ከክልሉ መንግስት በተሰጠው መሠረት ገዝቶ ነበር። በዚሁ ሂደት በተገኘው ትርፍ ዩኒየኑ የዱቄት ፋብሪካ ለማቋቋም ከፍተኛ እገዛ አድርጎለታል። በ2008 እ.ኤ.አ) ዳሞታ ወላይታ የገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒየን ማዳበሪያ ከውጭ የማስገባት ሥራ ውስጥ ገባ።

በ2009 (እ.ኤ.አ) ዩኒያኖች ከማዳበሪያ ማስገባት ሥራ እንዲወጡ ተደረገ በዚህ ምትክ የግብርና ግብአት አቅራቢ ኮርፓሬሽን በመንግስት ብቸኛ ወኪል ሆኖ ማዳበሪያ ለመላው ሀገሪቱ እንዲገዛ ተወሰነ የፌደራል መንግስት ዓላማው ማዳበሪያ በብዛት በአንድ ድርጅት

[9] ምንጭ፡ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የግብርና ግብይት ስርዓት ማጠናከሪያ ጥናት መሸጋገሪያ ሪፖርት (2) 2011 (እ.ኤ.አ)

አማካይነት እንዲቀርብና በብዛት በማስገባት የዋጋ ቅነሣ እንዲደረግ ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የደቡብ ክልል የገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን እንዲቋቋምና የማዳበሪያ ሥርጭት ሎጂስቱክስ እንዲመቻች ተደረገ፡፡

የማዳበሪያ ፍሰት በ2009 (እ.ኤ.አ) የነበረው ከታች ተገልፆል፡፡ ማዳበሪያ ከግብርና ግብአት አቅራቢ ኮርፓሬሽን ከተቀበለ በኂላ የገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን ለዩኒየኖች አሠራጨ፡፡ ከዚያም ዩኒያኖቹ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ካንንዘ በኂላ ለአርሶአደሮች እንዲሠራጭ አደረገ፡፡ በዚህ ረገድ የሕ/ሥራ ማህበራት ሚና የማዳበሪያ ሥርጭት ማመቻቸት ነው፡፡ ዩኒየኖችና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ለሚደያደርጉት ሥርጭት ማመቻቸት 3 ብርና 8 ብር በአንድ ኩንታል እንደቅደም ተከተላቸው ተቀብለዋል፡፡ በ2010 (እ.ኤ.አ) ከላይ የተቀመጠው አሠራር እንዲሻሻል ተደረገ፡፡ የገበሬዎች ሕ/ሥራ ማህበራት ፌደሬሽን ማዳበሪያ ቀጥታ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያኖችን በጐን በማለፍ አንንዘ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከጥቂት ዩኒያኖች የገቢ ምንጫቸው አንዱ የሆነውን እንዲያጣ ተደረገ፡፡፡




**ምስል 3.5-6 የማዳበሪያ ግብይት ፍሰት ቻርት በ2009 ዓ/ም**

በማናቸውም የሥርጭት ሥርዓት የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤትና ከቀበሌ አስተዳደር ጋር በመሆን ማዳበሪያ ለአርሶአደሮች ለማሠራጨት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የአንድ ዩኒያን ሥራ አስኪያጅ እንዳለው የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሥራ ጫና በዚህ ረገድ ከፍተኛ ነው፡፡፡ ከሚያገኙት ጥቅም ጋር ያልተመጣጠነ እንዲሁም በሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የቡዝነስ ሥራዎች እንደ ግብይት በመሳሰሉት እንዳይሳተፉ ጊዜ ተሻምቶባቸዋል፡፡

## 3.5.4 የሕ/ሥራ ዩኒያኖችና ሕ/ሥራ ማህበራት አስተዳደርና ፋይናንስ

### (1) የሕ/ሥራ ማህበራት የኦዲት ሥርዓት ሕግ

1) የሕ/ሥራ ማህበራት ሕግ የአዋጭነት ግምገማና የማነፃፀሪያ ነጥቦች ሁለቱም መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች በሕ/ሥራ ማህበራት አዋጅ መሠረት ኦዲት ይደረጋሉ፡፡ የሁለቱም የሂሣብ ባለሙያዎች የሂሳብ ምዝገባና የየዕለት ሽያጭና ወጪ ምዝገባ እንዲያጠኑ ያስፈልጋል፡፡ የሂሣብ መዝገብ የትርፍና ኪሣራ እስቴትመንትና ሀብትና ዕዳ መግለጫ በዓመቱ መጨረሻ የሚጠቃለል መሥራት አለባቸው፡፡ ኦዲተሮች "ከሕ/ሥራ ልማት ዋና የሥራ ሂደት" ተልከው መዝገቡን በዝርዝር ይመረምራሉ፡፡ የኦዲት ሥርዓትና ግዴታዎች በኦዲት መመሪያ በግልጽ የተቀመጡ ቢሆንም የሁሉንም መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና

ዩኒያኖች ኦዲት ለማከናወን ከባለሙያ እጥረትና ከሎጂስቲክስ ሥርዓት አለመመቸት ምክንያት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ጥቂት ዩኒያኖች በገጠር አካባቢ የሚገኙ በመሆኑ ኦዲት ለመደረግ ዕድል የማያገኙበት ጊዜ አለ፡፡ የመነሻ ነጥቦች ለውይይት ሊቀርቡ የሚገቡ ወይም የተለዩ ነጥቦች ከታች ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡

ሀ/ ሊከናወን የሚችል ኦዲት የጊዜ ሠሌዳ ባለው ሀብት መሠረት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

- ✓ ስንት ኦዲተሮች በእያንዳንዱ ዞን አሉ?
- ✓ አንድ ዩኒየን ወይም መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ኦዲት ለማድረግ ስንት ቀን ያስፈልጋል?
- ✓ ለእያንዳንዱ ዞን ስንት አበልና ትራንስፓርት ወጪ በዓመት ያስፈልጋል?
- ✓ ስንት ዩኒየኖችና መሥረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት በተቀመጠው ሁኔታ በተጨባጭ ኦዲት ሊደረጉ ይችላሉ?

ለ/ የኦዲት ውጤት ክለሳ ሊደረግ ይገባል

- ✓ የኦዲት ሥራ ከዓመታዊ ጊዜ ሰሌዳ አኳያ ተመዛዛኝነት ምን ይመስላል?
- ✓ ምን ያህል መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች በመቶኛ በዓመት ኦዲት ተደርገዋል?
- ✓ በእያንዳንዱ ኦዲተር ስንት ኦዲት ሥራዎች ተከናውነዋል /የኦዲተሮች የግል መዝገብ መከለስ አለበት/?
- ✓ የግብይትና ህ/ሥራ ቢሮ እንዴት የኦዲት ሪፓርት እንዴት ገመገመ?

ሐ/ ለኦዲት ሥራ በጀት መመደብ ያለበት በተጨባጭና ሊሠራ በሚችል ዕቅድ መሆን አለበት

- ✓ ለኦዲት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የአበልና የትራንስፓርት ወጪዎች ተሠልተዋል ወይ?
- ✓ አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል ኦዲትና ደመወዝ ተሠልቷል ወይ?
- ✓ የክፍያ ሥርዓት በተመለከተ ከቋሚ ደመወዝ ወደ ችሎታ ላይ ተመሥርቶ የሚከፈል ሥርዓት ለመሸጋገር ውይይት ተደርጓል ወይ?

2) በደቡብ ክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ የኦዲት አገልግሎት

41 ዩኒያኖችንና 1 ፌደራል ዩኒያን ኦዲት ሥራ ለመሸፈን 4 ኦዲተሮች ተመድበዋል፡፡ ባለፈው ዓመት ከተሰጣቸው ሥራ ከግማሽ በታች አከናውነዋል፡፡ የክልሉ ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ በሥራቸው ውጤት ተበሳጭቶ ተጨማሪ ኦዲት ሥራ እንዲያከናውኑ አበረታትቷቸዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ከ41 ዩኒየኖች 19 ዩኒየኖች ኦዲት ስራ በዓመቱ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ተከናውኗል፡፡ እንደ ክልሉ ቢሮ ኦዲተሮች የተመረጡ ዩኒየኖችንና የፌደራል ዩኒየን ኦዲት ሥራ በትራንስፓርትና የውሎ አበል በጀት እጥረት የዓመቱን ሥራ ሸፍነው አያውቁም፡፡ የኦዲት ሥራ ለማከናወን የሚያስፈልገው ጊዜ የሚወሰነው ኦዲት የሚያደርገውን ዩኒየን የሂሣብ አያያዝ ሥራዎቹ በአግባቡ በመያዝና ባለመያዝ ነው፡፡

ዩኒያኑ የሂሣብ መረጃው በአግባቡ የተመዘገበ ከሆነ የሂደቱ ስራ በ3 ቀናት ሊያልቅ ይችላል፡፡ ነገር ግን የሂሣብ መዝገቡ በአግባቡ ካልተያዘ ሣምንት ወይም ከዚያ በላይ የኦዲት ሥራውን ለማጠቃለል ሊወስድ ይችላል፡፡ አብዛኛዎቹ ዩኒያኖች የሂሣብ እስቴትመንት የትርፍና ኪሣራ እንዲሁም ሀብትና ዕዳ መግለጫ አልሠሩም፡፡ ከዚህ የተነሣ ኦዲተሮች እነዚህን ለመሥራት ተገደዋል፡፡ ኦዲተሮች የሚሰጡት አስተያየት የዩኒየኖች ሥራ አስኪያጆች የሂሣብ ባለሙያዎችን መቅጠር አለባቸው ይላሉ ይሁን እንጂ የሠለጠኑ የሂሣብ ባለሙያዎች ደመወዝ በተመዛዛኝ ከፍ ያለ ስለሆነ ዩኒየኖች እንደዚህ ችሎታና ብቃት ያላቸውን

ባለሙያዎች የሚስብ ደመወዝ ሊከፍሉ አይችሉም፡፡ ስለሆነም ዩኒየኖች የሂሣብ ሠራተኞችን አቅም ለማሳደግ (የኦዲት ሥራ የሚጠይቀውን ፊላጐት ለማሟላት) እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

የክልል ቢሮ ኦዲተሮች የሚሉት የእነርሱ ኃላፊነት ዩኒየኖችን ኦዲት ማድረግ ብቻ ሲሆን የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ኦዲት ሪፓርት ውጤት በወረዳ መቆጣጠር ከእነርሱ ኃላፊነት ውጪ እንደሆነ ነው፡፡ ድጋሚ ማየት ወይም የግምገማ ሥርዓት የኦዲት የመጨረሻ ውጤትና የሂሣብ መግለጫ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይት ሕ/ሥራ ጽ/ቤት መካከል የለም፡፡

3) ኦዲተሮች በወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት

በአንድ ወረዳ ከ2 እስከ 4 ኦዲተሮች ተመድበው ይሠራሉ፡፡ የቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ በወላይታ ዞን በተመለከተ 3 ኦዲተሮች ተመድበው 63 የተመዘገቡ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትን ሸፍነዋል፡፡ በዓመቱ ኦዲት ሊደረጉ የታቀዱ 39 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 24 መወረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት እየሠሩ ስላልሆነ አልታቀዱም፡፡ በቦሪቻ ወረዳ ሲዳማ ዞን 29 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የተመዘገቡት ያሉ ቢሆንም 8 ወይም 9 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ናቸው ኦዲት ሊደረጉ የታቀዱት፡፡ ሌሎቹ እየሠሩ ስላልሆነ ኦዲት መደረግ የለባቸውም፡፡ የዚህ ዓይነት እየሠሩ ያልሆኑ ማህበራት በየወረዳው ይገኛሉ፡፡ መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ሥራ ላይ ባልሆኑበት ጊዜ ኦዲተሩ ከሕ/ሥራ አደራጅ ጋር ግንኙነት ያደርግና ለሕ/ሥራ ማህበሩ መመሪያ እንዲያስተላልፍ ያደርጋሉ፡፡ ከ2 እስከ 3 ሕ/ሥራ ማህበራት አደራጆች በአንድ ወረዳ የሚቀመጡ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንድ አደራጅ በቀበሌ ተቀምጦ እየሠሩ ያልሆኑ መሰረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትን ከዕቅድ ውጭ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡

በወረዳ ሁለገብ ሕ/ሥራ ማህበራት ብዙም የሉም፡፡ አንድ ወይም ሁለት የሚሆኑ ለትርፍ ሥራ የሚንቀሳቀሱ ነበሩ፡፡ ብዙዎቹ የግብርና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሚሠሩት ማዳበሪያና ምርጥ ዘር በመንግስት ምደባ ሥርዓት መሠረት በማቅረብ ነው፡፡ የሽያጭ ዋጋ በኦፊሴላዊ ሁኔታ የተተመነ ነው፡፡ ስለሆነም ሥራው እንደ ትርፍ አስገኚ ቢዝነስ ሳይሆን ለአባላት አገልግሎት መስጠት ይሆናል፡፡ የወጣቶች መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና የብድር ሕ/ሥራ ማህበራት የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አብዛኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ የኦዲተሮች ዕቅድ በአብዛኛው በትርፋማ ባልሆኑ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

(2) የዩኒየኖችና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሂሣብ አስተዳደር

ዩኒያኖችና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ኦዲት ያልተጠናቀቀ ቢሆን እንኳን የሂሣብ ሪፓርታቸውን ማጠቃለልና የቢዝነስ ክንውን ሪፓርት ለጠቅላላ ጉባኤና ለቦርድ አባላት በየዓመቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የቢዝነስ ሥራ ግልፀኝነት ለሚንቀሳቀሱ ሁለገብ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች ሙስናን ለመከላከል ወሳኝ ነው፡፡

የመዝገብ አያያዝና የሂሣብ ሥራ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና ወረዳ ግብይትና ሕ/ሥራ ጽ/ቤት እንዲሁም በመንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ ተሻሽሏል፡፡ በአነስተኛ ደረጃ የሚገባና ወጪ የሚሆን ገንዘብ መመዝገብና በአመቱ መጨረሻ መጠቃለል አለበት፡፡ ሆኖም አብዛኛዎቹ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች አግባብነት ያለውን የሂሣብ አመራር ለማወቅ የአቅም ውስኑነት አለ፡፡ የመዝገብ አያያዛቸው የምዝገባ ሥራ በእጅ የሚሠራ ሲሆን ለጠቅላላ ጉባኤ ለማቅረብም ሆነ ለአጠቃቀም አመቺ አይደለም፡፡ የሂሣብ አስተዳዳር የበሰለ አሠራር አለመኖር በጣም የከፋ ችግር ከመሆኑም በላይ የአባላት የተዓማንነት ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ የተዓማንነት ችግር በአባላት መካከል መፍጠር መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች እንዲፈርሱ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ስለሆነም የሂሣብ አስተዳዳር መሻሻል ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች ልማትና ዘላቂነት አንዱ ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ ይታያል፡፡

እንደ አጋጣሚ ሆኖ የተከታታይ ጊዜ የረዥም ጊዜ ክንውን አልተካሄደም የሂሣብ መረጃ የወደፊት ቢዝነስ ለማሻሻል ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡ የጃይካ የጥናት ቡድን ባለሙያ የተመረጡ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች የሂሣብ ሪፓርት ለማየት በሞከረበት ጊዜ የተረዳው ነገር ቢኖር አብዛኛዎቹ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች የሂሣብ ዓመቱን እንኳን ሊወስኑ አልቻሉም፡፡ ለምሣሌ፡ የአንጋጫ ሁለገብ ሕ/ሥራ ማህበር የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 02 እና ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 08 የተመረጠ ሲሆን አንዱ የሂሣብ መዝጊያ ዓመት 2 ዓመት ከ10 ወር ሲሆን ሌላው ጊዜ ደግሞ 1 ዓመት ከ9 ወር ነው፡፡

አብዛኛበዎቹ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች ሂሣባቸውን የሚዘጉት ኦዲተሮች ሲመጡ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቁልፍ ችግር ነው፡፡ በአንድ በኩል ለጠቅላላ ጉባኤ ግልፀኝነት ሲጐድለው በሌላ በኩል የተከታታይ ጊዜ ትንተና የለም አብዛኛዎቹ የወረዳ ኦዲተሮች የሂሣብ ዓመት ጠቀሜታ ስለማየረዱ የሂሣብ አሠራር የ365 ቀናት በ1 ዓመት ጊዜ እንደሚጠቃለል ይዘነጉታል ወይም ተግባራዊ አያደርጉም፡፡ የመጀመሪያ ቅድሚያ የሚሰጠው መመሪያ ለኦዲተሮችና፣ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና/ዩኒኖች የሂሣብ ዓመት እንዲገነዘቡ ነው፡፡ አለዚያ በሂሣብ አስተዳዳር ዙሪያ ምንም የወደፊት ዕድገት አይታሰብም፡፡

የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒያኖች በሂሣብ አስተዳደር የሚታዩ ደካማ ነጥቦችና በዚህ ሰዓት ሊጠናከሩ የሚገቡ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

ሀ/ ትክክለኛ የሂሣብ ዓመት አግባብነት ባለው የቢዝነስ ዓመት መቋጨት አለበት

- ✓ የሂሣብ ዓመቱ ከቢዝነስ ወቅት ጋር በተዛመደ ሁኔታ እንደየምርት መሰብሰቢያ ወቅት ተቋጭቷል ወይ?
- ✓ ሂሣቡ በአግባቡ በተወሰነ ጊዜ ተዘግቷል ወይ?

ለ/ በትክክለኛ የሂሣብ አያያዝና አሠራር መሠረት ገቢዎችና ወጪዎች ከሚመለከታቸው ርዕሶች ጋር ተያይዞ ተመዝግቧል ወይ?

- ✓ የመዝገብ ያዡ በትክክለኛ የሂሣብ ርዕስ መሠረት ወጪና ገቢውን ይመዘግባል ወይ
- ✓ የመዝገብ ያዡ ዝርዝር ወጪና ገቢ ሂሣቦችን በየወሩ ለማጠቃለል ብቃት አለው ወይ?

ሐ/ የቢዝነስ ስራዎች በተከታታይ ጊዜ መተንተንና መከለስ አለበት

- ✓ የሽያጭ ወጪዎች ካለፈው አመት ጋር ተነፃፅረዋል ወይ?
- ✓ የሽያጭና የሽያጭ ወጪዎች መዋዠቅ ምክንያቶች ተለይተዋል ወይ?
- ✓ የቢዝነስ ክንውን አዝማሚያ ውይይት ተደርጓል ወይ?

መ/ ዘላቂነት ያለው ቢዝነስ እና ስጋት ያለው እና ትርፋማ ቢዝነስ ባላንስ መደረግ አለበት

- ✓ በጀቱ ለአባላት ዘላቂነት ላለው አገልግሎት እንዲውል ተደርጓል ወይ?
- ✓ ትርፋማ የሆነ ቢዝነስ ለመሣተፍ ፈጣን እርምጃ ተወስዷል ወይ?

ሠ/ የሚዝነስ ልምድ ልውውጥና ውይይት በአባላት መካከል መደረግ አለበት

ረ/ ከተጨባጭ የፋይናንስ ሁኔታ በመነሣት የረዥም ጊዜ የቢዝነስ እቅድ መዘጋጀት አለበት

- ✓ ምን አይነት ግንባታዎችና መሣሪያዎች ለወደፊት መተከል አለባቸው?
- ✓ የትኞቹ ግንባታዎችና መሣሪያዎች ከቢዝነስ ክንውን አኳያ ለግዢ ቅድሚያ ሊያገኙ ይገባል?
- ✓ አስፈላጊ ለሆነው መሣሪያ ወጪ ምን ያህል ነው?
- ✓ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን ለመግዛት የሂሣብ እቅዱ ምንድነው?

ሰ/ ለሂሣብ ሥራና ለሂሣብ አስተዳደር በጽ/ቤቱ የሚገኙ ከሆነ ኮምፒውተሮችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የጃይካ ጥናት ቡድን ከሙከራ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ የሚሆኑ ሁለት ዩኒያኖችና 4 መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትን በመምረጥ የሂሣብ ሪፓርታቸውን መርምሮ ነበር፡፡ የተመረጡት ዩኒየኖችና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የተመረጡት የተሻለ እንቅስቃሴ አላቸው ከሚባሉት ውስጥ ቢሆኑም የሂሣብ አስተዳዳር እጅግ ኂላቀር ከመሆኑ የተነሣ ሊመረመሩ አልቻሉም፡፡ አንድ ዩኒየን ብቻ ከ6 ዩኒያኖችና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ውስጥ የሂሣብ አመቱን በመቋጨት ብቁ ሲሆን ሌሎቹ ለትንተና ምቹ አልነበሩም፡፡

በጣም የተሻለ አቋም አላቸው ከሚባሉት 6 ሁለገብ ሕ/ሥራ ማህበራት መካከል የአንዱ ሂሣብ ኃላፊ ሂሣቡን ለማጠቃለል ኮምፒውተር አይጠቀምም፡፡ ከዚያም በላይ የክልል ግብይትነ ሕ/ሥራ ቢሮ ኦዲተር ሒሣቡን እንዲያስተካክል ይጠብቃል፡፡ በመንግሥታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች እርዳታ ለንብረት ቆጠራ ሥራ ድጋፍ የተሰጠ ኮምፒዩተር በስራ አስኪያጅ ቢሮ የተቀመጠ ቢሆንም ለሂሣብ ስራ ወይም ለቢዝነስ ትንተና ጥቅም ላይ ውሎ አያውቅም፡፡ በዚህ ሁኔታ በደቡብ ክልል የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሂሣብ አስዳደር ሥራ ለማሻሻል ረዥም መንገድ መሄድ አለባቸው፡፡

### (3) የዩኒያኖች የሂሣብ ሪፖርት

1) የሲዳማ ኤልቶ ሁለገብ ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒያን (ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 01, ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02, ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08)

ሠንጠረዥ 3.5-6 የሲዳማ ኤልቶ ሁለገብ ሕ/ሥራ ማህበር ዓሙና ትርፍና ኪሣራ ሪፖርት ያሣያል፡፡ የዚህ ዩኒያን ሥራ 62 አባላት ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር እህል የሚያመርተውን መደገፍ ነው፡፡ ሲዳማ ኤልቶ ዩኒን ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ለአባላት እና አባል ላልሆኑ ጭምር ከገበያ ዋጋ በታች በሆነ ዋጋ ያቀርባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዩኒየኑ በእህል ንግድ ይሳተፋል፡፡ ዩኒየኑ እህል ከአባላትና ከነጋዴዎች ገዝቶ ለገበያ ወይም ለአለም የምግብ ፕሮግራም ይሸጣል፡፡

ዩኒያኑ የተቋቋመው በ2003 (እ.ኤ.አ) ሲሆን በቢዝነስ ውስጥ የገባው በቅርብ ዓመት ውስጥ ሲሆን የቢዝነስ ስራዎቹ አሁንም አልተረጋጉም፡፡ የ3 ዓመት የሥራ ክንውን በማየት የሚከተሉት ጉዳዮች ይነሣሉ፡፡

ሀ) ከዋና ዋና ሥራዎች የገቢ መፈፀም፣ የሽያጭ ወጪና ጠቅላላ የትርፉ ዳርቻ፡

- የማዳበሪያ ሽያጭ መቀነስ፣
- የምርጥ ዘር ሽያጭ የተረጋጋ ቢሆንም ግዢዎች መዋዠቅ፣
- የእህል ንግድ ማደግ፣
- የማብቂያ ኢንቨንተሪ /ቀሪ እስቶክ/ የሽያጭ 10% መጨመር፣
- ጥቅል ትርፍ በአብዛኛው ለ3 ዓመታት የተረጋጋ ቢሆንም ሥራዎች መለዋወጥ አሳይተዋል፡፡

ለ) ጠቅላላ ወጪ

- የፐርሶኔል ወጪዎች እንደ ደመወዝና ጉልበት ክፍያ መጨመር፣
- ጠቅላላ ወጪ በ2010 (እ.ኤ.አ) ከቀዳሚው ዓመት በ140% መጨመር፣

ሐ/ የሥራ ማስኬጃና ሥራ ማስኬጃ ያልሆነ ገቢ

- የሥራ ማስኬጃ ትርፍ በ2009 የጨመረ ቢሆንም በ2010 (እ.ኤ.አ) መውረድ፣
- የሥራ ማስኬጃ ያልሆነ ትርፍ በ2010 (እ.ኤ.አ) ካለፈው ዓመት እስከ 10 ጊዜ በፍጥነት ማደግ፣

መ/ የተጣራ ትርፍ ወይም ኪሣራ

- የተጣራ ትርፍ በቅርብ ዓመታት በትንሹ መጨመር፣

ሠ/ ማጠቃለያ ግምገማ

- የሥራ ማስኬጃ ትርፍ ወይም ኪሣራ ውጤት ሲገመገም ዋና ዋና ሥራዎች ያልተረጋጉና በተሰጠው ጉዳይ እንደ የታቀዱ የሽማቾች ቁጥር መሠረት ያልታቀደ መሆን፣
- የገቢ ክፍፍል ከሥራ ማስኬጃ ካልሆነ ሥራዎች ከአጠቃላይ 30% የደረሰ ስለሆነ የቢዝነስ ዓይነት ማስፋት፣ መታሰብ አለበት፣
- ቋሚ ወጪ እንደ ፐርሶኔል ወጪ፣ የፍጆታ ወጪ ወዘተ በቢዝነስ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የጨመረ ቢሆንም ከጠቅላላ ወጪ ከ6-7% አካባቢ መቆየት፣
- ከፍተኛ ወጪ ያላቸው እንደ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ከፍላጐት ጋር የተሳሰሩ መሆን አለባቸው:: አለዚያ በመጋዘን የሚቀመጠው ንብረትና የኢንቬንተሪ ማኔጅመንት ወጪ ይጨምራል::

**ሠንጠረዥ 3.5-6 የሲዳማ ኤልቶ ዩኑያን ትርፍና ኪሳራ**

| ዝርዝረ | | 2008 (እ.ኤ.አ) | 2009 (እ.ኤ.አ) | 2010 (እ.ኤ.አ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. ከሥራ እንቅስቃሴ የተገናኘ ገቢ | | | | |
| 1.1 | ማዳበሪያ | 21,958,525 | 14,131,348 | 1,011,814 |
| 1.2 | ምርጥ አር | 909,716 | 1,054,508 | 713,995 |
| 1.3 | እህል | 879,419 | 1,069,495 | 14,115,844 |
| 1.4 | ሌሎች | 9,836 | | 313,754 |
| 1.0 | ከሽያጭ የተገኘ ገቢ ድምር (=ድምር(1.1:1.4)) | **23,757,496** | **16,255,351** | **16,155,406** |
| 2. የሽያጭ ወጪ | | | | |
| 2.1 | ማዳበሪያ | 21,348,866 | 13,179,662 | 764,626 |
| 2.2 | ምርጥ አር | 845,282 | 1,385,601 | 458,400 |
| 2.3 | እህል | 666,753 | 2,022,655 | 13,381,921 |
| 2.4 | ሌሎች | | | 265,410 |
| 2.5 | በዓመት የተካሄደ ሽያጭ (=ድምር(2.1:2.4)) | 22,860,901 | 16,587,918 | 14,870,358 |
| 2.6 | የመጀመሪያ ኢንቨንተሪ | 60,870 | 210,279 | 1,610,417 |
| 2.7 | ከአለፈው ዓመት የዞረ (=2.5+2.6) | 22,921,771 | 16,798,197 | 16,480,774 |
| 2.8 | የመጨረሻ እንቨንተሪ | -210,279 | -1,610,417 | -1,505,761 |
| 2.0 | የሽያጭ ወጪ ድምር (የእቃና አገልግሎት ወጪ ድምር) | **22,711,492** | **15,187,780** | **14,975,013** |
| 3.0 | ያልተጣራ ትርፍ/ኪሳራ (=1.0 — 2.0) ) | **1,046,004** | **1,067,571** | **1,180,393** |
| 4. አጠቃላይ (ሽያጭ፣ አስተዳደር) ወጪዎች | | | | |
| 4.1 | ደመወዝ | 72,630 | 49,617 | 119,012 |
| 4.2 | የጉልበት ወጪ | 38,618 | 111,172 | 254,666 |
| 4.3 | የጉዞ ወጪ | 512,123 | 74,948 | 140,030 |
| 4.4 | አላቂ ዕቃዎች | 38,072 | 41,038 | 107,573 |
| 4.5 | ማሳሪያዎች ጥገና | 5,045 | 7,102 | 18,761 |
| 4.6 | ለማዳበሪያ ሽራ | 1,390 | | 211,893 |
| 4.7 | ኮሚሽን | 17,593 | 43,600 | 29,962 |
| 4.8 | የመጋዘንና የሱቅ ክራይ | 36,750 | 18,000 | 55,300 |
| 4.9 | መዝናኛ | 5,315 | 7,103 | 43,820 |
| 4.10 | የህዝብ | 1,735 | | 3,495 |
| 4.11 | ዓመታዊ አገልግሎት ቅንስናሽ | 5,972 | 9,154 | 37,598 |
| 4.12 | ጥቃቅን ወጪዎች፣ ታክስ | 28,582 | 63,049 | 3,260 |
| 4.0 | ጠቅላላ ድምር (ሽያጭ፣ አስተዳደር) ወጪዎች | **763,823** | **424,782** | **1,025,369** |
| 5.0 | ትርፍ ወይም ኪሳራ | **282,181** | **642,789** | **155,023** |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6.0 ከሥራ እንቅስቃሴ ውጪ የተገኘ ትርፍ ወይንም ኪሳራ | | | | |
| 6.1 | ወለድ | 26,147 | 28,033 | 39,223 |
| 6.2 | ክራይ፣ አገልገሎትና ሌሎች | 20,205 | 23,937 | 518,155 |
| 6.3 | ምዝገባ | 2,500 | 500 | 8,500 |
| **6.0** | **ከሥራ እንቅስቃሴ ውጪ የተገኘ ትርፍ/ኪሳራ ድምር** | **48,852** | **52,471** | **565,877** |
| **7.0** | **የዘመኑየተጣራ ትረፍና ኪሳራ (=5.0 + 6.0)** | **331,033** | **695,259** | **720,901** |

ምንጭ: በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የእህል ሰብል ዩኒያን

## ሀብትና ዕዳ መግለጫ

የሲዳማ ኤልቶ ዩኒያን ሀብትና ዕዳ መፍለጫ በሠንጠረዥ 3.5-7 ተመልክቷል፡፡ ሊነሱ የሚገቡ ነጥቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

ሀ/ ሀብት

- የሚሰበሰብ ሂሣብ ክፍፍል የወቅቱ ዋጋ ያለው ንብረት 50% በ2010 መድረሱ
- በመጋዘን ያለ ንብረት በ2010 ዓ/ም መሆኑ
- ዕዳና ቋሚ ንብረት በ2008 (እ.ኤ.አ) ከነበረው 44,541 ብር በ2010 ወደ 1,101,446 ብር ይኸውም 25 ጊዜ ጨምሯል፡፡ ይህ የሆነበት ለመጋዘን ግንባታና ለማሽነሪ ግዢ እርዳታ ስለተገኘ ነው፡፡
- ጠቅላላ ዋጋ ያለው ንብረት በ2010 (እ.ኤ.አ) 8,658,092 ብር ደርሷል፡፡ ሆኖም አብዛኛው ተሰብሳቢ ሂሣብና ለእርዳታ የተሰጠ ነው፡፡

ለ/ ዕዳና ካፒታል

- ለገጠር ፋይናንስ ፈንድ ተከፋይ ሂሣብ በ2010 ዓ/ም 3,913,825 ብር ደርሷል፡፡ ይኸውም የጠቅላላ ሽያጭ ገቢ የዋና ዋና ሥራዎች አንድ አራተኛ ማለት ነው፡፡
- የትርፍ ክፍያ ለአባላት ይኸውም የጠቅላላ ተከፋይ ትርፍ 70% በ2010 ዓ/ም የወጪና ኪሣራ እንዲሆን ተወሰነ፡፡

ሐ/ ማጠቃለያ ግምገማ

- ዩኒየኑ ለሥራ ማስኬጃ ግዢ ገንዘብ መበደር እስከቻለ ድረስ ሥራቸው በዘላቂነት ይንቀሳቀሳል፡፡ ሆኖም የገጠር ፋይናንስ ፈንድ የፋይናንስ ሥራዎችን ካቆመ በኂላ ግልጽ የሆነ ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማግኘት የሚያስችል ግልጽ የሆነ እስትራቴጂ የለም፡፡
- የተሰብሳቢ ሂሣብ መጨመር በአግባቡ መታየት አለበት፡፡ አለዚያ የካሽ ፍሰት እጥረት ያጋጥማል፡፡

### ሠንጠረዥ 3.5-7 የሲዳማ ኤልቶ የሂሣብ ባላንስ ሽት

| ሀብት | | 2008 (እ.ኤ.አ) | 2009 (እ.ኤ.አ) | 2010 (እ.ኤ.አ) |
|---|---|---|---|---|
| 1. የወቅቱ ሀብት | | | | |
| 1.1 | በእጅ ያለ ገንዘብ | 69,375 | 26,135 | 15,654 |
| 1.2 | በባንክ ያለ ገንዘብ | 586,636 | 1,366,365 | 2,000,770 |
| 1.3 | በሰነድ ያለ ገንዘብ | 23,465 | 98,289 | 259,004 |
| 1.4 | ተሰብሳቢ | 1,874,344 | 1,815,864 | 3,729,942 |
| 1.5 | በመጋዘን ያለ ገንዘብ (stock) | 210,279 | 1,610,417 | 1,505,761 |
| 1.6 | ኢንቨስትሜንት | 40,000 | 40,000 | 100,000 |
| 1.0 | **የወቅቱ ሀብት ድምር** | **2,804,098** | **4,957,070** | **7,611,131** |
| 2. ቋሚ ሀብት | | | | |
| 2.1 | የማይንቀሳቀስ ሀብት | 44,541 | 522,053 | 1,101,446 |
| 2.2 | የአገልግሎት ቅንስናሽ | -7,733 | -16,887 | -54,485 |
| 2.0 | **የቋሚ ሀብት ድምር** | **36,808** | **505,166** | **1,046,961** |
| **3. የሀብት ድምር** | | **2,840,906** | **5,462,236** | **8,658,092** |
| **እዳና ካፒታል** | | | | |
| **4. ክፍያ** | | | | |
| 4.1 | የአጭር ጊዜ ክፍያ | | | |
| 4.1.1 | ለገጠር ፋይናንስ አገልግሎት የሚከፈል | 913,825 | 1,913,825 | 3,913,825 |

| ሀብት | | 2008 (እ.ኤ.አ) | 2009 (እ.ኤ.አ) | 2010 (እ.ኤ.አ) |
|---|---|---|---|---|
| 4.1.2 | ለወረዳ የሚከፈል | 279,938 | 341,286 | 998,446 |
| 4.1.3 | ለዘር ግዥ የሚከፈል | 122,240 | 558,683 | 103,772 |
| 4.1.4 | ሌሎች ተከፋይ( ለማህበራዊ አገልግሎት፣ ትምህርት) | 4,641 | 4,641 | 4,641 |
| 4.1.5 | ደመወዝ | 48,400 | | |
| 4.1.6 | ያልተወቀ በባንክ የተቀመጠ | 9,000 | 9,000 | 9,000 |
| 4.1.7 | ለአባላት የሚከፋፋል (70%) | 231,723 | 718,404 | 504,631 |
| 4.1.8 | **የአጭር ጊዜ ክፍያ ድምር** | **1,609,767** | **3,545,838** | **5,534,315** |
| 4.2 | **የረዥም ጊዜ ክፍያ ድምር** | **0** | **0** | **0** |
| 4.0 | **የክፍያ ድምር** | **1,609,767** | **3,545,838** | **5,534,315** |
| 5. ካፒታል (የባለቤት ንብረት) | | | | |
| 5.1 | የሀብት ድርሻ | 127,200 | 152,200 | 230,600 |
| 5.2 | የተስፋፋ የሥራ እንቅስቃሴ | 207,530 | 207,530 | 925,934 |
| 5.3 | የተከማቸ ትርፍ/ዕዳ | 208,950 | 417,528 | 633,799 |
| 5.4 | ካፒታል | 687,458 | 1,139,139 | 1,333,445 |
| 5.0 | **የባለቤት ንብረት ድምር** | **1,231,139** | **1,916,398** | **3,123,778** |
| **6.0 የእዳና የባለቤት ንብረት ድምር** | | **2,840,906** | **5,462,236** | **8,658,092** |

ምንጭ: በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የእህል ሰብል ዩኒያን

## 2) የአንጋጫ ህ/ሥራ ዩኒያን (ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02 ፣ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08)

የአንጋጫ ሕ/ሥራ ዩኒየን ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 02 "ጥራቱ ቁጥጥር"ና ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 08 "የመጋዘን አስተዳዳር" የተመረጠ ነው፡፡ በመሠረቱ እነርሱ የሚሠሩት የመዝገብ መያዝ ብቻ ነው፡፡ የሂሣብ ሪፓርት ሀብትና ዕዳ እና የትርፍና ኪሣራ በክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ኦዲትር ይሠራሉ፡፡ ሂሣቡን በራሳቸው ለመሥራት አቅም የላቸውም፡፡ ሥራ አስኪያጁና የሂሣብ መዝገብ ያዡ ሠራተኛ የፋይናንስ አስተዳዳር ጠቃሚነት ይረዳሉ፡፡ ስለዚህ የክልል ቢሮ ኦዲተር ወደ አንጋጫ ዩኒየን እንዲመጣ ይጠብቃሉ፡፡ ወደ ክልል ቢሮ ኦዲተሩ እንዲመጣ ተደጋጋሚ የስልክ ጥሪ ቢያደርጉም በበጀት እጥረት ምክንያት ኦዲተሮቹ በወቅቱ ሊመጡ አልቻሉም፡፡ ዩኒየኑ በአጠቃላይ 3 ጊዜ ኦዲት ተደርገዋል፡፡ በ1997 ዓ/ም፣ በ2000 ዓ/ም እና በ2002 ዓ/ም የሂሣብ መዝጊያ ወቅት በአግባቡ የተቋጨ አይደለም ከታች በሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት፡-

### ሠንጠረዥ 3.5-8 የሂሳብ ዘመን ( አንጋጫ የሕ/ሥራ ማህበር ዩኒያን)

| | ትርፍና ኪሳራ | | ሚዛን |
|---|---|---|---|
| | ቆይታ ጊዜ | የቀን ብዛት | |
| 1 | ～22/03/1997 ዓ/ም | ? | 22/03/1997ዓ/ም |
| 2 | 24/2/1998 ዓ/ም ～30/12/2000 ዓ/ም | 2 ዓመት ከ10 ወር ከ6 ቀናት | 30/12/2000ዓ/ም |
| 3 | 1/1/2001ዓ/ም～30/09/2002 ዓ/ም | 1 ዓመት 9 ወሮችs | 30/9/2002ዓ/ም |

የሂሣብ መዝጊያ ወቅት መወሰንን በሚመለከት ማንም አለማሳየቱ አዲስ ነገር ነው፡፡ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የሂሣብ መዝጊያ ወቅት ካልተወሰነ የተከታታይ ጊዜ ትንተና ለማድረግ አይቻልም፡፡ የሂሣብ ዓመቱ መለየት ያለበት እንደ የምርት መሰብሰቢያ ወቅት ዓይነት ሆኖ በወር የተለየ መሆን ይኖርበታል፡፡ የኦዲት አስተዳዳርና የሥራ መፈፀሚያ ሥርዓት ያለው ሆኖ በበለጠ ሥርዓታዊና በዕውቀት የተመሠረተ ባለሙያ ውጤቱን መከለስ አለበት፡፡ አለዚያ መረጃው ዋጋ ያጣል፡፡

### 3) ቦሎሶ ቦምቤ ሁለገብ የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር ቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ (ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05)

በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ቦሎሶ ቦምቤ ሁለገብ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ከቢዝነስ ትርፍ ለማግኘት የሞከረ ብቸኛው ሕ/ሥራ ማህበር ነው፡፡ ቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የዳሞታ ዩኒየን አባል ነው፡፡ ቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ከሁለት ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 05 የተመረጡ ማህበራት አንዱ ሲሆን የንፁሕ ደረቅ ዝንጅብል ቢዝነስ ለማስፋፋት የሚሠራ ነው፡፡ ቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በ1963 ዓ/ም የተቋቋመ ሲሆን በ1992 በአዲሱ የሕ/ሥራ ማህበር ሕግ መሠረት ታድሷል፡፡ የአባላቱ ብዛት 597 (574 ወንድና 23 ሴት) ዋና ዋና ምርቶች ቡናና ዝንጅበል ናቸው፡፡ የምርጥ ዘርና የማዳበሪያ አቅርቦት የሚካሄደው ለአባላት አገልግሎትና የማህበራዊ አስተዋጽኦ ነው፡፡ 8 ብር በ100 ኪሎ ግራም በመንግስት መመሪያ መሠረት ያስከፍላሉ፡፡ ቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር 5 ብር እና እያንዳንዱ ቀበሌ 3 ብር በ100 ኪሎ ግራም ይቀበላሉ፡፡ በቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ውስጥ 20 ቀበሌዎች አሉ፡፡

የቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር መዝገብ ያዡ የየዕለቱን ገቢና ወጪ የሚመዘግብ ሲሆን የሂሣብ ሪፓርት ለማጠቃለል አቅም የለውም፡፡ የወረዳው ኦዲተሮች የሂሣብ ሪፓርት ይሠራሉ፡፡ የቦሎሶ ቦምቤ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ያለበት ከወረዳው ጽ/ቤት አጠገብ በመሆኑ ኦዲተሮች በየጊዜው የሚጎበኙ ሲሆን ዓመታዊ ኦዲትም ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም የሂሣብ መዝጊያ ዓመት በአግባቡ አልተወሰነም፡፡ የአንድ ዓመት ጊዜ ለኦዲተሩ እንደሚመቸው የሚለዋወጥ ይመስላል ከታች እንደተመለከተው ምናልባት ኦዲተሮች የሂሣብ መዝጊያ ዓመት ትርጉሙ ላይገባቸው ይችላል፤ እንዲሁም የሂሣብ መዝጊያ ዓመት አንድ ዓመት መወሰን ያለበት ለምን እንደሆነ ላያውቁ ይችላሉ፡፡

**ሠንጠረዥ 3.5-9 የሂሳብ መግለጫ (ቦሎሶ ቦምቤ ሕ/ሥራ ማህበር)**

| | ትርፍና ኪሳራ | | ሚዛን |
|---|---|---|---|
| | ጊዜ ቆይታ | የቀን ብዛት | |
| 1 | 11/12/1999ዓ/ም ～28/11/2000ዓ/ም | 353 ቀናት | 28/11/2000ዓ/ም |
| 2 | 12/12/2000ዓ/ም～23/12/2001ዓ/ም | 1 ዓ/ም + 11ቀናት | 23/12/2001ዓ/ም |
| 3 | 23/12/2001ዓ/ም～24/01/2003ዓ/ም | 1 ዓ/ም + 32 ቀናት | 24/01/2000ዓ/ም |

### 4) ቦና ሁለገብ ህ/ሥራ ማህበር ቦና ወረዳ ሲዳማ ዞን /ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 02/

የቦና ሁለገብ ህ/ሥራ ማህበር የተቋቋመው በ1967 ዓ/ም ሲሆን እንደገና የታደሰው በ2001 ዓ/ም ነው፡፡ 450 አባላት ያሉት ሲሆን 410 ወንዶችና 40 ሴቶች ናቸው፡፡ ቦና ሁለገብ ህ/ሥራ ማህበር የሲዳማ ኤልቶ ዩኒየን አባል ነው፡፡ የቦና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 02 "የጥራት ቁጥጥር"ና ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08 "የመጋዘን አስተዳዳር" ግብርና ግብይት ማሻሻያ ሥርዓት ጥናት ተጠቃሚ ተመራጭ ነው፡፡ የቦና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር አባላት ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02 እና ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08 ሥልጠና ተሣትፈው እንዴት በጥራት መምራት እንደሚቻል የሚያመለክት ፓስተር ተቀብለዋል፡፡ የተሰጡት ፓስተሮች በጽ/ቤቱ ተለጥፈዋል፡፡

ዋና ዋና የሚነገዱ ምርቾች ቡናና እህል ናቸው፡፡ ቡና በዚህ አካባቢ በጣም ጠቃሚ የሆነ ካሽ ሰብል ቢሆንም የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ ግብርና ግብይት ማሻሻያ ሥርዓት ጥናት ቡናን ከገቢ ማስገኛ ሰብሎች ውስጥ አላካተተም፡፡

የቢዝነስ አስተዳደር ችሎታ ለመጨበጥ የጃይካ የጥናት ቡድን ስለ መጠን፣ የሽያጭ መጠንና የሚይዙት ሰብል ምርታማነት ጠይቀው ነበር፡፡ የእህሉ መጠን በክብደት ደረጃ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ቦሎቄ፣ አተርና ባቄላ ናቸው፡፡ እንደ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበሩ ሊቀመንበር፣ የምርት ደረጃ በሽያጭ መጠንና በምርታማነት በሠንጠረዥ 3-5-10 መሠረት የተቀመጠ ሲሆን አንዳንዶች ግን ደረጃው የተቀመጠው በቃለ-መጠይቅ ነው፡፡ በማለት ያስረዳሉ፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ይህ የሚያመለክተው የምርት ባህሪይ በቅርብ ጊዜ ያለውን የቢዝነስ የንግድ ልውውጥ ነው፡፡ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበሩ ምርቶችን በማስፋት ትርፍ ማግኘቱን ያረጋግጣል፡፡ የቢዝነስ ሥራቸውን በሂሣብ ሪፓርት አልተነተኑም፡፡ ነገር ግን የቢዝነስ አስተዳደር አስፈላጊነት በመጠን፣ በሽያጭና በትርፍ ማወቅ ችለዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.5-10 የእህል ሰብል ንግድ ሁኔታ (ቦና ሕ/ሥራ ማህበር)**

| | ብዛት | የሽያጭ መጠን | ትርፋማነት |
|---|---|---|---|
| በቆሎ | 1 | 2 | 6 |
| ቦሎቄ | 4 | 1 | 4 |
| ባቄላ | 6 | 4 | 3 |
| አተር | 5 | 3 | 2 |
| ስንዴ | 3 | 5 | 5 |
| ጤፍ | 2 | 6 | 1 |

የቦና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ሁለት ጊዜ ኦዲት ተደርጓል፡፡ የኦዲት ርዕሶቹ በደንብ የተደራጁ ካለመሆናቸውም በላይ የወጪ ዝርዝሩን በተከታታይ ጊዜ ትንተና ለማወዳደር አልተቻለም፡፡ ኦዲተሩ ያስቀመጡት አስተያየት የሂሣብ ባለሙያ እንዲቀጥሩ ሲሆን እሱንም በዚህ ዓመት አከናውነዋል፡፡ ዝርዝር ወጪዎች በየግሩፓቸው እንደሚያሰባስቡ ይጠበቃል፡፡ የተሰበሰቡትን ዝርዝር ወጪዎችን በሽያጭና የዕቃዎች ዋጋ፣ የትርፋማነት ትንተና በምርትና የንብረት ቆጠራ አስተዳዳር በጣም ቀላል ይሆናል፡፡ የጠቅላላ የማስፈፀሚያ ገቢና ወጪ የተያያዘ መሆን አለበት፡፡

የሂሣብ ሪፓርቱ የሂሣብ ዓመቱ በደንብ ባለመያዙ ያለፉት ዓመታት አፈፃፀም ለማወዳደር አልተቻለም፡፡ የዓመቱን መጀመሪያ ቀን በጥር መጀመሪያ ማድረጉ አስፈላጊ አይሆንም፤ ሆኖም አግባብ ያለው ቀን በምርት ካሌንደራቸው መሠረት መወሰን አለበት፡፡ የሂሣብ አስተዳደር ሥራ መሻሻል እንዳለበት ሉተኮር ይገባል፡፡

5) ባሊላ ሁለገብ የመጀመሪያ ደረጃ ሕ/ሥራ ማህበር ቦሪቻ ወረዳ ሲዳማ ዞን (ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 02)

የባሊላ ሁለገብ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር በ1991 ዓ/ም ተቋቋመ የአባላት ብዛት ጠቅላላ 500 (466 ወንዶች 34 ሴቶች) ሲሆን የሲዳማ ኤልቶ ሕ/ሥራ ዩኒያን አባል ነው፡፡ የባሊላ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የሙከራ ፕሮጀክት ትግበራ 02 "የጥራት ቁጥጥር"፣ ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 06 "የቦሎቄ ገበያ ሥፍራ ማሻሻያና ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08 "የመጋዘን አስተዳዳር" የተመረጠ ነው፡፡

ባሊላ የቦሎቄ ምርት እምቅ ኃይል አካባቢ ሲሆን በአካባቢው ያሉ ሕዝቦች የቦሎቄ ምርት በማስፋፋት የገቢ ማስገኛ ሰብል ሊያደርጉ ይሞክራሉ፡፡ የበሊላ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር ለቦሎቄ የገበያ ሥፍራ ለመገንባት ቦታ አዘጋጅተዋል፡፡ የመጋዘን ግንባታው ከቁጠባ በጀታቸውን በ300,000 ብር በመመደብ በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ መጋዘን ለቦሎቄ ቢዝነስ ምዝገባ አንዱ መመዘኛ ነው፡፡ ስለዚህ አግባብነት ያለውን የመጋዘን አስተዳዳር ዕውቀት ለማግኘት ሙከራ ትግበራ ፕሮጀክት 08 ሥልጠና ተሳትፈዋል፡፡

የቁጠባ ገንዘባቸውን መጋዘን ለመገንባት ተጠቅመዋል፡፡ ስለዚህ ብድር ከሲዳማ ኤልቶ ህ/ሥራ ዩኒየን በመጠቀም ቦሎቄ ከአባላትና አባል ካልሆኑት ይገዛሉ፡፡ የቦሎቄ የምርት ሁኔታ በዚህ ዓመት ጥሩ ነው፡፡ ቦቆሎ የአካባቢው ገበያ መደበኛ ምግብ ሲሆን በዓመት 1 ጊዜ ይመረታል፡፡ የቦሎቄ ምርት በግምት ትርፍ የሚያስገኝ ወደ ውጭ ገበያ የሚላክ ገቢ ማስገኛ ሰብል ሲሆን በዓመት ሁለት ጊዜ ሊመረት ይችላል፡፡ ሰዎች ለቦሎቄ እምቅ ኃይል እንዳለ ይገምታሉ፡፡

በሌላ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር አንድ ጊዜ ኦዲት ተደርጓል፡፡ ወደ ቦሪቻ የወረዳው ጽ/ቤት ኦዲተሮች እንዲመጡ ቢሄዱም አንዳንድ ጊዜ መጥተው መዝገብ አይተው ይመለሳሉ፡፡ በ2001 ዓ/ም የተጠቃለለው የሂሣብ ሪፓርት አንዳንድ ስህተቶች መኖሩ ሲረጋገጥ የወረዳው ጽ/ቤት ባለሙያና የጃይካ ጥናት ቡድን ማብራሪያ ጠይቀው ነበር፡፡ ሆኖም ኦደተሩ ሥራውን በመልቀቁ መልስ የሚሰጥ አልተገኘም፡፡

በሌላ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበር የሂሣብ ባለሙያ የትምህርት ዝግጅቱ ከፍተኛ ባይሆንም ግለሰቡ ትሁትና የ20 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ነው፡፡ የዋጋ መዋዠቅና የወጪዎች መጨመር በየጊዜው ለማህበሩ ሊቀመንበር ሪፓርት ያደርጋል፡፡ የወረዳው ጽ/ቤት አቅም ውሱን በመሆኑ የራሳቸው ሥራ ራሳቸው መምራት እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡

### (4) የረዥም ጊዜ እስትራቴጂክ ዕቅድ

አንዳንድ ሕ/ሥራ ማህበር ዩኒየኖች እንዴት የረዥም ጊዜ እስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት እንደሚችሉ ራስ አገዝ " የሚባል መነሻው ከአሜሪካን አገር የሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሥልጠና ሠጥቷቸዋል፡፡ ለወደፊት ቢዝነስ ዕድገት በማሰብ ተጨባጭ በሆነ መጠን ለንግድ ልውውጥና ለትርፍ ማቀድ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም የዕቅዳቸውን ይዘት በተለይ የሲዳማ ኤልቶ ሕ/ሥራ ዩኒየን ሲታይ ዕውን ለመሆን በጣም የተጋነነ ይመስላል፡፡ ለምሳሌ የእህል ንግድ ዝውውር መጠን ለ5 ዓመት ዕቅድ የተቀመጠው የ2010 (እ.ኤ.አ) 4 እጥፍ ነው፡፡ የትብብር ተግባራዊ ዘዴ የሥራ ጊዜ ሠሌዳ፣ ተዘዋዋሪ ገንዘብና አስፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል በእስትራቴጂክ ዕቅዱ አልታየም፡፡ የእስትራቴጂክ እቅዱ በተጨባጭ ሁኔታዎች በመነሣትና የሂሣብ መረጃ መሠረት እንደገና መከለስ አለበት፡፡ አንዳንድ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች ከገበያ ፍላጐት በመነሣት የምግብ ዘይትና ስኳር ንግድ ጀምረዋል፡፡ የዚህ ዓይነት አዲስ ቢዝነስ ሥራ እንደ ሁለተኛ ተግባር ይገመታል ምክንያቱም ከግብርና ሥራ ጋር የተያያዘ ባለመሆኑ፤ ነገር ግን እምቅ ኃይል ያለው ትርፋማ ቢዝነስ ነው፡፡ ዩኒየኖቹና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት እንደ ገበያው ሁኔታ ሥራቸውን ሊያሰፋ ይችላሉ፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ግን የሚታሰበው አባሎቻቸውን እንደሚጠቅሙና በክልሉ ለግብርና ልማት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይገመታል፡፡

## 3.5.5 ለሕብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ

የተለያዩ ተዋንያን የተለያየ ድጋፍ አቅማቸውን እንዲያሣድጉ ለሕ/ሥራ ማህበራት ለዩኒያኖች ተሠጥቷል፡፡ በዚህ ክፍል በሁለት ዘርፎች ለሕ/ሥራ ማህበራት ልማት የተደረገውን ድጋፍ እናተኩራለን፡፡ አንደኛው ቴክኒክ ድጋፍ ሲሆን ሁለተኛው የፋይናንስ ድጋፍ ይመለከታል፡፡ ከዚያም ከዩኒየኖች ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የተደረገው ድጋፍ በዝርዝር ይመለከታል፡፡

### (1) የቴክኒክ ድጋፍ

ለእህል ንግድ ሕ/ሥራ ማህበራት በአሁኑ ጊዜ የሥልጠና ፕሮግራም ተግባራዊ ያደረጉት የክልል ግብይትና ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቶች እና የዓለም የምግብ ፕሮግራም ናቸው፡፡

<u>የግብይትና ማህበራት ቢሮ</u>

የክልሉ ግብይትና ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ በማህበራት ልማት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዋና ዋና ኃላፊነቶች አንዱ የማህበራትን አቅም በማጠናከርና ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ ለገጠሩ ህ/ሠብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማስገኘት ነው፡፡ በዚህ እይታ የክልሉ ግብይትና ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ 4 ደረጃ መዋቅር አለው እነዚህም የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የኮሚኒቲ አደራጆች በቀበሌ ደረጃ ናቸው፡፡፡

በክልል ቢሮም በሴክተሩ መስመር ጽ/ቤቶች ለማህበራት የተሰጠው ሥልጠና የተለያዩ ርዕሶችን የያዘ ሲሆን ከእነዚህም የመዝገብ አያያዝ፣ የማህበራት ግብይት፣ የማህበራት ሕጎችና ደንቦች፣ የምርት ጥራት ቁጥጥርና የመጋዘን ማኔጅመንት ያካትታል፡፡ በመሠረቱ የሚደረገው የአሠልጣኞች ሥልጠና አቀራረብ ሲሆን የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ከዞንና ወረዳ ግብይት ጽ/ቤቶችና የኮሚኒቲ አደራጆች ድጋፍ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራትንና አርሶአደሮችን ያሰለጥናሉ፡፡ የክልል ቢሮ ባጋጠመው ከባድ የፋይናንስ እጥረት ምክንያት ይህ አቀራረብ በተክክል ተግባራዊ አልሆነም፡፡ በዚህ ምትክ የክልል ቢሮ ብዙ ጊዜ ከልማት አጋሮች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድረጅቶች እና አንዳንድ ጊዜ ከዩኒየኖች ጋር ሥልጠናውን ያዘጋጃል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የቢሮና የዞን ባለሙያዎች አሠልጣኝ እንዲሆኑና ሥልጠናውን የጠየቁ ድርጅቶች የሎጂስቲክና የፋይናንስ ሁኔታ ያሟላሉ ሠልጣኞችንም ይመለምላሉ፡፡

በሌላ አገላለፅ የሠልጠና ርዕሶችና ሠልጣኞች ይወስናሉ፡፡ የጠያቂው ድርጅት የተለዩ ኃላፊነቶችና ዓላማ በማንፀባረቅ (የክልል ቢሮ ላይሆን ይችላል) ሥልጠናው ይሰጣል፡፡ የአሠልጣኞች ማኑዋል በፌደራል የህብረት ሥራ ኤጀንሲ ተዘጋጅቷል፡፡ የኤጀንሲውን መምሪያ በማጣቀስ፡፡

የክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮና የዞን መምሪያ ባለሙያዎች ሥልጠናውን በሚሰጡበት ጊዜ የኤጀንሲውን ማኑዋል በማጣቀስ የራሳቸውን ማቴሪያል ያዘጋጃሉ፡፡ ማኑዋሎቹ በአብዛኛው ቲዮሪና ገላጭ ሲሆኑ የማህበራት አባላት የተማሩትን በማህበራቸው ዕለታዊ የማኔጅመንትና የሥራ አፈፃፀማቸው ተግባራዊ የሚያደርጉት አይደለም፡፡

<u>NGO</u>

በደቡብ ክልል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድረጅቶች ከእህል ንግድ ማህበራት ጋር ጠንካራ ተባባሪ ሆኖ የሚሠራ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድረጅቶች ራስ አገዛዝ የተባለ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ በደቡብ ክልል 4 ህብረት ሥራ ዩኒየኖች እነርሱም፡ ሲዳማ ኤልቶ፣ ሜልክ ሥልጢ፣ ዋልታ እና ዕድገት የዘር ማባዣ ሕ/ሥራ ዩኒያኖች በመምረጥ አብሮ ይሠራል፡፡ በ2004 (እ.ኤ.አ) ፕሮጀክቱ ከጀመረበት ግዜ አንስቶ ለእነዚህ ዩኒያኖች የተሰጡ ዋና ዋና ድጋፎች የማከተሉት ናቸው፡፡[10]

- ለማህበራት አባል አርሶአደሮች በአመራረት፣ የጥራት ማሻሻል እና የህ/ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴ የግንዛቤ ማሣደግ ሥልጠና መስጠት፣
- ምርጥ ዘር በማምረት ረገድ የቴክኒክ ድጋፍ በ4ቱ ዩኒየኖች ለታቀፉ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት መስጠት:-
- ማቺንግ ፈንድ (Matching Fund) ለመጋዘን ግንባታ፡ ዩኒየን 200,000 ብር ሲያዋጣ፣ NGO 400,000 ብር መስጠት፡-

[10] አንዳንድ ሥራዎች ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ዓላማቸው ግብ ከመታ በኂላ አቋርጠዋል፡፡

- በዮኒየን ምስረታ ወቅት መነሻ ገንዘብ (Seed money) መመደብ፡-
- የገበያ ትስስር መፍጠር፡-
- በአቢሲኒያ ባንክ ዩኒየኑ የባንክ ብድር /አቢሲኒያ ባንክ/ በሚጠይቅበት ጊዜ 50% የብድር ዋስትና መስጠት ናቸው፡፡

ሌላው በማህበራት ድጋፍ የሚሳተፈው VOCA የተባለ NGO ነው፡፡ "የግብርና ህ/ሥራ ፕሮግራም በኢትዮጵያ" (ACE) የተባለው ፕሮጀክት ከ1999 እና 2006 መካከል ተግባራዊ ሲሆን የገንዘብ ድጋፉ የተገኘው ከአሜሪካን መንግስት (USAID) ነው፡፡ ACE ትኩረት ያደረገው በ5 ዞኖች ሲዳማ፣ ጌዲኦ፣ ጉራጌ፣ ሃዲያ እና ካምባታ ጠምባሮ ሲሆን እነዚህ አካባቢዎች የግብርና እምቅ ኃይል ያላቸው ተብለው ነው፡፡ በመጀመሪያ ፕሮጀክቱ ለመንግስት ኃላፊዎች ተከታታይ ሥልጠና በማህበራት እንቅስቃሴ በማህበራት ሕግ፣ በግብይት፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በጥራት ቁጥጥርና ፍተሻ ሰጥቷል፡፡

በጠቅላላው ከ100 በላይ አሠልጣኞች ከአሜሪካን መጥተው ሥልጠናውን ሰጥተዋል፡፡ የሠለጠኑት ኃላፊዎች ሥልጠና ለማዘጋጀት ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት አባል አርሶአደሮች ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ሌላ በኢትዮጵያ የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ዩኒየን እንዲመሠርቱ ረድቷቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት 6 ዩኒየኖች ተመሥርተዋል፡፡ እነርሱም አዲስ ድርጅት አመሠራረት ላይ ሥልጠና ሠጥቷቸዋል፡፡ በኢትዮጵያ የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት ካቆመ 5 ዓመት አልፏል፡፡ ሆኖም ብዙ ሕ/ሥራ ማህበራት ዛሬም በኢትዮጵያ የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት ባደረጋቸው ሥራዎች ያደንቃሉ፡፡


<u>የዓለም የምግብ ፕሮግራም</u>

አንዱ ለደቡብ ክልል ሕ/ሥራ ማህበራት የስልጠና ፕሮግራም የሚያዘጋጀው የዓለም የምግብ ፕሮግራም ነው፡፡ የዓለም የምግብ ፕሮግራም አዲስ ፕሮግራም (ግዢ ለእድገት) የተሰፐ እንዲጀመር አድርጓል፡፡ የፕሮግራሙ አላማ የብርዕና አገዳ ሰብልና ጥራጥሬ ቀጥታ ከሕ/ሥራ ማህበራት መግዛት ነው፡፡ ስልጠና በጥራት ቁጥጥር፣ የመጋዘን ማኔጅመንት እና የዓለም የምግብ ፕሮግራም የግዢ እቅድ የተካሄደ ሲሆን ተሣታፊዎችም የመንግስት ሀላፊዎች፣ የዩኒየን ሃላፊዎችና መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ኮሚቴ አባላት ነበሩ፡፡ አንድ የዩኒያን ስራ አስኪያጅ ግዥ ለዕድገት ለሕ/ሥራ ዩኒያኖች ስለዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃና የእህል ሰብል ግብይት ግንዛቤ ስለአስጨበጣቸው አድንቋል፡፡

### (2) የፋይናንስ ድጋፍ

ካለበቂ የስራ ማስኬጃ ካፒታል ህ/ሥራ ማህበራት መቀጠል እንደማይችሉ ግልፅ ነው፡፡ በዓመቱ ውስጥ ምርቱ በሚገኝበት ጊዜ ሕ/ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው እና አባል ካልሆኑት ምርት መግዛት አለባቸው፡፡ በቂ የሆነ ገንዘብ በዚህ ወቅት መኖር ያስፈልጋል፡፡

እስከ 2010 (እ.ኤ.አ) ድረስ የገጠር ፋይናስ ፈንድ ለሕ/ሥራ ማህበራት የገንዘብ ብድር የሚሰጥ ብቸኛው ድርጅት ነበር፡፡ የገጠር ፋይናስ ፈንድ በክልሉ በ2004 (እ.ኤ.አ) የተቋቋመ እና ዓላማውም በአነስተኛ ወለድ ብድር ለገጠሩ ህ/ሠብ ማድረስ ነው፡፡ ብድር በሚሰጥበት ጊዜ ዋስትና አያስፈልገውም፡፡ የየገጠር ፋይናስ ፈንድ ስራ አፈፃፀም ዘዴው ከቻች ተመልክቷል፡፡




**ምስል 3.5-7 የገጠር ፋይናስ ፈንድ የሥራ አፈፃፀም ዘዴ**

መጀመሪያ የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የብድር ጥያቄ ለዩኒየኖች ከአመታዊ እቅድ ጋር ሲያቀርቡ የዩኒየኑ ማኔጅመንት ኮሚቴ ይገመግማል፡፡ 2 ዩኒየኖች የራሳቸውንና የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ጥያቄዎች የአደራጁ እና የብድር ማመልከቻ በዚያን ወቅት ለነበረው ለማህበራት ልማት ኤጀንሲ ለተቀባይነት ይልካሉ፡፡

የመጨረሻ ማጣሪያ በገጠር ፋይናንስ ፈንድ ከተደረገ በኋላ ብድሩ ለዩኒኖች ይሰጣል፡፡ ከዚያም ሕ/ሥራ ማህበራት ይከፋፈላል፡፡ የተሰጠው ብድር ለዩኒየኖችም ሆነ ማህበራት ይከፋፈላል፡፡ የተሰጠው ብድር ለዩኒየኖችም ሆነ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ለሥራ አፈፃፀማቸው በጣም ወሣኝ ነው፡፡ መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ከአርሶ አደሮች የገዙትን የእህል መጠን በአብዛኛው የሚወስነው ከዩኒያኖች በሚያገኙት የብድር መጠን ነው፡፡

ከዚህ ሌላ የገጠር ፋይናስ ፈንድ ወለድ 7.5% ሲሆን ለገጠሩ ህ/ሠብ የሚሰጡት በ1.5% ወለድ ሲሆን ይህም በጣም ዝቅተኛው ነው፡፡ የብድር ስምምነት በየገጠር ፋይናንስ ፈንድ እና በዩኒኖች መካከል ያለው ሃሣብ ዩኒየኑ 1.5% ወለድ ከዋናው ብድር ጋር ሲሆን ቀሪው 6% በዩኒየኑ ካፒታል ውስጥ ይታሰባል በሚል ነው፡፡ ከዚያም ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት በዩኒየኑ የሚሰጠው በ7.5% ወይም ከዚያ በላይ ወለድ ሲሆን በሁለቱ ወለድ መጠን መካከል ያለው ልዩነት የዩኒያኖች የፋይናንስ አቋማቸውን ለማሻሻል ይረዳል፡፡ እንደ ቀድሞ የገጠር ፋይናንስ ፈንድ የብድር አስተዳዳሪ የዩኒየኖች የዕዳ መላሽ መጠን በጣም አጥጋቢ የነበረ ቢሆንም በቀጥታ ለአርሶአደሮች በተሰጠው ዕዳ ላይ የመመለስ ችግር ታይቷል፡፡ በአጠቃላይ በግምት 200000 ሚሊዮን ብር በገጠር ፋይናንስ ፈንድ ለገጠሩ ህ/ሠብ በየዓመቱ ብድር ይሰጣል፡፡

የገጠር ፋይናንስ ፈንድ ስራውን በ2010 (እ.ኤ.አ) አቁሟል፡፡ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲቲዩት የየገጠር ፋይናስ ፈንድ ስራዎችን ተረክቦ እንዲመራ በክልሉ መንግስት ውክልና ተሰጥቷል፡፡ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ዋናው አላማ ዩኒየኖች ወይም መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ሣይሆኑ የአርሶ አደር ቡድኖች በመሆኑና ከዚህም ሌላ የብድር ውለታ ያለማክበር ችግር በማጤን የወለድ መጠን 18% አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን የንግድ ባንኮች የወለድ መጠን ከኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ዝቅ ያለ ይኸውም 7% አከባቢ ቢሆንም የዋስትና አስፈላጊነት ስላለ ለብዙዎቹ ዩኒየኖች ከንግድ ባንኮች ብድር ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ የገጠር ፋይናንስ ፈንድ መዘጋት ለማህበራት ምን ያህል የፋይናንስና የስራ አፈፃፀም ተፅዕኖ እንዳሣደረ መፈተሽ ይገባል፡፡

### (3) ከዩኒየኖች ለየመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የተሰጠ ድጋፍ

ከላይ እንደተገለፀው ዩኒየኖች እና የእነርሱ አባል መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ሁለቱም በጋራ በምርት ንግድ፣ በማዳበሪያ ስርጭት እና በብድር ግዢ ይሰማራሉ፡፡ ስለሆነም የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የቴክኒክና የስራ አፈፃፀም ውድድር በቀጥታ የዩኒየኖችን ስራ አፈፃፀም እና ተያይዞም ትርፋማነት ይነካል፡፡ አብዛኛዎቹ ዩኒየኖች ለአባል መሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት ጥቂት አቅም እና ተወዳዳሪነት ብቻ ነው ያላቸው፡፡ ያም ሆነ ይህ ጥቂት ዩኒየኖች የአቅም ማሣደግ ስራ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት በሚከተሉት ስራዎች ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

<u>የስልጠና ፕሮግራም</u>

ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት የሂሣብ አያያዝ፣ የጥራት ቁጥጥር እና የድርጅት አስተዳደር ስልጠና ተዘጋጅቷል፡፡ አሰልጣኞች ከዩኑያን፣ ከክልል ግብይትና ሕ/ሥራ ቢሮ ወይም ከመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚመለከተውን ዩኒያን የሚደግፍ ስልጠና ይሆናል፡፡

<u>የሥራ አስኪያጅ ቅጥር</u>

በ3.5.2 በተደረገው ገለፃ መሠረት አብዛኛዎች የመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት ከፋይናንስ እጥረት የተነሣ ስራ አስኪያጅ ሊቀጥሩ አይችሉም፡፡ ስለሆነም ዩኑያን ስራ አስኪያጅ ለመሠረታዊ ሕ/ሥራ ማህበራት በእነሱ ስም ይቀጥራል፡፡

## 3.6 የአሁኑ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅታዊ አሠራር

### 3.6.1 የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት

#### (1) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አመሠራረት

በኢንዱስትሪው ዘርፍ በተካሄደው ክፍተኛ የግብይት መሻሻል በ1990 (እ.አ.አ) መጀምሪያ የኢትዮጵያ የእህል ሰብል ኢኮኖሚ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሲደርስበት ነበር። በማዕከላዊ እዝ ሥር የነበረው የግል ነጋዴዎችን እንቅስቃሴ የሚገድብ የዋጋ ተመን እና የኮታ አሠራር ተወግዷል። በ1976 (እ.ኢ.አ) በዓለም ባንክ ድጋፍ እህል ሰብል በመግዛት ለተጠቃሚዎች ለማከፋፈል የተቋቋመው የእርሻ ገበያ ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ ዝቅ እያለ መጥቷል። የእርሻ ገበያ ድርጅት በኮታ ላይ ተመስርቶ ከ10%-50% የሚሆነውን አርሶአደሩን ምርት በዝቅተኛ ዋጋ ይገዛ ነበር። በኢኮኖሚ ሥርዓት የተደረገው ለውጥ የእርሻ ገበያ ድርጅት አሠራሩንና ተግባሩን እንዲቀይር አድርጓል።

በ1992 (እ.ኢ.አ) የእርሻ ገበያ ድርጅት ስምንቱን የቀጠና ጽ/ቤቶች በመዝጋቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ቁጥር ከ27 ወደ 11 ዝቅ ብሏል። በተጨማሪ ከ2013 የእህል ሰብል ግዥ ማዕከላት 80 ብቻ ስቀሩ የተቀረው ተዘግቷል። በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያ የእህል ገበያ ኢንተርኘይስ በመባል በአዲስ መልክ የዋጋ መረጋጋትና ክምችት ለመያዝ ተቋቁሟል።

በ1999 (እ.ኢ.አ) በቀጣይ ማሻሻያ በማድረግ የኢትዮጵያ የእህል ገበያ ኢንተርኘራይዝና የኢትዮጵያ ቅባትና ጥራጥሬ አክስዮን ኮርኘሮሽን ተዋህደው በመንግሥት በሌቤትነት ሥር በመሆን እንደገና በአዲስ መልክ ተቋቋመ። ይህ ድርጅት እንደቀድመው ዋጋ የማረጋጋት ሥራ ሳይሆኝ ለትርፍ የሚሠራና እህል ውጪ ሀገር መላክ ላይ ያተኮረ ነበር።

አብዛኛው የእህል ንግድ በግል ዘርፍ ይካሄዳል። ይሁንና ነፃ የእህል ገበያ እንደታሰበው ቀልጣፋ ሊሆን አልቻለም። የዋጋ አተማመን በግብይት ተሳታፊ ለሆኑ እኩል ግልጽ የማይሆንበት ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚከሰት ሲሆን ተገቢ ያልሆነ ስምምነቶች ይካሄዳሉ።

መንግሥት የገበያ ሥርዓት ማሻሻያ ሀሳብ በማቅረብ የምርት ገበያ እንዲቋቋም አድርጓል። የፌዴራል መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ የወጣው አዋጅ ቁጥር 550/2007 (እ.ኤ.አ) ስለምርት ግብይት የሚደነግግ ሲሆን በመስከረም 4 ቀን 2007 (/እ.ኢ.አ) አዋጅ ቁጥር 551/2007 መሠረት የምርት ገበያ ባለሥልጣን ተቋቁሟል። እነዚህ አዋጆች ለለኢትዮጵያ ምርት ገበያ መቋቋም ያትታሉ።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግንድ እንቅስቃሴን በ2008 (እ.ኢ.አ) ጀምሯል። የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ተገቢ የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር ላይ የተመሠረተ በጨረታ የሚካሄድ የግብይት ሥርዓትን አስተዋውቋል። ፍቃድ ያላቸው የተመዘገቡ ነጋዴዎች በሚሠጠው የጥራት ደረጃ ላይ ተመስርተው ይጫረታሉ። ዋጋም በፍላጐትና አቅርቦት ላይ ተመስርቶ ይወሰናል።

የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ቡና፣ ሰሊጥ፣ ነጭ በሎቄ፣ በቆሎና ስንዴ ለማገበያየት ያቀደ ቢሆንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድርስ ቡና በማገበያየት ላይ ተወስኖ ነበር። የታሰበውን ያህል ባይሆንም ሰሊጥና ነጭ በሎቄ ማገባየት እየተካሄደ ነው።


#### (2) የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ዓላማ

የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ገዥና ሻጭ ጥራትን ጠብቆ ለመገበያተና በዋጋ ልውውጥ ምርቶችን ለመቀባበል የሚመጡበት የገበያ ቦታ ነው። የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ራዕይ ዓለም አቀፍ የምርት መገበያያ አማራጭ ሆኖ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ማሳደግ ነው። የኢትዮጵያ

ምርት ገበያ ተልዕኮ ገዥና ሻጭን ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ማገናኘት፣ የገበያ ማሻሻያ ፈጠራና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆን ነው፡፡ ሁሌም የመማር፣ ሚዛናዊነትን የመጠበቅ እና በቁርጠኝነት የመሥራት እሴት አለው፡፡

### (3) የኢትዮጵያ የምርት ገበያ አወቃቀር

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የድህረ ገጽ የተመለከተው ድርጅታዊ አወቃቀር ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡ ዘመናዊ ዓለም አቀፍ የገበያ ሥርዓትን ማስፋፋት እንዲያስችል የምርምር የሥራ ክፍል ያለው ሲሆን የግብይት ሂደትም መምራት የሚያስችሉ የሥራ ዘርፍም አሉት፡፡




**ምስል 3.6-1 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅታዊ መዋቅር**

### (4) የድርጊት ተግባራት

#### 1) የገበያ ቦታ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋንኛ ተግባሩ በምርት መገበያያ ማዕከል የሚያካሂደው የሥራ ሂደት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ቡናና የቅባት ሰብሎች፣ ስንዴ፣ በቆሎና ጥራጥሬ ላይ ይሠራል፡፡

በሚያዝያ 2008 (እ.ኢ.አ) በተቀመጠው መነሻ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ምንም እንኳን ጥራቱን የጠበቀ የእህል ሰብል ባይኖርም የእህል ሰብል ግብይቱን እያካሄደ ነው፡፡ የእህል ሰብል የጥራት ደረጃ ዝቅ ያለ ሲሆን የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ የሚያሟላ አይደለም፡፡ አብዛኛው ነጋዴዎች ጅምላ ሻጭና አቀነባባሪዎችን ጨምሮ ራሳቸው በቦታ ላይ ተገኝተው በድርድር መግዛትን ይመርጣሉ፡፡ ነጋዴዎች የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አሠራር ጋር የተላመዱ አይደሉም፡፡ የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ እጥረትም አለ፡፡ በተጨማሪ በበቂ ሁኔታ የሚያጣራና የሚለይ መሣሪያ እንዲሁም የጥራት መቆጣጠሪያ ቁሳቁስ ተጠቅሞ በደረጃ መለየት ባለበት ሁኔታ ግንባር ቀደም ሆኖ በአዲስ የእህል ግብይት ሥርዓት ለማሳተፍ ነጋዴዎች ተነሳሽነት የላቸውም፡፡ ለምርት ጥራት ማሻሻያ የሚወጣው ወጪ በመሸጫ ዋጋ የተጠቃለለ መሆኑ እንዲሁም የትንስፖርት ወጪ ምናልባት ጨረታው

ባይሳካ በማን እንደሚሰፈን ያለመታወቁ ችግር ነው፡፡ በኢትዮጵያ የምርት ገበያ የሚካሄደው ጨረታ የማጓጓዝ ወጪን ለመሸፈን የሚያስችል ከፍተኛ ዋጋ መኖሩን አያረጋግጥም፡፡ ይህም በመሆኑ ነጋዴዎች በግብይት ሂደቱ ለመሳተፍ ደስተኛ ባለመሆናቸው ዝም ብለው የግብይት ሂደቱን መከታተሉ ይመረጣሉ፡፡ ይሁንና እንደ ዕድል የሰሊጥ ግብይት መጠን በተከታታይ እየጨመረ ያለ ሲሆን የነጭና ቦሎቄ ግብይት መጠንም በ2012 (እ.ኢ.አ) በጣም ጨምሯል፡፡

በኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት እስካሁን ስንዴ፣ ጥራጥሬና በቆሎ የማገበያት ሥራ አልተጀመረም፡፡ ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት የአካባቢ የእህል ሰብል ደረጃ በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል፡፡ ሠንጠረዥ 3.6-1 ከሚያዚያ 2008-2012 (እ.ኢ.አ) ያለውን የእህል ሰብል ግብይትን ያሳያል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት አማካኝነት የሚካሄደው የእህል ሰብል ግብይት ከተጠበቀው ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.6-1 በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል የተደረገ የእህል ግብይት ሚያዝያ 2008 - 2012**

| ምርት | ሚያዝያ - ታህሣስ 2008 | | ጥር - ታህሣስ 2009 | | ጥር - ታህሣስ 2010 | | ጥር - ታህሣስ 2011 | | ጥር -- 2012 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቶን | Birr/ቶን | ቶን | Birr/ቶን | ቶን | Birr/ቶን | ቶን | Birr/ቶን | ቶን | Birr/ቶን |
| ጥራጥሬ | 19,174 | 5,780 | 0 | NA | 18,599 | 7,250 | 42,988 | 8,740 | 47,388 | 8,390 |
| ሰሊጥ | NA | NA | 84 | 14,820 | 14,410 | 17,790 | 20,579 | 19,500 | 29,743 | 20,690 |
| ስንዴ | 675 | 5,800 | 0 | NA | 5 | 4,050 | 0 | NA | 0 | NA. |
| በቆሎ | 985 | 4,620 | 20 | 3,220 | 2,632 | 2,770 | 1,784 | 4,780 | 60 | 5,120 |

ምንጭ: የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድህረገጽ Unit : Volume (ton), Price (Birr/ton)

በሌላ በኩል በገበያ ማዕከሉ ቡና ለመገበያየት ያለው ፍላጐት ከፍተኛ በመሆኑ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቡና ማገበያየትን በ2008 (እ.ኢ.አ) ጀምሯል፡፡ ለኤክስፖርት ገበያ የሚቀርበው ቡና ጥራቱን የጠበቀ መሆኑ ተፈላጊ ሲሆን በምርቱ ዝውውር ሂደት የሚደረገው የጥራት ቁጥጥር ወሳኝ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት ነባር መጋዘኖችን በመጠገን የተወሰኑ የተለያዩ አረንጓዴ ቡና ማቀማቻ የሚሆን አዳዲስ መጋዘኖችን በመገንባት የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎች ቡና በሚመረትበት አካባቢ በመቋቋም ጥብቅ በሆነ መንገድ የቡና ጥራት በተመረተበት አካባቢ ተለይቶ ደረጃ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ በገበያ ማዕከሉም የሚደረግ የቡና ግብይት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በውጪ ሀገር ገበያ የሚሸጥ የቡና መጠን ከፍተኛ ስሆን ለወጪ ሀገር ገበያ የሚቀርበው ያልታጠበ ቡና ዋጋ መዋዠቅ ይታይበታል፡፡

2) መጋዘን

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተቀናጀ የመጋዘን ሥርዓት ያለው ሲሆን ምርቱን ከመቀበያ እስከ መጨረሻው በኢንዱስትሪ ተቀባይነት ያለው ደረጃ በየምርቱ ዓይነት ጠብቆ ማስረከብ በሚያስችል ነው፡፡ በዋናነት ትርፍ አምራች በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢ በሚገኙ የኢትዮጵያ መርት ገበያ መጋዘኖች ይከማቻል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡

- ናውና ማዘጋጀት፣ ደረጃ የመስጠት፣ መመዘንና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መስፈርት መሠረት በየመጋዘኑ የሚገኙ እህልና ቡና የደረጃ ሰርተፊኬት መስጠት
- መመዘን በኢትዮጵያ ምርት ገበያ መረጃ ሥርዓት ውስጥ በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ መዝግቦ መቀበል
- ገቢና ወጪ የእህል መመዝገብና ዕለታዊ የምርት ክምችት ሪፖርት ማድረግ

- ምርቱን በአግባቡ በመጋዘን መያዝ (በአግባቡ በመጋዘን መደርደር፣ የቢን ካርድ፣ የንብረት ዝርዝር ቆጠራ አስተዳደር)
- በኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና የአካባቢ መጋዘኖች መካከል ያለውን መረጃ ልውውጥ ወቅታዊ በማድረግ ይዞታና አቀራረብ በማሻሻል ሪፖርት የማድረግ
- የተረከቡት ምርት ጥራቱን በአግባቡ መጠበቅ

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘን አድራሻና የመያዝ አቅም በሠንጠረዥ 3.6-2 ተመልክታል፡፡ አብዛኛው መጋዘን ከኢትዮጵያ እህል ገበያ ድርጅት በክራይ የተገኘ ነው፡፡ በሀዋሣ፣ ዲላና ቦንጋ የሚገኙ የቡና መጋዘኖች በፍላጐት ላይ ተመስርቶ የተገነቡ አዲስ ናቸው፡፡ በማምረቻ አካባቢ የተቋቋሙት የሰሊጥ መጋዘኖች የወደፊቱ ፍላጐትን ከግምት ውስጥ አስገብተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.6-2 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መጋዘን አድራሻና የመያዝ አቅም**

| ተ .ቁ | አድራሻ | ምርት | | የመያዝ አቅም በኩንታል | ከአ/አበባ ያለው ርቀት (ኪ.ሜ) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ቡና | እህል | | |
| 1 | አዲስ አበባ (ዮሴፍ) | x | | 100,000 | - |
| 2 | Addis Ababa (ሳሪስ) | x | x | 300,000 | - |
| 3 | ድሬዳዋ | x | | 50,000 | 515 |
| 4 | ናዝሬት | | x | 50,000 | 90 |
| 5 | ቡሬ | | x | 50,000 | 410 |
| 6 | ነቀምት | | x | 50,000 | 330 |
| 7 | ሁመራ | | x | 50,000 | 900 |
| 8 | ሀዋሣ | x | | 200,000 | 273 |
| 9 | ጅማ | x | | 170,000 | 346 |
| 10 | ጎንደር | | x | 70,000 | 738 |
| 11 | ሁመራ | | x | 50,000 | 900 |

ምንጭ: የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድህረገጽ

### 3) ኤክስቴሽንና ትምህርት

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ተግባር የመገበያያ ቦታ መዘጋጀት ብቻ ሳይወሰን የምርቶች ጥራት ተጠብቆ ቀልጣፋ ግብይት እንዲሰፍን ጥረት ያደርጋል፡፡ የነፃ ገበያ ሥርዓት ብቻውን ቀልጣፋነትን፣ ጥራትና ሚዛናዊነትን ብቻውን ያሻሽላል ብሎ መጠበቅ አይቻልም፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚመለከታቸው አካላትን የማበረታታት፣ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ በመሥራትና ሥልጠና በመስጠት የምርት ግብይት የሚሻሻልበትን ሁኔታ የመምቻቸት ኃላፊነት አለበት፡፡ በተጨማሪም የሚመለከታቸው አካላት ስለዘመናዊ ግብይት አሠራርና ፍላጐት መረጃ በመስጠት ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃ የጠበቀ ንግድ እንዲያካሂዱ ይረዳል፡፡

የዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ከማስፋፋት አኳያ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለሚመለከተው አካላት ሴሚናር በመዘጋጀት ሥልጠና ሰጥቷል፡፡ የሚመለከታቸው አካላት ማሳተፍና ማበረታታት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋንኛ ተግባር እየሆነ መጥቷል፡፡ በዚህ ረገድ ከግብርና፣ ከንግድ ኢንዱስትሪና ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር መተባበር አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በዓለም አቀፍ ዕርዳታ ድርጅት በቴክኒክና በበጀት ይደጋፋል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የአስተዳደር ሥራ የሚሠሩ በምጣኔ ሀብትና አስተዳደር የሰለጠኑ ባለሙያዎች አሉት፡፡ ይሁንና በምርት አያያዝ እና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ የመፍጠር አቅም

ያላቸው የቴክኒክ ባለሙያዎች እጥረት አለበት። በኢትዮጵያ የምርት ገበያ በምርት ጥራት ማሻሻል ላይ የተሰጡ ስልጠናዎች ንድፈ ሀሳብ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን በገሀዱ የንግድ ሂደት ውስጥ ጥራትን ለማሻሻል የሚያበቂ የቴክኒክና የተግባር ክህሎት እንዲኖር ያሚያስችሉ አልነበሩም።

### 3.6.2 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት እንቅስቃሴ

ቡናን በተመለከተ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ስሩት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በጣም ይንቀሳቀሳል። በሀዋሣ፣ ዲላ፣ ቦንጋና ሶዶ የሚገኘው የቡና መጋዘንና ላብራቶሪ አዲስ የተገነቡ ወይንም የተስፋፉ ናቸው። የመጀመሪያ ደረጃ የጥራት ቁጥጥር ሥራ የዲላና ሶዶ በተገነቡ አዲስ መጋዘኖች በስተቀር በአግባቡ እየተካሄዱ ነው።

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በሀገሪቱ የእህል ሰብል በብዛት ከሚመረትባቸው አካባቢዎች አንዱ ሲሆን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በክልሉ ውስጥ የሚያካሄደው እህል ሰብል ግብይት እንቅስቃሴ አነስተኛ ነው። ከሀዋሣ ከተማ በ25 ኪ.ሜትር ርቀት በምትገኘው የሻሸመኔ ከተማ የሚገኙ ጅምላ ሻጭ ነጋዴዎችና ደላላዎች በኢትዮጵያ ምርት ገበያ እንቅስቃሴ ደስተኛ አይደሉም። አዲስ አበባ የሚገኙ ጅምላ ነጋዴዎች ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማዕከል ውጪ ይገበያያሉ። በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማዕከል የሚቀርበው ከአካባቢ ገበያ ከሚቀርበው እህል ብዙም የሚለይ አይደለም ብለው ያስባሉ።

ሻሸመኔ የሚገኘው የእህል መጋዘን ከኢትዮጵያ እህል ንግድ ኢንተርኘራዝ በክራይ የተገኘ ሲሆን ቀደም ሲል በእርሻ ገበያ ኮርፖሬሽን ወቅት የተገነባ ነው። ይህንን ምርት በታሰበው መሠረት ባለመቅረቡ ተሰርዟል። የዚህ መጋዘን ተጠቃሚዎች በአብዛኛው የግብርና ሕ/ሥራ ማህበራት ይሆናሉ ተብሎ የተገመተ ሲሆን በአግባቡ ተጠናክረው ወደ ሥራው ሊገቡ አልቻሉም። ይህም በመሆኑ የእህል ጥራትን ጠብቆ መገበያየቱ ብዙ ጊዜ እንዲሚጠይቅ ይገመታል።

አቀነባባሪዎች እንደ ዱቄት ፋብሪካዎችና ወፍጮ ቤቶች የመሳሰሉ በኢትዮጵያ የምርት ገበያ ማዕከላት መግዛቱ አስፈላጊ አይደለም። አብዛኛው አቀናባሪ በቋሚነት ከሚያቀርቡላቸው ደንቦች ጋር ዋጋ በግል በመደርደር ይገዛሉ። ዝቅተኛ ጥራት እና እንደ ድንጋይ የመሳሰሉ ባዕድ ነገር በሚፈጭበት ጊዜ ችግር ይፈጥራል። ዋጋ በምርት ላይ ተመሥርቶ የሚወሰን በመሆኑ የምርቱን ጥራት ለመጠበቅ አምራች ትኩረት እንድሰጥ የሚያነሳሳው ነገር የለም። እንደ ዱቄት ፋብሪካዎች አባባል በአካባቢ ገበያዎች ስንዴ በዱቄት መልክ ካልሆነ በብዛት አይቀርብም። ይህም በመሆኑ የዱቄት ፊብሪካዎች ፍላጐትና አቅርቦትን የማጣጣም ሥራ ይሠራሉ።

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በሆሳዕና ከተማ የሚገኘው ሌቻ ሃዳያ ዩኒያን የስንዴ ንግድ በመሥራት ውጤታማ ሆኗል። ሌቻ ሃዲያ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ መሥራቾች አባልነው። ይሁንና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ስንዴ አይገበያዩም። ከግንቦት 2009 (እ.ኢ.አ) ጀምሮ በመሥራት ላይ ያለ የራሱ የሆነ የዱቄት ፋብሪካ አቋቁሟል። ከአባል ሕ/ሥራ ማህበራት የሚሰበሰበው የስንዴ በመጋዘናቸው በማከማቸት በፍላጐት ላይ በመምሥረት ይፈጫሉ። ስንዴ ጥሬውን ከመሸጥ እሴት በመጨመር ዱቄቱን መሸጥ ትርፋማ ያደርጋል።

ከአምራቹ አኳያ የጥራት ደረጃው ዝቅ ባለቁጥር በዋጋ ድርድር ላይ ተመስርቶ መሸጥ ተስማሚ ነው። በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ጥራቱ ያልጠበቁ ምርት ግብይት ቦታ የለም። ተፈላጊው ጥራት ደረጃ ያልጠበቀ ምርት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የዋጋ ድርድር አይደረግም። ይህ የአምራቹ ስጋት ነው። በአካባቢ የሚገኙ አቀባባዮችና ጅምላ ነጋዴዎች

በዚህ ረገድ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ በተለየ በመደራደር ለመግዛት ፍቃደኛ ናቸው፡፡ የምርት ጥራት ዝቅተኛ ቢሆንም በእርካሽ ዋጋ ይገዛሉ፡፡ በሌላ  በኩል የማገበያየት ሥራ ለሚያካሂዱ ሰዎች መታያ በመስጠት ዘመናዊ ግብይትን ማደናቀፍ የተለመደ ነው፡፡

በተጨማሪ ከላይ ወደታች የሚሰጠው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አመራር እንዳንድ ጊዜ በአምራቾች፣ ነጋዴዎች እና የአካባቢ የመንግሥት አካላት ግጭትን ይፈጥራል፡፡ በጠረጴዛ ላይ የሚደረገው የግብይት ሥርዓት ማሻሻያ ጽንሰ-ሃሳብ በገሀዱ ዓለም ሁል ጊዜ በእያንዳንዱ ተዋኒያን ተቀባይነት አያገኝም፡፡ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተገለጸው የጥራት ማሻሻያና መልካም የጨረታ ሥራ ሂደት ጽንሰ-ሃሳብ በተግባር ኳንቲታቲብ ኢኮናሚክስ ሞዴል በመጠቀም ተፈትሾ አልተረጋገጠም፡፡ ከዚህም የጨረታ ሂደት የተገኘውን ጥቅም በተለይም ትርፉን መገመት አልተቻለም፡፡ ጊዜንና ወጪን ሳያገናዝቡ ማንኛውንም ነገር ተግባራዊ ማድረግ በቂ አይደልም፡፡

## 3.7 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የምግብ ዋስትና እንቅስቃሴ

### 3.7.1 በግብርና ቢሮ ቅድመ ማስጠንቀቅያና ምግብ ዋስት የሥራ ሂደት

#### (1) ድርጅታዊ መዋቅር

ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስትና የሥራ ሂደት በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ የምግብ ዋስትናን የሚያስተዳድር የሥራ ዘርፍ ነው። ቀደም ሲል በ2010 (እ.ኤ.አ) ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ እንደገና ከመዋቀሩ በፊት የሥራ ሂደቱ ተጠሪነቱ ለዚሁ ቢሮ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ተጠሪነቱ ለክልሉ ግብርና ቢሮ ከመሆኑ በስተቀር በድርጅታዊ መዋቀሩና የአሠራር ሃላፊነቱ ላይ የተለወጠ ነገር የለም።

ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስትና የሥራ ሂደት

| ቅድመ ማስጠንቀቂያ ንዑስ የሥራ ሂደት | የምግብ ዋስትና ንዑስ የሥራ ሂደት |
|---|---|
| ዋና ተግበራት፡<br>- የገበያ ዋጋ፣ የምግብ ምርት፣ ዝናብ፣ ወ.ዘ.ተ መረጃ መሰብስብ<br>- የተፈጥሮ አደጋ መረጃ መሰብሰብ (ተጎጂዎችን መለየት)<br>- በድንገተኛ አደጋ ወቅት ምግብ ማቅረብ | ዋና ተግባራት፡<br>- ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም (ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም)<br>+ ቀጥተኛ ዕርዳታ (በዕድሜ ለገፉ፣ለነፍሰጡር፣ አካል ጉዳተኞች)<br>+ ምግብ ለሥራ<br>- የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም<br>- የሠፈራ ፕሮግራም |

**ምስል 3.7-1 ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስትና የሥራ ሂደት ድርጅታዊ መዋቅርና ተግባር**

#### (2) የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ዝርዝር

የምግብ ዋስትና ንዑስ የሥራ ሂደት ብዙ የሰፍቲ ኔት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። የፕሮግራሙ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል።

##### 1) ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም

ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢ ያሉና በማህበረሰቡ ወይንም በቀበሌ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለተፈቀዳላቸው ቤተሰቦች በርካታ የሴፍቲ ኔት ተግባሮችን አከናውኗል። ለእነዚህ ቤተሰቦች የምግብ እርዳታ (አንዳንዴ ገንዘብ ማከፋፈልን ሊያካትት ይችላል) ለመስጠት ሁለት ዓይነት የሰፍቲ ኔት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

- ቀጥተኛ ዕርዳታ ተጎጂ ለሆኑ ቡድኖች እንደ በዕድሜ ለገፉ፣ለነፍሰጡር፣ አካል ጉዳተኞች
- ምግብ ለሥራ

ለማህበረሰብ ልማት ሥራ በምግብ ለሥራ ታሳታፊ ለሆኑ ምግብ ወይንም ገንዘብ ማስጠት። በሥራ ለታሳተፉ ሰዎች በቀን በሰው 3 ኪ.ግራም ምግብ ወይንም ብር 10.00 ሂሣብ ክፍያ ይፈጸማል። አንድ ሰው ከ5 ቀን ያልበለጠ በወር ይከፈለዋል። ለምሳሌ 4 ሰዎች ያለው ቤተሰብ በወር እስከ 60 ኪ.ግራም ምግብ ወይንም ብር 200.00 ሊያገኝ ይችላል። (3ኪ.ግራም በሰው X 5 ቀን X 4 ሰው ወይንም ብር 10.00 X 5 ቀን X 4 ሰው በቤተሰብ)

ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም የምግብ ለሥራ ፕሮግራም በዓመት ለስድስት ወራት ከጥር እስከ

ሰኔ በአለው ጊዜ ያካሂዳል፡፡ በመሠረታዊነት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት በገንዘብ የሚከፈል ሲሆን በመጨረሻዎቹ ሦስት ወራት ምግብ ይሰጣል፡፡ በዚህ ዓይነት ክፍያው እንዲሆን የታሰበው በምግብ ለሥራ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች በአካባቢው ያለውን ትርፍ ምርት መግዛት እንዲችሉ ነው፡፡ ይህ የመኸር ምርትን በመግዛት የምግብ ዋጋ ያማረጋጋት አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል ከሚያዝያ እስከ ሰኔ በአለው ጊዜ በእነዚህ የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካበቢዎች የምግብ እጥረት ስለሚኖር የምግብ ዋጋ ይጨምራል፡፡ ስለዚህም ነው ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም  በገንዘብ ምትክ ምግብ የሚሰጠው፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ በ2010 (እ፣ኤ.አ) ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ታሳታፊዎች 1.8 ሚሊዮን እነደሚሆኑ ተገምቷል፡፡ በመሆኑም በፕሮግራሙ ክፍያ ለመፈጸም ብር 255 ሚሊዮን ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ወር እንዲሁም 63000 ቶን ምግብ ለመጨረሻዎቹ ሦስት ወራት ያሰፈልጋል፡፡ በግብርና ምርት እና ግብይት ላይ ይህ ትልቅ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ያስከተለውን ለውጥ የሚያሳይ ግምገማ እሰካሁን ድረስ አልተካሄደም፡፡

ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ለምግብ ለሥራ ከጥር እስከ መጋቢት በአለው ጊዜ በገንዘብ ፋንታ ምግብ ያቀርባል፡፡ ይህም ያለፈው መኸር ምርት አነስተኛ ይሆናል ተብሎ በተተነበየበትና የምግብ ዋጋ ከፍ በሚልበት ወቅት ነው፡፡ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ንዑስ የሥራ ሂደት የዚህ ዓይነት ትንበያ በማድረግ አስፈላጊው ምግብ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

በምግብ ለሥራ ፕሮግራም የሚሠሩ የማህበረሰብ ልማት ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የአፈር ጥበቃ ሥራ
- ገጠር መንገድ
- የውሃ ተቋም ግንባታ (ምንጭ)
- ትምህርት ቤት ግንባታ
- የገበሬ ማስለጠኛ ማዕከል ግንባታ
- የእንጨት ድልድይ ሥራ.

2) የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም በምግብ ለሥራ ፕሮግራም የታቀፉ ሰዎች የራሳቸውን ጥሪት/ንብረት በመፍጠር ከልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም እንዲመረቁ ለማበረታታት የታቀደ ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም አማካኝነት ለአንድ ቤተሰብ እስከ ብር 4000.00 መነሻ ካፒታል በማበደር አንዳንድ ኢኮኖሚያዊ ሥራዎችን እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡ የዚህ ፕሮግራም ዋንኛ ፓኬጆች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የእንስሳት ፓኬጅ
- ከብት ማድለብ
- የበግ ድለባ ፓኬጂ
- አነስተኛ መስኖ ሥራ
- የሰብል ምርት ልማት
- የአትክልት ልማት
- የአህያ ጋሪ
- ንብ ዕርባታ
- ሌሎች

ብድሩ ተከፍሎ በ4 ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡ ለዚህም ሲባል ነው ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ተበዳሪዎች ገንዘቡን አዋጪ በሚሆኑ ሥራዎች ላይ በማዋል ብድሩን እንዲመልሱ የሚጠብቀው፡፡ ከሥራ ሂደቱ እንደተገኘው መረጃ የብድር አመላለሱ 1-2% ብቻ ነው፡፡ በ2009

(እ.ኤ.አ) የዚህ ፕሮግራም በጀት ብር 120 ሚሊዮን ደርሶ የነበረ ሲሆን ብር 45 ሚሊዮን እስከ መጋቢት 2010 (እ.ኤ.አ) ተሰራጭቷል፡፡

የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምግብ ዋስትና የሥራ ሂደት አቻ ባለሙያ የዚህ ጥናት አሠራር በማድነቅ ወደፊቱ ጥራቱን የጠበቀ የዋጋና ትርፍ የእህል ሰብል ያለባቸው አካባቢዎች መረጃ ታትሞ የሚቀርብበት ሥርዓት እንደሚዘርጋ ይጠብቃል፡፡

3) ሠፈራ ፕረግራም

ይህ ፕሮግራም አላማ አድረጎ የሚንቀሳቀሰው የምግብ ዋስትና ካልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች ሰዎችን ወስዶ የህዝብ ብዛት በሌለባቸው አካባቢ ማስፈር ነው፡፡ ፕሮገራሙ ከ78 ወረዳዎች ለምግብ እጥረት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ወስዶ በክልሉ ምዕራባዊ ክፍል እንደ ቤንች ማጂ በአሉት 12 ወረዳዎች ማስፍር ይፈልጋል፡፡ ከ2004 እስከ 2008 (እ.ኤ.አ) በአለው ጊዜ 42000 አባወራዎች ወደ ሠፈራ ጣቢያ ገብተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለእርሻ ተስማሚ መሬት እጥረት የተነሳ የሠፈራ ፕሮግረም ሥራ ቀንሷል፡፡ በሠፈራ ፕሮግራሙ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ 2 ሄ/ር የእርሻ መሬትና 1000 ካሬ ሜትር ቀዬ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪ ዘር፣ የእርሻ መሣሪያ እና ብር 30.00 እስከ ስምንት ወር በአለው ጊዜ ይሰጣል፡፡

በቂ መንገድ ባለመኖሩ ሳቢያ ሠፋሪዎች በትርፍነት የሚያመርቱተን ምርት ወደ ገበያ ለማውጣትና ገዥ ነጋዴ ለመግኘት ይቸገራሉ፡፡ ይሁንና ይህም በመሆኑ ወደ ቀድሞ ቦታቸው ለመመለስ የሚፈልጉ ሠፋሪዎች ቁጥር ትንሽ ነው፡፡